“ኢዴፓ የገደለ ዝሆን ጀግና አይባልም”



ኢዘርግ

2008 ዓ.ም

ማስታወሻ ၊

እዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ታሪኮች በሙሉ 70% ምናባዊ ፈጠራ ሲሆኑ 30% እውነተኛ ታሪክ ላይ የተንጠላጠሉ ናቸው፡፡

# ቃ

አዘርግ 2008

አዲስ አበባ ፡፡



Scanned by CamScanner

## ማስታወሻ 2

ይህን አዝናኝ አስተማሪ መፅሐፍ መልሶ ለማሳተም

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው::

ኮፒራይት © 2008 አዘርግ

## ቀደምት ስራዎች

1. የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል — 2003 (ገበያ ላይ የለም)
2. ኢያሪኮ 777 — 2004
3. ኢያሪኮ 888 — 2004
4. ኢያሪኮ 999 — 2005
5. አዳምና ሄዋን — 2005 (ገበያ ላይ የለም)
6. አቢሲኒያ 24 — 2005
7. አ ... ዘንደኪ — 2006
8. አ ... ያያያ — 2006
9. በኢያሪኮ ከተማ — 2007
10. ሹክ ቱስ — 2007
11. ሽርብትን — 2008

መልካም ንባብ ...!!



Scanned by CamScanner

## ማስታወሻ 3
## ለውድ ተደራሲያን
## ለማኮብኮቢያ ያህል

1. እኔም የአላህ መልዕክተኛ ነኝ!!
2. በቅድስት ማርያም ቀልድ የለም!!
3. ንጉሱ ስፒ ኖዛ
4. 5ቱ የፍቅር እርከኖች
5. ቫዮርሲት ለገሰ
6. ምርጥ ቆሀልት
7. የፍቅር ተመን
8. እውን መማር ያስከብራል... ?"
9. 4 ወሳኝ ጥያቄዎች
10. የባርነት አይነቶች
11. የወሲብ ጥያቄ
12. መሻሻል የለበትም?
13. ኦ... ገንዘብ
14. ቢያንጀን ኢትዮጵያዊ
15. የሐረሩ አሊ... 16 ዘ. ቹዝን ዋን... 17 እኛ እና አረብ ...18 እኛ እና ፈስ... 19 እኛ እና ካሎሪ... 20 እኛ እና ዲሞክራሲ... 21 ሶሲ Rich ... 22 አኔሲሞሲ.. 23 እንደ ኮከብ ያበሩ ... 24 ጂሀድ አውጃለው... 25 እኛ እና ንግድ... 26 እኛ እና አረብ 2... የሚሉ 26 ታሪኮች ... ናቸው::

እነዚህ አጠር አጠር ያሉ ቁርጥራጭ ታሪኮች በሌሎች በታተሙት መፅሐፍት ላይ ለመውጣት ቋምጠው የቀሩ ነበሩ፤ አሁን ለእነሱም ዘመናቸው ደርሶ ለህትመት የበቁ ናቸው ... ህይወት መዝራት ማለት ይህ ነው!!

በተረፈ እነዚህን ቁርጥራጭ ታሪኮች ለመፃፍ የተፈለገበት እስከ ዛሬ የታተሙትን አስራ አንድ መፅሐፍትን ለማጠቃለል ጭምር መሆኑ ነው ፤ ጀማሪ ፀሐፍት ለገፀባህርይ ምርጫነት ልትጠቀሙባቸው ትችሉ ይሆናል... ወደ ሌላ ቋንቋ ለውጣችሁ ይህን መፅሐፍ ማሳተም መብታችሁ ነው፤ ለማንኛውም የአፃፃፍ ስልታቸው "ቃለመጠይቃዊ" በሚለው እንጂ የአጭር ልቦለድም ሆነ የወግ አፃፃፍንም መርህ አለመከተላቸውን ከወዲሁ ልብ እንድትሉልኝ እፈልጋለሁ...::

ቸር ንባብ!!
ከትልቅ ምስጋና ጋር
አዲስ አበባ
አዘርግ 2008

ለአስተያየት አልያም ጥያቄ
0911 04 89 65 ላይ አጭር የፅሁፍ መልዕክት ብቻ ይላኩልኝ::



Scanned by CamScanner

# የስጦታ ገፀ በረከት

ለውድ ______________________

ከ ______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

ቀን ______________________

ፊርማ ______________________



Scanned by CamScanner

# እኔም የአላህ

# መልዕክተኛ ነኝ!!

በእውነተኛ ፈገግታ አሸብርቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሙን ሲነግረኝ ተገርሜ ነበር!!

"ሙሳይሊማህ አቡበከር እባላለሁ"

"እህ" አልኩት፡፡

"ሙሳይሊማህ"

የነገረኝን ስም እርግጠኛ ለመሆን በድጋሚ ጠየኩት፡፡

"ሙሳይሊማህ?"

"ትክክል!"

"ትርጉሙ ምንድንነው?"

"እኔንጃ" አለኝ... አብዛኛው ኢትዮጵያዊያን ስለሚወጣልን ስም ትርጉም አናውቅም፤ ስሙን ያወጡልን ወላጆቻችንም ፍቺውን አይነግሩንም፡፡ ይህ አንዱ ሊቀረፍ የሚገባ የኢትዮጵያዊያን ትልቅ ችግር ነው፡፡ "ስም ከመቃብር በላይ ይውላል... ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይበልጣል" በሚባልባት ኢትዮጵያ በልጆች ላይ ማንነት መቀረፅ መጀመር ያለበት ከስም መሆን አለበት... በአባባሉ የምናምንበት ከሆነ!!

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አብሮን የተማረ "ሰው አትመን" የሚባል ወጣት ነበር፡፡ እስቡት ይህ ልጅ እንዴት ሰው ያምናል? ሌላውስ እንዴት እሱን ያምናል?... ቅዱስ የተባለ ልጅ በተግባር "እርኩስ" የሚሆነው ቤተሰቦቹ ስለ ልጁ ስም ፍቺ እየነገሩ ኮትኩተው ባለማሳደጋቸው ሊሆን ይችላል...!! ባጋጣሚ "ፐሉቶ ቻላቸው" ከሚባል ልጅ ጋር ተዋውቄ ስለ ፐሉቶ ስጠይቀው የሚያውቀው ነገር የለም... (ለማንኛውም እባካችሁ ቤተሰቦች ለልጆቻችሁ ቢያንስ ወጣ ያለ ስም ስታወጡ ፍቺውን መንገር እንዳትረሱ!! ወጣቶችም የስማችሁን ፍቺ ለማወቅ ሆነ ስማችሁን በተግባር ለመሆን ጥረት አድርጉ!!) ወደ ሙሳይሊማህ ጉዳይ ልመለስ

"ቤተሰቦችህ አልነገሩህም?"



Scanned by CamScanner

"አልነገሩኝም... እኔም ተጨንቄበት ስለማላውቅ አልጠየኳቸውም"

"ይህን ስም ከዚህ በፊት እንተም ሰምተኸው አታውቅም?"

"አላውቅም"

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግር ኳስ ጨዋታ የተነሳ የተዋወኩት የከሚሴው ተወላጅ ሙሳይሊማህ ግራኝ ነው:: በዓለማችን ካሉት ወደ ስምንት ቢሊዮን ከሚቆጠሩ ህዝቦች 15% Google ላይ ባነበብኩት አንድ ጥናት ግራኝ ናቸው:: የሚገርመው አብዛኛው ግራኝ ሰዎች ወይ ወጣ ያለ ባህሪ አልያም ወጣ ያለ የጭንቅላት አስተሳሰብ አላቸው:: በዓለማችን ላይ ከዝና ማማ እንደኮከብ ደምቀው ከተቀመጡት ስመጥር ግራኝ የእጅ ጽህፈት ያላቸው ሰዎች ጥቂቱን ለመጥራት ያህል አሪስቶትል፤ ሊኦናርዶ ዳቪንቺ፣ አልበርት አንስታይን፣ ቢልጌትስ፣ ጆርጅ ቡሽ፣ አብርሃም ሊንከን፣ ቤንጃሚን ናትናያሁ፣ አንጀሊና ጆሊ፣ ጁሊየስ ቄሳር፣ ቻርሊ ቻፕሊን፣ ማህተማ ጋንዲ፣ባራክ አባማ፣ ሰሊንዲዮን... የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል:: ይህን ዜና ለሙሳይሊማህ ነግሬዋለሁ... ምናልባት የተደበቀ ችሎታ ሊኖረው ስለሚችል እንዲጠቀምበት!! አንዳንዴ በህይወት ጉዞ ከእያንዳንዱ ነገር ጀርባ አንዳች የሆነ ምክንያት አለው::

"ስለ ስምህ ብነግርህስ?"

"ደስ ይለኛል"

"ስለ ነብዩ ሙሐመድ እና ሙሳይሊማህ ምንም የምታውቀው ነገር የለም?"

"በነገራችን ላይ የመጣሁት ከከሚሴ ገጠርማ መንደር ነው:: ለማንበብ ብፈልግም በርካታ መፅሐፍትን ማግኘት ጨርሶ አይቻልም፤ በዚያ ላይ እናቴ እና አባቴ እንኳን መፅሐፍትን እንዳነብ ቀርቶ የምማረውን ትምህርት እንኳ አቋርጬ በቀጥታ እናትና አባቴ የተሰማሩበት ንግድ ውስጥ እንድገባ ነው የሚፈልጉት:: እዚህ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት እናትና አባቴ ጋር አንድ ለትምህርት ቀና ግንዛቤ ያለውን አጎታችንን አማላጅነት ልኬ ነው!! ሀቁን ለመናገር ስለ እስልምና ሆነ ስለ ነብያችን ነብዩ ሙሐመድ ብዙ ነገር ልነግርህ አልችልም፤ አሁን ግን እዚህ ዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ብዙ መፅሐፍት ስላሉ ባለኝ ትርፍ ጊዜ በርካታ መፅሐፍትን ለማንበብ እቅድ አለኝ"

"አሪፍ እቅድ ነው:: በአጋጣሚ መጠቀም ብልህነት ነው:: ለማንኛውም በ40 ዓመቱ የአላህ መልዕክተኛ ለመሆን የበቃው ሙሐመድ በእስልምና ተከታዮች ሲታወቅ እና አጅግ



Scanned by CamScanner

በርካታ ተከታዮችን እያፈራ ሲመጣ፣ ስለ አላህ እየሰበከ ዝናው እየገነነ ሲመጣ፣ በዘመኑ ከነበሩት በስልጣን ጥማት እና ከፍተኛ ቁሳዊነት የሚታወቅ አንድ ሰው እነሆ እኔም የአላህ ሌላኛው መልዕክተኛ ነኝ!! ለእኔም መላዕኩ ጅብሪል (ገብርኤል) መልዕከት እንደ ሙሐመድ እየላከልኝ ነው፤ እኔንም ተቀበሉኝ ማለት ጀመረ... ይህ ጉዳይ በጣም እየከረረ መጣና ይህ ሰው ለእስልምና ከባድ ፈተና ሆነ! ለእስልምና ከፍተኛ ራስምታት ሆነ! የሙሐመድ ተከታዮችን ግራ ማጋባት ተያያዘው:: ይበልጥ ጉዳዩ ጦዘና "አል-ያማማህ" በተባለ ታሪካዊ ጦርነት ላይ የቁርአን 460 የሚጠጉ ሀፊዞችን እና 310 የሚጠጉ የነብዩ ሙሐመድን የልብ ጓደኞችን እየመረጠ በመግደል ቁርአን ለቀጣይ ትውልዶች እንዳይተላለፍ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረ ግን ያልተሳካለት ባጠቃላይ እስላሞች አጥብቀው የሚጠሉት የነበረ ሰው ነበር ሙሳይሊማህ!! እና ይህን ስም እንዴት አወጡልህ ብዬ ገርሞኝ እኮ ነው"

"አ... አመሠግናለሁ"

"በነገራችን ላይ ተጨማሪ ታሪክ ማንበብ ከፈለክ ቤተመፅሐፍ ውስጥ አንድ መፅሐፍ አለ አሳይሃለው"

"ደስ ይለኛል! አንተ እስላም ነህ?"

"አይደለሁም"

"ታዲያ ስለ እስልምና ለምን ለማንበብ ፈለክ?"

"ወደፊት በትርፍ ጊዜዬ በሥነፅሁፍ ለመዝናናት እቅድ አለኝ... መረጃ ደግሞ ጠቃሚ ነገር ነው፤ አየህ ያን መፅሐፍ ማንበቤ አሁን ቢያንስ ለአንተ የስምህን ጉዳይ ለመንገር አበቃኝ"

ሙሳይሊማህ በተስማምቻለሁ ራሱን ነቀነቀ:: የከሚሴው ገጠርማ ተወላጅ፤ እጅግ በጣም ለስላሳ የሆነ ፀባይ የነበረውን ተማሪ ግን ከአንድ ዓመት በላይ አላየሁትም፤ በሁለተኛው ዓመት የከፍል ጓደኞቹን ስጠይቃቸው እንደ ተጫረ ነገሩኝ... በጣም ነበር ያዘንኩት! ለትምህርት ሆነ ባለዲግሪ ለመሆን እጅግ ከፍተኛ ጉጉት የነበረው ተማሪ ነበር:: በብዛት ቤተመፅሐፍ ስገባ በከፍተኛው እየቸከለ እመለከተው ነበር... አሁን የከሚሴው ደስ የሚል ፀባይ የነበረው ሙሳይሊማህ የት ደርሶ ይሆን? ሀብታም ነጋዴ ሆኖ ይሆን? አላውቅም!! ቢሆንም እስከ መቼም ይህን ወጣት ለማስታወስ የምታበቃኝ አንዲት ንግግር አለችው::



Scanned by CamScanner

አንድ ጊዜ ኳስ ተጫውተን ስንጨርስ

"ለምን ግን የተማረ ነጋዴ አትሆንም? ንግድን ለምን ጠላኸው?" ስለው በፈገግታ ተሞልቶ የተናገራት ይቺን አባባል ነበር...

"እኔ ሀብታም ሆነ ነጋዴ መሆን አልሻም ፤ የሀብታሞች ሆነ የነጋዴዎች ትግል ህዝቡን በቅንነት ማገልገል ሳይሆን ከእነርሱ ተሸሎ የተገኘውን ለመብለጥ መፍጨርጨር ብቻ ነውና!!"

(ማስታወሻ፡- ስለነብዩ ሙሐመድ የበለጠ መረጃ ለማንበብ ከፈለጉ 'ሸርብትን' መፅሐፍን ይመልከቱ)



Scanned by CamScanner

# በቅድስት ማርያም ቀልድ የለም!!

እስላሞች ማርያምን "መርየም" ይሏታል፤ ከመልካም ሴቶች አንዷ እንደነበረች በቁርአን ትጠቀሳለች... ፕሮቴስታንቶች ማርያም የኢየሱስ እናት እንደሆነች ቢያምኑም ማርያም አማላጅ ነች በሚለው ሀሳብ ጨርሶ አይስማሙም!! ስለ ማርያም ከተነሳ ከዓለም ላይ ከሚገኙት ሀይማኖቶች ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሶች የተለየ ቦታ የሚሰጣት የለም! የኢትዮጵያዊያን ኦርቶዶክሶች በማርያም ቀልድ የላቸውም! ለማርያም ግዙፍ ክብር፣ ትልቅ ቦታ፣ ቢቃላት የማይገለፅ ፍቅር አላቸው!! በአጭሩ በእምዬ ማርያም ቀልድ የላቸውም!!

ለማንኛውም ወደ ጥበቡ እንመለስ፡፡ ጥበቡ የኢኮኖሚክስ ተማሪ ነበር፡፡ ከጥበቡ ጋር ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተዋወቅነው ቤተመፅሐፍት ውስጥ ነበር፡፡ የሁለታችንም የት/ት ዘርፍ የማይገናኝ ቢሆንም ያገናኘን ለፍልስፍና መፅሐፍት ያለን ፍቅር ነበር፡፡ ጥቤ የሻሻ ልጅ ነው፡፡ ስዕል ቢጤም ይሞካከራል ... እንዲገፋበት አበረታታው ነበር... በዚህ በስዕሉ ግን አንድ ምሽት ከፍተኛ ጦርነት ተነሳ!! አራት የደብረማርቆስ ልጆች ጥቤን ከዩኒቨርሲቲ ሲወጣ ጠብቃው እንደ አባብ ቀጠቀጡት፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ መኝታ ቤቱ ልጠይቀው ሄድኩኝ፡፡

"ምን ተፈጠረ ጥቤ?"

"ቀጠቀጡኝ"

"እነማን?"

"የደብረማርቆስ ልጆች ናቸው አንደኛውን አንተም ታውቀዋለህ! አንድ ቀን ካንተ ጋር ሲያወራ ተመልከቸዋለው"

"ስሙ ማን ነው"

"እህ... አባይ"

"አባይ የፔዳጎጂ ተማሪው?"

"ይሆናል የምን ተማሪ እንደሆነ አላውቅም ብቻ እሱ እና ጓደኞቹ ናቸው የቀጠቀጡኝ"



Scanned by CamScanner

"ምክንያቱን ማወቅ እችላለሁ?"

" በስዕል የተነሳ"

እውነቱን ለመናገር ጥበቡ በጣም ምስኪን ልጅ ነው:: ትህትና ያለው ልጅ ነው:: ሰላማዊ ሰው ነው:: አንዳንድ ጊዜ ግን ሴይጣኑ ብቅ ትላለች! ይህ ደግሞ ከቤተሰቡ የመጣ ጣጣ ነው፤ ስለ ቤተሰቦቹ ሲነግረኝ አዝኜለት ነበር፤ ስለ ቤተሰቡ የነገረኝ አንድ ቀን ጣና ሐይቅ ልንዝናና ስንሄድ በሩ ጋር አንድ ጠና ያሉ ቄስ ቆመው ነበር፤ ጥበቡ ሆን ብሎ ገፈተራቸው... በጣም ነበር የደነገጥኩት

"ምነው ጥቤ?" አልኩት::

"ቄሶችን በጣም ነው እንደግራኝ አህመድ የምጠላቸው"

"ለምን?

"አንተ ቄስ ትወዳለህ?"

"አልጠላቸውም! አልወዳቸውምም!"

"ቆይ ግን አንተ ልጅ Atheists ነህ እንዴ?"

"እምነት የለሽ እንኳ አይደለሁም"

"እኔ ቄስ እጠላለሁ! እንደ ግራኝ አህመድ ብጨርሳቸው ራሱ ደስ ይለኛል:: ምን መሰለህ እናቴ የ17 ዓመት ልጅ እያለች ቤታችን በሚመጣ ቄስ ተደፍራ ነው የወለደችኝ ... ከዚህ በተጨማሪ በሌሎች ሁለት ቄሶች የተነሳ ንክ ሆናለች!! እኔን ያሳደገኝ የእናቴ ወንድም ነበር... ብቻ ታሪኩ ብዙ ስለሆነ ተወው" አለኝ:: አላስጨነኩትም:: ማስጨነቅ የሚባል ነገር የት አወድና?

"አልገባኝም በስዕል የተነሳ ማለት?"

"ጠዋት ዶርም አካባቢ የሳልኩትን ስዕሎች ሚጢጢዬ ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት እያሳየሁ ነበር... ስዕሎቹን የማውቃቸውም ሆነ የማላውቃቸው ተማሪዎች እያዩ ነበር... Any way እኛ አገር ያለው በጣም ግዙፍ ችግር ሀሳብን በሀሳብ ከማሳመን ይልቅ እንደ ጋርዮሽ ስርዓት በዱላ ለማሳመን መጣር ነው!! ሀበሻ በክርክር እንደማያሸንፍህ ሲያውቅ በዱላ ይቀውርሃል!! እኔ ላይም የተከሰተው ይህ ነው!! እነዚያ አራት ቀሽሞች ናቸው ከዩኒቨርሲቲው ሰወጣ ጠብቀው የቀጠቀጡኝ! They are Typical example of ሀበሻ!!" ገና ሲለኝ በድንጋጤ አየሁት::

"ያን የሳልከውን ለእኔ ያሳየኸኝን የኢየሱስ እና ማርያምን ስዕል አሳየዋቸው



Scanned by CamScanner

እንዳትለኝ?"

"ትክክል! ሰዓሊ እኮ የተሰማውን ነው የሚያንፀባርቀው"

ሻሽመኔ ከራስታዎች መንደር ድክድክ እያለ ያደገው ጥበቡ በራስታዎች ፍልስፍና ያምናል፤ በዚህ ዙሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ስዕሎቹን ሲያሳየኝ ሁለት የሚገርሙ ውብ ስዕሎች አሳይቶኝ ነበር፡፡ አንደኛው የኢየሱስ ስቅለት ነው፤ ሁለተኛው የማርያም ነው፡፡

"ይህ የኢየሱስ ምስል ነው! የኢየሱስ መልከ ጥቁር ወይም ነጭ አልነበረም! ጠይም የኢትዮጵያ መልከ ያለው እና ከርዳዳ ፀጉር ያለው ነበር፡፡ ፈረንጆቹ ብልጥ ስለሆኑ እና ለጥቁር ያላቸውን ንቀት ለመናገር ኢየሱስን ነጭ! ሴይጣንን ጥቁር አድርገው ስለውታል... ይቺ የምታምር ጥቁር መልከ ያላት! ትንሽዬ አፍንጫ ያላት ሴት ደግሞ የኢየሱስ እናት ማርያም ነች... አፍሪካዊያን ሰዓሊዎች የኢየሱስንም ሆነ የማርያምን ስዕል ጥቁር አድርገው ቢስሉ አሁን በዓለም ላይ ያለው የነጭ የበላይነት ያከትም ነበር!! ከእኛ ሀበሾች ባህል በጣም የምጠላው ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" አለኝ፡፡

"እህ" አልኩት፡፡

"የነጭ አምልኮ አለብን! በዚያ ላይ ለየት ያለ ሀሳብ ይዘህ ብትመጣ ሀሳብን በሀሳብ ተከራክሮ ከማሸነፍ ይልቅ አንተን ማግለል ወይም ዱላ ይቀድማቸዋል! ይህ ደግሞ ላለመሰልጠናችንም ሆነ ገና የአስተሳሰብ እንጭጭ እንደሆንን ያሳብቅብናል፡፡ በዚህ በኢየሱስ ስዕል እና ማርያም የተነሳ ሻሽመኔ ስንት ጊዜ ቀጥቅጠውኛል መሰለህ! በተለይ በማርያም የተነሳ ስንት ጊዜ ቀውረውኛል መሰለህ!"

"ይህን የሳልከውን እያሳየሀቸው ነው?"

"ያ! አየህ ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ኢየሱስ ከማርያም በከብት በረት ያለወሲብ በተዓምር ተወለደ ከሚለው ዜና ግርምት ተሞልቼ ስለማርያም እና ኢየሱስ ብዙ ለማወቅ ብዙ ጥረት አድርጌያለሁ!! ብዙ ለማንበብ ጥረት አድርጌያለሁ! በእኛ ሀበሻ ምድር ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ ዝርዝር ነገር ለማወቅ ጥያቄ ብትጠይቅ እንደሀጢያተኛ ነው የምትቆጠረው!! ይህ ትልቁ ቀሽሙ አመለካከታችን ነው! እኔ ደግሞ መጠየቅ እወዳለሁ... አንድ ጊዜ በሰፈራችን የግንቦት ልደታ ሲከበር አንድ አውቃለሁ ባይ ቄስ ሲለፈልፍ ነቆርኩት፡፡ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ ወይ? አልኩት በንቀት እየተመለከተኝ ጠይቅ አልኩት፡፡

"የኢየሱስ አባት ማን ነው?"



Scanned by CamScanner

"እግዚአብሔር"

"እንዴት? የኢየሱስ አባት አናጢ የነበረው ዮሴፍ ነው! ምክንያቱም ኢየሱስን እስከ 33 ዓመቱ ያሳደገው ሆነ ያደገው በአባቱ ዮሴፍ ቤት ነው አይደለም?"

"ኢየሱስ በግብረሥጋ ግንኙነት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም የተወለደ ስለሆነ አባቱ ዮሴፍ አይደለም! ዮሴፍ ጠባቂው ነበር"

"እሺ ማርያም ኢየሱስን በመንፈስ ያለወሲብ ከወለደችው በኋላ በቀሪ ህይወቷ ልጆች ወልዳለች አይደለም?"

"ልክ ነው"

"ታዲያ እስከ ዛሬ ለምን ድንግል እንላታለን?"

ለዚች ቀላል እና ተራ ጥያቄ ምላሽ ስላጣ የማርያምን ክብር ዝቅ ያደረኩበት መስሎት በቁጣ በዝምታ ሲመለከተኝ

"እሺ የማርያም መልክ አሁን እንደምናየው ነጭ የፈረንጅ ስዕል ነው ወይስ ጥቁር መልክ ነበር ያላት? በዚያ ላይ ፈጣሪ በምድር ላይ በምንም አይነት ምስል እንዳታመልኩ ይል የለምንስ?` ስለው በያዘው መስቀል ግንባሬ ላይ ቀውሮ አደማኝ! ሌሎች በቦታው የነበሩ ሁሉ ተከራክረው ከማሳመን ይልቅ ከኔ የተሻለ ሀሳብ ስለሌላቸው ከቄሱ ጋር አብረው ቀጠቀጡኝ ሲል ነበር ያጫወተኝ፡፡

"አንተ ግን ምላሹን አጥተሃው ነው?"

"መልሱ እኮ ቀላል ነው፡፡ ድንግል ማርያም በዚያን ዘመን ከነበሩ ሴቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠችው ልበቀና ስለሆነች ነው! በዘመኑ ከነበሩ ሴቶች ሁሉ እጅግ ንፁህ ልብ ያላት መልካም ሴት ስለነበረች ነው፤ በዚህ የተነሳ ያለ አንዳች ወሲብ በሚገርም ጥበብ ኢየሱስን ስለወለደች ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ከፍቅረኛዋ ወንበር ሰሪው አናጢ ባሏ ጋር ወሲብ አድርጋ ልጆች ወልዳለች! (በእርግጥ ይህን ሀሳብ የማይቀበሉ አሉ) ኢየሱስ ወደ ሰማይ አርጓል! ማርያም እዚው ምድር ላይ ቀርታለች! አየህ የእኔ ትልቅ ጥያቄ የነበረው ኦርቶዶክሶች እና ፕሮቴስታንቶች በሚወዛገቡበት ማርያም ታማልዳለች እና ማርያም በጭራሽ ልታማልድ አትችልም! ታማልዳለች በዚህ በዚህ ምክንያቶች... አታማልድም በዚህ በዚህ ምክንያቶች እያሉ በሚወዛገቡበት ነጥብ ላይ ሳይሆን የእኔ ትኩረት በማርያም መልክ ላይ ነው! ልቧ ቆንጆ ነው



Scanned by CamScanner

እንጂ በመልክ ረገድ እንኳ የእኔ ማርያም መልኳ ጥቁር ናት፤ ቆንጆ ቢጤም አይደለችም!!"

እንግዲህ በዚው ስዕል የተነሳ ነው ጥቤን እነዚያ በማርያም ቀልድ የማያውቁ አራት የደብረማርቆስ ልጆች የቀጠቀጡት... እነዚያ የደብረማርቆስ ልጆች ደግሞ እንኳን ስለ ማርያም ተነስቶ ይቅርና የእናታቸው ስም በክፉ ሲነሳ እንኳ...ምላጭ ለመዋጥ የሚደርሱ ነበሩ...

ሰዓሊው ጥቤ... በአሁኑ ሰዓት ራሺያ ይገኛል:: የማርያም ስም በተነሳ ቁጥር ትዝ የሚለኝ ጥቤ ነው:: ከመፅሐፍት ማንበብ ጋር በተያያዘ ጥቤ በነገረኝ የሃነኪሙራካሚ አሪፍ አባባል ስለ ጥቤ እና ማርያም ያነሳሁትን ልዝጋበት...

"ሁሉም ሰው የሚያነባቸውን መፅሐፍት ብቻ የምታነብ ከሆነ ሁሉም ሰው ከሚያስበው ውጭ አታስብም"

<u>ማስታወሻ</u>፡- በኢየሱስ እና ማርያም ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ሽርብትን ላይ አለሎት



Scanned by CamScanner

# ንጉሱ ስፒኖዛ

ዋው!! የሸገር ልጅ የሆነው እና የህግ ተማሪ የነበረው ንጉሱ አያሌው ዩኒቨርሲቲ ካወኳቸው ምርጥ አንባቢዎች እና የፍልስፍና አድናቂዎች አንደኛው ነበር፡፡ ምርጥ ምርጥ ታሪኮችን ነግሮኛል፤ በተለይ መጀመሪያ የነገረኝን ምርጥ ታሪክ መቼም አልረሳትም!! ወሬው የተነሳው መንገድ ላይ አንዲት የሞተች አይጥ አይተን ነበር

"አይጥ ትፈራለህ?" አለኝ

"ታስጠላኛለች ግን አልፈራትም" አልኩት፡፡

"እኔ ታሳዝነኛለች ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? አይጥ ለመኖር እንቅልፍ የላትም፤ ጥርሷ ሾሎ እንዳይገድላት በየሴኮንዱ በጥርሷ የሆነ ነገር እየበላች ጥርሷን መሞረድ አለባት፤ በዚህ መሠረት የፈረንሳዊው ዝነኛ ፀሐፊ ጃን ባፐቲስት ሞልየር አንድ ሰው መብላት ያለበት ለመኖር እንጂ ለመብላት መሆን የለበትም የሚለው አባባል በጭራሽ ለአይጦች አይሠራም!! ምክንያቱም አይጥ መብላት አቆመች ማለት ሞተች ማለት ነው፡፡ የእኛ የኢትዮጵያዊያኖችን ኑሮ ግለፅ ብትለኝ ራሱ የአይጥ ኑሮ ነው የምንኖረው! ለመኖር መብላት ብቻ!! ይልቅ ከአይጥ ጋር በተያያዘ አንዲት አሪፍ ታሪክ አለች ከዚህ በፊት ነግሬህ ይሆን?"

"ከአይጥ ጋር በተያያዘ? በጭራሽ!!"

"ልንገርህ ?"

" በፍቅር አዳምጣለሁ"

" በ1895 ዓ.ም መጨረሻ ያኔ ብረት ውድ በነበረበት ዘመን አንድ ምስኪን ሰው በጣም ለሚወደው ጓደኛው 500 ሺ ብር የሚያወጣ ብረት ለአንድ ወር በአደራ እንዲጠብቅለት አስቀምጦ በመርከብ ሌላ ሀገር ይሄዳል፡፡ በመርከብ ጉዞ ያልታሰበ ነገር ይፈጠርና ከስድስት ወራት በኋላ ተመልሶ ይመጣል!! ጓደኛው ጋር በማምራት ብረቱን ይጠይቀዋል"

"ውይ ጓደኛዬ የሚገርም ነገር ተፈጠረ እኮ!! ያንተን ብረት ማንም እንዳይደርስበት መሬት ቆፍሬ በአፈር አልብሼው ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ አፈሩን ገልጠው ብረቱን አይጦች ቁርጥም አድርገው አልበሉትም" አለው



Scanned by CamScanner

"እየቀለድክ ነው?"

"በጭራሽ"

"ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው አይጥ ብረት የሚበላው?"

"እኔም ገርሞኛል ፤ ግን ብረትህ በአይጥ ስለተበላ ምንም ማድረግ አልችልም!! አዝናለው!!"

"ይሁና!!" ብሎት ምስኪኑ ሰው ወደ ቤቱ ሄዶ ለረጅም ሰዓት አሰላሰለ፡፡ ፍርድ ቤት እንዳይወስደው ብረቱን ለጓደኛው ሲሰጥ ያየ አንዳች ምስክር የለም! የተለዋወጡት ህጋዊ ወረቀት የለም!... እናም በመጨረሻ ወሰነ፡፡ ዝግጅት አድርጎ በምሽት የጓደኛው ቤት በማምራት በጣም የምታምረውን ልጁን በከፍተኛ ጥንቃቄ ደጅ ስትወጣ ጠብቆ ምጭለፍ አድርጎ ደበቃት... በነጋታው ጓደኛው ቤት ሲያመራ ጓደኛው በፍፁም ሀዘን ልቡ ተሰብሮ ተመለከተ፡፡ ምንም ባላወቀ

' ምነው ወዳጄ ምን ገጠመህ?' አለው

'የምወዳት ልጄ ትላንት ጠፋች'

' እንዴት ምሽት ላይ ነው?'

' አዎ'

' ትላንት?'

'አዎ'

'አይቻታለሁ'

'እባክህ ንገረኝ የት ነው ያየሃት?'

'አንድ አሞራ ይዞዋት ሲበር'

'ከመቼ ጀምሮ ነው የሰባት ዓመት ልጅን አሞራ ከመሬት ላይ አንስቶ የሚበረው?'

'ከመቼ ጀምሮ ነው አይጥ ብረት መብላት የጀመረው?' አለውና ብረቱን በዘዴ አስመለሰ!!'

ንጉሱ አያሌውን ብዙዎች ስፒኖዛ እያሉ ይጠሩት ነበር፤ የሆላንድ ፈላስፋ ለሆነው ስፒኖዛ ከፍተኛ አድናቂ ነበር፡፡ 'ከሁሉም በታች ራሳቸውን ያዋረዱና ትሁት ናቸው ተብለው የሚታመኑ አብዛኛውን ጊዜ ቀናተኞችና ከሁሉም በላይ ለመሆን ምኞት ያላቸው ሰዎች ናቸው' የሚለው ዝነኛው ስፒኖዛን በተመለከተ ብዙ ነገር አውርተናል፡፡ አንድ ጊዜ



Scanned by CamScanner

'ብነገራችን ላይ ኢቲክስ የተሰኘውን ድንቅ የስፒኖዛ መፅሐፍ አንብበሃል?" አለኝ

"ከየት አባቴ አግኝቼው?"

"የሚገርምህ ይህን ድንቅ መፅሐፍ ስፒኖዛ ፅፎ እንደጨረሰ በቀጥታ ወደ ሆላንድ የፍልስፍና መፅሐፍት ማህበር ነበር ያመራው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ አንድ መፅሐፍ ለማሳተም ማህበሩ ውስጥ የነበሩት ዘጠኝ የሚጠጉ ፈላስፎች ይታተም ብለው እውቅና ማስጠት አለባቸው፡ እናም የስፒኖዛን ኢቲክስ የተሰኘ ድንቅ መጽሐፍ አጣጥመው አነበቡ፤ የሁሉንም የሚበልጥ ድንቅ መጽሐፍ ነበር:: በሚስጢር ውሳኔ ወሰኑ:: 'ይህ መጽሐፍ እኛ እስከዛሬ ከፃፍነው በጣም የሚበልጥ ስለሆነ ቢታተም ከብራችንን ዝቅ ስለሚያደርግ መታተም የለበትም' በማለት የማይረባ መፅሐፍ ነው በሚል ለስፒኖዛ መለሱለት 1664 ዓ.ም የተፃፈው ይህ ዝነኛ መፅሐፍ ከአመታት ከስፒኖዛ ሞት በኋላ ታትሞ ድንቅ መፅሐፍነቱን አስመስከሯል፤ ስለ ኩራት ያለውን ሰምተሃል?"

"አልሰማሁም"

"በእኛ ሀገር ኩራት እና ኩራተኛ ሰው አይወደድም :: ስፒኖዛን ኩራት ምንድን ነው አሉት 'ኩራት ሰው እራሱን ከፍ አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ ደስታ ነው' አላቸው:: ሰው ብቻውን ሊኖር ይችላል ወይ ሲሉት 'በጭራሽ ሰው ከንቱ ማህበራዊ እንስሳ ነው' ሲል መለሰ... በተለይ በጣም የምወድለት ንግግሩን ልንገርህ አንተም በአዕምሮህ መዝግብለት"

"እሺ".

"ከዕውቀት ይልቅ ማግኘት የሚያስቸግረው መልካም ሥነምግባርን ነው:: በተለይ በወጣትነት ዘመን ደብዛዋ ከጠፉ ደግሞ እንደገና የማግኘቱ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው" በማለት ወጣቶች ታላቅ እውቀት ቢኖራቸው እንኳ በቂ ሥነ ምግባር ከሌላቸው እውቀት ያለ ሥነምግባር ከንቱ መሆኗን ለዓለም ህዝብ ሹክ ያለው ገና በ1664 ዓ.ም ገደማ ነበር"

... ለሥነ ፅሁፍ ከፍተኛ ፍቅር እንዲኖረኝ ካደረጉኝ ሰዎች አንደኛው የነበረው ንጉሱ አያሌው (ስፒኖዛ) በሚገርም የፍቅር አጋጣሚ ስፒኖዛ ይኖርበት ከነበረ የሆላንድ ግዛት ከመጣች ሆላንዳዊት ጋር አሁን በፍቅር ክንፍ እያሉ ነው... 99% እንደሚጋቡ ተስፋ አለኝ... ንጉሱ ስፒኖዛን ሁልጊዜ የማስታውሰበት አንዲት ምክር አለችው፤ ከማንም በላይ ውስጤን የሚያነበው ንጉሱ ነበር::

"ደራሲ ነገር መሆን ትፈልጋለህ እንዴ?" አለኝ አንድ ጊዜ



Scanned by CamScanner

"ደራሲ ሳይሆን ፀሐፊ ነገር"

"እንግዳውስ ጥሩ አዳማጭ እና ጥሩ አንባቢ ሁን! በተጨማሪ ለየት ያለ የራስህን መንገድ ለመፍጠር ሞክር! እንደማንም ሳይሆን በራስ መንገድ የሚሰማህን ብቻ ፃፍ! በሥነ ፅሁፍ ውስጥ ለመቆየት ካሰብክ ለማንም ሙገሳ ሆነ ወቀሳ ትኩረት አትስጥ! የሚቻልህ ከሆነ ስሜትህን ብቻ መከተል ነው! ብዙዎች በሥነፅሁፍ የማይሳካላቸው ለምን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"ንገረኝ"

"ሌላውን ለመሆን በሚያደርጉት መንገድ ግራ እየተጋቡ እና በሚሰጣቸው ትችት ከመማር ይልቅ ቅስማቸው ተሰብሮ እየተው ነው"

"አመሠግናለው!" ነበር የዚያን ጊዜ ያልኩት፤ ዛሬም ከስንት ዓመት በኋላ ለንጉሱ ስፒኖዛ ያለኝ አንዲት ቃል ብቻ ነች፡፡ አ...መ...ሠ...ግ...ና... ለ... ው...!!



Scanned by CamScanner

# 5ቱ የፍቅር

# እርከኖች

ስለ ቤርሳቤህ በእርግጥ በኢያሪኮ ከተማ ውስጥ በገፀባህሪነት ያቀረብኳት ባለታሪክ ነች:: በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ጣና ሀይቅ የተዋወኳት አስገራሚ ውብት እና ጭንቅላት የነበራት ወጣት ነበረች... አቤት የፈገግታዋ ውበት! አቤት ያላት ትህትና ብዛቱ! አቤት ለሰው ልጅ ያላት ከብር...!! በቀላሉ ከማንም ጋር መግባባት የምትችል ወጣት ነበረች!! እጅግ አያሌ ወንዶች በፍቅሯ ያብዱ ነበር... ለነገሩ ቢያብዱ ራሱ አይገርምም... ሲያንሳት ነው!!

አንድ ዕለት የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለን ነው፤ የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት ፈተና ጨርሰን ጣና ሐይቅ እየቆዘምኩ ሳለሁ ቤርሲ መጣች

"እንዴ ወደ አዲስ አበባ አልሄድሽም?"

"ዘንድሮ አልሄድም"

"ፍቅረኛሽ አልናፈቀሽም?"

"ኧረ በጣም ናፍቆኛል"

"እና"

"ባህር ዳር ሊመጣ ተስማምተናል"

ስለ ፍቅረኛዋ ነው የምናወራው:: በጣም የምትወደው በንግድ ስራ ላይ የተሠማራ ፍቅረኛ እንዳላት ነግራኛለች፤ ፍቅራቸው ከዘጠነኛ ክፍል እንደ ጀመረ ጭምር ሹክክ ብላኛለች... በጣም እንደምትወደው ጭምር...

"ኦ! እሪፍ ጊዜ እንደምታሳልፉ ተስፋ አለኝ"

"ይመስለኛል! አምስት ዓመት ሆነን፤ እናም ከአምስት ዓመት በኋላ ወደ ደረጃ ሶስት ልንገባ ወስነናል"

"አልገባኝም"

"በፍቅር ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ ባለሙያዎች የእውነተኛ ፍቅር ደረጃን በአምስት ይከፍሉታል"



Scanned by CamScanner

"ይቺ አሪፍ መረጃ ነች፣ ይነገረኛ።"

"ምን ጣጣ አለው" በማለት ስለ አምስቱ የእውነተኛ የፍቅር ደረጃዎች ነገረችኝ፡፡ ቤርሲ የነገረችኝ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል... እውነተኛ ፍቅር በሁለቱም ተፋቃሪዎች መሀከል እንዳለ ለማወቅም ሆነ ለመገምገም የሚረዳ ዘዴ ጭምር ነው... እነዚህ አምስት መናበቦች በሁለቱም ተፋቃሪ ወገኖች ውስጥ ከሌሉ እውነተኛ ፍቅር ነው ለማለት አይቻልም...!!

አምስቱ የእውነተኛ ፍቅር እርከኖች

**መነሻ ምክንያት**
**(1ኛ ደረጃ)**

⇒ ተጨባጭ ምክንያት

⇒ አጋጣሚ

⇒ ትውውቅ

⇒ መረጃ መለዋወጥ

⇒ መደዋወል

⇒ ሻይ ቡና ማለት

**ቅርብ ግንኙነት**
**(2ተኛ ደረጃ)**



Scanned by CamScanner

⇒ መቀራረብ

⇒ አብሮ መሆን

⇒ በጋራ ነገሮችን ማከናወን

⇒ የመገናኘት_

⇒ የመተያየት

⇒ የመወያየት_

↓

**ጥልቅ ስሜት**
**(3ተኛ ደረጃ)**

⇒ የመፈላለግ

⇒ የመሳሳም

⇒ የወሲብ

⇒ የመነካካት

⇒ በደስታ የመሞላት

⇒ የመሳብ

⇒ የመነፋፈቅ

↓

**መስዋዕትነት**
**(4ተኛ ደረጃ)**



Scanned by CamScanner

⇒ መተሳሰብ

⇒ ከራስ ፍላጎት ፍቅረኛን ማስቀደም

⇒ ፍቅርን ዘላቂ ለማድረግ መጣር

⇒ መስዋዕትነት መክፈል

⇒ ለጋብቻ መጠያየቅ

⇒ ፈተናዎችን ማለፍ



**አንድነት**
**(5ተኛ ደረጃ)**

⇒ በአንድ ልብ መተንፈስ

⇒ ለአንድ ዓላማ መኖር

⇒ ልጆችን በእውቀት መገንባት

⇒ መተማመን

⇒ መከባበር

⇒ በተግባር የሚገለፅ ፍቅር

"ኦ! አሪፍ ገለፃ ነው! ግን እንዴት ማወቅ ይቻላል? ማለቴ በፍቅር ዓለም በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ስለ ራስሽ አንድን ሰው እንደምትወጂው እና እንደማትወጂው ውስጥሽ ያለውን የራስሽን ስሜት እንጂ በእርግጠኝነት ይህ ሰው ወይም ይቺ ሴት ትወደኛለች ማለት ይቻላል?"

"ይቻላል"

"እንዴት?"

"ፍቅር በተግባር መገለፅ አለበት"

"እሀ! ከፍተኛ የማስመሰል ችሎታ እና የመተወን ብቃት ያለው ሰው ቢያጋጥምሽስ?"



Scanned by CamScanner

እርግጥ ልክ ነህ! እውነቱን ለመናገር እኛ ሴቶች የሚወደንን ወንድ ሆነ ሙድ እየያዘብን ያለንን ወንድ ለመለየት በጣም እንቸገራለን! ከተግባር ይልቅ ምላስን ማመን ይቀናናል! ቢሆንም አንዲት ሴት ልቧን ለወንድ ከመስጠቷ በፊት የተወሰነ ዙሪያ ቀኙን መመልከት ግዴታዋ ነው:: አስር ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ ይባል የለም እንዴ... በዚያ ላይ ፍቅር ውስጥ ይህ ሰው ነገ ሊጎዳኝ ይችላል ብለህ ካሰብክ ቀድሞውኑ አላፈቀርከም ማለት ነው:: ወደ ፍቅር ስትገባ "ፍቅር ሲአልም ገነትም ሊሆን ይችላል" የሚለውን መራር ሀቅ ማወቅ አለብህ! የሚመጣውን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለብህ... የምልህ "ነገ" በእኛ ቁጥጥር ስር የለችም!! መደራደር የምትችለው በ"ዛሬ" ላይ ብቻ ነው"

"በዚህ ሀሳብ እስማማለው"

"ቢሆንም ከልቡ የሚያፈቅርህን እውነተኛ አፍቃሪ ወይም የሚወድህን ሰው መለየት እኮ አትቸገርም:: ለምሳሌ ከአምስቱ የፍቅር እርከኖች ደረጃ አንድ በሆነ አጋጣሚ ከሆነ ሰው ጋር ብትጀናጀን.. ከዚያ ቀስ በቀስ ወደ ደረጃ ሁለት ቅርብ ግንኙነት ገብተህ ለምሳሌ አንተ ያፈቀርካትን ሴት መቀራረብ ፣ ቶሎቶሎ መገናኘት፣ ከእርሷ ጋር መወያየት፣ አብሮ ብዙ ሰዓታት ማሳለፍ ትፈልጋለህ... እሷ አንተ የምትሰጣትን ቦታ የማትሰጥህ ከሆነ ... ለምሳሌ ላንተ አሞኛል ብላህ ቤቷ ተኝታ በየደቂቃው ተጨንቀህ ጤናዋን እየደወልክ የምትጠይቃት ከሆነ በተቃራኒው ግን አንተ አሞህ እሷ ለአንተ ግድ የሌላት ከሆነ... አንተ ፍቅራችሁ ጠንክር የሚልበትን ዘዴ እየፈለክ እሷ ግድ የለሽ ከሆነች... ባጠቃላይ አንተ ውስጥ ያለው መሻት እና ተግባር እርሷ ጋር በተመሳሳይ ከሌላ አለመፈለግህን አውቀህ እንዴት አልተፈለኩም ብለህ እልህ ሳትጋባ ቶሎ መቀንጠስ ነው"

"እልህ ፍቅር አይጨምርም?"

"ቀላል! ይበልጥ እኮ ፍቅር ውስጥ ወድቀህ ስቃይህን የምትበላው ለምን አልተፈቀርኩም? እኔ ምን ያንሰኛል? ከእኔ ምን እጥታ ነው? እንዴት ቀርባ ትሸሽኛለች? በሚሉት ጥያቄዎች ይበልጥ ከራስህ ጋር ስትወዛገብ ይበልጥ ስለ ልጅቷ ብዙ ሰዓት ስለምታስብ አፍቅረሃት ትገኛለህ... የአብዛኛው የሴቶችም ሆነ የወንዶች ችግር ይህ ነው! በተለይ ማንም የጣለውን ሲያነሱበት ደስ አይለውም የሚባለው ግዙፍ እውነት ነው! በዚያ ላይ አንዳንዴ ስለ አንድ ነገር ይበልጥ ትልቅ ትኩረት የምትሰጠው ያን ነገር ስታጣው ነው!! ይህ ይህ ነገር በፍቅር ላይ እና ተፋቃሪዎች ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሯል! ወደፊትም ይፈጥራል"



Scanned by CamScanner

"እና ከፍቅረኛሽ ጋር ደረጃ ሶስት ልትገቡ ወስናቹኋል?"

"በትክክል!"

"ጥያቄ መቀጠል እችላለሁ?"

"መብትህ?"

"የትኛውን ነው? የመፈላለግ? የመሳሳም? የመሳብ? የወሲብ? የመነካካት? በደስታ የመሞላት?"

"ሁሉንም በተለይ ወሲብ ልትለው ትችላለህ"

"መጀመሪያ ማን ነው የጠየቀው?"

"ማንኛዋም ድንግል ሴት እስከ ጋብቻዋ ቀን ድረስ እኮ ድንግል ሆና ብትቆይ ደስ ይላታል! የግድ ሲሆን እና ፍቅረኛዋን ላለማጣት የምትፈልግ ከሆነ ብቻ ወደ ወሲብ ትገባለች... እሱም ቢሆን አፍቃሪዋ እስከ ሚጠይቃት ትጠብቃለች እንጂ አትጠይቅም... ለማንኛውም ፍቅረኛዬ ነው የወሲብ ጥያቄ ያነሳው"

"ስለዚህ ከጋብቻ በፊት ወሲብ ማድረግ ሀጢያት ነው የሚለውን ህግ..."

"ይህ ጥያቄ ይለፈኝ"

"እሺ ሌላ ጥያቄ"

" ቀጥል"

"እንቢ ብትይውስ ኖሮ?"

"I think ውሳኔዬን ይቀበለዋል ብዬ እገምታለሁ እኛ ሀገር ትልቁ ችግር የሀበሻ ወንዶችን ስለወሲብ ማሳመን ነው! የሀበሻ ወንዶችን በፍቅር ልታምናቸው ትችላለህ!! በወሲብ ግን ማመን አትችልም! እውነቱን ለመናገር ሴት አንድ ጊዜ ከልቧ ወንድን ካፈቀረች እንኳን ከሌላ ወንድ ጋር ወሲብ ለማድረግ ከንፈሯን እንኳ ማስነካት ሀጢያት ነው የሚመስላት! ወንዶች ግን ብዙም ጣጣ የላቸውም:: ብዙዎች የሚነግሩኝ ይህን ነው፤ ለዚያውም በተጨባጭ መረጃ አስደግፈው!! እስቲ አንተን አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ! በጣም የምትወዳት ፍቅረኛህን ወሲብ አምሮህ ወሲብ እናድርግ ብለህ ጠይቀህት እንቢ ብትልህ ምን ታደርጋለህ? ብዙ ጊዜ ወንዶች ለምትወዱዋት ሴት የወሲብ ጥያቄ የምታነሱት በጣም ወሲብ ሲያምራችሁ፣ ፍቅረኛችሁ እንደምትወዳችሁ ለማወቅ አልያም ለመለየት ሰበብ ፍለጋ ነው ይባላል"

"እህ... ለማሳመን ጥረት አደርጋለሁ! አሳማኝ ምክንያት ካላት እና ከልቤ የምወዳት



Scanned by CamScanner

ከሆነ እቀበላለሁ"

"እሺ ሁለተኛ ፣ ሶስተኛ ፣ አራተኛ... ጊዜ ጠይቀህ እንቢ ብትልህስ?"

"ቤርሲ!!"

"አቤት"

"አልዋሸሽም ! ከሁለት ጊዜ በላይ እንኳ አልጠይቃትም! መቼም ወሲብ እናቴ ላይ ከወጣ ሴጋ አልመታም"

"ሴጋ መምታት ችግር አለው?"

"በጣም!!"

"ንገረኝ"

"በእርግጥ በፊት ሴጋ መምታት ብዙም የሚጎዳ ነገር እንደሌለው፣ ያልበዛ ከሆነ ጥሩ እንደሆነ፣ ወጪ ቆጣቢ እንደሆነ ይወራ ነበር፤ በቅርቡ ተመራማሪዎች ሴጋ ላይ ጥናት አድርገናል! አዲስ ግኝት አግኝተናል አሉ"

"አሉ!!"

"አሉ!!"

"ይነገረኛ"

"ምነው ቸኮልሽ ሴጋ ትመቻለሽ እንዴ?"

"ሞዛዛ ነገር ነህ!!"

"እናልሽ በአዲሱ ጥናት ሴጋ በብዛት መምታት ሆነ ሱሰኛ መሆን ራስ ወዳድ ያደርጋል፣ ወሲብ ሲያደርጉ ቶሎ የመጨረስ ችግር ያስከትላል፣ ከተቃራኒ ፆታ ጋር በወሲብ ለመጣጣም እንከን ይፈጥራል! በተለይ ቆሞ ሴጋ መምታት ከነርቭ ጋር ለተያያዘ ችግር ያጋጥማል አሉ፡፡"

"ወደ ቅድሙ ጥያቄ እንመለስ፡፡ እና አንተ ብትሆን ምን ታደርጋለህ?"

"ያው plan B ነዋ!!"

"What's plan B?"

"እንዴ ቤርሲ ይህማ የወንዶች ጉዳይ ነው"

"ስለዚህ እኔ እንቢ ብለውም የእኔ ፍቅረኛ አንተ መናገር ያልፈለከውን plan B አለው ማለት ነው?"



Scanned by CamScanner

"No!! ሁሉም ወንዶች አንድ ናቸው እንዴ?"

"የሀበሻ ወንዶች ሁሉ ኮተት አያጣችሁም!!" አለችና ሣቀች፡፡

ከዚህ በላይ ስለ ቤርሲ መጻፍ አልችልም... ይህ ከቤርሲ የተሰጠኝ ማስጠንቀቂያ ነው... ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ አምስቱ የፍቅር እርከኖች የነገረችኝ ቤርሲ ነች፡፡ "አዘርግ" የሚለውን ስያሜ ያወጣችልኝም ቤርሲ ናት... የሀብታም ልጅ የነበረችው ቤርሲ እጅግ በርካታ መፅሐፍትን እንዳነብ በዩኒቨርሲቲ ቆይታችን ሳትሰስት ትሰጠኝ ነበር ... እነዚያ መፅሐፍት ለዛሬው ማንነቴ ትልቅ ድርሻ ነበራቸው... ያነሳሁትን የቤርሲን አንዲት ቁንፅል ታሪክ በቤርሲ የዘወትር አባባል ልጨርሳት፡-

"ሴት ልጅ ፍቅር በሌለበት መኖር አይቻላትም"



Scanned by CamScanner

# ቫዮርሲት ለገሰ

በዩኒቨርሲቲ መማር ደስ ከሚለው ነገር አንደኛው ከመላው የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚመጡ ተማሪዎች ጋር መተዋወቅ ፣ መረጃ መለዋወጥ፣ ባህላቸውን መረዳት፣ አመለካከታቸውን ማወቅ… የመሰሉት ናቸው፡፡ በተለይ ለእኔ አይነቱ የሥነ ፅሑፍ ቢጤ ፍቅር ላለው ደግሞ ትልቅ መነሳሳት ይፈጥርለታል! በሽ ገፀባህሪያትን ያገኛል! ህይወትን በተለያዩ መነጽራት ለማየት አሪፍ አጋጣሚ ያገኛል!

በእርግጥ ስለ አስራ ሶስቱ የፍቅር አይነቶችም ሆነ በዓለም ላይ ስላሉት የወሲብ አይነቶች በስፋት በኢያሪኮ 999 ላይ አብራርቻለሁ፤ በዚች ፅሁፍ ደግሞ የተወሰኑትን ብቻ በስም እንኳ ላስቃኛችሁ… በዚህ አጋጣሚ ስለ ወሲብ የተለያዩ መረጃዎችን እንዳጠራቅም ሆነ እንዳውቅ ያደረገኝ ገና የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለን በአርሰናል ኳስ የተነሳ የተዋወቅነው የዳንግላው ተወላጅ የሆነው ለገሰ ነበር፡፡

ለገሠ ለየት ያለ ወጣት ነበር፡፡ የሚያመሳስለን ሁለታችንም የኳስ አፍቃሪዎች መሆናችን ነበር፡፡ ያፋቀረን ቴሪ ዳንኤል አንሪ ነበር፡፡ ሁለታችንም የአንሪ አድናቂዎች ነበርን፡፡ ኳስ ካለ የቀደመ ወንበር መያዝ ግዴታው ነበር፡፡ በዚያው ጓደኛ ለመሆን ቻልን… በተለይ የለገሠ ወጣ ያለ ባህሪ ለሥነ ፅሁፍ የሚሆን ነበርና ለእኔ ተመቸኝ፡፡ አንድ ጊዜ ጨዋታ ጀመርን

"በጥንቁልና ታምናለህ?" አለኝ፡፡

"አላምንም"

"በመተት?"

"አላምንም"

"በሙጠምጢም?"

"አላምንም"

"በመስተፋቅር?"

"አላምንም"

"እናንተ የአዲስ አበባ ልጆች ደግሞ ትልቅ ችግር አለባችሁ!!"

"እንዴት?"



Scanned by CamScanner

"ቢያንስ በመስተፋቅር ማመን ነበረብህ"

"ሲባል እኮ እሰማለሁ ግን ፉገራ ነው የሚመስለኝ"

ለገሰ የሴት ነገር አይሆንለትም! እንደ ለገሰ ሴት ሲያይ አይኑ የሚፈጥ ወንድ አይቼ አላውቅም! ከዚያ ደግሞ የሚናገረውን ነገር አያጣም::

"ተመልከት ይቺ ሴት እምሷ ጣፋጭ ነው"

"በዓይን ዓይቶ መናገር ይቻላል?" እለዋለሁ::

"የሴት ልጅን እምስ ጣፋጭነት በተረከዟ ማወቅ ይቻላል! ይህ ደግሞ ሀቅ እንደሆነ በብዙ ምሳሌዎች አረጋግጫለው!!"

"ንገረኝ ዘዴውን"

የተለያዩ ሴቶች ሲያልፉ እያሳየ ይነግረኛል፤ የዚች ጣፋጭ ነው! የዚች ውሃ ውሃ የሚል ነው! የዚች ገራገር ነው! የዚች ግማታም ነው! የዚች ስሜት አልባ ነው!!

"መስተፋቅር አሰርተህ ታውቃለህ" አልኩት::

" ምን ጥያቄ አለው! ሁሉም እኛ ከተማ የሚጠቀሙበት ነው"

"ሁሉም? ለማመን እቸገራለው!!"

"በለው"

"እዚህ ዩኒቨርሲቲ ትጠቀምበታለህ?"

"ለእኔ ሳይሆን ለሁለት ልጆች አሰርቼ ተጠቅመውበታል!!"

"ሰውን በመተት መያዝ ግን Fair ነው?"

ዝም አለኝ::

"እሺ አንተስ? ማለቴ ያፈቀርካት ሴት የለችም ወይስ ሴት መጀንጀን ለአንተ ቀላል ነው?"

"አዎ ይህ ለእኔ ተራ ነገር ነው... ይልቅ አንድ ችግር አለብኝ፤ እዚህ ባህር ዳር ሆነ ዳንግላ እያለሁ ብዙ ጊዜ ከሴቶች ጋር ወሲብ ለማድረግ ጥሬ ነበር ፤ ግን ምንም አይነት ስሜትም ሆነ ደስታ አላገኘሁም!! እጅግ በጣም ከፍተኛ ደስታ የማገኘው የወሲብ ፊልም ሳይ አልያም ሌሎች ሰዎች ወሲብ ሲያደርጉ ስመለከት ነው... እዚህ ዩኒቨርሲቲ ከምሽቱ አምስት ሰዓት በኋላ ግቢውን እየዞርኩ ተደብቀው ወሲብ የሚያደርጉ፣ የሚሳሳሙ ተማሪዎችን ሳይ እንዴት በደስታ እፈነጥዛለሁ መሰለህ!!"



Scanned by CamScanner

"እየቀለድክ ነው"


"አባቱ ይሙት!!"

ይቺን ጉዳይ በመያዝ በዩኒቨርሲቲዎችን ውስጥ ስለ ወሲብ የሚያወሩ በርካታ መፅሐፍትን አየሁ፤ በቂ መረጃ የለም፡ ባህር ዳር ከተማ የሚገኘው እየሩሳሌም ቤተመፅሐፍት ውስጥ አንድ ግድንግድ የወሲብ መፅሐፍ ሳነብ መረጃውን አገኘሁ… በዓለማችን ላይ በተለያዩ ነገሮች የወሲብ እርካታ የሚያገኙ ሰዎች እንዳሉ ተገነዘብኩ፡፡ ከበርካቶቹ ጥቂቶቹን እነሆ:-

⇒ ቫዮርሲት (ቫዮሪዝም) (ቫዮሪስቶች):- ወሲብን በማየት ብቻ የሚደሰቱ… በተለይ ቀጥታ ወሲብ የሚያደርጉ ሰዎችን እየተመለከቱ የሚረኩ ሰዎች! እነዚህ ሰዎች በወሲብ ከፍተኛ እርካታ ላይ የሚደርሱት አልያም ስሜት ውስጥ ገብተው የሚረጩት ወሲብ በማድረግ ሳይሆን በማየት ብቻ ነው

⇒ፓራፊሊያ:- ድንበር የሳተ እና ጤነኛ ያልሆነ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ወሲብ በመፈፀም ልዕለ እርካታ ላይ የሚደርሱ ሰዎች ናቸው፤ በዚህ ስር የሚጠቀሱ 14 አይነት የወሲብ ዘሮች ቢኖሩም በኢያሪኮ 999 ላይ ያልተጠቀሱትን ብቻ እንመልከት

ፓራፊሊያ






Scanned by CamScanner

⇒ ሳዲዝም (ሳዲስት) እነዚህ ከሴቶች ጋር ወሲብ ሲያደርጉ ማሰቃየት የሚወዱ፣ ራሳቸውም መሰቃየት የሚወዱ፣ ጭካኔ የተሞላበት ወሲብ የሚያደርጉ... ሰውነታቸውን በመገረፍ የሚረኩ... ሴቷን በጣም እያሰቃዩ በሴቷ ስቃይ የሚደሰቱ ... ባስ ካለም በጥርሳቸው የሚነካከሱ ናቸው::

⇒ ማሶቺዝም:- ሴቶች ሲሆኑ ወሲብ ላይ እርካታ የሚያገኙት ወንዱ ሲያሰቃያቸው፤ ሲደበድባቸው... እያነሳ መሬት ላይ እያፈረጠ ወሲብ ሲፈጽምባቸው... እየደበደበ ሲያስለቅሳቸው ከፍተኛ ጉልበት እየተጠቀመ ብቻ ወሲብ ሲያደርጋቸው... የሚረኩ ናቸው፤ ወሲብ ላይ ከፍተኛ ስሜት ውስጥ የሚገቡት ወንዱ ሲቀጠቅጣቸው እና ሲወግራቸው ብቻ ይሆናል... ባጠቃላይ ስቃይ የተሞላበት ወሲብ ሲያደርጉ የሚረኩ ናቸው...

⇒ ዞፊሊያ :- ከሰው ልጅ ጋር አልያም ከተቃራኒ ፆታቸው ጋር ሳይሆን በወሲብ ከፍተኛ እርካታ የሚያገኙት ከእንስሳት ጋር ብቻ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉ ጥናቶች አህያ፣ በግ፣ ፍየል... በእነዚህ ሰዎች ይመረጣል፤ በተለይ በርካታ ከአህያ ጋር ወሲብ የሚያደርጉ አሉ እነዚህ ሰዎች ሚስት ቢያገቡ እንኳ እርካታ የላቸውም (በዚህ ጉዳይ ላይ ሹክቱስ መጽሐፍ ላይ በዝርዝር አስቀምጫለሁ)

⇒ ኔዎፊሊያ:- ከስምንት ዓመት በታች ከሆኑ ህጻናት ጋር ብቻ ወሲብ በማድረግ (በመድፈር) የሚረኩ አረመኔዎች ናቸው:: ትናንሽ ህፃናትን እየደፈሩ በህፃናቱ ስቃይ ከፍተኛ ሀሴት የሚያገኙ ሰዎች ናቸው..

⇒ ሎስት መርደር :- ከወሲብ እርካታ በኋላ (በብዛት የዚህ ወሲብ አባላት ወንዶች ናቸው) ወሲብ ያደረጓትን ሴት በማሰቃየት ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ እንዳታደርግ የሚገድሉ እና ከወሲብ በኋላ በመግደል ከፍተኛ የእርካታ ጫፍ ላይ የሚደርሱ ናቸው!! ... በጣም በርካታ ናቸው:: ከገዛ ልጃቸው ጋር ወሲብ ማድረግ የሚያረካቸው አሉ... ወንድምና እህት ወሲብ የሚያደርጉ አሉ (ቂብቶጥራ ወሲብ ይባላል)... ከአንድ ሰው ጋር ብቻ እስከ መጨረሻ ወሲብ ማድረግ የማይፈልጉ (ከአንድ ሰው ጋር አንድ ጊዜ ብቻ ወሲብ በማድረግ የሚለዩ አሉ)... እነዚህ ሰዎች በጭራሽ ፍቅረኛ የሚባል መያዝ አይፈልጉም... ብቻ ከወሲብ ጋር በተያያዘ ለማመን የሚያስቸግር እና ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም የሚባለውን የሀበሻ ተረት የሚያስታውሱ ዜናዎች እና እውነታዎች አሉ...



Scanned by CamScanner

ድብልቅልቅ የሆነችው ህይወት በፍላጎትም ድብልቅልቅ የሆኑ ሰዎችን ፈጥራለች!!
ድብልቅልቅ የሆነችው ህይወት በፍላጎትም ድብልቅልቅ የሆኑ ሰዎችን ፈጥራለች!! አይ ይቺ ህይወት ብለን መገረም ብቻ ይበቃል..??(በዚህ ኢጋጣሚ ሥነፅሁፍ ውስጥ ለመግባት የምትመኙ ወጣቶች እንዴት ወጣ ያለች መረጃ ስታገኙ እስከ መጨረሻ ሰፋ ያለ መረጃ ለማግኘት ጥረት እንድታደርጉ ምክር ቢጤ ለግሻለሁ! ለገፀባህሪያት ቀረፃ በጣም ይጠቅማቹዋልና... የአንዴት ነገርን መረጃ ለማግኘት ስታነቡ በዚያው በርካታ ነገሮችን በማንበብ አውቀት ታገኛላችሁና...)

ማጠቃለያ:- መልካሙ ዜና የዳንግላው ተወላጅ ለገሰ ከዩኒቨርሲቲ ምርቃት በኋላ ባህር ዳር በ2005 ዓ.ም ተገናኘተን... በከፍተኛ የሥነልቦና ምክር ራሱን በመለወጥ የነበረበትን የወሲብ ፊልም በማየት ሆነ... ወሲብ የሚያደርጉ ሰዎችን እየተደበቀ በማየት የሚረካውን ነገር በመተው እንዴት የዳንግላ ቀሽት መጥበሱን ሹከቱስ ብሎኛል፤ ለመሆኑ የተለየ የወሲብ ችግር ያለበት ፍቅረኛ ቢኖራችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

ሀ. መለየት

ለ. ችግሩን ለመቅረፍ መጣር

መልስ ______________________________

______________________________

______________________________

ምክንያት ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________



Scanned by CamScanner

# ምርጡ ቆሀልት

እነሆ በ2004 በኢያሪኮ መፅሐፍ ላይ ታሪኩን የፃፍኩለት አፍ የሚያስከፍተው የጆንቋ አስተማሪውን በ2006 ዓ.ም ትንሿ ስታዲየውም ዕለተ ማክሰኞ የእጅ ኳስ ለማየት ገብቼ ድንገት አገኘሁት፡፡ ሞቅ ያለ ሠላምታ ተለዋወጥን...

"እሺ"

"አማን ነው"

"መምህርነት?"

"ውይ ሳልነግርህ"

"ምኑን?"

"አበቃ"

"አበቃ?"

"በዚህ ዓመት መስከረም ላይ አቆምኩት"

"ለምን?"

"ለምን አይባልም! ኢትዮጵያ ውስጥ አስተማሪ ስራ ተውኩ ሲልህ እንኳን ደስ አለህ ነው የሚባለው"

"አንተ እኮ ብዙዎች የሚያከብሩህ አስተማሪ ነበርክ?"

"መኖር አለብኝ! የተሻለ ስራ አገኘሁ! ተውኩት! በእርግጥ የሆነ ጊዜ ወደ መምህርነት መመለሴ አይቀርም! እስከ መጨረሻውማ መምህርነቴን አልተውም"

"እና አሁን ምን እየሰራህ ነው?"

"ሙሉ ጊዜዬን ለፖለቲካ ሰጥቻለሁ፡፡"

ከዚህ ስራውን ካቆመ ድንቅ ብዙዎች ስለብቃቱ ሲያወሩለት ከነበረ መምህር ጋር በ2004 ዓ.ም ላይ ቋንቋን በተመለከተ ያወራሁትን መቼም ልረሳው አልችልም፡፡

"እንደነገርከኝ አንተ የኢንግሊዝኛ አስተማሪ ነህ?"

"ልክ ነው"

"ስንት ቋንቋ አቀላጥፈህ መናገር ትችላለህ?"



Scanned by CamScanner

"ኢትን የፎች ቋንቋ በተጨማሪ እየጠናሁ እገኛለሁ፣ ለጊዜው ሰባት ቋንቋ እችላለሁ"

"ሰባት?"

"አዎ"

"ማወቅ ይቻላል?"

"አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ጉራግኛ፣ ኢንግሊዝኛ፣ አረብኛ እና መንደሪና"

"ስለዚህ ከቋንቋ ጋር በተያያዘ በርካታ ስራዎች መስራት ትችላለህ ማለት ነው? በተለይ አስተርጓሚነት! የቋንቋ አስተማሪነት!..."

"ልክነህ"

"እንደ ኢንግሊዝኛ አስተማሪነትህ በቅርቡ በየትምህርት ቤቱ አማርኛ ቋንቋ እንዲነገር መንግስት እያደረገ ነው:: በየክፍላገሩ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲናገሩም እየተደረገ ነው! አንተ ይህን ሀሳብ ትቃወማለህ መሰለኝ"

"መቃወም አይደለም! ቋንቋ እኮ ውበት ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሉ መባል ራሱ እኮ ውበት ነው! እኔ ለቋንቋ ልዩ ፍቅር አለኝ! እስከምሞት ቢያንስ ወደ ሀያ የሚጠጉ ቋንቋዎችን ለማወቅ ጥረት አደርጋለሁ:: እናም ህፃናት አፍ በሚፈቱበት ቋንቋ ቢናገሩም ሆነ ቢማሩ መልካም ነገር ነው:: እኔ የምለው አፍ ከሚፈቱበት ቋንቋ ጋር መሳ ለመሳ ኢንግሊዝኛ ቋንቋንም በሚገባ እንዲማሩ ነው፤ ምክንያቱም ህጉን ያረቀቁልን ባለስልጣናት ይህ ጉዳይ ቁብ አይሰጣቸውም የእነርሱ ልጆች እኮ የሚማሩት እጅግ ውድ በሆኑ ት/ቤቶች እና የውጪ ሀገራትን የት/ት ፖሊሲ የሚከተሉ እንደ ሊሴ፣ ሳንፎርድ፣ አሜሪካ ስኩል፣ ብርቲሽ ኢንተርናሽናል፣ አይ.ሲ.ኤስ... መሰል እጅግ ወድ የግል ት/ቤቶች ውስጥ ነው:: በሌላ በኩል ከመንግስት ት/ቤት የጨረሱና ስማቸውን እንኳ በኢንግሊዝኛ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲገቡ መፃፍ የሚያቅታቸው በርካታ ከመንግስት ት/ቤት የወጡ ተማሪዎች አሉ! ኢንግሊዝኛ ተራራ የሚሆንባቸው አሉ... አየህ እኔ የምለው በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ት/ት የሚሰጠው ሙሉ ለሙሉ በኢንግሊዝኛ ቋንቋ እስከሆነ ድረስ ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ልዩ ትኩረት ለኢንግሊዝኛ ቋንቋ መስጠት አለባቸው ነው እንጂ ከዚህ ከማይረባው ዘረኝነት ጋር በተያያዘ አይደለም"

"ገብቶኛል! ይህን ጥያቄ ላነሳልህ ነበር:: በቅርቡ አንድ ምሁር ስሙን እናቆየውና ቋንቋ የማንነት መገለጫ ነው ሲል ሰማሁት! ይህን ሀሳብ እንዴት ትደውረዋለህ?"



Scanned by CamScanner

"ትደውረዋለህ?"

"አሀ"

"የዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ አነጋገር ነች?"

"አሀ"

"ማንነት በሚለው በጭራሽ አልስማማም! ቋንቋ መግባቢያ እና ማህበራዊ ህይወትን ቀላል ከሚያደርጉት አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው:: እኔ ቋንቋን ዘለው ከዘር ፣ ብሔር፣ ማንነት ጋር የሚያላትሙ ሰዎች አይመቹኝም:: ለምን መሰለህ ለምሳሌ እኔ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አማርኛ፣ ትግርኛ፣ አሮምኛ፣ እና ጉራግኛ እችላለሁ! በዚህ ስሌት አማርኛ ስለተናገርኩ አማራ ነኝ? አሮምኛ ስለተናገርኩ አሮሞ ነኝ? ትግርኛ ስለተናገርኩ ትግሬ ነኝ? ጉራግኛ ስለተናገርኩ ጉራጌ ነኝ ማለት ነው? በጭራሽ!! ይህ ተራ ተጠይቅ ነው! አንተ ፍላጎት ካለህ ብዙ ቋንቋዎች ማወቅ እና ማጥናት ትችላለህ! እኔ ኢንግሊዝኛ አቀላጥፌ እናገራለሁ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ!! አረብኛ አቀላጥፌ እናገራለሁ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ!! የቻይና ቋንቋ የሆነውን መንደሪና አቀላጥፌ እናገራለሁ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ... እንደዚህ በቀላሉ ማሰብ ነው እንጂ ከዘር እና ብሔር አልያም ማንነት ጋር ለማላተም ሙከራ የሚያደርጉ አዋቂ ነን ባዮች አይመቹኝም! ስለዚህ ቋንቋ ከመግባቢያነት ባለፈ የማንነት መገለጫ ነው የሚለው ሎጂክ አይዋጥልኝም:: ፍላጎት ካለህ ማንኛውንም ቋንቋ ማወቅ ትችላለህ:: የተለያዩ ቋንቋዎችን መናገር ትችላለህ!! በሌላ በኩል ቋንቋ ውበት ነው! አንድ የሚያደርገን ኢትዮጵያዊነታችን ነው:: የኢትዮጵያ ምሁራን ተብዬዎች አንዳንዴ እንደ ጭልፋ ጠማማ አስተሳሰብ ነው ያላቸው:: በህዝቡ መሀከል ፍቅር እና ኢትዮጵያዊነትን ከመስበክ ይልቅ የሆነ ምድብ እንዲወዳቸው ከመፈለግ ብቻ የተሳሳተ ቀመር ለማስተጋባት ጥረት ያደርጋሉ! በዚህ አጋጣሚ ስለ ሬኔ ዴካርት ላንሳልህ! መቼም ታውቀዋለህ?"

"አዎ 1596 ዓ.ም በፈረንሳይ የተወለደ እድሜ ልኩን ሳያገባ በወንደላጤነት ያሳለፈ ምርጥ ፈላስፋ እና የሂሳብ አዋቂ የነበረውን?"

"ትክክል! ከሬኔ ዴካርት ሁለት የምወድለት ምርጥ አባባሎች አሉት:: የመጀመሪያው ጥሩ ጭንቅላት መያዝ ብቻ አይበቃም ዋናው ቁም ነገር ጥቅም ላይ የማዋሉ ጉዳይ ነው ሲል ሁለተኛዋ ደግሞ ታላላቅ ጭንቅላቶች ታላላቅ ስራዎችን ለማበርከት የሚችሉትን ያህል ግዙፍ ተንኮልንም ሊፈፅሙ ይችላሉ... የሚሉ ናቸው:: እነዚህን አባባሎች የተናገረው ኢትዮጵያ



Scanned by CamScanner

ወሳኝ ምሁራን ነን ለሚሉት ሰዎች ይመስለኛል!! ብዙ ጊዜ እኛ ሀገር ሳስተውል የኢትዮጵያ ምሁራን ችግርን ከመፍታት ይልቅ ችግርን ሲያባብሱ እና ትንሽ ችግር የነበረችውን ይበልጥ ሲያገዝፉዋት እመለከታለሁ!! የሀገርን ችግር የማይፈታ ምሁር ደግሞ በቁሙ የሞተ ነው.. የዚያን ዕለት ከወጣቱ መምህር ጋር ብዙ ነገር ነበር ያወራነው:: ያ ምርጥ መምህር የነበረ ወጣት ዛሬ ትልቁን የመምህርነት ሙያውን በመተው ከፖለቲካው ጎራ መቀላቀሉን ሲነግረኝ ይቺ ኢትዮጵያ አንድ ምርጥ የቋንቋ አስተማሪዋን ስላጣች እውነቱን ለመናገር ደስታ አልተሰማኝም ነበር... በወጣቱ ውሳኔ መግባት ብችል እንዴት ሀሴት በተሰማኝ ነበር... ግን አልቻልም!!

ስለዚህ ወጣት በ2007 ዓ.ም በሰማሁት ዜና ይበልጥ ሀዘኔን ጨመረው! በዚህ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ በሆነ ፖለቲካችን የተነሳ እስር ቤት ገባ የሚል ዜና ነበር የተነገረኝ... አይ አንቺ ኢትዮጵያ በማለት ከራሴ ጋር እሰጥ አገባ ሰጠምኩ...::

(ማስታወሻ:- ከቋንቋ ጋር በተያያዘ ብዙ መረጃዎችን ከፈለጉ ኢያሪኮ 888ትን ይመልከቱ)



Scanned by CamScanner

# የፍቅር ተመን

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ በፍልስፍና ፍቅር እብድ ካሉ ተማሪዎች አንደኛው ደምሴ ወራሽ ነበር፡፡ ቶሎ ቶሎ ማውራት የሚወድ የጎንደር ልጅ ነበር፡፡ የዚህ ወጣት ስም "ዣን ዣክ ሩሶ" ነበር፡፡ ስለፈረንሳዊው የፍልስፍና ጸሐፊ ሳያወራለት የሚውልበት ቀን የለም... ብዙዎች በአጋጣሚ አንዲት የፍልስፍና መፅሐፍ አነበበ ያቺ ደግሞ የዣን ዣክ ሩሶ ነች! ከዚያ ውጪ ስለማንም ቢጠየቅ የማያውቅ ጨዋ ነው እያሉ የቅርብ ጓደኞቹ ይቦጭቁት፤ ይከትፉት ነበር... ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ምሽት በዩኒቨርሲቲያችን ዝነኛ በሆነው ብሶት አደባባይ ጋር ተገለተን

"በነገራችን ላይ ይቦጭቁሃል" አልኩት

"ምን እያሉ?"

"ከሩሶ ሌላ ፈላስፋ አያውቅም! ስለዚያ ነው በየቀኑ ባገኛት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ሩሶ የሚያወራው ይሉሃል"

"ሩሶ ምን ይላል መሰለህ? 'ዓለም እያንዳንዱ ሰው ልዩ ልዩ ገጸባህሪያትን ወክሎ የሚጫወትባት አሰቂኝ የትያትር መድረክ ናት' በዚህ መሠረት አንዳንዶች ሰውን ለማማት እና ለቡጨቃ ብቻ ይፈጠራሉ! በተለይ አንዱ በዋነኛነት የሚቦጭቀኝ ሀይሌ ነው፤ በጣም የሚገርምህ አንድ ጊዜ መኝታ ቤቱ ስሄድ የኢንግሊዛዊውን ፈላስፋ ጃን ሎክ እና የቮልቴርን ሁለት መፅሐፍት ይዞ አየሁት! ለአራት ቀናት ብቻ አንብቤ ለመመለስ ለመንኩት! ግግም አለ! በጭራሽ እንደማይሰጠኝ ነገረኝ! አየህ የሀበሻ ባህሪ! እንዳነብ ሰጥቶኝ ሳላነብ ቀርቼ ቢቦጭቀኝ ደስ ይለኛል... የሀበሻ ትልቅ ድከመት እና ችግር ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" ,

"ንገረኝ"

"ምንም ነገር ሳያደርግልህ ሺ ነገር ካንተ ይጠብቃል! የሆነች ነገር ስትጠይቀው ይሸሽሃል! ለማንኛውም ከሀበሻ ጋር መኖር አስቸጋሪ ነው፤ ቢሆንም በሩሶ ገለፃ 'ሰው ነፃ ሆኖ የተወለደ ቢሆንም የትም ቦታ የሚገኘው በእስር ላይ ነው' ስለሚል ሁሉንም ችለህ መኖር ነው፡፡ የሚገርምህ በ1718 ዓ.ም በጄኔቭ ውስጥ የተወለደው ሩሶ ገና የ12 ዓመት ልጅ እያለ ወደ ሰዓት አዳሽ አባቱ ጋር አመራ፡፡ የሩሶ አባት ልጃቸው የእርሳቸውን ሙያ በሚገባ ቀስሞ እንቱ



Scanned by CamScanner

የተባለ ሰዓት አዳሽ እንዲሆን ነበር፤ እርሱ ግን ገና በልጅነቱ ልቡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የበሬተ ነበር፤ እናም ለአባቱ ገና ትንሽ ብላቴና እያለ ጥያቄ አነሳለት

' አባቴ '


' አቤት '

' ሰዎች ሁሉ ስለ አንተ ጥሩ ነገር የሚያወሩት እና አንተን ሲያዩ የሚደሰቱት ለምንድን ነው?'

' ሰዎች እንዲወዱህ ከፈለክ ሁሌ ትልቅነት እንዲሰማቸው አድርግ! እኔም ያን ዘዴ እየተጠቀምኩ ነው' ነበር ያሉት:: አየህ በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የእኔን በርካታ የፍልስፍና መፅሐፍት አንባቢነት የሚያወሩ ከሆነ እኔን ያነግሱኛል! የእኔን አላንባቢነት እያወሩ እነሱ አንባቢ እየመሰሉ ይነግሳሉ! ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግዙፍ ችግር አዋቂ መስሎ መታየት እና አዋቂ ለመባል በከንቱ መዳከር ነው!! ቀኝም ነፈስ ግራ ትልቁ እውነታ እኔን አደነቁኝ፣ በጨቁኝ፣ በሀሜት ከተፉኝ ምንም አይመስለኝም!! ምክንያቱም ከ እያንዳንዱ ሀሜተኛ እና በጫቂ ጀርባ አላዋቂነት አለችና"

ደምሴን ሁሌ የማስታውሰው ስለ ፍቅር ጨዋታ አንስተን ባጫወተኝ ጉዳይ ነው:: ስለ ፍቅር እዛው ብሶት አደባባይ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ እያለን ያስረዳኝ ይህን ነበር

አስኪርቢቶ አውጥቶ በወረቀት ላይ ሁለት ስዕል መሰል ነገሮች በመስራት አሳየኝ...






Scanned by CamScanner

"አስረዳኝ"

"አትቸኩል"

"እሺ"

" አምላክ እሺ ይበልህ "

"እሺ"

" እሺ ሳይሆን አሜን ነው የሚባለው"

"አሜን!!"

"ቁጥሩ የአፍቃሪዎች የልባቸው ምት ከ 120% ሲቀመጥ ሲሆን፣ ድሮ ፣አሁን፣ ወደፊት የሚባሉት የፍቅር ጊዜያት በዘመን ሲመዘኑ ናቸው፤ ይህ ግራፍ ይበልጥ እንዲገባህ በምሳሌ ላስረዳህ"

"ደስ ይለኛል"

"ስለ ፍቅር ሲነሳ ሁለት አሪፍ አሪፍ ታሪኮች አንብቤያለሁ! አንደኛዋ በ1826 ዓ.ም ገደማ በኢንግሊዝ ሀገር የተጻፈች ነች፡፡ አንድ ወጣት በአንዲት ሴት ፍቅር እብድ አለ! ይቺን ያፈቀርኳትን ሴት ካላገባው እኔ ከንቱ ነኝ! ይቺ ሴት ለእኔ ዓለሜ ናት አለ! የሚገርመው የዚያች ሴት አባት ደግሞ ልጁን በጣሙን ይወዳት ነበርና ያ ወጣት ለአባቷ የፍቅር ጥያቄ ሲያቀርብላቸው በደስታ ተውጠው


"እንደምትለው ልጄን ትወዳታለህ?"

"በቃላት መናገር አልችልም"

"ፈተናውን ካለፍክ ያንተ ናት"

"የምን ፈተና?"

"እስከዛሬ ልጄን ለማግባት 18 ወንዶች ወድቀዋል ... አንተ... ብለው ፈተናውን ነገሩት"






Scanned by CamScanner

ሁለት ቤቶች አሉ፡፡ ሁለቱም ቤቶች ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ከሁለቱ ቤቶች ውስጥ አንደኛው ውስጥ ያቺ ውብ ሴት አለች፤ ሁለተኛው ቤት ውስጥ አንድ የተራበ አንበሳ አለ ... ስለዚህ የምትወዳት ከሆነ በድፍረት ከሁለቱ ቤቶች አንደኛውን መርጠህ ከፍተህ ትገባለህ! የፍቅር አምላክ ከረዳህ ፍቅረኛህን ታገኛለህ! የፍቅር አምላክ ካልረዳህ በተራበው አንበሳ ትበላለህ እስከዛሬ አስራ ስምንቱ ልጇን እንወዳታለን ያሉ ወንዶች ፈተናውን እንፈተንም ብለው ጥለው ሄደዋል' አሉት፡፡ ያ በልጅቷ ፍቅር ከንፍ ያለው ወጣት 'ምንም ችግር የለም እወዳታለሁ! ፍቅሬን በተግባር ጭምር አገልፃለሁ' በማለት ማለ፡፡ ቀን ተቆረጠ፡፡ አንድ ማለዳ ጠዋት ከሁለቱ ቤቶች በድፍረት በልቡ ለፍቅር አምላክ እየፀለየ ከሁለቱ ቤት አንደኛው ጋር ገባ፡፡ የፍቅር አምላክ ከእርሱ ጋር ስላልነበረች በተራበው አንበሳ ተቆርጥሞ ተበልቶ ሞተ... ይህ የድሮ ታሪክ ነው፡፡ በቅርቡ በ1998 ያነበብኩትን ታሪክ ልቀጥልልህ?"

"ቀጥል"

"ሁለት በፍቅር ሰክረናል! በፍቅር አብደናል! ካንተ ውጪ ጨርሶ ለአንዲት ደቂቃ እንኳ ልኖር አልችልም! ካንቺ ውጪ ለአንዲት ሴኮንድ እንኳ ጨርሶ ልተነፍስ አልችልም የሚባባሉ ሁለት ፍቅረኞች እጅግ ረጅም ተራራ ላይ ወጡ፡፡ በፍቅር ታሪክ አዲስ ነገር ሰርተው ስማቸውን ሊያስጠሩ ወሰኑ፡፡ ብዙ ከተወያዩ በኋላ በቃ ከዚህ ተራራ ላይ ተፈጥፍጠን እንሙት! ተባባሉ! ተስማሙ! እጣ ሲጣጣሉ ወንዱ መጀመሪያ ወጣለት! የፍቅረኛውን ከንፈር ሳም አደረገና ከተራራው ላይ ዘለለ... ይህን ያየችው አፍቃሪው ውዴ እወድሃለሁ! እስከሞት የሚያደርስ ፍቅር ግን የለኝም! አዝናለሁ! ብላ ከተራራው ላይ መውረድ ጀመረች... ወደታች በፍጥነት እየተንደረደረ ያለው ወንድ አፍቃሪ... ይሄኔ እሷም ከተራራው ላይ ራሷን ወደታች ፈጥፍጣለች ስለዚህ ምንም ብወዳት ራሴን መግደል የለብኝም በማለት በጀርባው ከጃኬቱ ጋር በድብቅ አድርጎት የነበረውን ፓራሹት (መንሳፈፊያ) ጠቅ አድርጎት በአየር ላይ መንሳፈፍ ጀመረ!! ይህ የሁለቱ ታሪክ የዘመኑን የፍቅር አካሄድ ይጠቁመናል!!"

"ወደፊትስ?" አልኩት፡፡

"ይቺ ምድር የምትጠፋው በ2929 ዓ.ም ነው፡፡ ይቺ ምድር ከመጥፋቷ በፊት በ2626 ዓ.ም ዓለምን የሚያስተዳድራት ሴይጣን (ሊሲፈር) (666) ይሆናል!! በዚያን ጊዜ አንተ እንዲትን ሴት ስታፈቅር የፍቅር መገለጫህ የሚሆነው በዚህ ዘመን እንዳለው ያቺን ሴት



Scanned by CamScanner

አግብቶ አብሮ መኖር፣ ልጅ መውለድ... ወዘተ ሳይሆን የምትወዳትን ሴት እንዳፈቀርኳት ለመግለፅ ያቺን ሴት መግደል ይሆናል፣ ምናልባት ይሄ ምን ይገርማል? በዚህ ዘመንም ስለማፈቅራት እያሉ የሚገድሉ አኮ አሉ! ሰምተናል! ብለህ ልትጠይቀኝ ትችል ይሆናል! በዚያ ዘመን መግደል ወንጀል አይሆንም!! በዚያ ዘመን መግደል ወንጀል የሚሆነው የገደልከውን ሰው በምግብ መልከ አልበላም ካልከ ብቻ ይሆናል!! ስለዚህ በዚያ ዘመን የፍቅር መገለጫ መግደል እና መመገብ ይሆናል ማለት ነው:: ያወራሁልህ ስለ ዖታዊ ፍቅር መሆኑን ግን እንዳትዘነጋ" ነበር ያለኝ::

ደምሴ በአሁኑ ሰዓት አንድ የፍልስፍና መፅሐፍ አዘጋጅቶ እያጠናቀቀ ይገኛል... እስቲ ይቺን የደምሴን ወሬ አንብባችሁ ስትጨርሱ አንድ ጥያቄ ለራሳችሁ አንሱ... ለመሆኑ ለምታፈቅሩት ሰው ሆነ ለፍቅር የእናንተ የፍቅር ተመን የት ድረስ ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ምክንያት _______________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________



Scanned by CamScanner

# አውን መማር ያስከብራል!

# ሀገርን ያኮራል ...??

ሐምሌ 5፣ 2007ዓ.ም ከጠዋቱ 5:00 ሰዓት ላይ ... በዚች ቀን ዕለተ እሁድ እቤት ውስጥ ነበርኩ:: የተለመደውን ከ5-6 ሰዓት የሚቀርበውን የእሁድ የስፖርት ዝግጅት ለማየት ብዙም የማልመለከተውን እና የማይመስጠኝን EBC ስከፍት ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ቀጥታ ስርጭት ለመጀመሪያ ጊዜ ዩኒቨርሲቲው ያስመረቃቸውን ተማሪዎች በተመለከተ ዝግጅት እየታየ ነበር:: ብዙም ሳይቆይ ፊደል ባንድ መማር ያስከብራል ... መማር ያስከብራል... ሀገርን ያኮራል... ጥበብን..." የሚል የተለመደች ዜማ አቀረቡ...

ብቻዬን ስለነበርኩ በቀጥታ ራሴን የጠየኩት እውነት እምዬ ኢትዮጵያ ውስጥ መማር ያስከብራል?? እውነት እማማ ኢትዮጵያ ውስጥ መማር ሀገርን ያኮራል?? ለመሆኑ ይቺ እማማ ኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ ከመላው አገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ከ30 በላይ ዩኒቨርሲቲዎች... ከብዙ የመንግስትና የግል ኮሌጆች ውስጥ እጅግ በርካታ ተማሪዎች በተለያዩ ማዕረግ ይመረቃሉ... ይህ እውነት ነው:: ለአንዲት ታዳጊ ሀገር እጅግ በርካታ የተማሩ፣ እውቀታቸውን በንባብ ያዳበሩ፣ በተግባር የተፈተሹ፣ አመለካከታቸውን በቀለም ትምህርት የሞሉ፤ ምሩቃን ለአንዲት ሀገር ወሳኝ ናቸው!! ብስራት ናቸው!! ትልቅ የምስራች ናቸው::

ዋናው ጥያቄ ግን እውነት ይቺ እማማ ኢትዮጵያ ለመሆኑ በየዓመቱ ምን ያህል ተመራቂ ተማሪዎችን ነው የምትፈልገው? ... እውነት በመላው አገሪቱ የሚመረቀው ይሄ ሁሉ ወፈዘራሽ ተመራቂ! በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ተመራቂዎች... እውነት በቂ እውቀት! በቃል ሳይሆን በተግባር የተፈተነ እውቀት! በራስ መተማመን የተሞላበት እውቀት! ራስን ሆነ ይቺ ኢትዮጵያ የምንላትን አገራችንን ለመለወጥ በሚያበቃ ጠንካራ የማይናወጥ ማንነት የተሞሉ ናቸውን?? ወይስ ለወሬ እና ለቱልቱላ ብቻ ባዶ ጭንቅላት ላይ ቆብ የመድፋት ድራማ ነው?? እውነት እንነጋገርና ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ለጥራት ነው ለቁጥር??

ለምንድን ነው እጅግ በርካታ ተማሪዎች ስራ አጥተው የበዘኑት? ለምንድን ነው



Scanned by CamScanner

ከዩኒቨርሲቲዎቻችን በዲግሪ /ዲፕሎማ... የተመረቁ በርካታ ኢትዮጵያዊያን አንስቶች ስራ አጥተው ገላቸውን እየሸጡ ለመኖር ምሽት በየጎዳናው ራቁት ቀረሽ ልብስ ለብሰው የሚቆሙት?... ለምንድን ነው ከብራቸውን የሸቀሉት? ለምንድነው በየጫት ቤቱ የሚገኙት?

በዓለማችን ላይ እንደ ህንድ ከዩኒቨርሲቲ መመረቅ ተራ የሆነባት እና እንደ ብርቅ የማይታይባት ሀገር የለችም:: በህንድ አገር መመረቅ ተራ ነገር ነው:: ለምሳሌ በህንድ በ1998 ዓ.ም በተደረገ ጥናት ከህንድ መላው አገሪቱ በዓመት ውስጥ ከሚገኙት University of madras, University of Calcutta, university of Mumbai... ከመሰሉት ከ1857 ዓ.ም ጀምሮ ከተጀመሩት ዩኒቨርሲቲዎች ጨምሮ በህንድ ውስጥ ህጋዊ እውቅና ያላቸው 724 ዩኒቨርሲቲዎች እና 1360 ኮሌጆች ይገኛሉ ... ከእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች መሀከል በእርግጠኝነት በስራ ገበታ ላይ የሚገቡት 35% ቱ ብቻ ናቸው:: እንግዲህ 65%ቱ ስራ አጥ ናቸው ማለት ነው ወይም በእኛ ሀገር መጤ ቋንቋ "ይደራጃሉ" ማለት ነው... እንግዲህ ይህ ለህንድ ትልቅ ከስረት ነው... በህንድ ዲግሪ መያዝ ጠብ የሚል ነገር አይፈጥርም...!!

ይህ የህንድ ታሪክ በእማማ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይከሰት ከህንድ ድክመት መማር በፍጥነት አለብን ... መንግስት እንደሚለው "ተማሪዎች የመንግስትን እጅ ሳይጠብቁ በራሳቸው ስራ ፈጣሪ ይሆናሉ" የሚል ከሆነ ለተማሪዎች ከአስረኛ ክፍል ጀምሮ ስለ ስራ ፈጣሪነት ማስተማር አለብን:: ዲግሪ አስይዞ ድንጋይ ማስጠረብ ስራ ፈጣሪነት አይደለም!! ተማሪዎች በራስ መተማመን እንዲኖራቸው፣ ራሳቸውን እንዲችሉ ገና ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ ህይወታቸውን እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ ማስተማር አለብን እንጂ አንዳች መሠረት የሌለው እና ስለ ኢንተርፕሬነርሺፕ ምንም ያልተማረን እና ምንም እውቀት የሌለውን ወጣት ድንገት " በል ዲግሪ ይዘሃል የራስህን ስራ በመፍጠር ተዳደር እንጂ መንግስት ስራ አይሰጥህም!" ማለት ስላቅ ይመስለኛል... ለእኔ:: ሀቅም ነው:: በዚች ደቂቃ ከራሴ ጋር የተወያየሁት ይህን ነው:: ስለዚህ ምን ይሻላል??

እስቲ ተማሪዎችን ለአላማ የምናስተምራቸው ከሆነ ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቅ:: ከመላው ሀገሪቱ በየዓመቱ ከሚመረቁት ተማሪዎች መሀከል ምን ያህሉ

⇒ በነባር የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ይቀጠራሉ?



Scanned by CamScanner

⇒ በአዲስ የሚከፈቱ የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ይቀጠራሉ?

⇒ በነባር የግል መስሪያ ቤት ውስጥ ይቀጠራሉ?

⇒ በአዲስ የግል መስሪያ ቤት ውስጥ ይቀጠራሉ ?

⇒ ስንቶች የራሳቸውን ስራ ይጀምራሉ ?

⇒ ስንቶች በማህበር ይደራጃሉ?

⇒ ስንቶች ወደ ውጪ ሀገራት ይጓዛሉ ?

⇒ ስንቶች ስራ አጥ ሊሆኑ ይችላሉ ?

... እነዚህን ወሳኝ ጥያቄዎች መጠየቅ ብርቅ መቼም አይሆንም! ከዚያ በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች እንዳሉ በእርግጠኝነት ይታወቃል:: ስንት ተማሪዎች በየዓመቱ እንደሚመረቁም በእርግጠኝነት ይታወቃል (ማወቅ ይቻላል)... ተማሪን በየዩኒቨርሲቲው አስመርቀው የራስህ ጉዳይ ! የአርባ ቀን እድልህ ያውጣህ ማለት ተገቢ አይደለም!! ተማሪዎች ለቁጥር ሳይሆን ለተግባር መመረቅ ይኖርባቸዋል... ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ግራ የሚገባኝ ይህን ትውልድ ትልቁም ትንሹም እየተነሳ "ያትውልድ እንዲህ ነበር ይህ ትውልድ እንዲህ ነው" የሚሉት ጉድ ነው:: ምንም በሌለበት ወጣቱን የሚቀጠቅጠው እና ሂስ መስጠት የሚወደው መብዛቱ ነው:: ይህ ነገር ብዙ የሚያነጋግር ስለሆነ ለማንኛውም የእኔን እይታ በሚከተሉት መልኩ አስቀምጫለሁ:-

⇒ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ሆኑ ኮሌጆች ለቁጥር ብዛት ሳይሆን በጥራት የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ለማስመረቅ ጥረት ቢያደርጉ! እያግበሰበሱ ባያስመርቁ::

⇒ ወጣቱ ከምርቃት በኋላ የመንግስትን ሆነ የግል መስሪያ ቤቶችን ከፍት የስራ ቦታ መጠበቅ የለበትም! በራሱ ስኬታማ መሆን አለበት! ከተባለ ገና ከሁለተኛ ደረጃ (ከተቻለ ከመጀመሪያ ደረጃ) ለተማሪዎች ስለ ገንዘብ አያያዝ፣ ስለ አላማ፣ ለምን እንደተፈጠርን፣ ስለ ስኬት ፣ ስለ ኢንተርፕሬነርሺፕ፣ በግል እንዴት ስኬታማ መሆን እንደሚቻል፣ ስለ ለውጥ... ስለበራስ መተማመን... ጠንካራ ትምህርት እየሰጡ ማሳደግ እንጂ ምንም ነገር ባልተማሩበት ቅድመ ሁኔታ ከመሬት ተነስቶ ከምርቃት በኋላ የራሳችሁን ስራ ፍጠሩ እያሉ በአዕምሮ ዝግጁ ያልሆኑትን እና ስለ ጠንክሮ መስራት ምንም ግንዛቤ የሌላቸውን ተማሪዎች መወጠር ትርፉ ጭንቀት መጨመር ብቻ ይሆናል! ለስደት ልባቸውን ማነሳሳት ይሆናል::



Scanned by CamScanner

⇒ ስራ የሚገኝባቸው መንገዶች ኢትዮጵያዊነት እና በቂ እውቀት መያዝ እንጂ በዘመዳዘመድ ፡ በሙስና፣ በዘረኝነት፣ በፖለቲካ ንኪኪ ላይ ያልተመሠረተ ማድረግ ተቀዳሚ መርህ መሆን ይኖርበታል!!

⇒ ለወጣቶች ከቃል ትምህርት ይልቅ በተግባር ላይ የተመሠረተ በራስ መተማመን እንዲኖራቸው የሚያደርግ እውቀት መሙላት ይጠበቃል፡፡

⇒ ከቤተሰብ ጀምሮ በልጆች አስተዳደግ ላይ ለውጥ ማምጣት ልጆች የእግዜር ፀጋ ናቸው እየተባለ ሚዛን በማይደፋ ምክንያት ከአቅም በላይ የሆኑ ልጆችን መፈልፈል ትርፉ ለራስም ለሀገርም ሸክም መሆን ስለሆነ የሚወለዱት ልጆች መጠን ላይ ግልፅ ውይይት ማድረግ ይጠበቃል...

⇒ እጅግ በተወሰኑ ሰዎች እጅ ላይ የሚገኘው የሀገሪቱ ሀብት እና የተወሰኑ ሰዎች ፈላጭ ቆራጭ የሆኑበት አሰራር በፍጥነት ሊወገድ ይገባል!!

⇒ እያንዳንዱ ዜጋ ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊ እና ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል አዕምሮ እንዲኖረው የሚያስደርግ የትምህርት መርህን መዘርጋት!! ልጆችን በሀገር ፍቅር እየሞሉ ማሳደግ ሊጠቀሱ ይችላሉ !

ከዚህም በላይ የተሻሉ በርካታ ሀሳቦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ መቼም እነዚህን መላምቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ምሁራኖቻችን ጆሮ ዳባ ልበስ ካልሆነ በስተቀር አይገነዘቡትም ማለት ስላቅ ይሆንብኛል... ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ችግር የተፈጠረው እኔ ካገኘሁ ስለሌላቸው ምን አገባኝ! እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አይነት ሰዎች መብዛት እና የግል ጥቅም አፍቃሪነት ይመስለኛል እንጂ እማማ ኢትዮጵያ ለዘጠና ሚሊዮን ህዝቦቿ ቀርቶ ለሌላውም የሚበቃ ሀብት አላት!! በዚህ እርግጠኛ ነኝ!!

ለማንኛውም ወጣቶች በፈተናዎች ብዙም ሳትረበሹ ከጥልቅ ጨለማ ውስጥ የብርሃን ፍንጣቂ ለመፈለግ ጥረታችሁን እንዳታቋርጡ... ህይወት ጥረት እና ትግል ትሻለች!! ከምንም በላይ በአንድ ነገር ግብ ለመምታት ጠንካራ ዲሲፕሊን ያስፈልጋል... በዚህ ደግሞ ታዋቂው ደራሲ ስቴቨን ኮቪይ "በሰባቱ የስኬታማ ሰዎች ባህሪያት" መፅሐፍ ውስጥ ያስቀመጠው አንዱ ወሳኝ ጉዳይ Begin with the end in mind ነው፡፡ የመጨረሻውን አውቆ መጀመር!! ወዴት እንደምትሄድን የማታውቅን መርከብ ንፋሱም አያግዛትም ይባል የለንስ?? አለበለዚያ ስኬታማ መሆን አይቻልም፡፡ ወጣቶች ምንም ሆነ ምንም ራሳችሁን ለመለወጥ ከመጣር እንዳትቦዝኑ...!!



Scanned by CamScanner

# 4 ወሳኝ ጥያቄዎች ...

ለሚስቱ ባል ፍሊጋ የሚለውን መጽሐፍ አርማት ለመስራት እንዲሁም ራሴን Re-freash ለማድረግ በጣም ወደ ምወዳት ሀዋሳ ሄጄ ነበር... አጅግ የሚያዝናናኝ ሌዊ ሪዞልት ውስጥ በመቀመጥ ሐይቁን በተመስጦ እያየሁ ሳለ ነበር አጠገቤ አንዲት ሴት መጥታ የተቀመጠችው:: ገና እንደተቀመጠች ቀድማኝ ሠላምታ የሰጠችኝ እርሷ ነበረች፤ ወዲያው እኔ ገመትኩ፤ ይቺ ሴት በእርግጠኝነት ከአፍሪካ ሀገር የመጣች ነች!!

ቀለል ያለች ነች:: ደስ የሚል ኢንግሊዝኛ ትናገራለች ፤ ብዙ ሳንቸገር መበርጨቅ ጀመርን:: ከኡጋንዳ የመጣች የጋብቻ አስተማሪና አማካሪ ነች... ስለ ኡጋንዳ ሆነ ስለ ኢትዮጵያ በመጠኑ መረጃ ተለዋወጥን:: ባለቤቷ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ እና ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ እንደመጣች አወጋችኝ ... ከዚያ አጋጣሚውን በመጠቀም ከሙያዋ ጋር በተያያዘ አስር ጥያቄዎችን አነሳሁላት!! ይቺ የ26 ዓመት ኡጋንዳዊት እያብራራችልኝ ነገረችኝ:: ከአስሩ ጥያቄዎች እነሆ አራቱን ብቻ ላቃምሳችሁ:-

1

"ለምንድን ነው ሴቶች ከወንድ ይልቅ ብዙ የሚያወሩት?"

"ልክ ነው በአሁኑ ወቅት በርካታ ጥናቶች እንዳረጋገጡት በአንድ ቀን ውስጥ ወንዶች በአማካኝ ከ18ሺ እስከ 23 ሺ ቃላትን ይጠቀማሉ ፤ በተቃራኒው ሴቶች ከ38ሺ እስከ 43ሺ ቃላትን ይጠቀማሉ:: አየህ ወንዶች ነገሮችን በቀላሉ እና በተመረጡ ቃላት ማስረዳት ሲችሉ ሴቶች አንድን ተመሳሳይ ነገር ለማስረዳት ከወንዶች የበለጠ ቃላትን ይጠቀማሉ፤ ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች ብዙ ባወሩ ቁጥር ውስጣቸው እርካታ ይሰጣቸዋል፤ ለዚያ ነው ሴቶች ከልቡ ለሚያዳምጣቸው ወንድ ልዩ ቦታ የሚሰጡት:: ዋናው ማወቅ ያለብን በተለይ ሴቶች ችግራቸውን ሲያወሩን በቀዳማዊነት ለችግራቸው መፍትሔ እንድንሰጣቸው ከሚል አስቤ ሳይሆን እንድናዳምጣቸው ብቻ ስለሚፈልጉ ነው:: ከልብ ማዳመጥ ራሱ ትልቅ ህክምና መሆኑን ወንዶች እስካሁን አልተረዱላቸውም! አያሳዝንም? የብዙ ሴቶች የበሽታ ምንጭ ከልብ የሚያዳምጣቸውን ወንድ ማጣት ነው:: አይገርምም?"

2



Scanned by CamScanner

"ከሴቶች የወር አበባ ጋር በተያያዘ በእርግጥ ተፈጥሮአዊው በሆነው መንገድ ማለትም በቀን ቆጠራ አንዲት ሴት እርግዝናን መከላከል ትችላለች? የእውነት ይሠራል?"

"why not?" በማለት ጀመረች፡፡

"ይሠራል፤ ነገር ግን ይህ የቀን ቆጠራ ዘዴ በእርግጠኝነት ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ለሆኑ ሴቶች ብቻ ነው እንጂ በየወሩ በተለያየ ምክንያት የወር አበባ አመጣጣቸው ለሚዛባ ሴቶች በጭራሽ አይሠራም፡፡ ይህን ነገር በምሳሌ ላስረዳህ?"

"እደሰታለው"

"ለምሳሌ አንዲት ጤነኛ የሆነች ሴት የወር አበባዋ ሳይዛነፍ በየ28 ቀናት ይመጣል እንበል፤ ይቺ ሴት የወር አበባዋ የማይዛነፍ ከሆነ የወሲብ ህይወቷ ላይ መቼ እንደምታረግዝ እና መቼ ወሲብ ብታደርግ እንደማታረግዝ ማወቅ ትችላለች፤ ይህን በስሌት ማየት እንችላለን፡፡

$$\left\{ \begin{array}{l} 28 \div 2 = 14 \\ 14 - 4 = 10 \\ 14 + 4 = 18 \\ \text{(10 - 18 ባሉት ቀናት)} \end{array} \right\}$$

ይህ ቀመር የወር አበባ ሲካፈል ለሁለት፣ የተገኘው ውጤት ሲቀነስ አራት እና ሲደመር አራት በሚል ስሌት ይሰላል፤ ይህን ግኝት በምርምር ያገኘችው ኢንግሊዛዊት ተመራማሪ ናት፤ በዚህ መሠረት ይቺ ሴት ከ10-18 ባሉት ቀናት በእርግጠኝነት ልታረግዝ ስለምትችል መጠንቀቅ ይኖርባታል፡፡ በሌላ በኩል ማርገዝ ከፈለገች በእነዚህ ቀናት ቀን ሳይሆን ምሽት ላይ ወሲብ ብታደርግ ይመከራል፡፡



Scanned by CamScanner

የወሩ ቀናት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | |
| 28 | 29 | 30 | | | |

9 ቀናት ሲደመር
አምስት (9+5)
14 የእርግዝና
ቀናት አሉ!!

ተጨማሪ ምሳሌ

አንዲት ጤነኛ የሆነች እና ያለመዛባት በየ ሀያ ስድስት ቀናቱ ልዩነት የወር አበባዋ የሚመጣባት ሴት በቀመሩ መሠረት

A÷ 2 = B-4 /B+4 =C

26 ÷2 = 13

13– 4 = 9

13 + 4 = 17

(ከ 9-17 ባሉት ቀናት)

እንዳልኩህ ይህ ቀመር በእርግጠኝነት የሚሰራው ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ለሆኑ እና የወር አበባ ዑደታቸው ለማይዛባባቸው ሴቶች ብቻ ነው:: ለሁሉም ሴቶች ስለማይሠራ መጠቀም የለባቸውም:: በዚያ ላይ በቅርቡ በተደረሰበት ጥናት የወንድ ስፐርም ከ5 እስከ 6 ቀናት በሴቷ ማህፀን ግርግዳ ላይ ሳይሞት ሊኖር ስለሚችል በጣም መጠንቀቅ ይገባል::"

## 3

"ከወሲብ ጋር በተያያዘ የወሲብ ችሎታ እና ፍላጎት እድሜ በጨመረ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል የሚል ጥናት አንብቤ ነበር ልክ ነው??"


" 100% ትክክል ነው:: አሁንም የምናወራው ለጤነኛ ሰዎች እና ምንም አይነት የወሲብ ማነቃቂያ ስለማይጠቀሙት ሰዎች ብቻ ነው:: ይህ ጥናት የወሲብ ማነቃቂያ የሚጠጡ ሆነ የሚዋጡ ኪኒኖችን የሚጠቀሙትን አይመለከትም:: በዚህ መሠረት በአሳማኝ



Scanned by CamScanner

ምርምር በተደረሰበት ግኝት በዚህ መልኩ ማየት እንችላለን፡፡

የወሲብ ብቃት እና ፍላጎት




(የእድሜ መጠን)

ይህ ማለት ለምሳሌ አንድ ጤነኛ ከ16-19 ዓመት ያለ/ያለች ወጣት በአንድ ወር ውስጥ ለ14 ጊዜያት ወሲብ የማድረግ ችሎታም ሆነ ፍላጎት ይኖራቸዋል ማለት ነው፤ እንደምንመገበው ምግብ አይነት፣ እንደየ እምነታችን ፣ ስለ ወሲብ ባለን አመለካከት ፣ እንደተፈጥሮአችን እንዲሁም በብዛት ስለ ወሲብ የምናስብበት አጋጣሚዎች የወሲብ ፍላጎታችን ከፍ ሆነ ዝቅ ሊል ይችላል፡፡ እዚህ ጋር ሴተኛ አዳሪዎች በቀን ውስጥም ሆነ በወር ውስጥ ከበርካታ ወንዶች ጋር ይወጣሉ፤ ይህ ጥናት ታማኝነቱን አያሳጣውም ወይ ላልከው ጥያቄ ሴተኛ አዳሪዎቹ እያደረጉ ያሉት እውነተኛ ስሜት ውስጥ እየገቡ ሳይሆን የውሸት ድራማ እና የማስመሰል ድርጊት ብቻ ነው 'ፋልሴቶ' ወሲብ ይባላል"



Scanned by CamScanner

## 4

"ከአድሜ ጋር በተያያዘ በተለይ አንዲት ሴት በስንት ዓመት የሚበልጣትን ወንድ ብታገባ ይመከራል?"

"በእርግጥ ፍቅር ህግ የለውም፤ ደንብ ግን ይኖረዋል! ፍቅር በእድሜ ልዩነት አይወሰንም!! ቢሆንም ወሲብ ግን ይወሰናል፤ ባጠቃላይ የሰዎችን ፍላጎት መግታት ሆነ በምርጫቸው መግባት ተገቢ ባይሆንም እንደጋብቻ አስተማሪነቴ እና አማካሪነቴ ከወሲብ ጋር በተያያዘ በጋብቻ ውስጥ ግጭት እንዳይኖር አልያም ከሁለቱ አንዳቸው እንዳይወሰልቱ አንዲት ሴት ከ9-14 ዓመት በላይ የሚበልጣትን ወንድ ባታገባ ይመረጣል፤ በወሲብ አለመጣጣም የተነሳ ትዳራቸው እንዳይቀዘቅዝ ወንዶች ደግሞ በእድሜ ከ5-9 ዓመት የምትበልጣቸውን ሴት ባያገቡ ይመከራል፡፡ እርግጥ ፍቅር በእድሜ ልዩነት ሊገደብ አይችልም!! አንድን ሰው ስናፈቅር ደግሞ ከነድክመቱ ጭምር ማፍቅር አለብን"

ይቺን ፅሁፍ በኡጋንዳዊቷ ወጣት ንግግር ማጠናቀቁ ተገቢ መሰለኝ...

"ብዙ ሀገራት ዞሬያለው እንደ ኢትዮጵያ ሴቶች በተፈጥሮ ውብ ቆዳ ያላቸውን አላየሁም! ይህ በጣም የሚገርም ነው! እነዚህ ውብ ሴቶች ከሚገኙበት ሀገር ባል በማግኘቴ ደግሞ እድለኛ ነኝ እላለው!!"



Scanned by CamScanner

# የባርነት አይነቶች

እውነተኛ ስሟ ባይሆንም በሸርብትን መፅሐፍ የተነሳ ስለ ማሳጅ ቤት የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት በቀልጣፋው ዳዊት መ. የተነሳ ያገኘዋት ቤቲ ቀልጣፋ ቢጤ ነች!!

"እንደተነገረኝ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀሻል?"

"ተመርቄያለው"

"ምን አጠናሽ?"

"ሶሲዮሎጂ"

"ታዲያ ሶሲዮሎጂ እና ማሳጅ ቤት ምን አገናኛቸው?"

"ብዙ ጣርኩ ስራ የለም ስለዚህ ለጊዜው ገንዘብ ስለሚያስፈልገኝ ገባሁበት! ጥሩም መጥፎም ነገር አለው (ስለማሳጅ ቤት አስገራሚ ህይወት በዝርዝር ሸርብትን መፅሐፍ ላይ ከበቂ በላይ መረጃ እና ታሪክ ስላለ በዚህ ላይ መድገም ማሰልቸት እንዳይሆንብኝ ፈርቼ ተውኩት)

"በተመረቅሽበት ሙያ ባለመስራትሽ ማን ነው የከሰረው?"

"እኔም! ኢትዮጵያም ከስራለች! የሚገርምህ በተመረኩበት ስራ ባገኝ ራሱ ማታ ማታ ማሳጅ የምሠራ ይመስለኛል:: ጥሩ ገንዘብ ከማግኘት በተጨማሪ ስለ ወንዶች ፀባይ ለማጥናት አሪፍ ቦታ ነው"

(እኔ ቤቲን የፈለኩበትን ጉዳይ እንደጨረስኩ በቀጥታ ወደ ቤቲ ጉዳይ ገባሁኝ)

"ዩኒቨርሲቲ እያለሽ መጽሐፍ ፅፈሽ ነበር?"

"ሁለት ምዕራፍ ነገር ይቀረኛል 90% የሚሆነውን ጨርሻለው፤ ቀሪውን የሆነ ጊዜ ላይ ሰረጋጋ እጨርሰዋለሁ የሚል ግምት አለኝ"

"ስለ ሀሳቡ ማውራት እንችላለን?"

"ስለ ባርነት የሚያወራ ነው!! ባርነት ድሮ ነበር፤ አሁንም ዘመናዊ ባርነት አለ! ወደፊትም ባርነት መልኩን ቀይሮ ይቀጥላል... በዚህ መልኩ የኔ መፃፍ የሚያውጠነጥነው በተለያዩ ይጠቅሙናል ብለን በምናስባቸው ነገሮች እንዴት ባርነት ውስጥ እንደምንገባ የሚያሳይ ነው:: በጣም በርካታ ከሆኑት እኔ ያነሳሁት አስራ ሁለቱን ብቻ ነው እነዚህም ...



Scanned by CamScanner

⇒ የሀይማኖት ባርነት

⇒ የአስተሳሰብ ባርነት

⇒ የጠባብነት ባርነት

⇒ የዘረኝነት ባርነት

⇒ የፍቅር ባርነት

⇒ የጥገኝነት ባርነት

⇒ የገንዘብ ባርነት

⇒ የወሲብ ባርነት

⇒ የሱስ ባርነት

⇒ የጊዜን ጥቅም ያለማወቅ ባርነት

⇒ ማንነትን የማጣት ባርነት

⇒ ለምን ምድር ላይ እንደ መጣን ያለማወቅ ባርነት... እየህ እኔ የምፅፈው መፅሐፍ እንደ ልቦለድ እየፈጠርኩ የምትቸከችከው አይደለም፤ ብዙ መፅሐፍትን ማገላበጥ፣ ከብዙ ባለሙያዎች ጋር መረጃ መለዋወጥ አለብህ፡፡ ለምሳሌ ስለ ሀይማኖት ባርነት ለመፃፍ ከበርካታ የተለያዩ የሀይማኖት ሰባኪዎች ሆነ የቲዎሎጂ ሰዎች ጋር ማውራት አለብህ፡፡ ሀይማኖት ምንድን ነው? ሰዎች ለምን ሀይማኖት ያስፈልጋቸዋል? የሀይማኖት ባርነት ምንድን ነው? ጉዳቱስ ምን ያክል ነው? መሰል ጥያቄዎችን ለመዳሰስ ጥረት የሚያደርግ መፅሐፍ ነው!! በህይወት ላይ ልክ እያደረክ መስሎህ እስረኛ ሆነህ ትቀራለህ!! በብዛት ባርነት ውስጥ የምንገባው ስለ አንድ ነገር በስሱ ብቻ በማወቃችን የተነሳ የሚከሰት ነው”

“ባጠቃላይ በህይወታችን ውስጥ ማንኛውም ሰው በእርግጠኝነት በአንድ አይነት ባርነት መታሰሩ አይቀርም፡፡ አሉታዊ ባርነት እንዳለ ሁሉ አዎንታዊ ባርነትም አለ፡፡ ለምሳሌ አንዲት ሴት ፍቅር ያዘኝ በሚል ሰበብ አንድን ወጣት ወዷ ህይወቷን በአግባቡ ላትመራ ትችል ይሆናል!! በሌላ በኩል በፍቅር የተነሳ ደግሞ የፍቅር አነቃቂ ሀይልን በመጠቀም ሕይወቱን ቀና የሚያደርግም አለ፡፡ ከእያንዳንዱ ስኬት ጀርባ ፍቅር ሊኖር የግድ ነው፡፡ ወሲብ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ የወሲብ እስረኛ መሆን ደግሞ ባንጻሩ ህይወታችንን ያበላሻታል፤ በተለይ ብዙዎቻችን ግራ የምንጋባው ለምን ምድር ላይ እንደመጣን ባለማወቅ ባርነት የተነሳ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ሳስብ የነበረውን ልንገርህ?”



Scanned by CamScanner

"እሺ!!"

"ከልጅነቴ ጀምሮ በጣም ይማርከኝ የነበረው ነገር ጥያቄ መጠየቅ ነበር:: እናቴን እማሚ ለምንድነው ምድር ላይ የመጣሁት? ስላት ጥሩ ሚስት እና እናት ለመሆን አለችኝ:: አባቴን ስጠይቀው ጥሩ ህይወት ኖረሽ ለመሞት አለኝ... ቤታችን የሚመጣን ቄስ ስጠይቀው እግዚአብሔርን ለማገልገል አለኝ... አንድ ወጥ የሆነ መልስ አላገኘሁም ነበር እናም ይቺን ጥያቄ ለማወቅ ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ ራሴን በጥልቅ መጠየቅ እና ምላሽ ለማግኘት መትጋት ጀመርኩ!! እየህ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ትልቁ ስኬት የሚባለው ምድር ላይ ለምን እንደመጣ በተደጋጋሚ ራሱን ከጠየቀ በኋላ ምላሽ ሲያገኝ ነው:: መጀመሪያ ገደማ ብዙዎች እየደጋገሙ ሲነግሩኝ እኔ ምድር ላይ የመጣሁት ጥሩ ሚስት እና ልጆች ለመውለድ ብቻ እንዳልሆነ አወኩኝ:: በእርግጥ እናቶች ልጆችን በማሳደግ የሚያጠፉት ጊዜ በዋዛ የሚታይ አይደለም!! ለዚያ ነው ከእያንዳንዱ ስኬታማ ወንድ ጀርባ አንዲት ጠንካራ ሴት አለች የሚባለው፤ ግን የሴቶች ስኬት ከቤት አደባባይ ላይ የሚታይ ጭምር መሆኑ ገባኝ! ልጅ መውለድ ፣ ባል ማግባት ለሴት ልጅ ህይወቷን ጣፋጭ የሚያደርጉላት ነገሮች ናቸው እንጂ የመጨረሻ የሴት ህልም ጥሩ ሚስት በመሆን የወንድን እጅ እየጠበቀች መኖር አለመሆኑን ተረዳሁ:: በልጅነቴ የነበረውን የሴት ልጅ ትልቁ ስኬት ጋብቻ ነው የሚለውን ሀሳቤን ሰረዝኩት፤ ግን አሁን ድረስ በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ጉዳይ ብዙዎች ለምን ምድር ላይ መጣሁ? ለሚለው እጅግ ወሳኝ ጥያቄ ምላሽ ካላገኙ በሕይወታቸው ግራ የተጋቡ ይሆናሉ"

"አልገባኝም?"

"ምኑ?"

"እና አሁን በእርግጠኝነት አንቺ ምድር ላይ የመጣሽበት ዓላማ ምንድ ነው?"

" በተመረኩበት ሶሲዮሎጂ በሚመጡት አስር ዓመቶች የማህበረሰቡን ችግር የሚቀርፉ አራት ጥናቶች ለማጥናት እቅዴን ጨርሻለሁ:: ለጥናቴ የሚረዳኝ ገንዘብ ለማሰባሰብ የግድ መስራት ነበረብኝ፤ ለጊዜው በማሳጅ ቤት አገኘሁ፤ በእርግጠኝነት ይህን ስራ ማቆያ እንጂ የእኔ ዓላማ ስላልሆነ ባልተወውም ብዙ ጊዜዬን አላጠፋበትም:: ከጥናቴ ባሻገር ብዙ ማንበብ እና ከብዙ ሰዎች ጋር በመገናኘት የምጽፈውን ያን የመጨረሻ ሁለት ምዕራፍ የቀረኝን ወደ ሥነ ልቦና የሚጠጋውን መፅሐፌን ማሳተም ሌላው እቅዴ ነው::"

"እሪፍ ነገር ነው:: ስላንቺ ከዳዊት ጋር በትንሹ ስናወራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወንዶች



Scanned by CamScanner

ንክ ናት ይሉሽ ነበር"

ሣቀች።

"ኢጋነንከው!! ንክ ሳይሆን ሴቷ ሶቅራጥስ ነበር የሚሉኝ"

"ለምን?"

"እንደምታየኝ እና ብዙዎች ሳይሆን ሁሉም ወንዶች እንደሚሉኝ ቆንጆ ነገር ነኝ፤ በእርግጥ የሴት ልጅ ውበት መሆን ያለበት ቀና አስተሳሰቧና ሩቅ አሳቢ መሆኗ ነው። ሴላ ርዕስ አላንሳልህና ጥያቄህን በአጭሩ ለመመለስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተለይ የመጀመሪያ ዓመት ላይ ለሴት ልጆች ትልቅ ፈተና የሚሆነው የትምህርቱ ከባድ መሆን ሳይሆን በየደቂቃው ሊጀነጅኗት ከሚመጡ ወንዶች ምላስ ራሷን መጠበቅ ነው፤ በተለይ የሶስተኛ ዓመት እና ተመራቂ ተማሪዎች አቤት! ፍሬሽ ተማሪ የሆነች ሴትን ለመጥበስ ያላቸው ጉጉት! ሴራ! ውጣውረድ! የውሸት ክምር! የቃላት ክምር!... ያን ነገር ማለፍ ነው ለሴቶች ትልቅ ፈተና የሚሆነው፤ ይህን ነገር ገና ከሀይስኩል ጀምሮ እሰማ ስለነበር ይህን የወንዶች የጅንጀና መሰናከል እንዴት መወጣት እንዳለብኝ ሳውጠነጥን ቆየሁና ድንገት የፈላስፋውን ሶቅራጥስን ታሪክ በማንበብ ሳጣጥም በዚያው የሶቅራጥስ የመጠየቅ ስልት ለእኔ እንደሚሰራ አወኩኝ። ተገበርኩት። የሀበሻ ወንዶች ደግሞ ጥያቄ የምታበዛ ሴት ስለማይወዱ በቀላሉ ይርቁኛል። ለእኔ እንደሀበሻ ወንዶች ምኝ የለም!! የሀበሻ ወንዶች ሴትን በቶሎ ያምናሉ! የሀበሻ ወንዶችን በቀላሉ መግደል የምትፈልግ ከሆነ ሁለት ነገር ብቻ ማድረግ ይበቃል

- በሚያስቀውም በማያስቀውም ነገር መገልፈጥ
- አንተ እኮ የተለየህ ወንድ ነህ ማለት!! ቢቃ የሀበሻ ወንዶችን በእነዚህ ሁለት ነገሮች በቁጥጥር ስር ማድረግ ትችላለህ። ለማንኛውም በርካታ ወንዶች ሊጀነጅኑኝ ሲጠጉ... እኔ በጥያቄ አወጥራቸዋለሁ"

"ለምሳሌ?"

"እስቲ ብዙ ምስኪን ወንዶች በሚጠቀሙበት የጅንጀና አባባል እኔን አናግረኝ"

"እንዳንቺ ያለች ውብ አይቼ አላውቅም"

"ውብ ነው ያልከኝ?"

"የተለየች ውብ!!"

"ውብ ምንድን ነው? ውብ ለመሆኔ ምን ማስረጃ አለህ? የውበት መስፈርቱ ምንድን



Scanned by CamScanner

ነው? ውብ ባልሆን ኖሮ አታናግረኝም ነበር ማለት ነው? ለመልከ ጥፉ ሴት ከብር የለህም ማለት ነው? የእግዜር ፍጡር የሆኑትን የሰው ልጆች ውብ ነሽ መልከጥፉ ነሽ ብሎ መጥራት ተገቢ ነው? እስከዛሬ ስንት ውብ ሴቶችን ጀነጀንክ? ውብ ብለን የምንጠራው ነገር ለመሆኑ ውብ ሆኖ ስለተፈጠረ ነው ወይስ ውብ ነው ብለን ስለተስማማን ነው? መሰል ጥያቄዎችን በማከታተል አንዳችም ፈገግ ሳልል እጠይቃለሁ... አንዳንዶች በፀሐይ ሙዝ ቀቅለን የበላን አራዳ ነን ባዮች የጅንጀናውን ዘዴ ለወጥ በማድረግ ከእኔ ውበት ይርቁና ስለሌላ ነገር ለማውራት ይሞክራሉ፤ ለምሳሌ ስንት ሰዓት ሆነ? የሆነቦታ ልጠይቅሽ? እባክሽ ስልኬ ባትሪ ዘግቶ ነው ምልክት አድርጊልኝ? እህቴን ትመስያለሽ... ዛሬ ቀኑ ደስ አይልም? የሆነ ቦታ አውቅሻለሁ እንዴ? ሻይ ልጋብዝሽ... ይህ ሙዚቃ አያምርም? አንድ ቀልድ ልንገርሽ? መሰል ከሰዎች ጋር ለመግባባት ይረዳሉ የሚባሉ የመተዋወቂያ ንግግሮችን ይጠቀማሉ፤ እኔ ከወንዶች ጋር በነፃነት ማውራት እወዳለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን ንግግሮች በመጠቀም ወደ ጅንጀና እናመራለን ካሉ እኔም በመጡበት ሀሳብ ጥያቄዬን መቀጠሌን አላቆምም!! በነገራችን ላይ ሰዎችን ጥያቄ እንደመጠየቅ እና መልሱን እንደ መስማት የሚያረካኝ ነገር የለም፡፡ በእኔ የህይወት ልምድ የተረዳሁት ግን የሀበሻ ወንዶች አዋቂ እና አዋቂ መስላ የምትታይን ሆነ በእውቀት የምትበልጣቸውን ሴት ይሸሻሉ! ይህ ጥልቅ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ ርዕስ ይመስለኛል፤ ምናልባት ከባርነቶች አንደኛው ይሆናል!!"

በጣም የሚገርመው ይህን ጉዳይ እና ስለማሳጅ ከቤቲ ጋር ካወራን ሶስት ወራት በኋላ ሁለት ዜናዎች የቤቲ የቅርብ ጓደኛ እና ያስተዋወቀኝ ዳዊት መ. ነገረኝ፡፡ ጥሩ እና መጥፎ ዜና!!

"ቤቲ UN ውስጥ በተመረቀችበት ስራ ጀመረች ... እንዲሁም ቤታቸው በእሳት ተቃጥሎ ስትፅፈው የነበረው መፅሐፍ ተቃጠለ" የሚል ነበር፡፡ ስለ የባርነት አይነቶች የሚያወራው መፅሐፍ በመቃጠሉ የእውነት አዝኛለሁ... አንድ መፅሐፍ በድጋሚ በመጀመሪያው ሙድ ሆኖ መፃፍ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ በሚገባ አውቃለሁ!! የቤቲ የባርነት መፅሐፍ በድጋሚ ህይወት ዘርቶ ለህትመት እስከሚበቃ በወሬያችን መሀከል በጣም እንደምታደንቀው በነገረችኝ በዝነኛው የሥነ ባህርይ ተመራማሪ በሆነው ሲግመንድ ፍሮይድ ተወዳጅ ወርቅማ አባባል የቤቲን ቁንፅል ታሪክ ልቋጭበት፡

"ማንበብ ያለብን ለመቃረን ወይም የሰውን ስህተት ለመፈለግ ሳይሆን ለመዘመን፣ ለመማር፣ ራስን ለመለወጥ እና ለማወቅ ይሁን!!"



Scanned by CamScanner

# የወሲብ ጥያቄ ...?

በእርግጥ ይህ ከወሲብ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ጥያቄ በኢያሪኮ 999 እና በኢያ ከተማ በሚለው መፅሐፍት ላይ በሰፋት ያነሳሁት ቢሆንም እነሆ በመጠኑ አንዲት ታ በማንሳት ለመከለስ ልጣር፡፡

ከበርካታ የተለያዩ ሴቶች ጥያቄዎች በአጭር የፅሁፍ መልዕክት ይመጡልኛል በተለይ የዲያና ጥያቄ በቂ እና የሌሎችን ሴቶች ጭምር የሚወክል ይመስለኛል... ለማንኛውም ለዲያና ደውዬላት ያወራነውን እነሆ!

"እኔ ድንግል ሴት ነኝ፤ እስካሁን ከወሲብ ጋር በተያያዘ አራት ወጣቶችን አጥቻለሁ"

"እንዴት?"

"ለወሲብ ይጠይቁኛል እንቢ ስላቸው ይለዩኛል"

"የቆዩበት ጊዜ?"

"የመጀመሪያው ሁለት ዓመት፣ ሁለተኛው ፍቅረኛዬ አንድ ዓመት ፣ ሶስተኛው ፍቅረኛዬ አራት ወር... በቅርቡ የተለየኝ የመጨረሻ ፍቅረኛዬ አምስት ወራት ብቻ ቆይተን ተለያየን፤ በዚህ የተነሳ እየተጎዳሁ ነው! ለምንድነው ወንዶች ሁሉ ለወሲብ የሚፈልጉኝ?"

"ስንት ዓመትሽ ነው?"

"በቅርቡ 25 ይሞላኛል"

"ከጋብቻ በፊት ወሲብ ማድረግ ያልፈለግሽው በየትኛው ምክንያት ነው

ሀ. ከጋብቻ በፊት ወሲብ ማድረግ ሀጢያት ስለሆነ (ሀይማኖታዊ)

ለ. ከወሲብ ጋር ከሚመጡ ችግሮች ራስን ለመጠበቅ

ሐ. ወሲብ ካደረኩ ወንዶች ይሸሹኛል ፍርሃት (ተጠቅመው ይጥሉኛል)

መ. የቤተሰብ ህግን በማክበር?"

"ትልቁ ምክንያቴ 'ሀ' ነው፡፡ ጋብቻ ቅዱስ ነው ብዬ ስለማምን ወሲብ ለመጀመ የወሰንኩት ሳገባ ብቻ ነው"

"ይህ የማይሻር ውሳኔሽ ነው?"

"አዎ!"

"ጥሩ! ይህን ውሳኔሽን ለአራቱ ወንዶች አስቀድመሽ ነግረሻቸው ነበር?"



Scanned by CamScanner

"ማለት?"

"ፍቅረኛ ለመሆን ስትስማሙ እና ስትግባቡ ከወሲብ ጋር በተያያዘ በጨዋታ መልክ ነግረሻቸው ነበር?"

"አልተናገርኩም"

"ስለዚህ አንቺ ጋርም ጥፋት አለ፤ ምክንያቱም ሁሉም ባይሆን አብዛኛው ወንድ ፍቅርን የሚፈልገው በወሲብ ውስጥ ነው፤ ይህ የአብዛኛው ወንድ ስለ ፍቅር ያለ እሳቤ ነው:: አብዛኛው ወንዶች በቅድሚያ ወሲብ ቀጥሎ ፍቅር የሚል እና ወሲብን በቀላሉ የመመልከት ነገር አላቸው ፤ ይህን የወንዶች ባህሪ ማወቅ አለብሽ:: በዚያው ልክ ደግሞ ልክ እንዳንቺ ከወሲብ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ አቋም ያለው ወንድ አታጪም:: ካንቺ ፍልስፍና ጋር የሚዛመድ ትክክለኛ ወንድ ግን አልመረጥሽም ወይም ስለምርጫሽ መረጃ አልሰጠሻቸውም"

"እንዴት?"

"ለምሳሌ ከመጀመሪያው ሆነ ከሁለተኛው ፍቅረኛሽ ጋር በወሲብ የተነሳ ስትለያዩ ሶስተኛ ለመጣው ወይም አራተኛ ለመጣው ፍቅረኛሽ ከሁለቱ ወንዶች ጋር በምን ምክንያት እንደተለያያችሁ አልነገርሻቸውም?"

"አልተናገርኩም"

"በህይወታችን ላይ እኮ አንድ የማንደራደርበትን ውሳኔ ስንወስን ያን ውሳኔያችንን በግልፅ መናገር ሆነ ማሳወቅ ይኖርብናል:: በተጨማሪ በውሳኔያችን የተነሳ የሚያጋጥመንን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል ራሳችንን ዝግጁ ማድረግ አለብን፤ ስለዚህ ይህን ውሳኔሽን ፍቅረኛ ለመያዝ ስትወስኚ በሚገባ በግልፅ መወያየት እና ውሳኔሽን የሚያከብር ሆነ እንዳንቺ ተመሳሳይ አመለካከት ያለው አፍቃሪ ማግኘትሽ አይቀርም የሚል ተስፋ አለኝ"

"ጥፋተኛ ነሽ እያልከኝ ነው?"

"በጭራሽ:: ውሳኔሽን ከልቤ አከብራለሁ!! ውሳኔሽን በግልፅ ብትናገሪ ያንቺንም የወንዶቹንም ጊዜ ሳይቃጠል ነገሩን መፍታት ትችያለሽ! ወንዶቹን ተጠያቂ ከማድረግ በተጨማሪ አንቺም በውሳኔሽ እስከ መጨረሻ እፀናለሁ ካልሽ እና ያመንሽበት ነገር መስዋዕት የሚጠይቅ ከሆነ መስዋዕት መክፈል አለብሽ:: ትክክለኛውን ወንድ እስከምታገኚ ፍሊጋሽን መቀጠል አለብሽ ግን በግልፅ ተናገሪ!!"

"እሞክራለሁ"



Scanned by CamScanner

"በነገራችን ላይ ፍቅረኛሽ ችግር የለውም ወሲብ ጋብቻ ስንፈፅም እንጀምራለን አለሽ ማለት ሙሉ ለሙሉ ያፈቅርሻል ማለት ላይሆን ይችላል"

"ማለት?"

"አንዳንቹው በሀይማኖት የተነሳ ከጋብቻ በፊት ራሱን ከወሲብ ግንኙነት ያራቀ ካልሆነ በስተቀር ካንቺ ሌላ ከሌሎች ሴቶች ጋር ወሲብ እያደረገ ስሜቱን ማስተንፈስ አለ ይችላል! ይህንንም ማጤን ተገቢ ነው"

በእርግጥ እኔ የስነልቦና ባለሙያ አይደለሁም:: ከዚች ወጣት ጋር ያወራሁት በቀላል ተጠይቃዊ ህግ (Logic) መሠረት ላይ ብቻ በመንተራሳት ነው:: ለማንኛውም ተፋቃሪዎች ከወሲብ ጋር በተያያዘ በነፃነት እና በግልፅነት እንድታወሩ ምኞቴ ነው:: በሁለት ፍቅረኞች መሀከል ግን መቼም ቢሆን ትልቁ ጥያቄ ከወሲብ ጋር በተያያዘ መሆኑ ይቀጥላል... ፍቅር ካለ የወሲብ ጥያቄ አይቀርም... ትልቁ ቁም ነገር እንዴት አፈታዋለሁ? የሚለው ነው:: HIV በሽታ አለ... እርግዝና አለ... የወሲብ ሱሰኛ መሆን አለ... ይህን ጉዳይ ወጣት ተፋቃሪዎች በሚገባ ለማጤን እና ከተሻለው ውሳኔያችሁ ጋር ለመታረቅ ሞክሩ...!!

## ከምንም በላይ

ቅድሚያ መስጠት ላለባችሁ ነገር ቅድሚያ መስጠት ከብልህነትም አልፎ ጥበብ ነው:: ሁሌ ራሳችሁን መጠየቅ ያለባችሁ ወሳኝ ጥያቄ አሁን ባለሁበት እድሜዬ በወሳኝነት የሚያስፈልገኝ ነገር ምንድን ነው? ህይወቴን ለመለወጥ መጣር ነው ያለብኝ ወይስ ለስሜቴ እስረኛ መሆን? ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________::



Scanned by CamScanner

# መሻሻል የለበትም...?

ይቺን ፅሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ በአንድ አጋጣሚ ሴት ቤት የመጡ ሽማግሌዎችን ወሬ ከሰማሁ በኋላ ነበር... ከብዙ ወሬዎች በኋላ አንደኛው ሽማግሌ ለወንድ ሽማግሌዎች "የልጁ ስራ ምንድ ነው? ልጅቷን ለማኖር በቂ ገንዘብ አለው ወይ?" የሚል ነበር::

በእርግጥ በሁሉም ባይሆን በተወሰኑ ሀበሻዊ ባህሎቻችን እደሰታለሁ:: ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ባለው የሽምግልና ሀሳብ እደሰታለሁ፤ ግን ይቺ ጥያቄ አትመችም!! በዚህ በሰለጠነ ዓለም ለእኔ ትጎረብጣለች:: እንዴ እስከ መቼ ነው ኢትዮጵያዊያን ሴቶች የወንዶች የኢኮኖሚ እስረኛ የሚሆኑት? በዚህ በ21ኛው የእውቀት ዘመን ለምንድን ነው? ለወንዱ ብቻ ስራ አለህ ወይ? በቂ ገንዘብ አለህ ወይ የሚባለው? ለምንድነው ይህን ጥያቄ ለሁለቱም የማይጠየቁት? በእኔ እምነት ሴቶች ስራ ሲይዙ፣ በኢኮኖሚ ጠንካራ ሲሆኑ ይበልጥ የሚጠቀሙትም ሆነ ደስተኛ ሆነው የሚኖሩት ራሳቸው ሴቶች ናቸው!! እናም ይቺ ጥያቄ መሻሻል አለባት:: እንደሚመስለኝ እና መሆን እንዳለበትም ጋብቻ የወንዱም የሴቷም ሠላማዊ ጦርነት ነው:: ሁለቱም የሚታገሉበት!!

ሽማግሌ ተብዬዎች ትልቁን ሚና መጫወት ያለባቸው ወጣቶች በስሜት ተነሳስተው ትልቅ ሀላፊነት የሚያስፈልገውን ጋብቻ ውስጥ ዕቃዕቃ ጨዋታ መስሎዋቸው ዘለው እንዳይጣዱ የህይወት ልምዳቸውን እና እውነታውን መምከር አለባቸው እንጂ ሴቶችን የቁም እስረኛ ለማድረግ ኃላፊነቱን ወንዶች ላይ ብቻ መጫን ያለባቸው አይመስለኝም...!!

(ወጣቶች ከማግባታችሁ በፊት የግዴታ ማወቅ ያለባችሁ ሀያ አምስት ወሳኝ ጥያቄዎችን ማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ ሹክቱስ መፅሐፍን ማንበብ ትችላላችሁ)

ሁለተኛዋ እጅግ በጣም ያስታወከችኝ ጥያቄ "የልጁ ዘር ምንድን ነው?" የምትለዋ ነበረች:: ምን አይነት ከንቱ ጥያቄ ነው እባካችሁ... አሁን እድሜያቸው ከስልሳ በላይ ካለፋቸው ሽማግሌዎች ይህን መሰል የማይረባ ጥያቄ ይነሳል? መፋቀራቸው አይበቃም? ኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ አይበቃም? የእግዜር ፍጡሮች መሆናቸው ብቻ አይበቃም? አሁን ለመጋባት ዘር መቁጠር በዚህ በሰለጠነ የእውቀት ዘመን ምን ይባላል?

በዚህ የማይረባ ጥያቄ ይሄን ጊዜ ስንት ሊጋቡ የሚፈልጉ ወጣቶች ተለያይተው ይሆን ? ... ቤት ይቁጠረው::



Scanned by CamScanner

# ኦ... ገንዘብ !!

ከሀያ ስምንት ዓመቱ ጣፋጭ እንደበት ያለው አንድሪያስ ዳግማዊ ጋር የተዋወቅነው በሠላም ባሰ የተነሳ ነው። አ ዘንደኪ (A Man from Paris) መጽሐፍትን ለማዘጋጀት የሞና ገጸባህሪውን ትዕይንት ከተማ የሆነችውን የሀረር ከተማን በሚገባ ለማየት ወደ ሐረር እየተጓዝኩ ነበር፤ በሠላም ባስ ስንሄድ አጠገቤ ከተቀመጠው እንድሪያስ ጋር የተዋወቅነው።

ወጣቱ የጨሰ የሐረር ልጅ ነበር። ከፍተኛ የት/ት ፍቅር እና ችሎታ ስለነበረው ተወዳድሮ በልጅነቱ ኢንግሊዝ ሄደ። ተመረቀ። እዛው ስራ ጀመረ። ገና ስለ ስራው ሲነግረኝ ነበር ግርምቱ የጀመረው

"ምንድ ነው የምትሰራው?"

" አስተማሪ ነኝ"

" የምን?"


"ስለ ገንዘብ አያያዝ እና አጠቃቀም"

"ስለ ገንዘብ ...??"

"ብዙዎች ይህን ስል ግር ይላቸዋል። ስለ ገንዘብ አጠቃቀም በዓለማችን ላይ እንደ አንድ ትምህርት አይነት የሚሰጠው በእንግሊዝ እና ኖርዌይ ብቻ ነው። በዚች Survival of the fittest በሚባልባት አለማችን ውስጥ ገና ከልጅነትህ ጀምሮ በዋነኛነት መማር ካለብህ ነገሮች አንደኛው ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ባህል ነው። እኔ በዋነኛነት ለህፃናት የማስተምረው ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ስለ ማባከን ባህሪ (spending habits) እና የመቆጠብ ባህሪ (saving habits) ነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሆኑ ወጣቶች ትልቁ ችግር ስለ ገንዘብ አለማወቅ ነው። ህፃናትን ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለ ገንዘብ አጠቃቀም እውቀት ከጨበጡ ያን እውቀት ተግባራዊ ያደርጉታል! እዚህ ጋር እውቀት " እውቀት" ነው የሚባለው በተግባር ልትጠቀምበት ከቻልክ ብቻ ነው፤ ስለ አንድ ነገር አውቀህ በተግባር የማትጠቀምበት ከሆነ እውቀት አይባልም!! በተግባር የተጠቀምከው እውቀት ደግሞ ባህሪ ይሆናል! ባህሪ ደግሞ እንተነትን ይመሠርታል! እንተነት ደግሞ ማንነት ይሆናል"



Scanned by CamScanner




"ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ዋና ዋና ነጥብ የሚባሉትን ነገሮች ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ቪክቶር ሁጎን ታውቀዋለህ?"

" ሁለት መፅሐፍ አንብቤለታለሁ"

"ያ ዝነኛ ደራሲ አንዲት አሪፍ አባባል አለችው ስለ አንድ ነገር የበለጠ ለማወቅና ለመጠቀም ከፈለክ የተማርከውንም ሆነ ያነበብከውን እውቀት ሁሉ ለምታገኘው ሰው ሆነ (በምታገኘው) ባገኘኸው አጋጣሚ ሁሉ አስተላልፈው ይላል:: እኔም በእዚህ አምናለሁ፤ ስለዚህ ለመስማት ፍቃደኛ ከሆንክ ምን ቸገረኝ! ለእኔ ደስታ ነው"

(ከሚናገረው ዋና ዋና ነጥቡን በማስታወሻ ደብተሬ ላይ እያሰፈርኩት ነው)

"what is success? How can a person called successful? ለሚል ጥያቄ አንዱ የስኬት መገለጫ የገንዘብ አጠቃቀምን ማወቅ እና የገንዘብ ሀይልን መረዳት ነው:: ለምሳሌ እኔ በምኖርበት ኢንግሊዝ ትልቁ ስኬት የሀገሪቱን ትልቅ ማዕረግ 'sir' የሚለውን ማዕረግ መቀበል ነው:: የመጀመሪያ ደረጃ ስኬት የሚባለው ደግሞ የግል ቤት፣ መኪና፣ ሚስት፣ የራስን ዕለታዊ የግል ወጪን መቻል፤ ከሰዎች እርዳታ ውጪ በራስ ጥረት መኖር መቻል የመጀመሪያ ስኬት ነው:: ታዲያ የመጀመሪያ ስኬት ላይ ለመድረስ በህጋዊ መንገድ ብቻ መሆን አለበት! ሰርቆ ሀብታም መሆን፣ በሙስና ሀብታም መሆን፣ አጭበርብሮ ሀብታም መሆን ከስኬት አይቆጠርም፤ ስለዚህ አንዱ የስኬት መለኪያ የገንዘብ አጠቃቀምን ማወቅ መቻል ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ከቤተሰቦችህ ጋር እስከምትሞት ድረስ መኖር ትችላለህ:: እንደ አውሮፓ በ18 ዓመትህ ራስህን ችለህ ከቤት ውጣ ብትባል! ስለ ገንዘብ



Scanned by CamScanner

አጠቃቀም ሳታውቅ፣ ገንዘብን እንዴት እንደምታገኘው ሳታውቅ ውሃ ይበላሀል። በእርግጥ የሰውን ባህል መረዳዳት ነው፤ የተራበን ማብላት ነው፤ ኢንግሊዝ ልመና አስነዋሪ እና አሰቃቂ ነገር ነው፤ ለነገሩ ብትለምንም አይሰጡህም ኢንግሊዞች ገንዘብ ላይ በጣም ቋጣሪ ናቸው። ኢንግሊዞች ለህፃናት ት/ቤት ውስጥ ምን እያሉ እንደሚያስተምሯቸው ታውቃለህ?"

"ንገረኝ"

"የጥቁር ህዝቦች አንዱ ባህሪ መለመን ነው፤ ለምነው መብላት እንጂ ሠርተው መብላት አይወዱም!! ለማንኛውም ስለ ገንዘብ ዋና ዋና የሚባሉትን 12 ነጥቦች ልንገርህ?"

"እሺ"

"አንደኛ ነጥብ thinking inside of the circle Vs thinking outside of the circle ሲባል ሰምተህ ታውቃለህ?

?

ከገንዘብ ጋር በተያያዘ መጀመሪያ ማወቅ ያለብህ ትልቁ ቁምነገር ገንዘብ ከማግኘትህ በፊት ራስህን መጠየቅ ያለብህ ሶስት ወሳኝ ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው

1. ምን አደርግበታለሁ? ______________________

______________________________________

______________________________________

______________________________________

2. እንዴት አገኘዋለሁ? ______________________

______________________________________

______________________________________

______________________________________

3. ቀጥሎስ ምን ይመጣል? ______________________

______________________________________

______________________________________

______________________________________

በገንዘብ ትልቅ ስኬት ላይ ለመድረስ ገንዘቡ አንተ ጋር ሳይመጣ አስቀድመህ ማሰብ



Scanned by CamScanner

ነው:: 'አዕምሮ የፀነሰውን ያገኘዋል' የሚል አሪፍ የደብሊው ኤለመንት አባባል አለ:: ብዙዎች ግን ይህን ማሰብ ይፈራሉ 'ገንዘቡን ካገኘሁት በኋላ አቅዳለሁ እንጂ በባዶ ሜዳ ለምን በእጄ ላይ ስለሌለ ነገር እያውጠነጠንኩ እጨነቃለሁ' የሚሉ ሰነፎች አሉ፤ ይህ አይነት አስተሳሰብ ካለህ በጭራሽ ገንዘብን እንዴት አገኘዋለሁ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት አትችልም!! ይህን ካወክ ደግሞ ገንዘብን እንዴት ማብዛት እንደምትችል ኢታውቅም ማለት ይሆናል"

"ሁለተኛ ነጥብ! ፈጣሪ የሰጠህን ልዩ ችሎታህን ሽጥ ( እውቀትን) ተጠቀምበት! አየህ ሁለት የገንዘብ አይነቶች አሉ የሚጨበጥ ገንዘብ እና የማይጨበጥ ገንዘብ ( Mental Resources) ብዙዎች በማይጨበጠው ገንዘባቸው ሳይጠቀሙበት ይሞታሉ፤ ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ የሆነ የተሰጠው ፀጋ አለው፤ ያን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ በእርጋታ ማሰብ አለበት! እዚህ ጋር ነብሱን ፈጣሪ ይማረውና የሙንሮን አባባል ማስታወስ ተገቢ ነው God created each person with a unique vision. He has tremendous plans for you that no one else can accomplish. The tragic thing is that many people live their whole lives without every recognizing visions."

"ሶስተኛ ነጥብ! ትርፍ ጊዜህን ሽጥ !! ለምሳሌ በተመረከበት ሙያ የሆነ መስሪያ ቤት ውስጥ ቀን ተቀጥረህ ለስምንት ሰዓት ያህል ትሰራለህ እንበል:: ለምሳሌ የወር ደሞዝህ 2500 ብር ነው እንበል:: ይህን በስሌት ማስቀመጥ ነው:: 2500x12 ወራት = 30,000 ሺ ብር በአንድ ዓመት ታገኛለህ፤ ከዚህ ላይ የቤት ወጪ፣ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለታክሲ... ወዘተ እያልክ ወርሀዊ በጀት ታስቀምጣለህ፤ ለመንግስት የሚቆራረጥ አለ... በቀረችው ብርህ ምን እንደምትሰራ በእርግጠኝነት ማወቅ አለብህ! የዚህ ባህል በብዛት ስለሌለን አብዛኛው የወር ደሞዙን የሚጨርሰው 15 ቀናት ሳይሞላ ነው፤ ከዚያ ድንገት ብሩ ሲያልቅ ውይ ይሄ ብር በረከት የለውም ይላል! ከዚህ ጋር ለአንድ መስሪያ ቤት ስምንት ሰዓት ከሰራህ ከዚያ በተረፈችው ጊዜህ ተጨማሪ የሆነ ስራ መስራት ትችላለህ ፤ በዚህ ተጨማሪ ገቢ ታገኛለህ! ባጠቃላይ ባለህ ችሎታ ትርፍ ጊዜህን ወደ ብር ለመለወጥ ጥረት ማድረግ አለብህ!! የምታገኘውን ብር በወጉ መጠቀም አለብህ!!"



Scanned by CamScanner

'አራተኛ ነጥብ! አንድ ብርን ማክበር ካላወክ 100 ብርን ማክበር አትችልም:: ምክንያቱም ትንሿን ሳታከብር ትልቁን ማክበር አትችልምና! አንድ ጊዜ አንድ ዘበኛ አባቴ ቀጠረ! ለዘበኛው ጥያቄ አቀረበለት

'ታማኝ ነህ?'

'አዎ'

'ገንዘብ አትሰርቅም?'

'በጭራሽ ጌታዬ!' አለ:: ዘበኛው ስራ በጀመረ በነጋታው አባቴ መሬት የሚታይ ቦታ ላይ አንድ ብር ጣለ... የሚሆነውን ሳሎን ተቀምጠን ስንከታተል ዘበኛው አንድ ብሯን አነሳና ኪሱ ውስጥ ከተታት፤ አባቴ ወደ ውጪ ሲወጣ ለዘበኛው ' ታማኝ አይደለህም ተባረሃል! ቢቃሉ መሠረት የማይገኝ ሰው ሁሉ ሌባ ነው! በዚያ ላይ ለትንሿ ያልታመነ ለትልቁ መታመኑ አጠራጣሪ ነው' አለው

' ጌታዬ ምን አጠፋው ገና በአንድ ቀን?'

'አንድ ብር ሰርቀሃል'

'መቼ?'

'ከመሬት ላይ አንስተህ በዝምታ ኪስህ ውስጥ ከተትክ' ዘበኛው ምን እንዳለ ታውቃለህ? ' አቤት ሀብታም! ቆንቋና ! ለአንድ ብር ያካብዳሉ እንዴ!' በማለት ስራውን ጥሎ ጠፋ:: በገንዘብ ህግ አንድ ብርን የማታከብር ከሆነ 100 ብርን ልታከብር አትችልም:: ለምሳሌ ሱቅ ገብተህ 8 ብር የተተመነን ዕቃ በሰባት ብር ነጋዴው አንድ ብር ከስር አይሸጥልህም! ከአንድ ሚሊዮን ብር ላይ አንድ ብር ብትቀንስ አንድ ሚሊዮን ብር የለህም ያለህ 999,999 ብሮች ይሆናሉ! ቆንቋና እና ገብጋብ ተብሎ መጠራት ያለበት ብሩን በአግባቡ መጠቀም የማይችል ሰው ነው:: ለምሳሌ 2500 ብር የወር ደመወዝ የሚከፈለው ሰው ለስምንት ሰዓት ይሠራል፤ በዚህ መሠረት እሁድ ሲቀነስ በአንድ ወር ውስጥ 26 ቀናት በስምንት ሰዓት ሲባዙ

26 x8 =208 ሰዓታት = 2500 ÷ 208 ሰዓታት! አየህ በአንድ ሠዓት የሚከፈለው 12 ብር

ነው!! በዚህ መልኩ ማየት አለብህ"

"አምስተኛ ነጥብ! ከሌሎች ጋር እኩል ለመሆን በሚል ብቻ ገንዘብ አታውጣ! በሰው ሳትገዛ እንደራስህ ኑር! ደረጃህን ለይ! የራስህን የኪስ አቅም ባገናዘበ መልኩ ብቻ ኑር!!



Scanned by CamScanner

ይሉኝታን የመሰለ አስቀያሚ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ የለም:: በቅርቡ ከአንድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር የድሮ ጓደኛዬ ጋር ሳወራ በጣም የሚወዳት ፍቅረኛው እንደተለየችው አወጋኝ:: ለምን ስለው የፍቅረኛው ጓደኛ የሆነ ሀብታም ጠብሳለች እና ከዚያ ሀብታም ጋር በጣም ውድ ቤቶች ትዞራለች! በጣም ያዝናናታል! ውድ ውድ ዕቃዎችን ገዝቶ ይሠጣታል! ያቺ ፍቅረኛው በጓደኛዋ ቀንታ ልጁን የእከሌ ፍቅረኛ ይሀን ያደርጋል አንተ... ማለት ጀመረች.:: ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ቤተሰብ ሁለት ነገር ያወርስሃል ፤ ድህነት እና የአስተሳሰብ ድህነት፤ እዚህ ጋር ልጁ ያላትን ልንገርህ

'የእኔ ፍቅር እንደነሱ ለመዝናናት ጠንክረን ሠርተን ገንዘብ ማምጣት አለብን! ዝሆን ይፈሳል፤ አይጥም ትፈሳለች ግን አይጥ እንደ ዝሆን ልፍሳ ብትል ተሰንጥቃ ትሞታለች! እኔ ላደርግልሽ የምችለው የአቅሜን እና የኪሴን ያህል ብቻ ነው!' ነበር ያላት... እውነቱን ነው:: ጓደኛህ ሽራተን ገብቶ ሚሪንዳ በ45 ብር ከጠጣ አንተ ከእሱ እኩል አቅም ከሌለህ ከሱቅ ሚሪንዳ በ7 ብር ገዝተህ መጠጣት ትችላለህ:: ጓደኛህ አስር ቢራ ከጠጣ አንተም መጠጣት ካለብህ የአቅምህን አንድ ወይም ሁለት ብቻ መሆን እንዳለበት ወስነህ መሄድ አለብህ!!"

"ስድስተኛ ነጥብ! ከተቻለ ተቀጣሪ ከመሆን ብዙ ገንዘብ ለማግኘት የራስህን ስራ ለመስራት ጣር! ለሰው (መስሪያ ቤት) ስትሰራ ለመስሪያ ቤቱ ለምታወጣው ሀይል የሚከፈልህ 1 % እንኳ አትሞላም! ስለዚህ የራስህን ስራ ምንም ሆነች ምንም መስራትን የመሰለ ነገር የለም!!"

"ሰባተኛ ነጥብ! አንዲት የጥንት አሪፍ የኢንግሊዝኛ አባባል አለች An idle mind is the devils workshop ትላለች! የማይሠራ አዕምሮ የሴይጣን ቤተመቅደስ ነው በሚል አቻ ፍቺ መጠቀም ይቻላል!! በምንም ተዓምር ስራ ፈተህ ከመቀመጥ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ጥቂት ገንዘብ የምታስገኝ ስራም ቢሆን መስራት አለብህ! በምንም ተዓምር ለምነህ መብላትን መልመድ የለብህም!! የማንም ሰው ጥገኛ ሆነህ መኖር የለብህም:: በምንም ተዓምር ሳትሰራ መብላት ትልቁ ሀጢያት መሆኑን መዘንጋት የለብህም!!"


"ስምንተኛ ነጥብ! መቆጠብ በጣም መልካም ነገር ቢሆንም ብዙ ብር ባንክ አታስቀምጥ:: ለምሳሌ በዚህ ዓመት ባንክ ቤት ውስጥ 20,000 ሺ ብር ቢኖርህ እና አንድ ዓመት ሙሉ ባንክ ቤት ውስጥ ቢቀመጥ ባንኩ በየወሩ ጠብ የሚያደርጋት ተጨምሮ የሆነች በመቶዎች የምትቆጠር ብር ገደማ ልታድግልህ ትችል ይሆናል:: የሚያሳዝነው ግን የብር ዋጋ



Scanned by CamScanner

ሆነ የመግዛት አቅሙ ስለሚቀንስ ያንተ ብር ዋጋ ወደ 19,000 ሺ. ብር ይቀንሳል:: በትንሹ 1,000 ሺ. ብር ትከስራለህ ማለት ነው፤ ስለዚህ መቆጠብ እንዳለ ሆኖ የተሻለው ብሩ በእንቅስቃሴ ወይም ስራ ላይ ቢውል የተሻለ ይሆናል:: ለምሳሌ የ10 ሺ. ብር አከሲዮን ብትገዛ የተሻለ ታተርፋለህ! በ10 ሺ. ብር ለብቻህ ወይም ከሚታመኑ ጓደኞችህ ጋር በህብረት የሆነ ነገር ብትሰራበት የተሻለ ትርፍ ታገኛለህ! ለዚያ ነው Money makes Money የሚባለው"

"ዘጠነኛ ነጥብ! ባልንጀሮችህን በጥንቃቄ ምረጥ! በህይወት ላይ ሶስት አይነት ባልንጀሮች አሉ፤




ሀ. ገንዘብ የሚያመጡ (+Ve) (የሚጠቅሙህ)

ለ. ገንዘብ የሚያስወጡ (-Ve) (የማይጠቅሙህ)

ሐ. ጉዳትም ጥቅምም የሌላቸው ( ዜሮ)

ገንዘብ የሚያመጡ አንተን በሀሳብ በመምከር ፣ የተሻለውን ነገር በመንገር ፣ በማበረታታት፣ ገንዘብህን ሆነ ጊዜህን እንድትጠቀምበት የሚያደርጉ አሪፍ ባልንጀሮች ናቸው:: ባንፃሩ ገንዘብ የሚያስወጡት ደግሞ አንተን ማኖ እያስገቡ ፣ የሚበዘብዙህ ፣ በሌሎች ሰዎች ላብ የሚኖሩ፣ ከአቅድህ ውጪ እንድትኖር የሚያቀሳስሩ፣ ምንም ህልም የሌላቸው፣ ስለ ገንዘብ ቀና አመለካከት የሌላቸውን ሰዎች መራቅ አለብህ:: በፕሮግራም መመራት አለብህ:: ለምሳሌ ገንዘብ ስላለው ብቻ ዕቃ የሚገዛ ጓደኛ ካለህ አንተም ዝም ብለህ ዕቃ ያለ ፕሮግራም መግዛት



Scanned by CamScanner

የለብህም!! ዕቃ ስትገዛ በ[illegible]ንነት መግዛት ያለብህ በጣም አስፈላጊውን ብቻ እና ልትጠቀምበት የምትችለውን ብቻ መሆን አለብህ:: ለምሳሌ የ2500 ብር ደሞዝተኛ ሆነህ የ3000 ሺ ብር ሞባይል ብትገዛ ይህ በኢኮኖሚክስ ህግ poor Spending habit እንዳለብህ እና ለገንዘብ ከብር እንደሌለህ ያሳያል ማለት ነው:: በአንድ ነገር ሱሰኛ ከሆንክና ሱሰኛ በሆንክበት ነገር ገንዘብ የምታጠፋ ከሆነ አሁንም poor Spending habit እንዳለብህ ያሳያል! ለገንዘብ ከብር እና ፍቅር ከሌለህ ገንዘብ ሁሌ የምትሄደው ወደ ሚያፈቅራት እና የሚያከብራት ጋር ነው:: ገንዘብን ስታገኛት ከተጫወትክባት ስታጣት ትጫወትብሃለች የሚል አሪፍ ቆየት ያለች አባባል አለች"

"አስረኛ ነጥብ! የቺኮች ቁጥርን ቀንስ! በርካታ ቺኮችን መጥበስ በኢኮኖሚክስ Free fall (መፈጥፈጥ) ይባላል:: አንዳንድ ወንዶች በርካታ ቺኮች መጥበስ አራዳነት ይመስላቸዋል:: ዋናው የሚረሱት ነገር በርካታ ቺኮች ጠበስክ ማለት ለሞባይል ወጪ፣ ለምግብ፣ ለማዝናናት... ለስጦታ... በርካታ ገንዘብ እንደሚወጣ ይረሱታል! በዚያ ላይ የምታጠፋው ጊዜ በገንዘብ ሲተመን እጅግ በጣም ብዙ ነው፤ ለዚያ ነው አዋቂዎች ከቺኮች በፊት ራስህን መለወጥን አስቀድም፤ በተለይ ለሁሉም ጊዜ አለው የሚል መርህ ተከተል የሚሉት፤ በሌላ በኩል ደግሞ አንዲት ቺክ ብቻ ጠብሰህ ያቺ ቺክ ለገንዘብ ክብር ያላት ከሆነች በገንዘብ አወጣጥ እና አጠቃቀም ላይ ካንተ ጋር ተመሳሳይ ሙድ ካላት አሪፍ ነው! እንደዚች አይነት ቀና አመለካከት ያላት ቺክ ጋር ህይወትን አሪፍ ታደርጋታለህ! አንተም ቶሎ በህይወትህ ለውጥ ታመጣለህ!!"

"አስራ አንደኛ ነጥብ! ገንዘብን አፍቅር እንጂ አታምልክ! አንዳንዶች በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ገንዘብ ማፍቀር ሀጢያት ነው! ገንዘብ የሴይጣን አስረኛ ያደርጋል፣ ገንዘብ ከእግዚአብሔር ያራርቃል... የሚሉ ስህተት የሆኑ አባባሎች አሉ፤ ይነገራሉም:: ይህ ከእውነታ የራቀ ነው:: ገንዘብ ማፍቀር ማለት በአግባቡ መጠቀም፤ መንከባከብ፤ ተገቢውን ክብር መስጠት፣ ያለምክንያት አለማውጣት ማለት ነው!! ለፍቶ! ጥሮ! ግሮ ማግኘት ነው:: ገንዘብን ማምለክ ግን በገንዘብ ሰዎችን ለመግዛት መጣር፣ ገንዘብ ሁሉን ነገር ያደርጋል ብሎ ማመን፣ ገንዘብ ለማግኘት ሙስና እና ተገቢ ያልሆነ ህገወጥ ስራ መስራት! የተበላሸ ዕቃ መሸጥ! ገንዘብ ለማግኘት ማንኛውንም ህገወጥ ነገር ማድረግ በተጨማሪ በገንዘብ መጠቀም ሲገባህ ተስገብግበህ አለመጠቀም! መልሼ ሌላ ገንዘብ አላገኝም ብለህ መጨነቅ እና ቋጥሮ መያዝ!



Scanned by CamScanner

ለገንዘብ ሲባል ራስን ለአጉል አምልኮ ማስገዛት ማለት ነው፤ ገንዘብን ማምለክ ማለት እንጂ ብዙ ገንዘብ ማፍራትም ሆነ ሀብታም መሆን ገንዘብ አምላኪነት ማለት አይደለም:: ሀብታም መሆን ማለት እግዚአብሔርን መርሳት ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር የአንተ ሀብታም መሆንም ሆነ ደሀ መሆን አያስጨንቀውም:: ልብህን ብቻ ነው የሚፈልገው:: ድህነትን ግን አይወድም! ድህነት የስንፍና መገለጫ ነውና... በተረፈ ገንዘብን ስታሳድድ ራስህን ሆነ ፈጣሪን ከረሳህ ያኔ ገንዘብ አምላኪ ሆንክ ማለት ነው::"

"አስራ ሁለተኛ ነጥብ! ከገንዘብ ጋር አትቀበርም! ስለዚህ ባለህ ገንዘብ እስከቻልከው ድረስ መልካም ነገር ለመስራት ጣር:: ገንዘብህን በትን! ማለት ሳይሆን መልካም ነገር ላይ ማዋል እና ለሚረዱት መርዳት ራሱን የቻለ ጥበብ ነው::"

"እጅግ በጣም አመሰግናለሁ"

" ምርቃት ልመርቅህል?"

"በፍቅር አዳምጣለሁ"

"A fool and his money are soon parted ይባላል፤ ሀቅ ነው፤ ደደብ ሰዎች ገንዘባቸውን ያለ አግባብ ያጠፉትና በፍጥነት ለድህነት ይጋለጣሉ... እንዳልኩህ ገንዘብ በጥንቃቄ የሚይዛትን ትፈልጋለች::

⇒ Health is better than wealth የዓለም ትልቁ ሀብት ጤነኛ ሰው ነው:: ጤነኛ ለመሆን ግን መብላት አለብህ! ለመብላት መግዛት አለብህ! ለመግዛት ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋል::

⇒ ሚኔ 6፥7 እና መክ. 5፥10 መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን አንብብ

⇒ አባቴ ከልጅነቴ ጀምሮ የሚነግረኝ አንዲት አሪፍ አባባል አለችው:: የኢትዮጵያ አባቶች ትልቁ ችግራቸው ልጆች ገንዘብ ሲጠይቋቸው በቀላሉ ይሰጣሉ፤ በዚህ የተነሳ ልጆች ገንዘብ በቀላሉ የሚገኝ አድርገው ያስባሉ It's not easy to get money we have to work hard to make money, we can't just walk around and pick it like fruit from the trees. ለዚያ ነው አባቴ ሁሌ Money doesn't grow on trees ሲለኝ የነበረው ::

⇒ አዋቂዎች Money isn't everything ይላሉ:: ለምን ስትላቸው ምክንያቱም



Scanned by CamScanner

ገንዘብ ስላለህ ብቻ በገንዘብ የማትገዛቸው በርካታ ነገሮች አሉና በማለት ይጠቅሳሉ:: ለምሳሌ ፍቅርን፣ እውነተኛ ጓደኝነትን ፣ አየርን... ጤናን... ማስተዋልን... ጥበብን... በገንዘብ መግዛት ትችላለህ???

⇒ በአስራ ሁለተኛው ነጥብ ላይ እንዳነሳሁት You can't take money with you when you die! ይህ ትልቁ ማወቅ ያለብን ነገር ነው!! በገንዘብ ልትጠቀምበት የምትችለው በህይወት እስካለህ ድረስ ብቻ ነው:: ይህ ሲባል ነገ እሞታለሁ! ስቀበር ሁሉን ነገር ትቼ ራቁቴን እቀበራለሁ ብለህ ባለህ ገንዘብ ጠጣበት! ብላበት! ሀገወጥ ሁንበት ማለት ግን አይደለም:: አንተ ከሞትክ በኋላ ሌላ ሰው ሊጠቀምበት እንደሚችልም ልታወቅ ይገባሃል:: በሕይወታችን ለሌሎች መኖር ራሱ ትልቅነት እና ጥበብ ጭምር ነው::"

ከወጣቱ በኢንግሊዝ ሀገር የገንዘብ መምህር ጋር ካወራሁት በመጠኑ ይህን ይመስላል:: ለመሆኑ የእናንተ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ እይታ ምንድን ነው? ________

____________________________________________

____________________________________________

ለመሆኑ ወጣቶች ስለ ገንዘብ አያያዝ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በግልፅነት አውርታችሁ ታውቃላችሁ? ____________________________________________

____________________________________________

ስለ ገንዘብ አያያዝ ማወቅ ራሱ አንዱ ስኬት መሆኑን ግን እንዳትረሱ... በተለይ ቤተሰቦች ስለገንዘብ አያያዝ ለልጆቻችሁ ማስተማር ትልቁ ጥበብ መሆኑን እንዳትዘነጉ!!

ሠናይ የገንዘብ አያያዝ እመኝላቹኋለሁ !!



Scanned by CamScanner

# ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ

## 1

እነሆ ቃል ሥጋ ይሆን ዘንድ ጊዜው ደረሰና አንዲት ንጹህ ሴት መመረጥ የግድ ሆነ... ምድር ላይ ከነበሩት ሴቶች መሀከል አንዲት አረማመዷ፣ አነጋገሯ ፣ አሣሣቋ፣ ሰውነቷ... ሁሉ ግርማሞገስ ያላት! ልበንፁህ ሴት ተገኘች:: እነሆ የወሲብ ህግን በጣሰ! ሊታመን በሚያስቸግር ሁኔታ በጥበብ ተጀምሮ ጥበብ በበዛበት ሁኔታ ህጻኑ ኢየሱስ ከማርያም ተወለደ!! ምድር እልል ብላ ተቀበለችው::

ግን ትንሹ ኢየሱስ በተወለደበት ሊያድግ አይችልምና ከእናቱ ጋር ግብፅ በማምራት እድሜው ከፍ ሲል ወደ እየሩሳሌም ተመለሰ... ትንሹ ኢየሱስ ገና የ 15 ዓመት ልጅ እያለ ዝናው ገነነ! የሆነ የተለየ፣ የሆነ ከህፃናቱ ሁሉ መስዕብ ያለው፣ እርጋታ ያለው፣ የአነጋገር ለዛ እንዳለው ታወቀ... አናጢው አባቱ ዮሴፍ ጭምር በኢየሱስ ሁኔታ ይገረም! ይደነቅ ገባ!!

ከዕለታት በአንደኛው ቀን ትንሹ ኢየሱስ አንዲት እጅግ የምታምር ልጅ ብቻዋን ተቀምጣ ስቅስቅ እያለች ስታለቅስ ተመለከተ... በፍቅር ተሞልቶ ቀረባት!!

"ሠላም ላንቺ ይሁን የእኔ እህት"

"ሠላም ላንተም ይሁን"

"ስለምን እንባ ከአይኖችሽ ይፈልቃሉ?"

" ተመልከት! በጣም የሚያምር ፀጉር ነበረኝ! ድንገት እሳት ላይ ወድቄ ተቃጠለብኝ እናም በዚህ የተነሳ በድጋሚ በእሳቱ የተነሳ ፀጉር ስለማይበቅልልኝ እያለቀስኩ ነው! የሴት ልጅ ውበት መገለጫ እኮ ፀጉር ነው"

ትንሹ ኢየሱስ በእርጋታ ተጠጋትና እሳት ያቃጠለውን ጭንቅላቷን ነካካው.. ተዓምር ተፈጠረ... የዚያች ትንሽዬ ብላቴና ፀጉር በድጋሚ በቀለ!!

"እባክህ ስምህ ማን ነው? ይህንንስ እንዴት ልታደርግ ቻልክ?" አለችው በደስታ የተሞላችው ልጅ:: ትንሹ ኢየሱስ በእርጋታ ምንም ሳይላት ሄደ...



Scanned by CamScanner

## 2

ትንሹ ኢየሱስ በሚኖርበት መንደር የሚኖር ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ የሚባል ልጅ አለ:: ትንሹ የ14 ዓመት ቢያንጃን በእነ ኢየሱስ ሰፈር እጅግ በውበት የተንቆጠቆጠች ከትንሹ እስከ ትልቁ በውበቷ የሚፈዙላት የውበት ምሳሌ የሆነች ኤፍራን የተባለች ልጅ አለች:: ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ በኤፍራን ፍቅር ከንፏል! ሰክሯል! ፍርጥ ብሏል! እርግጥ ኤፍራንም እንደ ቢያንጃን በፍቅር ስከር ባትልም ቢያንጃንን ትወደዋለች! ደስ ይላታል! ከእርሱ ጋር ጊዜዋን እየተሳሳቀች ማሳለፍ ሀሴቷ ነው!!

## 3

የትንሹ ኢየሱስ ዝና እየጨመረ መጣ:: ከትንሽ እስከ ትልቁ የሚያወራው ስለ ትንሹ ኢየሱስ ሆነ

"ይህን ልጅ ተመልከቱ ሲናገር ከአንደበቱ ማር ይንጠባጠባል! እርጋታው ልብን ያጠፋል! አንዳች የሚማርክ መግነጢሳዊ ሀይል ያለው ብላቴና ነው ! ከእድሜ አቻዎቹ ሁሉ የተለየ ነው..." የሚሉ ሰዎች በዙ!! በተጨማሪ ሲያወራ ጣፋጭ አንደበቱን ለመስማት ብዙዎች ይከቡት ገቡ...!!

## 4

ከእነ ኢየሱስ መንደር የሚኖሩ አንድ የቀለም ቀማሚ አዛውንት አሉ:: ትልቁ አዛውንት ጋር ሲገባ ትንሹ ኢየሱስ በሶስት ጣሳዎች ውስጥ የተለያዩ ቀለማት ተመለከተ

"ምን እየሰሩ ነው አባቴ"

"ቀለም ላይ ምርምር እያደረኩ ነው! ስንት ዓይነት ቀለም እንዳለ ለማወቅ እፅዋትን በማድረቅ እየጨመኩ ነው! ቅጠላቸውን"

ትንሹ ኢየሱስ በዝምታ ተመለከተ::

"ይህ ቀይ ቀለም ይባላል... ይህ አረንጓዴ ቀለም ... ይህ ቢጫ ቀለም ነው..." በማለት ለትንሹ ኢየሱስ አስረዱት:: ትንሹ ኢየሱስ ድንገት ሶስቱ ቀለማት ቢደባለቁ ምን ይፈጠራል? የሚል ሀሳብ መጣለትና አዛውንቱ ሳያዩት ሶስቱን ቀለማት አንስቶ አደባለቃቸው:: በመሀከል አዛውንቱ ቀና ሲሉ ባዩት ነገር እጅግ በጣም ተበሳጩ! በስንት ሙከራ ያገኙት ቀለም ሲደበላለቅ ተናደዱ!



Scanned by CamScanner

"ምን ነካህ ኢየሱስ? ድካሜን ሁሉ ከንቱ አደረከው! ለምን ቀላቀልክብኝ?" አሉት::

ትንሹ ኢየሱስ ምንም ሳይናገር አንድ ጣሳ ውስጥ የነበረውን ቀለም በተቀሩት ሁለቱ ውስጥ መለሳቸው:: ቀለማቱ በድጋሚ እንደነበሩ ሆነው ሽማግሌው ሲመለከቱ በደስታ እና በግርምት አይናቸው ፈጠጠ:: ለማመን ተሳናቸው...!!

## 5

የትንሹ ኢየሱስ ዝና፣ የትንሹ ኢየሱስ ስም ! በየቦታው መነሳት ቀጠለ... ይህን ነገር የሰማችው ትንሿ ኤፍራን ሰለቸኝ ሳትል ኢየሱስ ይገኝበታል የተባለችበት ቦታ በመሄድ በፍፁም ፈገግታ ተሞልታ ኢየሱስን ተዋወቀችው፤ ታዲያ ለማረጋገጥ

"ስምህ ማን ነው?" ብላው

"ኢየሱስ ነኝ" ካላት ሴኮንድ ጀምሮ የልብ ምቷ ጨመረ!! እስከዛሬ ካየቻቸው ወንዶች ሁሉ የተለየ... የሆነ በቃላት ሊገለፅ የማይችል ፣ እርጋታ ፣ የሚስብ ነገር እንዳለው ልቧ ሹክ አላት... እናም ወዲያው በትንሹ ኢየሱስ ፍቅር ተመታች! ልቧን ከቢያንጃን ይልቅ ለ ኢየሱስ ወዲያውኑ ሰጠች... ቢያንጃንን Dump ለማድረግ ወሰነች!!

## 6

ትንሿ ውብ ኤፍራን በፍፁም ፈገግታ ተሞልታ! በፍፁም ሀሴት ውስጥ ሆና! እየዘለለች ስትሄድ መንገድ ላይ ከቢያንጃን ኢትዮጵያዊ ጋር ተገጣጠመች

"ስለምን የበዛ ደስታ ከፊትሽ ይነበባል" አላት

"ኢየሱስን ተዋወኩት"

"እና?"

"ልቤ በደስታ እየመታች ነው"

"እሰቲ እንጥሌ ይቆረጥ በይ!!"

"እንጥሌ ይቆረጥ" ብላ ማለችለት::

"እና?"



Scanned by CamScanner

"ከንተ ይልቅ ከእርሱ ፍቅር የሚይዘኝ ይመስለኛል! ደስታ እየተሰማኝ ነው"

"ተደባድቢ ካሸነፍኩትስ?"

"አይመስለኝም! እርሱ ላይ የተለየ መስህብ አለው!! ገና አይኑን እንደተመለከትክ ልብህን ፍስስ የሚያደርግህ ነገር አለው እና እንጦሌ ይቆረጥ የምታሸንፈው አይመስለኝም"

"ተደባድቢ ካሸነፍኩትስ?"

"ያንተው ነኝ"

"እንጦሌ ይቆረጥ?"

"እንጦሌ ይቆረጥ!!"

## 7

ወሬ ንፉስ ነው:: የትንሹ ኢየሱስ ዝነኝነት እየተወራ ይበልጥ መሰራጨት ቀጠለ:: የዚያች ውብ ኤፍራን በኢየሱስ ፍቅር መከነፍ ተወራ!! የቢያንጂን ኢትዮጵያዊ ከትንሹ ኢየሱስ ጋር ለመፋለም መጋበዝ ተወራ!! ወሬው ተበተነ...! ዜናውን መላው ህዝብ ሰማው!!

## 8

ቢያንጂን ኢትዮጵያዊ ምን ማድረግ እንዳለበት ከራሱ ጋር ለመወያየት ከሰፈራቸው ከሚገኝ ተራራ ላይ ብቻውን ወጣ:: ከተራራው ላይ አንድ ሽማግሌ ተቀምጦ ድንገት ተመለከተ:: እጅግ የሚያምረው ነጭ በነጭ ያደረገ ፍፁም እርጋታ የተላበሰው ሽማግሌ ወደ ትንሹ ቢያንጂን ተጠጋ

"ሠላም ላንተ ይሁን ልጄ?"

" ሠላም ለእርሶም ይሁን አባቴ"

"ለምን ከፊትህ ላይ ሀዘን ይነበባልን?"

"ከአንድ ልጅ ጋር ልደባደብ ነበር ግን ፈራሁ"

"ለምንድነው የምትጣላው? ፀብ እኮ የመልካም ልጅ ባህሪ አይደለም!!"

"የምወዳትን ልጅ ለማግኘት ስል ነው አባቴ"

"ነው እንዴ?"

"አዎ! ግን ፈራሁ! ገና ልጁን አይኑን ሳይ ልቤ ራደ! ልቤ ቀለጠች! ዓይኖቹ ውስጥ እጅግ የተለየ ውበት አየሁ! ገረመኝ! ፈራሁ!!"



Scanned by CamScanner

"የልጁ ስም ኢየሱስ ነው?"

"አዎ አባቴ እንዴት አወቁ?"

"ይህን ማወቅ ቀላል ነው! ይህ ተወርቷል! ያልተወራውን ስላንተ ግን የማያውቀውን ልንገርህ?"

"ስለ እኔ አባቴ"

"እህ"

"እሺ"

"ከብብትህ ስር ትንሽ ጠባሳ አለች! ታሳምምሃለች ከዛሬ በኋላ ግን ተፈውሰሃል"

ትንሹ ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ በፍጥነት እስከዛሬ ለማንም ያላሳየውን ቦታ በእጁ ዳሰሰ!! ተዓምር ነው!! እውነትም ድኖለታል፡፡

"ለመሆኑ እርሶ ማን ኖት?"

"እኔ ኢየሱስ ነኝ"

"አልገባኝም አባቴ?"

ኢየሱስ ምንም ሳይናገር የቢያንጃንን ፀጉር ዳበስ አደረገ፡፡ ከቢያንጃን አጠገብ ተነስቶ ሄደ... ቢያንጃን በግርምት ሽማግሌውን ተመለከተ ... እየሆነ ያለው ነገር ግራ ገባው!! ውስጡ ግን ሽማግሌው ኢየሱስ ነኝ ያለው ሰው ፀጉሩን ነካ ካደረገው ሴኮንድ ጀምሮ በአንዳች ደስ የሚያሰኝ ስሜት ተሞላ! ውስጡ በቃላት ሊነገር በማይችል ደስታ ተሞላ... ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ በግርምት ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ተመለከተ...

## 9

ተራራ ላይ ስላገኘው እና ፀጉሩን ሲነካው በደስታ ስለሞላው ኢየሱስ ነኝ ስላለው ሽማግሌ ለማውራት ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ ከተራራው ላይ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ በከፍተኛ ደስታ

እየዘለለ...

እየነጠረ..

እየሣቀ...

## 10

ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ በከፍተኛ ደስታ ተሞልቶ ከመንደሩ ሲደርስ ድንገት ውቧ ኤፍራንን አገኛት፤ ልክ አጠገቡ ስትደርስ በፍፁም ፈገግታ ተሞልቶ



Scanned by CamScanner

"በቃ ድብድቡን ትቼዋለሁ አላት፡፡

"ስለምን ቢባል ?"

" ውስጤ በፍቅር ተሞላ!"

"ምን ማለት ነው?"

"ከፍቅርም በላይ ፍቅር አገኘሁ"

"የምታወራው በፍፁም አልገባኝም?"

"እንጦሴ ይቆረጥ ድብድቡን ትቼዋለሁ"

"እንጦሴ ይቆረጥ በል"

"እንጦሴ ይቆረጥ!!"

ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ ያጋጠመውን ሁሉ በእርጋታ ለትንሿ ውብ ኤፍራን ነገራት፡፡ ኤፍራን የሰማችውን ባለማመን በተግባር ለማየት ኢየሱስን ፍለጋ ፈርጥጣ ሄደች... ቢያንጃን ኢትዮጵያዊ እየነጠረ ወደ ቤቱ ማምራት ያዘ... ስለ ኢየሱስ ሊያወራ!!

ስለ ትንሹ ኢየሱስ የተነሳውን ጢኖ ታሪክ ለምን በዚቹ የኢየሱስ ንግግር እንቋጫትም?

"... ነገር ግን ኢየሱስ ህፃናትን ተውአቸው ወደእኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግስተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና..."



Scanned by CamScanner

# የሐረሩ አሊ...!

"... አንዳንዶች በመጠጥ ፍቅር ይወድቃሉ! ሰው እንዴት ከመጠጥ በፍቅር ይወድቃል? አንዳንዶች ከሀሜት ፍቅር ይወድቃሉ! ሰው እንዴት ከሀሜት በፍቅር ይወድቃል? አንዳንዶች በስንፍና በፍቅር ይወድቃሉ! ሰው እንዴት ከስንፍና በፍቅር ይወድቃል? አንዳንዶች ከጨለማ በፍቅር ይወድቃሉ! ሰው እንዴት ከጨለማ በፍቅር ይወድቃል? አንዳንዶች ጫት ከመቃም በፍቅር ይወድቃሉ! ሰው እንዴት ከጫት መቃም በፍቅር ይወድቃል? አንዳንዶች ከኢየሱስ በፍቅር ይወድቃሉ... አንዳንዶች ከሙሐመድ በፍቅር ይወድቃሉ... አንዳንዶች ከቡድሃ በፍቅር ይወድቃሉ... አንዳንዶች ከክሪሽና በፍቅር ይወድቃሉ... አንዳንዶች ከኮንፊሺየስ በፍቅር ይወድቃሉ... አንድ ነገር ግን አስተውልሃል?"

"ምን አልኩት"

"አምላክ የሚባሉት በሙሉ ፆታቸው ወንድ ነው"

"አዎ"

"ለምን የሚል ጥያቄ ራስህን ጠይቀህ ታውቃለህ? አወከውም አላወከውም እኔ በፍቅር የወደኩት ከነብዩ ሙሀመድ ጋር ነው:: የእርሳቸውን ታሪክ ሳነብ እና ስሰማ ነው ያደኩት:: በተለይ ስለ ነብዩ ሙሐመድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁትን ሁለት ታሪኮች መቼም አልረሳቸውም:: መስማት ትፈልጋለህ?"

"ምን ችግር አለው? በነብዩ ሙሀመድ ባላምንም ታሪካቸውን ለመስማት ችግር የለብኝም"

"ልንገርሃ?"

" አዳምጣለሁ!!"

"እነዚህን የነብዩን ሁለት ታሪኮች የሰማሁት ገና የስምንት ዓመት ፈልፈላ እያለሁ ነበር:: በልጅነት አዕምሮ የሰማኸውን ጥሩም ሆነ አስቀያሚ ታሪክ ሁልጊዜ ታስታውሳለህ:: ለማንኛውም ከነብያችን ምክር የመጀመሪያው "በታላቁ አላህ እመንና ግመልህን አጥብቀህ እሰር' የምትል ነበረች:: ነብያችን ይህን ያሉት በአንድ ወቅት የነብዩ ሙሐመድን ጣፋጭ ቃላት ለማድመጥ ምዕመናን ተሰባስበው መጡ:: ከመሀከላቸው አንዱ በተመስጦ ሲያዳምጥና በጋለ ስሜት ከልቡ ሲፀልይ ቆይቶ ምሽት ላይ ተሰናበተ፤ ሆኖም ወዲያውኑ እየሮጠ ተመልሶ

አሪታውን ለቀቀው::"

"ነብያችን ሆይ! ዛሬ ማለዳ ላይ የአምላክ ነብይ የሆኑትን እርስዎን ለማድመጥ በግመል መጣሁ:: አሁን ግመሌ ጠፍቷል:: በዙሪያ ገባው ግመሌ አይታይም:: እኔ ታዛዥዎ ነኝ:: ቃላትዎን ተቀብያለሁ:: በአምላክ ኃያልነትም አምናለሁ:: አሁን ጌታዬ ግመል ጠፋብኝ! እናስ ይህ መንፈሳዊ ፍትህ ነው? ለአማኝነቴ የሚከፈለኝስ በረከት ነውን? ለፀሎቴ የሚደርሰኝ ምላሽ ይህ ነው?' በማለት ሀዘኑን ለነብዩ ሙሀመድ ገለፀ:: ሙሐመድም የምሬት ቃላቱን በጥሞና ካዳመጡ በኋላ ርህራሄ በተሞላበት ቃናና ፈገግታ

"በአምላክህ ተማምነህ ግመልህን አጥብቀህ እሰር!!' ሲሉ አሰናበቱት! አሪፍ ነች አይደለም?"

"ለተገነዘበው ትልቅ ቁም ነገር አለው"

"ሁለተኛዋ ነብዩ ሙሀመድ ሲያስተምሩ ሁል ጊዜ ከልቡ ያመነ እና ለእውነት የደፈረ ማሸነፍ እንደሚችል ይናገሩ ነበር፤ ይህን ንግግር በተግባር አሊ ይተገብራል:: አየህ የዚያን ጊዜ ነብዩ ሙሀመድ ከትትል በዝቶባቸው ከቦታ ቦታ በመሰደድ ላይ ሳሉ አሊ የሚባለው አማቻቸው ደብቆ ሊያወጣቸው አሰበ:: ነብዩን ረዘም ባለ ቅርጫት ውስጥ ደብቆ በእናቱ በመሸከም ጉዞ ጀመረና ዘቦች ከቆሙበት ኬላ ላይ ደረሰ::

'የተሸከምከው ምንድ ነው' ሲል ጠየቀው ከዘቦቹ አንዱ ፈርጠም ያለ ቆጣ ብሎ

'ነብዩ ሙሐመድን' በማለት መለሰለት:: ወቅታዊ ቀልድ የመሰላቸው እነዚያ ዘቦች በሰሙት ነገር በሳቅ ተንከትክተው እንዲያልፍ ፈቀዱለት!!"

ሐረር በአጋጣሚ ሳይሆን በጓደኛዬ አማካኝነት የተዋወኩት አሊ ቶሎ ቶሎ ማውራት የሚወድ ወጣት ነው:: በተለይ በዝምታ የሚያዳምጠው ካገኘ ማቆሚያ የለውም፤ ግን ምን መናገር እንዳለበት ያውቃል... ስለ ነብዩ ሙሀመድ ማውራት እጅግ ያረካዋል... ማህበራዊ ህይወት በጣም የገባው... እንጀራ የሆነ ፀባይ ያለው ወጣት ነው!! ሐረርን በሚገባ ያሳየኝ አሊ ነበር፤ በጉብኝታችን መሀከል

"አሁን የቀረን ጅብ ማየት ነው! ጅብን ስጋ እያበላህ ፎቶ መነሳት ትችላለህ" አለኝ::

"በጭራሽ" አልኩት::

"ለምን?"

"ብዙ ምቾት አይሰጠኝም"



Scanned by CamScanner

"እንዴ! ከአዲስ አበባ የመጡ እኮ ትልቁ ማየት የሚፈልጉት ትዕይንት የጅቡን ጉዳይ ነው"

"እኔ በጭራሽ ማየት አልሻም"

"ፈርተህ ነው? ለማዳ ናቸው እኮ"

"ፈርቼ ምናምን ሳይሆን... በቃ ይለፈኝ!!" አልኩት:: ታዲያ የሚገርመው ምሽት ላይ ከአሊ ጋር ተለያይቼ እልጋ ወደ ያዝኩበት ሆቴል ሱክሱክ እያልኩ ስሄድ ሁለት ጅቦች መንገድ ላይ (በተለምዶ ሹፌር ሰፈር ዩኒቨርሲቲው ጋር) ዘና እያሉ ሲሄዱ አየሁ... የመጣው ይምጣ በማለት ባጠገባቸው አለፍኩ!! ከቁብም አልቆጠሩኝም! ቀና ብለው እንኳ ሳይመለከቱኝ አለፉኝ_ አይ የሐረር ጅቦች አልኩኝ ለራሴ ... ምስኪን ጅቦች::

በነጋታው ይህን ጉዳይ መኮንኖች መዝናኛ ውስጥ ተቀምጠን ለአሊ ስነግረው ፈገግ አለ:: ከዚያ አንድ አሪፍ ነገር ተናገረ:: በሐረሩ አሊ... ስለራሱ አሊ ያነሳሁትን ቅንጫቢ ታሪክ ልዝጋው::

"ሰው በሊታ ናቸው የሚባሉትን እንስሳት እንኳ ፍቅር ከሰጠሃቸው ፍቅር ይሰጡሃል! እርስ በእርሳችን ብንፋቀር ደግሞ የት እንደርስ እንደ ነበር አስበው!! ይቺን ዓለም መቀየር የሚያስችለው ትልቁ መሳሪያ ፍቅር ብቻ ነው!!"



Scanned by CamScanner

# ዘ ቹዝን ዋን...!!

ጨላጣ የሆነ የሸገር ልጅ ነበር፡፡ ከአማርኛ ይልቅ ኢንግሊዝኛ መናገር የሚቀናው የሀብታም ልጅ ነበር፡፡ ከማይክ ጌታቸው ጋር ያስተዋወቀን የኢኮኖሚክስ ተማሪ የሆነው ጥቢ ነበር... ማይክ ምንም ጨላጣ ቢሆን ለደሀ የሚሆን ልብ አለው... እኔ እንኳ እስከማውቀው ለዘጠኝ መማር የማይችሉ ተማሪዎች የቁሳቁስ እና የገንዘብ እርዳታ እያደረገ እንዲመረቁ አድርጓል (ምንም ይህን ነገር ለማንም ያልተናገረ ቢሆንም...)

ጨላጣው ማይክ ሁልጊዜ መናገር የሚወዳት የዝነኛው ደራሲ ሙንሮ አባባል ነበረችው፡፡

"There are three kinds of people in the world. First, there are those who never seem to be aware that things are happening around them. Second, there are those who ask, what just happened? Third , there are those who make things happen! ዋናው ነገር እኛ ከየትኛው ምድብ እንደሆንን ማወቁ ነው"

"አንተ ከየትኛው ነህ?" ሲባል

"those who make things happen!" ይላል (እውነቱን ነበር ዛሬ የአንድ መስሪያ ቤት ባለቤት ከመሆን ባሻገር በርከት ያሉ ሠራተኞችን ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል)

ከማይክ ጋር በተያያዘ ሁለት ነገሮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ስለ ዘ ቹዝን ዋን ነው፡፡ ማይክ ከብዙዎች ጋር ሽንጡን ገትሮ ይከራከርበት ከነበረው ሀሳብ አንደኛው ለእያንዳንዱ ነገር የራሱ የተመረጠ ዘ ቹዝን ዋን አለው የሚል እምነት አለው፡፡ በዚች ሀሳቡ አንድ ወቅት በተማሪዎች መዝናኛ ውስጥ ሻይ ቋ እያደረግን አውርተን ነበር

"ለምሳሌ ሁሉም ሰው ሙዚቀኛ መሆን ይችላል?"

"አይችልም"



Scanned by CamScanner

"ሁሉም ሰው መሪ መሆን ይችላል"

"አይችልም"

"ሁሉም ሰው ሰዓሊ?"

"አይችልም"

"እንደበተ ርቱዑ ተናጋሪ?"

"አይችልም"

"ሰባኪ?"

"አይችልም"

"That is way I'm talking about the choose one! እያንዳንዱ ሰው ምድር ላይ ሲመጣ አንዳች የሚሰራው ስራ አለው!! በእርግጠኝነት God created every one with a special Gift and talent! አንድ ሰው ሁሉንም መሆን አይችልም! በመሆኑም በአንድ ነገር ላይ ብቻ ትኩረት እና ጥበብ ይሰጠዋል!! በእርግጥ አንዳንዴ በሙከራ ፣ በጥረት፣ በልምምድ የምትካነው ነገር ሊኖር ይችላል፤ ግን የፈለገ ጥረት ብታደርግ ፣ ብትሞክር፣ ልምምድ ብታደርግም መሆን የማትችላቸው ነገሮችም አሉ፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው አንድ ነገር ለመሆን ይፈጠራል!! በዚህ መሠረት አስተማሪ ለመሆን የሚፈጠር አለ! መላ ህይወቱን መንገድ የሚያጸዳ አለ! ሌባ ለመሆን፣ ዘፋኝ፣ ዘማሪ፣ ኮሜዲያን፣ ተናጋሪ፣ መሪ፣ አልቃሽ፣ ለማኝ፣ ፀጉር ሰሪ... ወታደር ፣ ትራፊክ... ነጋዴ... ወዘተ ለመሆን ትፈጠራለህ! አንተ ለምትሆነው ነገር የተመረጥክ ዘ ቹዝን ዋን ነህ ማለት ነው:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ አንደኛ ሀብታም ማን ነው?"

"አላሙዲን"

"ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልክ እንደ አላሙዲን ሀብታም ሊሆን ይችላል?"

"ሁሉም! አይታሰብም"

"አንተ አላሙዲን ሀብታም የሆነው ወጥሮ በመስራቱ የስራው ውጤት ነው ብለህ ማሰብ ትችላለህ ለእኔ ግን ከአላሙዲን ጥረት ጀርባ ዋናው ነገር አላሙዲን ሀብታም ለመሆን ዘ ቹዝን ዋን ነው:: ቀነኒሳ፣ ደራርቱ፣ አበበ ቢቂላ፣ ቴዲ አፍሮ፣



Scanned by CamScanner

ከበደ ሚካኤል... ዘ ቹዝን ዋን ናቸው:: ሌላውን ነገር ለታሪክ እና ለህዝቡ ትተነው እነ ኢያሱ ፣ ቴዎድሮስ ፣ ዮሐንስ፣ ምኒሊክ ፣ መንግስቱ፣ ኃይለስላሴ፣ ሀይለማርያም_ ኢትዮጵያን ለመምራት ዘ ቹዝን ዋን ነበሩ:: ቢቃ ሲፈጠሩ ዕጣ ፋንታቸው ላይ ይህ ነገር ተቀምጦላቸው ነበርና ቦታውን ለማግኘት ችለዋል:: ለምሳሌ እኔ እግርኳስ ተጫዋች ወይ ደራሲ ወይ ጋዜጠኛ ወይ ሰባኪ ወይ ሌባ... ወይ ወታደር ለመሆን አልተፈጠርኩም!! እኔ የተፈጠርኩት ነጋዴ ለመሆን ነው:: የተሰጠኝን ችሎታ በአግባቡ ከተጠቀምኩበት ስኬታማ እሆን ይሆናል!! ሯጭ ሁን ብትለኝ መሆን አልችልም!! ሯጭ የሚሆኑት ለሯጭነት የተፈጠሩ ትልቅ ሳንባ ያላቸው ዘ ቹዝን ዋን ብቻ ናቸው" የሚል አመለካከት አለው:: በማይክ ገለፃ እያንዳንዱ ሰው በሆነበት (ለሚሆንበት) ነገር ተፈጥሮ እንዲሆን የመረጠችለት ፀጋው ነው የሚል እይታ አለው:: ለመሆኑ ይህ የማይክ ሀሳብ ይዋጥላቹዋል?

ሀ. አዎ!

ምክንያቱም ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ለ. በጭራሽ!

ምክንያቱም ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

አንድ ጊዜ አንዲት የነገሌ ቦረና ተማሪ እንዳረገዘችና በእርግዝናዋ የተነሳ ልጅቷ ትምህርቷን አቋርጣ ከዩኒቨርሲቲው እንደወጣች ለጉድ ይወራ ገባ!! ከልጅቷ ጀርባ ያለው ተማሪ ደግሞ ማይክ እንደሆነ ይወራ እና በሀሜት ይቆረጠም ገባ!! ምንም እንኳ ማይክ ቺኮችን በቃላት ጠብ እያደረገ የሚፈጃቸው ቢሆንም ከነገረኝ ፍልስፍናው እና ከእርግዝና ጋር በተያያዘም ሆነ HIV በሽታን ከመከላከል ጋር ባለው ወጥ አቋም አንጻር ማይክ በጭራሽ ይህን ነገር ሊሠራ እንደማይችል እኔ በሚገባ አውቅ ነበር ፤ እናም ጣጣ ሳላበዛ ጠየኩት::

"የግል ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ?"



Scanned by CamScanner

መብትህ?"

"ህሜትነ? ከጀርባህ የሚወራውን ነገር?"

"መብትህ ነው! በነገራችን ላይ አንድ ቆየት ያለች አሪፍ አባባል ልንገርህ why people talk behind your back? For 3 reasons, when they can't reach your level, when they don't have, what you have, when they try to copy your life style, but they can't. this is why people talk behind your back! እኔ አይጨንቀኝም! ምክንያቱም ሰውን ምንም መረጃ ሳይኖራቸው ለማማት ብቻ እና ተቀምጠ እንደ ስራ ፈት የመንደር ሴት ለመቦጨቅ የሚፈጠሩ ሰዎች አሉ! ሀሜተኛ ለመሆን ዘ ቹዝን ዋን ሰዎች አሉ! ዋናው ነገር ሀሜት ከእውነት በላይ ልትሆን ስለማትችል አንተ ህይወትህን መቀጠል ነው!! ለዚያ ነው አረቦች ውሻው ይጮሃል ግመሉ ጉዞውን ቀጥሏል የምል ምርጥ ጥቅስ ያላቸው anyway ጥያቄህን ቀጥል"

"የነገሌ ቦረናዋ ልጅ በእርግዝና ምክንያት ትምህርት ማቋረጥ ጀርባ እጅህ አለበት?"

"የለበትም!!"

"ከተማ አብረሃት ሁለት ጊዜ ታይተሃል?"

"so what? ምን ችግር አለው ታዲያ? ከአንዲት ሴት ጋር መታየት ብርቅ ነው? ይህ በቂ ማስረጃ ነው?"

"ሊሆን አይችልም" አልኩት:: ትንሽ ቆይቶ መናገር ቀጠለ::

"any way አንተ ያው ወደፊት ፀሐፊ ቢጤ ስለምትሆን እውነታውን ልንገርህ! በእርግጥ ከነገሌዋ ልጅ ጋር ከተማ ከሁለት ጊዜም በላይ አብረን ወጥተናል:: ምን መሰለህ የሆነጊዜ ማታ ወክ ሳደርግ የቡና ተከሉ ውስጥ ይቺ የነገሌ ቦረና ልጅ ተቀምጣ ብቻዋን እያለቀሰች ነበር:: ሴት ልጅ እያለቀሰች አይተህ የማትራራ ከሆነ አንተ የሴት ጠላት ነህ ማለት ነው:: እናትህን አትወዳትም ማለት ነው:: ለሴት ከብር የለህም ማለት ነው... በቃ ቀረብኳት በተቻለኝ መጠን አባበልኳት::

"ምን ሆነሽ ነው ?"

ዝም ::



Scanned by CamScanner

"ሳትፈሪ ንገሪኝ እኔም እናት አለችኝ፡፡ ሁለት እህቶች አሉኝ... ፍቅረኛ አለችኝ... የሴት ልጅ ችግር የእኔም ችግር ነው! ያጋጠመሽን ንገሪኝ የምችለው ከሆነ እረዳሻለሁ! አባቴ ይሙት ብዬሻለሁ!!"

ዝም፡፡

"ግዴለሽም ንገሪኝ!!"

ዝም፡፡

"እሺ ስምሽ ማን ነው?"

"ፀ... ሐ...ይ"

"በጣም አሪፍ ስም ነው! ስንተኛ ዓመት ነሽ?"

"የመጀመሪያ ዓመት "

"ምን አጋጥሞሽ ነው ታዲያ?"

"እውነት ልንገርህ ትረዳኛለህ?"

"አባቴ ይሙት! እረዳሻለሁ"

"እርጉዝ ነኝ..." በማለት ሁሉንም ነገር በዝርዝር ነገረችኝ፡፡ የአራተኛ ዓመት የህግ ተማሪ ነው ያስረገዛት... እንዳረገዘች ሲያውቅ አላውቅሽም አላት... ልጅቷ ደግሞ የወር አበባዋ እየተዛባ ስለሚመጣ ችላ ብላው ነበር፡፡ ድንግል ነበረች፡፡ ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ አድርገው ነበር፡፡... ልጅቷ ደግሞ ስለወሲብ ብዙ እውቀት አልነበራትም... በቃ ከተማ ለማስወረድ ጉዳዩን ለማንም ሳትናገር ሆስፒታሎች ሙከራ አደረግን ግን ፅንሱ ከሁለት ወራት በላይ ስለሆነው ማስወረድ አልቻለችም... በቃ ይህን ጉዳይ ለአባቴ ነግሬው ለተወሰነ ነገር ብሎ 15,000 ሺ ብር ገደማ በመስጠት ወደ ነገሌ እንድታመራ አድርገናል... ትልቁ እውነታ ይሄ ነው!! አየህ የዚች ልጅ ዕጣፈንታ ሲፃፍ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለች ማርገዝ! ልጅ መውለድ የሚል ነበር ማለት ነው!!"

ማይክ እንዲህ አይነት ችግር ፈቺ እና ለሴቶች የሚራራ ልብ ቢኖረውም በጣፋጭ ምላሱ ደግሞ ብዙ ሴቶችን እንደፈጀ አውቃለሁ፡፡ በጣም በርካታ ሴቶች ሲባሉበት አይቻለሁ!



Scanned by CamScanner

በተለይ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ማንም አይደፍራትም የምትባል ውብ የጋዜጠኝነት ተማሪ ለማውጣት የቀደመው ወንድ አልነበረም! በርካቶች ግን ጆሬ ጥለውባት ነበር! ሲባሉባት ነበር (እረ እኔ ራሱ በዓይን ፍቅር ለተወሰነ ጊዜ ቀምሼ ነበር! የምትገርም ወጣት ነበረች)

በዚው ወደ ማይክ ሁለተኛ ነጥብ እናምራ!! ማይክ ለሴት ልጆች ሶስት ህግ አለው፤ በእነዚህ ሶስቱ ህጎች ይመራል... ሴቶችን ይፈጃል ይላሉ... ይህ ሀሜት ሳይሆን ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው... በተለይ ያቺ የብዙዎቻችንን ልብ የሰረቀችው የጋዜጠኝነት ውብ ቁመና ያላት፤ ውብ መልክ ያላት! ውብ ቅርፅ ያላት! ግን ውበቷን ስለምታውቅ መሬት ለመርገጥ የሚቀፋትን ወጣት ማይክ እንዳወጣት ለጉድ ሲወራ! ሲወደስ! ሲሞካሽ፣ እሰይ የእኛ ጀግና ሲባል ማይክን ፈልጌ አገኘሁት (በዚህ ፅሁፍ እውነተኛ ስሟን ባነሳ ጥሩ አይደለምና... ለጨዋታ ያህል ማርሲላስ እንበላት)

"ማርሲላስን አወጣሀት?"

"ትወዳታለህ አይደለም?" አለኝ፡፡

"የዓይን ፍቅር! እንዴት ጠየከኝ ግን ይህን ነገር ለማንም ተናግሬ አላውቅም"

"I know ... ካፍቴሪያ ውስጥ በፍቅር አይን ስትመለከታት አይቻለሁ... በተጨማሪ አንድ ሁለት ጊዜ በርቀት ስትከተላት አይቻለሁ!! ለነገሩ እድለኛ ነች! ሁሉም ሰው ይወዳታል! ሁሉም እንደሚወዳትም በእርግጠኝነት እሷም ታውቃለች፤ በእርግጥ እስከ ጉራዋ ደስ ትላለች! እንደዚች አይነት ሴት ለወሲብ እንጂ ለጋብቻ የሚፈልጋት ሰው በብዛት አይኖርም... ብዙዎች ሞከሩ... እኔ ግን ጠብ አደረኳት! ወሲብ ላይም ምንም አትልም! የሰውነቷ ልስላሴ ግን አስደናቂ ነው!!"

"እንዴት ወይም ለምን ተሳካልህ ማለት ይቻላል?"

"ሴቶችን በተመለከተ ሁሌ የምከተላቸው ሶስት ህጎች አሉኝ!! እስካሁን ስኬታማ እየሆንኩባቸው ነው"

"ሶስት?"

"እህ"

"ምንድናቸው?"

"አንደኛ"

"እሺ"



Scanned by CamScanner

"ወርቃማ ህግ አንድ! ማንም የማያደንቅላትን ነገር ፈልገህ አድንቅ"

"ሁለተኛ?"

"ሴት እና ድመት አንድ መሆናቸውን ጠንቅቀህ እወቅ"

"ሶስተኛ"

"ጉጉት ፍጠርባት"

"በአጭሩ በእነዚህ በሶስት ስልቶች ተጠቅመህ ማርሲላስን ጠብ አደረኳት እያልከኝ ነው!!"

"90% አዎ 10% ደግሞ ግንባርም አለኝ"

"ማብራሪያ ስለ ህግ አንድ"

"አንድን ነገር ስታይ ሁሉም ሰዎች የሚያዩትን ነገር ካየህ ከሁሉም የተለየህ አላየህም! በህይወት ላይ ሁሌ ማየት ያለብህ ሳጥኑ ውስጥ ያለውን እና ከሳጥኑ ውጪ ስላለው ነገር መሆን አለበት! በስኬት ህግ ወይም The power of attraction low መሠረት በአንድ ነገር ስኬታማ ለመሆን ስለምትፈልገው ነገር መሳብ ነው!! የምትፈልገው ነገር ያንተ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አለብህ:: ይህ ህግ ለሴትም ይረዳል:: ይቺን ሁሉም የሚመኛትን ፤ ይቺን ራሷን እንደ ኪሎፓትራ የምትቆጥርን ወጣት እንዴት አገኛታለሁ? ለሚለው ጥያቄ ከሌሎች ወንዶች ይልቅ የተለየውን ነገር ፈልጌ ነገርኳት! ትኩረቷን በቀላሉ አገኘሁ! ማንኛዋም ሴት የሆነ የተለየ ነገር አላት ያን ለማወቅ ትኩረት መስጠት አለብህ! ህግ አንድ በል"

"ህግ ሁለት?"

"ሴት እና ድመት አንድ መሆናቸውን እወቅ:: ሴትና ድመትን አንድ የሚያደርጋቸው አንድ ባህሪ አላቸው:: ሁለቱም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት ትኩረት ከሰጣቸው ይልቅ ትኩረት ለነፈጋቸው ነው:: አንዲት ሴት አፍቅራህ በቀላሉ ካገኘችህ ወይም በቀላሉ የእርሷ ማድረግ የምትችል ከመሰላት ያንተ ዋጋ ስለሚረከስባት ወዲያው ላንተ ያላት ቦታ ይቀንሳል! በቀላሉ የሚገኝ ነገር ዋጋው ርካሽ ይሆን የለም? በዚያ መልኩ አስበው!!"

"በኢኮኖሚክስ ህግ ማለት ነዋ!?"

"ትክክል!!"

"ሶስተኛ ህግ"



Scanned by CamScanner

"እያንዳንዱ ሰው ስለ ራሱ መስማት ይወዳል! መጠኑ ይለያይ እንጂ እያንዳንዱ ሰው መደነቅን፣ ስለራሱ ሲወራ ማዳመጥን ይወዳል... ከእያንዳንዱ ሰው ይበልጥ ደግሞ ሴቶች ስለራሳቸው መስማት ጣፋጭ ምግባቸው ነው:: ስለራሳቸው ስታወራላቸው ወሲብ ሲያደርጉ ከሚሰጣቸው ሀሴት የበለጠ ይደሰታሉ!! ይህን ደካማ ባህሪያቸውን በመያዝ ካንተ የሚጠበቀው ጉጉት መፍጠር ብቻ ነው"

"ግልፅ አድርገው"

"ለመጀመሪያ ጊዜ ማርሲላስን ስተዋወቃት ምን እንዳልኳት ታውቃለህ? Hi አልኳትና ጨበጥኳት ... ከዚያ Diary of a wimpy kid 1 and 2 የተሰኘውን እሩፍ የህፃናት ፊልም አይተሻል ወይ አልኳት... እኔ ፊልሙን እንዳየችው እርግጠኛ ስለነበርኩ ነው:: እሷም `አዎ' ስትለኝ በጣም ጥሩ ነው ሁለት የምነግርሽ ምርጥ ነገሮች አሉኝ:: አሁን ክፍል ለመግባት ስለምቸኩል ሌላ ጊዜ ባጋጣሚ ስንገናኝ እነግርሻለሁ አልኩና ይቅርታ ጠይቄ ሄድኩኝ:: ይቺ ውብ፣ ይቺ ጉረኛ፣ ይቺ ለራሷ ከፍተኛ ግምት የምትሰጥ ፣ ወንዶች ሁሉ እንዲያመልኳት የምትፈልግ ሴት ናት!! ይህን ስለማውቅ ሆነ ብዬ ለወር ዘጋዋት_ ለማንኛውም አስተነፈስኳት! በድጋሚ ግን ወሲብ ሳይሆን ጉንጯን እንኳ አልስማትም! በአራት ነጥብ ዘጋዋት... ለምን ብለህ እንዳትጠይቀኝ... የእኔ ትልቁ ደስታ እንዲህ ጢባር የምትነሰንስ፣ ከእኔ በላይ ሌላ ሴት ምድሪቱ ላይ የለችም የምትል ሴትን ማስተንፈስ የእኔ እርካታ ነው! እስካሁን ጠይቋያት እንቢ ያለችኝ ሴት የለችም... ባጭሩ ይህን ካልኩህ ይበቃሃል"

እነሆ ከዘመናት በኋላ ማይከን ያገኘሁት በስኬት ጎዳና ላይ ነው... እንዳጫወተኝ አሁን ባለው ህይወቱ ደስተኛ ነው፤ ከዩኒቨርሲቲ ምርቃት በኋላ ግን ቺኮችን ማተራመሱን በጭራሽ በመተው ጊዜውን ሁሉ ለስራው መስጠቱን አውግቶኛል

"አሁን ቺኮች ቢጠበሱ ራሱ አይሸቱኝም! አሁን ሙሉ ጊዜዬን ሰጥቼ የምሠራው ስራዬን ብቻ ነው! አሁን ሰዓቱ ወጥሬ የምሠራበት ነው! ከዚህ በኋላ ለእኔ የቺኮች ጭን ስር መገኘት ብርቄ አይደለም!! እውነቱን ለመናገር ስለ ትላንት የዩኒቨርሲቲ ህይወቴ ሳስበው በጣም እናደዳለሁ! ብዙ ማንበብ እችል ነበር! ብዙ ማወቅ እችል ነበር፤ በተለይ ቺኮችን በሶስቱ ህጎች እየሸወድኩ ማውጣቴን ዛሬ ሳስበው በጣም እናደዳለሁ! ከእንደኔ ለሴት ልጅ ከብር አለኝ ከሚል ሰው አይጠበቅም ነበር፤ በዚያ ላይ የአንድን ሰው ደካማ ጎን ፈልገ



Scanned by CamScanner

በደካማ ጎኑ ማሸነፍ ራሱ ድክመት ነው! ካሜሮያዊያን አንዲት አሪፍ አባባል አለቻቸው 'አይጥ የገደለ ዝሆን ጀግና አይባልም' የምትል ነበር ያለኝ:: እናም በንግድ አለም ላይ በመሠማራት ታሪክ ለመስራት እየተውተረተረ ይገኛል... ይቅናው::



Scanned by CamScanner

# እኛ እና አረብ

ሶፊያ ትባላለች። ስለ አባቷ፣ ስለውበቷ፣ ስለቁመቷ... ማንነቷ እንዳወራ ፍቃድ አልተሰጠኝም... ስትናገር ደስ የምትለው ሶፊያን ያገኘዋት በሰውበሰው አቢሲኒያ 24ትን ስፅፍ ነበር፤ በአቢሲኒያ 24 መፅሐፍ ላይ ስለ አረብ ሀገራት በመጠኑ አንስቼ ነበር፤ ተጨማሪ ትሆን ዘንድ ይቺ ተቆርጣ የቀረች የሶፊያ ታሪክን ማንሳቱ ተገቢ ሆነ...

" ስንት ዓመትሽ ነው?"

"በቅርቡ 28 ሞላኝ"

"እ... ወደ ሰላሳ እየሮጥሽ ነዋ?"

"መሆኑ ነው! ጊዜ ሳታውቀው ነው የሚሮጠው"

"የት ነበርሽ?"

"አራት ዓመት የመን... አራት ዓመት ኩዌት"

"ስምንት ዓመት አረብ አገራት?"

"ትክክል"

"አሁን ምን አለሽ?"

"ማለት?"

"ማለቴ ኢትዮጵያ ውስጥ ለምን ተመለሽ?"

"ታሪኩ ብዙ ነው በኋላ አብረን ሄደን አሳይሃለሁ ለጊዜው ትልቅ የሴቶች ፀጉር ቤት አለኝ"

"ዓላማሽ ፀጉር ቤት መክፈት ነበር?"

"አልነበረም"

"ማወቅ ይቻላል?"

"በሀያ ዓመቴ ከኢትዮጵያ ስወጣ የነበረኝ ትልቁ ህልም ደሀ ቤተሰቦቼን መርዳት የሚል እቅድ ነበር፤ እናቴ እና ሁለት ታናናሽ እህቶች አሉኝ፤ አባቴ ቀበሌ የኢህአዴግ ወሬ አቀባይ ነበር፤ የብዙ ሰዎችን ጉዳይ እያቃጠረ ሲያስቸግር ቂም የቋጠሩበት ግለሰቦች አንድ ምሽት አናቱን ብለውት ቱቦ ውስጥ ሞቶ ተገኘ፤ በዚህ የተነሳ ሙሉ ለሙሉ ሀላፊነት እኔ ላይ ወደቀ"

"ከዚያ አረብ ሀገር ለመሄድ ወሰንሽ?"



Scanned by CamScanner

"አዎ"

"ገንዘብ ከየት አገኘሽ?"

"ብዙ ጥረት አድርጌ ነበር ግን አጣሁ"

"እና"

"እና... ራሴን ሸጥኩ"

"ማለት?"

"ድንግል ነበርኩኝ"

"እ"

"ሰፈራችን አንድ ሀብታም ሰውዬ ሁሌ ስገባ ስወጣ ይጎነትለኝ ነበር"

"መጎንተል ማለት?"

"መጀንጀን ነዋ"

"ምን አይነት ጅንጀና"

"ጅንጀናም አይነት አለው እንዴ?"

"ሁለት አይነት፡፡ ደረቅ ጅንጀና እና እርጥብ ጅንጀና"

"አስረዳኝ"

"ደረቁ እንዲው ውበትን እና ተፈጥሮን ለማድነቅ ብቻ ሲሆን... እርጥቡ ደግሞ ለወሲብ፣ ለጋብቻ ፣ ለፍቅረኝነት..."

"ለወሲብ ብቻ"

"ቀጥታ ለወሲብ?"

"ሶስት ጊዜያት ያህል ለወሲብ ብቻ እንደሆነ እና የፈለኩትን ገንዘብ እንደሚሰጠኝ... ከፈለኩኝም ቅምጡ ሊያደርገኝ እንደሚፈልግ ሁሉ ነግሮኛል"

"ባለሚስት ነዋ"

"ከሚስትም በተጨማሪ ሁለት ዩኒቨርሲቲ የሚማሩ ተማሪዎችም አሉት"

"ሼባ ነዋ! ሹገር ዳዲ??"

"በለው"

"እሺ"

"በቃ አጋጣሚውን ለመጠቀም ለእርሱ በለው ለእርሳቸው ድንግሌን ሸጥኩለት!



Scanned by CamScanner

ችግሬን በግልፅ ነግሬው! ለሁለት ሳምንታት ያህል እስከሚሰለቸው በወሲብ ከተጫወተብኝ በኋላ ተጨማሪ ገንዘብ ጨምሮ በመስጠት ከኢትዮጵያ ወጣሁ:: በእርግጥ እዚው ኢትዮጵያ እንድቀመጥ ማለቴ ቅምጡ በመሆን ገንዘብ እንደሚሰጠኝ ነግሮኝ ነበር:: እኔ በዚህ ዘመን ወንድን እምና ቅምጥ ለመሆን የምታስብ ሴት አብድ ብቻ ነች አልኩና ሄድኩኝ!! እስበው እስቲ ለሁለት ልጆቹ እና ለህጋዊ ሚስቱ ያልታመነ እንዴት ለእኔ ሊታመን ይችላል?"

"ከዚያ...??"

"ያጋጣሚ ሆኖ እኔ አዲስ አበባ ተወልጄ በማደጌ ቋንቋም ሆነ በተወሰነ መልኩ የምግብ ሆነ የቤት አያያዝ አውቃለሁ... የመጀመሪያ ሁለት ዓመት እንዲት ጨርሜሳ አሮጊት የመጠበቅ ስራ ነበር የሰራሁት... ያው ፈተና አለ! የባህል ልዩነት አለ... የቤተሰቦቼን ህይወት ለመለወጥ የማገኛት ገንዘብ በቂ አልነበረችም:: በመሀከል የመን እያለሁ ከአንዲት የደሴ ልጅ ጋር ተዋወኩኝ... ከዚያ አዲስ አቅድ መጣልኝ"

"ማን ናት?"

"ራ.መ.አ ትባላለች አሁን አብዳለች"

"እ... በጣም ያሳዝናል:: ከማበዷ በፊት ያለውን ታሪክ ንገሪኝ"

"ከራ.መ.አ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ስንገናኝ እርሷ የመን አምስት ዓመት ሆኗት ነበር፤ ስናወራ ደሴ ለሚገኙት ሁለት ወንድሞቿ ታከሲ እንደገዛች፤ ለእናቷ ሱቅ እንደከፈተች ለአባቷ መንቀሳቀሻ ገንዘብ እንደላከችላቸው ስትነግረኝ በጣም ተገርሜ ነበር:: እንዴት ይህን ሁሉ ለማድረግ ቻልሽ ስላት ገመናዋን ነገረችኝ"

"ምን ነበር?"

"የመን ከመጣች በሁለተኛው ወር ላይ ነበር የወሲብ ንግድ የጀመረችው ስትሰራበት ከነበረው ቤት ሰውዬ ጋር... በተጨማሪ ሰውየው ሳያውቅ ከሁለት ወንድ ልጆቹ ጋር በድብቅ ወሲብ እያደረገች ብር ታገኝ ጀመር... ከዚያ ቀስ በቀስ ከሌሎች የሰውየው ጓደኞች ጋር የወሲብ ንግዷን አስፋፋች... በቃ ራሷን እየሸጠች ቤተሰቦቿን ለወጠች... እኔ እንዳየሁት አብዛኞቹ አረብ ሀገር ያሉ ሴቶች ትልቁ አላማቸው ራሳቸውን ለመለወጥ ሳይሆን ለቤተሰባቸው ህይወት ሲሉ ነው ህይወታቸው የሚበላሸው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ገንዘቡን እንጂ ገንዘቡ የሚመጣበትን መንገድ በጭራሽ አያውቁትም! የሚገርምህ አሁን ድረስ የማውቃቸው ከአምስት የበለጡ ከከፍለ ሀገር የመጡ ሴቶች ለቤተሰቦቻቸው አረብ ሀገር ነን



Scanned by CamScanner

ብላው እየኖሩ አዲስ አበባ ውስጥ በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርተው ገንዘብ የሚልኩ አሉ! አውቃቸዋለሁ"

"ልክ ነሽ ሲባል ሠምቻለሁ! ለጊዜው ወዳንቺ ታሪክ እንመለስ"

"ከዚያ እኔም ራሴን ለመሸጥ ወሰንኩ"

"በወሲብ?"

"አዎ"

"ከማን ጀመርሽ?"

ሣቀች:: ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሣቀች ነው መሰለኝ ሳቋ ደስ ይላል… ዋው በዚያ ላይ የጥርሷ ውበት!!

"አ… ጥርሶችሽ በጣም ያምራሉ! የጥርስ ማስታወቂያ ብትሰሪ የሚያዋጣሽ ይመስለኛል"

"እንዴ! ቃለ መጠይቅ ብለህ ጅንጀና ጀመርክ?" አለችና በድጋሚ ሣቀች:: ከዚያ ትንሽ ቆይታ ንግግሯን ቀጠለች::

"ከምሰራበት ቤት ሰውዬ ጋር"

"እንዴት?"

"እንደ አረብ ወንዶች ሻፋዳ አለ ብለህ ነው? የኢትዮጵያ ሴቶች ሁሉ በእነሱ ዓይን ሸርሙጦች ነን!! ትንሽ ምልክት ያላወቀ መስዬ ሰጠሁት… ባለቤቱ ስራ ስትሄድ ጠብቆ ምንም ሳያንገራግር ጠየቀኝ"

"ምን አይነት ጥያቄ"

"እንዴ አንተ ሁሉንም ነገር ነው ማወቅ የምትፈልገው? መገመት ያቅትሃል?"

"አያቅተኝም ግን ታሪኩን ለአንባቢያን ስለምጽፈው እኔ በተረዳሁበት መንገድ እነርሱ ላይረዱት ይችላሉ"

"እሀ… ለካ ለአንባቢያን… እሺ ቀጥል"

"ምን አይነት ጥያቄ ነበር?"

"I wish making love with you! አለኝ በነገራችን ላይ አረቦች ኢንግሊዝኛ መናገር አይፈልጉም አረብኛ የተቀደሰ ቋንቋ ነው ብለው ያስባሉ በጣም ጥቂቶች ብቻ መጠነኛ የተሰባበረ ኢንግሊዝኛ ሲናገሩ ሰምቻለሁ ለማንኛውም what? አልኩት ባላወቀ"



Scanned by CamScanner

"I wish to have sex with you" በድጋሚ ሲለኝ

"Oh No!" አልኩት፡፡ "አራም" የሚል ቃል ግን አልተጠቀምኩም፡፡

`Please`

`No` አልኩት

`Why?`

`what about you wife?`

`don't worry about her`

ራሴን ነቀነኩኝ፡፡ ይህን ያደረኩት ሆነብዬ ነበር፡፡ ለሁለት ምክንያቶች ነበር፤

"ምንድናቸው?"

"አንደኛ የሴቶች ወግ አለ፤ መግደርደር አለብኝ፤ ሁለተኛ ከሰውዬው የማገኘውን ገንዘብ መጠን ከፍ ለማድረግ ራሴን መካብ አለብኝ፡፡ ሀጢያት መስራቴ ካልቀረ ብዙ ሊከፈለኝ ይገባል"

"እና ተሳካልሽ"

"በጣም፡፡ በዚያ ላይ ሰውየው ቆቅ ነው ወዲያው መኝታ ቤቱ ሄደና እጅግ ያላሰብኩትን የየመን ገንዘብ ይዞ መጣ... ምንም ሳልግደረደር እሺ አልኩት፡፡ የሚገርመው ግን ወሲብ አላደረግንም"

"ማለት?"

"ደሜን ብቻ ወስዶ ሄደ"

"ደሜን?"

"HIV ምርመራ... ከዚህ ተመርምሬ ነው የሄድኩት ግን አረቦች የኢትዮጵያ ሴቶችን አያምኑም"

"ገባኝ"

"ከዚያ እንዳላረግዝ ፈርቼ ከትባት ወሰድኩኝ፡፡ በቃ ለስድስት ወር ወሲብ ከእርሱ ጋር አደረኩኝ! ሚስቱ ስትጠረጥር ከፎቅ ላይ በንዴት እንዳትፈጠፍጠኝ ሰግቼ በፍጥነት ሌላ ቤት ገባሁ... በቃ... ከዚያ.. በስፋት ገባሁበት ... ያው የቤተሰቦቼን ህይወት ለመለወጥ ራሴን ሸጥኩ፤ የወሲብ ሰራተኛ ሆንኩኝ... በመሀከል ከአንድ አረብ ጋር ሳላስበው ፍቅር ያዘኝ"



Scanned by CamScanner

"ፍቅር?"

"ፍቅር!!"

"የተለየ አረብ ነበር፡፡ ለሴት ልጅ ክብር አለው፡፡ ሴትን ልጅ እንዴት መንከባከብ እንዳለበት ያውቅበታል፡፡ አዛኝ ነው! መልካም ነው! ከፈለግሽ እዚህ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሄደን አግብቼሽ እንኑር ብሎኝ ሁሉ ነበር ፤ ግን አድለቢስ ነኝ! ያን ምርጥ አረብ አጣሁት! እውነት ከአረብ ወንዶች ሁሉ የተለየ ለሰው ልጅ ሁሉ ክብር ያለው ነበር"

"ምን ተፈጠረ?"

"ስለ እኔ ሲያጠያይቅ ደረሰበት"

"ምኑን?"

"ዋሽቼው ነበር"

"ምን ብለሽ"

"ጨዋ ነኝ ብዬ ነዋ"

"ድንግል ነኝ ብለሽው?"

"ወሲብ ማድረጌንእማ ነግሬዋለሁ፡፡ ከብዙ ወንዶች ጋር መማገጤን አልነገርኩትም ነበር! የሚገርምህ እውነታውን ስነግረው ከወር በኋላ ሀሳቡን በመቀየር እሱም ይወደኝ ስለነበር እሺ ወደ አገርሽ እንሂድ አለኝ"

"ጥሩ ሰው ነው ማለት ነዋ!?"

"በለው"

"ከዚያ?"

"አንዲት ኩኩሻ የምትባል የዝዋይ ልጅ ነበረች በጣም ትቀናብኝ ነበር፤ ላገባ ወደ አገር ቤት ልሄድ እንደሆነ ስትሰማ በቅናት ድብን ብላ ለዚያ ምስኪን ደግ እና መልካም አረብ ሹከ አለችው"

"ምኑን?"

ሶፊያ ለረጅም ሴኮንዶች በዝምታ ተሞላች፡፡ እኔም ዝምታዋን በዝምታ ጠበኩት፡፡ በመጨረሻ ተናገረች

"በቂጤ ሁሉ ወሲብ ማድረጌን ነገረችው" አለችና ራሷን በሀዘኔታ ነቀነቀችው...፡፡ ከዚያ ንግግሯን ቀጠለች፡፡



Scanned by CamScanner

"በቃ በዚህ የተነሳ ተለየኝ... እኔን ላለማየት ወደኩዌት መሄዱን ሰማሁ:: ውስጤ ተሰበረ! አለቀስኩኝ! ታውቃለህ የእኔ መሆን እንደማይችል ስገነዘብ ይበልጥ አፈቀርኩት! ይበልጥ ተመኘሁት! ይበልጥ ስለ እርሱ ማለም ጀመርኩኝ... ግን ምን ዋጋ አለው? ያ ደግሰው አመለጠኝ! እርሱን ለመርሳት ሲጋራ እና መጠጥ ጀመርኩኝ ከዚያ አላስችል ሲለኝ ከአንድ ጓደኛው አድራሻውን ተቀብዬ ደወልኩለት... ግን ሊያናግረኝ ፍቃደኛ አልነበረም"

"ቆይ ከልብ ይወድሽ ነበር?"

"እኔ በጣም እወደው ነበር እርሱ በጣም ያስብልኝ ነበር:: ለሴት ልጅ ደግሞ ፍቅር ወረት ስለሆነ የሚያስብላት እና የሚንከባከባት ወንድ ይሻላታል የሚል እምነት አለኝ! እርሱ ወሲብ ላይ የማይናወጥ አቋም ነበረው:: `ሴት ልጅ ከብሯን መጠበቅ አለባት! በተለይ ወሲብ ላይ ጨዋ መሆን አለባት` የሚል ውሳኔ ነበረው:: ሸሌ ሚስት እንድትኖረው ማንስ ይፈልጋል? አንተ ራስህ ሚስትህ ከብዙ ወንዶች ጋር የማገጠች ሸሌ ብትሆን ደስ ይልሃል? ታገባታለህንስ? ራስህን ጠይቅ? ለዚያ ነው! አሁን የተረዳሁት እውነታ ወንዶች ሸሌ ጋር ይሄዳሉ! ሸሌ ሚስት ለማግባት ግን አይፈለጉም:: በዚያ ላይ ራሳቸው ሸሌ ጋር እየሄዱ ልጅቷን ሸሌ ይሏታል እንጂ ራሳቸውን እንደ ሸሌ አይቆጥሩትም! ይህ የወንዶች አመለካከት በጣም ያስቀኛል::"

"እሺ"

"አንድ አረፍ ሀብታም በአጋጣሚ በገንዘቡ ለወሲብ ገዛኝና በጣም ተመቸሁት:: በመሀከል ነጋዴ እንደሆነ ነገረኝ:: ይበልጥ ደስ ያለኝ ኩዌት እንደሚሠራ እና የመን አገር ለሥራ እንደመጣ ነገረኝ... በቃ አገርህ ውሰደኝ ብዬ ሞትኩበት:: እንቢ እንዳይለኝ አይቶ የማያውቀውን ወሲብ በመስጠት አረካሁት ወንድ ደግሞ በተለይ የኢትዮጵያ እና አረብ ወንድ ሴት ልጅ በምግብ እና በወሲብ ካስደሰተቻቸው በቀላሉ ይገዙልሃል እናም እሺ አለኝ"

"በቃ?"

"በቃ በቀላሉ እሺ"

"አልፈራሽም?"

"ምኑን?"

"የማታውቂው ሀገር መሄድን?"

"እኔ እኮ ፍቅር ውስጥ ነኝ"

"ለካ ፍቅር እውር ነው"



Scanned by CamScanner

"እውር ነው:: እስማማለሁ"

"ነገሩ በቀላሉ አለቀ? ከየመን ወደ ኩዌት መሄድ ቀላል ነው?"

"ገንዘብ ካለህ ሁሉ ነገር ቀላል ነው:: በዚያ ላይ አረቡ የናጠጠ ሀብታም ነበር"

"ስለዚህ ብዙም ሳትቸገሪ ኩዌት ገባሽ"

"ገባሁ!!"

"በቅምጥነት ማለት ነው?"

"ታዲያ ወንድ ፍለጋ ነው ካልኩት እንዴት ደስ ይለዋል? አፍቅሬያለሁ!! እንዳንተ ያስደሰተኝ ወንድ የለም!! ትንሽ ጊዜ አጥናኝና ከተስማማሁ አግባኝ ምናምን ብዬ ቸብችቤው ነው"

"ቸብችቤው?"

"በውሸት ሞላሁት ለማለት ፈልጌ ነው"

"እሺ"

"ኩዌት ሄድኩኝ:: አሪፍ ሆቴል አስቀመጠኝ:: እሱ ስራ ሲሄድ እኔ ቀንቀን ፍቅረኛዬን እያውጠነጠንኩ እውላለሁ! ለካ ስሙን አልነገርኩህም አህመድ ይባላል፤ እናልህ አህመድን ደወልኩለት ፤ በስንት ሙከራ ስልኩን አነሳልኝ... እርሱን ለማየት እንደመጣሁ ነገርኩት... በስንት ልመና በአካል ተገናኝተን እንድናወራ ቀጠርኩት... ተገናኘን::"

"በስንተኛው ቀን መሆኑ ነው?"

"አራተኛ ቀን"

"እሺ"

"አወራን!! እንደምወደው ለእርሱ ስል ከየመን ድረስ እንደመጣው... በቃ ለእርሱ ያለኝን ፍቅር ሳልደብቅ ገለፅኩለት:: ተስማማን::"

"በምን?"

"ላስብበት አንድ ሳምንት ይሰጠኝ በሚል"

"ደስ አለሽ?"

"ደስ አለሽ ወይ? በደስታ አበድኩ እንጂ የማደርገውን ነበር ያሳጣኝ... ምን ዋጋ አለው በነጋታው መልሼ ግራ ተጋባው?"

"ምን ተፈጠረ?"



Scanned by CamScanner

"ኩዌት ያመጣኝ ሀብታም አረብ ናስር ይባላል፤ 44 ዓመቱ ነበር:: የ14 እና የ15 ዓመት ሴት ልጆች አሉት:: እናታቸው በካንሰር ህመም ሞታለች... በነጋታው በፍፁም ደስታ ተሞልቶ መጣ... ምን ተገኘ? ስለው ደስታውን ነገረኝ... ደስታው ግን ለእኔ ግራ መጋት ፈጠረብኝ"

"ምን ነበር?"

"በደስታ ሰክሮ ስለ እኔ ለሁለቱ ልጆቹ እንደ ነገራቸው እና ፍቃድ እንደሰጡት ነገረኝ! እናም ለእኔ ክብር ሲባል ከሳምንት በኋላ ዋና ቤቱ በመጠነኛ የቀለበት ሥነ ሥርዓት ቤቱ እንደምገባ አጫወተኝ"

"ኡ"

"ልክ ነህ ኡ... ያስብላል... እየሀ እኔ ስዋሽው አላወቀም:: ተከትዬው ኩዌት ሳመራ የእውነት አፍቅሬው መስሎት ነበር... ሁለቱ ልጆቹ እንቢ ቢሉት እና እኔን ባይመርጡለት ኖሮ ራሱ ከእኔ ጋር ቤት በመከራየት ለመኖር ወስኖ ነበር"

"ወዶሻል ማለት ነው?"

"እንደዛ በለው"

"ከዚያስ?" አልኳት:: አዛ የነበረውን እና ጠረጴዛ ላይ የነበረውን ውሃ አንስታ ግጥም አድርጋ ጠጣችው... በሀሳብ ኩዌት እንደሄደች ያስታውቃል ... ለተወሰነ ጊዜ አሁንም ዝም አልኳት:: ራሷ ከሀሳቧ ተመለሰች.. ስለ ሶፊያ ውበት! ቁመት! ሰውነት እንዳወራ ፍቃድ ባትሰጠኝም ስለ ሀቅ ከጥርሶቿ በተጨማሪ መግነጢሳዊ ውበት እና መስዕብ ያላቸው ውብ ዓይኖች አሏት... አንዳች የሚረጨት አስደማሚ ውበት አላቸው!!

"ናስር ራሱ ጥሩ ሰው ነው:: መስሪያ ቤቱ ወሰደኝ:: እኔ መስራት የምፈልገውን ጠየቀኝ... ያለ ስራ የቤት እመቤት ብቻ መሆን እንድቀመጥ እንደማይፈልግ ለስራ ከፍተኛ ክብር እንዳለው አጫወተኝ ... ሁለቱ ልጆቹም ለምን እንደሆነ ባላውቅም በፍቅር ነበር የሚያዋሩኝ! ደስ የሚሉ ልጆች ነበሩ.. በቃ ሁሉ ነገር እኔ የምመኘው አይነት ነበር... ያው ለቀለበት ቀኔ አንድ ቀን ሲቀረኝ ለአህመድ ደወልኩለት ሊያገባኝ እንደማይችል ነገረኝ"

"ቃል በቃል?"

"አዎ! ቃል በቃል አዝናለሁ ላገባሽ አልችልም ነበር ያለኝ"

"እሺ ወደ ቀለበቱ?"



Scanned by CamScanner

"ምን ጥያቄ አለ? በመጠነኛ የቀለበት ሥነ ስርዓት ቃል ኪዳን ገባሁለት፡፡ ከስድስት ወራት በኋላ ኢትዮጵያ ሄደን ልንጋባ እንችላለን ለሚለው ሀሳብ ተስማማን"

"ምን ተሰማሽ?"

"ግራ መጋባት ! ሀዘን እና ደስታ! አሰበው እኔ ኩዌት ያመራሁት ፍቅረኛዬን ፍለጋ ነበር እንጂ እንዲህ በቀላሉ ቀለበት ምናምን የሚል ግምት አልነበረኝም"

"ያልገባኝ"

"እህ"

"ናስር ስለ ቤተሰቡ አልነገረሽም ነበር?"

"ልጆች እንዳሉት ነግሮኛል... ስለሚስቱ ግን ኩዌት ስንደርስ እነግርሻለሁ ነበር ያለኝ፤ አየህ እኔ ያኔ ይህ ሁሉ ነገር ይመጣል ብዬ ሀሳቡ ስላልነበረኝ ፍቅረኛዬ አህመድን ለማግኘት ብቻ ናስርን መረማመጃ ነበር አድርጌው የመጣሁት! አንድ ፐርሰንት እንኳ ያገባኛል የሚል ግምት አልነበረኝም"

"ሳታስቢው ቀለበት አሰርሽ?"

"አሰርኩ! ትልቅ ቪላ ቤት ገባሁ... ስራ ጀመርኩ ... ሁለት ወር ሲሞላኝ ደስታዬን በቃላት መናገር አቃተኝ! በቃ የናስር እንክብካቤ ፣ የልጆቹ ፍቅር፣ በነገራችን ላይ በመጠኑ እናታቸውን ቁርጥ እመስል ነበር... ትልቅ የሚያምር ፎቶ ሳሎኑ ውስጥ ነበር... ብቻ ያላሰብኩት ልዩ ህይወት ውስጥ ገባው... ደስተኛ ህይወት ጀመርኩ ... አባት እና ሁለት ልጆቹ ከአረቦች ዘንድ ጨርሶ ይኖራል ብለህ በህልምህ እንኳ የማታስበውን ፍቅር ሰጡኝ... በቃ እኔም ደስተኛ ሆንኩኝ"

"ጨዋታውን እንቀጥላለን ስለ ህይማኖት አልነገርሽኝም ምን ነበርሽ?"

"ይህ ጥያቄ ይለፈኝ"

"እሺ ወደ ጨዋታሽ ተመለሺ?"

"እውነቱን ለመናገር አረቦች ጨካኝናቸው፡፤ ለሰው ልጅ ሰብዓዊነት ይጎላቸዋል... ለመናገር የሚከብዱ ዘግናኝ ነገሮችን ይሠራሉ፤ ግን ሁሉም አረቦች ጨካኝ አይደሉም! ፍቅርን የሚያውቁ እና ፍቅር ከሰጠሀቸው የበለጠ ፍቅር የሚሰጡህ ምርጥ ናስርን የመሰሉ ደጋግ አረቦችም አሉ! እንክብካቤውን ልነግርህ አልችልም! ስራ ቦታ ስለ ስራዬ ቀን ቀን በቀላሉ እንዴት እንደምሰራ ያስረዳኛል ... ያዝናናኛል... በዚያ ላይ ሁለቱ ልጆቹ የሚሠጡኝ ፍቅር እና



Scanned by CamScanner

አከብሮት ልነግርህ አልችልም! እኔ ራሱ ሳስብው ለማመን ነበር የሚያስቸግረኝ"

"እድለኛ ነሽ!"

"ነበር ግን አልተጠቀምኩበትም"

"ማለት?"

"እድል በር የምታንኳኳው አንዴ ነውና በወጉ ተጠቀምባት የሚባለው ትልቅ አባባል ነበር!! ዋን ዋጋ አለው? ፍቅር ግን እውር ነው"

"ማለት?"

"ሶስት ወር ከ15 ቀናት በኋላ ሳላስበው አህመድ ደወለ"

"ደወለ!?"

"ደወለ!! አግኝቼ ላናግርሽ እፈልጋለሁ አለኝ"

"እና?"

"ምን እና አለው ለናስር ምክንያት ፈጥሬበት የቀጠረኝ ቦታ ሄድኩኝ:: ከዚያ ሁሉ ነገር ውሃ በላው"

"አልገባኝም?"

"ፍቅርሽን ተቀብያለሁ አወድሻለሁ አለኝ"

በዝምታ አየዋት:: ምን መናገር እንዳለብኝ ግራ ስለገባኝ ነበር...

"ምን እንደነካኝ አላውቅም ወዲያው አልጋ ቤት ተያይዘን ገባን... የሚገርም ወሲብ አደረግን"

"ወሲብ?"

"በጣም እኮ ነው የምወደው"

"ቃለበቱን አላየም?"

"ምኝ አደረከኝ እንዴ? አውልቄ ደብቄው ነበር!!"

ይቅርታ ጠይቃኝ በመነሳት ሽንት ቤት በመሄድ ከአፍታ ቆይታ በኋላ ተመልሳ መጣች... ኖር በማለት በአከብሮት ከወንበሬ ብድግ በማለት ወንበር ስቤ አስቀመጥኳት... ይመስለኛል አልቅሳ ፊቷን በውሃ ታጥባ ነው የተመለሰችው... ግምት ነው::

"አመሠግናለሁ"

"ምንም አይደለም" አልኳት::



Scanned by CamScanner

"አብረን አደርን"

"አብራችሁ አደራችሁ???

"ልክ ነው ያስብላል!! ፍቅር እውር ነው!! ከአህመድ ጋር እቅፍ እንዳደረኩት ብሞት! ደርቄ ብቀር ራሱ ደስ ይለኝ ነበር... እንቢ ለማለት ሆነ እርሱን ጥሎ ቤት የመሄድ ፍላጎት አልነበረኝም ፤ ባለቤቴ እንዳይጨቀጭቀኝ ስልኩን ዘግቼበት ነበር

በዝምታ ብቻ አየዋት...::

በትዝታ መነፅር ራሷን ነቀነቀች... ኩዌት በሀሳብ እንደሄደች ገባኝ... ዝም አልኳት...

"ስለ እኛ ሴቶች ሁለት የሚገርሙ አባባሎች አሉ ልንገርህ?"

"እንዴታ"

"የመጀመሪያው ሴት ልጅ ከረዳት ይልቅ የበዳትን ታስታውሳለች ሲሆን ሁለተኛው ሴት ልጅ ከሚያፈቅራት ወንድ ይልቅ ለምታፈቅረው ልቧን ትሸጣለች... በቃ እኔ ላይም የሆነው ይህ ነው:: በጣም የሚገርምህ እነዚያ ጨካኝ፤ አውሬ በምላቸው ሰዎች መሀከል የናስር አይነት መልካም ሰው ማግኘት መታደል ነው... በነጋታው ቤት ስገባ ናስር ስራ አልሄደም ነበር... ሁለቱ ልጆችም ቤት ውስጥ አልነበሩም ... ከፈለገ አንቆ መግደልም ሆነ ከፎቅ ላይ ወርውሮ ሊገለኝ ይችል ነበር፤ ግን የተባረከ ሰው ስለሆነ በፍቅር ብቻ አስተናገደኝ... አየህ እርሱ ለቀለበቱ ታማኝ ስለ ነበር እኔ በአንዲት ቀን ብቻ ተዋረድኩ"

"አወቀ"

"ሙሉ ለሙሉ"

"እንዴት?"

"በፍቅር የሰከረ ሰው የሚያደርገውን መቼ ያውቃል? መች ያስተውላል? ውርደት በፍጥነት ተከናነቢ ሲለኝ ጓደኛ ነው ብሎ ያስተዋወቀኝ ሰው ሆቴል ነበር ያደርኩት!! ናስር በቃላት የማይገለፅ ትዕግስተኛ ሰው ነበር... ሌሊቱን ሙሉ የመን ደውሎ ስለ እኔ አጣርተው እንዲነግሩት አድርጓል... መረጃ አግኝቷል ... በፍቅር ሳመኝ:: ሠላምታ ሰጠኝ:: አጠገቤ ተቀመጠ::"

"የእውነት ትዕግስተኛ ሰው ነው"

"እየነገርኩህ! የተለየ ሰው ነው"

"እሺ"



Scanned by CamScanner

"ሁሉን ነገር አውቄያለሁ! ወድጄሽ ነበር! የሚገርምሽ ልጆቼ ራሱ በጣም ነበር የወደዱሽ… ማታ ራሱ የት ሄደች እያሉ ሲጨቀጭቁኝ ነበር:: አውቃለሁ ወጣት ነሽ! ፍቅር አስቸጋሪ ነው… መጀመሪያውኑ እኮ እውነቱን ብትነግሪኝ እኔ አንቺን ለመርዳት አጥር ነበር… ነገሮች አይበላሹም ነበር… እኔ በፍቅር አምናለሁ! አካልሽ እንጂ ልብሽ የሌላ ሰው ከሆነ ምንም ማድረግ አልችልም!! ነገሮችን እስከምታስተካክይ ከእኔ ጋር መቀመጥ አልከለክልሽም! እኔን ያሳደገችኝ ሴት ናት! አባት የለኝም… እኔ ለሴት ልጅ ትልቅ ከብር ስላለኝ ይህ ነገር በጓደኛዬ ሆቴል ቢፈጸምም እኔ ለክብሬ የምጨነቅ አይነት ሰው አይደለሁም፤ ባንቺ ላይ እጄን ለመሰንዘር አይደለም ሃሳቡ እንኳ የለኝም አለችና ትንፋሽ ወሰዳ

"ብዙ ነገር ነበር የመከረኝ!! የፈለኩትን የመወሰን መብቴ የእኔ እንደሆነ ነበር የነገረኝ፤ ይህ ጉዳይ በምንም ሁኔታ ሁለቱ ልጆቹ እንዳይሰሙ ነበር የለመነኝ… እንደዚያች ቀን ሰቅሰቅ ብዬ ያለቀስኩበት ቀን የለችም!! አነባሁ! አለቀስኩ!! ለምን እያልኩኝ ራሴን ጠየኩኝ:: በቃ የዚያን መልካም ሰው አይን ማየት ስለፈራሁ ቀለበቱን ቤት አስቀምጬ ቅሌን ጨርቄን ሳልል… ከቤቱ ወጣሁ::፤ ወደ ማታ ራሴን ሳረጋጋ ለአህመድ ደወልኩለት፤ ተገናኘን ፤ አብረን በድጋሚ አደርን!! የዚያችም ምሽት የሚገርም ወሲብ ነበር ያደረኩት! ምን እንደ ገረመኝ ታውቃለህ?"

"እህ"

"ድብን ያለ ፍቅር ይዞህ ያውቃል"

"ድብን ያለ?"

"በቃ ሁሉ ነገርን የሚያስረሳ! ዓለምን ሁሉ የሚያስረሳ! በአንድ ጊዜ በልዩ ደስታ የሚሞላ…"

"አላጋጠመኝም"

"ቆይ ፍቅረኛ አለችህ?"

"ለጊዜው የለኝም"

"ለማስረዳት እንዲቀለኝ ነበር"

"ነገሪኝ ስሚትሽን መረዳት አያቅተኝም"

"እህ… ለካ ፀሐፊ ነገር ነህ… በቃ አህመድ ከንድ ስር ስገባ ውስጤ በደስታ ቀለጠች! ሁሉን ነገር ረሳሁት! ከዚያ መልካም ሰው ይልቅ አህመድን ልቤ መረጠ!! ፍቅር እውር መሆኑን የዚያች ምሽት በሚገባ ተገነዘብኩኝ:: ሊሊቱን ሙሉ በሀሴት ስከሬ አደርኩኝ



Scanned by CamScanner

የፍቅር ሀሁን... ለእርሱ ስል ከየመን ኩዌት ከሄድኩለት አህመድ ጋር... ለእርሱ ስል ቀለበቴን ከጣልኩለት አህመድ ጋር ለመቀጠል ወሰንኩ። በፍቅር እብድ ለማለት ተዘጋጀሁ!! አህመድን ከፈጣሪ በላይም እንደምወደው ነገርኩት"

ከዚያስ? የሶፊያ መጨረሻ ምን ሆነ? በክፍል ሁለት የሶፊያ ታሪክ ይቀጥላል... (አይዞዋችሁ ክፍል ሁለት በዚው መፅሐፍ ላይ ነው... በክፍል አንድ ያወራነው ይህን ብቻ ነበር... አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ትልቁ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፊት ለፊት ተቀምጠን... ክፍል ሁለትን ከሶስት ታሪኮች በኋላ እስከምታነቡ ክፍል አንድን በዓለም ላይ በጣም ዝነኛ በሆነችው በኩዌቶች አባባል እንሰናበት

"እግር የሌለው ሰው እስከማይ ድረስ ጫማ ስለሌለኝ አዝን ነበር!!"



Scanned by CamScanner

# እኛ እና ፈስ

ይቺን ፅሁፍ ለመፃፍ መነሻ የሆነችኝ 'ቤቲ ሎከር ናት' ፡፡ እውነተኛ ስሟን መጠቀም አልፈልግም፤ እኔም አልደሰትም፤ እርሷም ትበላኛለች፡፡ የማናጅመንት ተማሪ የነበረችው ቤቲ የአዲስ አበባ ልጅ ነበረች… ዝሆን የሚያክል ቁመና ነበራት! የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለች አያሌ ወንዶች ከበቧት… ቤቲም ሙቀት ተሰማት … ከዚያ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ አስቀያሚውን ታሪክ ፃፈች! ከአንድ ዶርም ውስጥ የሚጋሩ ስምንት ተማሪዎች አወጧት!! በሀበሻ ምድር ስም መለጠፍ ብርቅ አይደለምና ወዲያው ቤቲ ሎከር የሚል ስያሜ ተሰጣት! ከዚያማ የህዝብ ሽንት ቤት ናት! ለጠየቃት ሁሉ ጭኗን ትከፍታለች… እኔ ማንን ስከለክል አይተህ ነው እያለች ታለቅሳለች አሉ (በእርግጥም ይህ ሀቅ ጭምር ነበር)

የእኔን ትኩረት በጣም የሳበው ይህ ጉዳዩ ሳይሆን ዛፍ የምታክለዋን ቤቲን በጭራሽ የሚደግማት ባለመኖሩ ነበር! ሁሉም አንድ ጊዜ ከቀመሳት በኋላ ቀይ ካርድ ይሰጣታል፤ ታዲያ የመጀመሪያ ዓመት በበርካታ ወንዶች ተከባ የነበረችው ዛፍ የምታክለዋ ግዙፍ ቂጥ የነበራት ቤቲ… ሁለተኛ ዓመት ቀዘቀዘች፡፡ ጠዋትና ማታ ውሎዋ ቤተከርስቲያን ሆነ… ሀይለኛ "ወጪኒ" ሆነች… ያቺ ስንቶች ያሸረግዱላት የነበረች ወጣት ራሷን ጥላ ስመለከት ሴት ልጅና ፅጌሬዳ አበባ አንድ ናቸው ፤ አንድ ጊዜ ሲቀጠፉ ይጠወልጋሉ የሚባለውን እያስታወስኩ ከቤቲ ስብራት ጀርባ ያለውን ምክንያት ለማወቅ የቤቲን ድንግልናዋን በጥሶላታል እየተባለ የሚወራለትን በእግር ኳስ የተነሳ የተግባባውትን የ Biology ተማሪ የሆነውን ያሬድን አነጋገርኩት! ያሬድ በጣም አሪፍ ልጅ ነው፡፡ ግልፅ! እውነቱን የሚናገር! ሰውን ለመርዳት የሚጥር! እርጋታ ጭምር ያለው ወጣት! (አሁን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ይሠራል)

"ከቤቲ መቀዝቀዝ ጀርባ እጅህ አለበት?"

"ማለት?"

"መጀመሪያ ካንተ ጋር ነበር ወሲብ…"

" በነገራችን ላይ እኔ እንደማልዋሽ ታውቃለህ? እኔ በጭራሽ ቤቲን አልጀነጀንኳትም! የአስተማሪዎች ካፍቴሪያ ውስጥ ራሷ መጥታ ተዋወቀችኝ … የWelcome ፕሮግራም ላይ ጓደኛዬ ጠርቶኝ ስሄድ በድጋሚ መጥታ አዋራችኝ… በቀጥታ ወሲብ አድርጋ እንደማታውቅ



Scanned by CamScanner

እና ወሲብ ማድረግ እንደምትፈልግ ብቻ ነገረችኝ! በቃ በስምምነት የተፈፀመ ወሲብ ነበር በስምምነት ተለያየን! እንደነገረችኝ አባቷ እስር ነበር የያዛት! ከቤት ት/ቤት ፣ ከት/ቤት ቤት ነበረች! አሁን ነፃ ስትወጣ አባቷን የተበቀለችው መስሎዋት ነው:: ለማንም ወንድ በቀላሉ እየተኛች የሚገኘው... እንዳንዴ ወንዶች ስንባል በጣም ባለጌዎች ነን! አብሮዋት የተኙት ሁሉ አወሩባት! ከዚያ ሁሉም ሸሻት... በቃ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለሰች፤ እንደ እኔ ጥሩ ውሳኔ ነው የወሰነችው"

"ምንድነው ያወሩባት?"

"አልሰማህም?"

"ምኑን?"

"የቤቲ ቅፅል ስም ማን ነው?"

"ቤቲ ሎከር"

"ሌላስ?"

"አልሰማሁም"

"ቤቲ ፈሶ!! Miss Fart"

"ፈሶ?"

"ከቤቲ ጋር በድጋሚ አልጋ ላይ የሚወድቅ ወንድ የለም! ማንም ሰው እኮ ይፈሳል! ትንሹ አንጀት ውስጥ ምግብ ሲፈጭ ወይም አንጀታችን ውስጥ ኬሚካል ሪያክሽን፣ ባክቴሪያ ፣ እንዲሁም ወደ ውስጣችን ስንበላ፣ ስንጠጣ በተለይ አያወራን የምንበላ ከሆነ ያልተፈለገ አየር ሲገባ እንፈሳለን! እንዳንዴም ሰገራ ቤት መሄድ ኖሮብን ከረሳን ሰገራ ቤት እንድንሄድ ሰውነታችን በፈስ አማካኝነት ምልክት ይሰጠናል.. ባጭሩ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ይፈሳል! በእርግጥ ሶስት አይነት የፈስ አይነቶች አሉ:: የማይሸት ፈስ፣ ለተወሰነች ጊዜ የሚሸት ፣ በጣም የሚሰነፍጥ (Stink) ... እናም የቤቲ ፈስ እጅግ በጣም የሚሰነፍጥ! ሊያስታውከህ ሁሉ የሚደርስ በጣም የሚገማ ነው:: አብረን ያደርን ጊዜ ያየሁትን ስቃይ እኔ ነኝ የማውቀው በዚህ የተነሳ ወሬው ተዛመተ ወንዶች ሸሹዋት... ሴት ልጅ ደግሞ ምራሉዋ በፍጥነት ነው የሚነዳው፣ የዶርሚ ልጆች ራሱ እሷ መኝታ ቤት ውስጥ ካለች አይገቡም! አይተኙም"

የቤቲን ፈሶን ጉዳይ እዚህ ላይ ልግታውና ወደ ፈስ እንመለስ... በሀገርኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ከፈስ ጋር የሚከተሉት ይጠቀሳሉ



Scanned by CamScanner

⇒ ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም!

⇒ ፈስቶ ቂጥን መያዝ

⇒ ፈስ በምንጠ እየተለቀመ ነው

⇒ አባት ፈስቶ በልጅ አመካኘ

መሰል ተረትና ምሳሌዎች ይጠቀሳሉ፤ በተጨማሪ በአማርኛ ፈሊጣዊ አነጋገር "ፈሳም" ፈሪ፣ በራሱ የማይተማመን ፣ አቋም የሌለው ሰው ማለት ነው... ለማንኛውም የBiology ተማሪ ከነበረው ያሬድ ጋር ስለፈስ ይህን አወራን...

"እንደ Biology ተማሪነትህ ስለፈስ ማንበብህ አይቀርም! ፈስ ቅድም ያልከኝ እንዳለ ሆኖ በሳይንስ እንዴት ይታያል?"

"ማንኛውም ጤነኛ ሰው ይፈሳል! በዓለም ላይ የማይፈሳ ሰው የለም:: እንዳልከው በሳይንሱ አንድ ጊዜ ስትፈሳ በዚያች ፈስ ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች አሉባት

59% ናይትሮጂን

21% አይድሮጂን

9% ካርቦንዳይ ኦክሳይድ

7% ሜንቴን

4% ኦክስጅን

1% ሰልፈር

አየህ ይህ ሁሉ በአንዲት ፈስ ውስጥ የሚገኝ ነገር ነው፡፤ በሳይንስ በከፍተኛ ጥናት እንደተደረሰበት በቀን ውስጥ ወንዶች አስር ጊዜ በትንሹ ሲፈሱ ሴቶች ደግሞ 14 ጊዜያት ይፈሳሉ ማለት ነው፤ ስለዚህ ከወንድ ይልቅ ሴቶች ይፈሳሉ ማለት ይቻላል"

"እህ... ለምሳሌ እኔ የማልፈሳበት ብዙ ጊዜ አለኝ አንተ ራሱ በየቀኑ ትፈሳለህ እንዴ?"

"ሊገርምህ ይችላል ግን ይህ ሀቅ ነው! We can't really cheat nature, even if you mange to hold your fart in all day በእርግጠኝነት ማታ ተኝተህ አንተ ሳታውቀው ትፈሳለህ:: በዚያ ላይ እንደነገርኩህ ቀላል ፈስ፣ መካከለኛ ፈስ፣ ከባድ ፈስ አለ! ቀላል ፈስ ከሆነ ያለህ እንኳን ሌላ ሰው አንተ ራሱ ስትፈሳ ላይታወቅህ ትችላለህ! ቀን አልፈሳህም ማለት ማታ አትፈሳም ማለት ግን አይደለም!! የሚገርምህ ከሰው



Scanned by CamScanner

ሊጅ ይልቅ በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚፈሱት Termites ናቸው"

"ስለ ግማቱ ሳይንስ የሚለው አለው?"

"አለው!! ዋናው እውነታ ባለሙያዎች በጥብቅ የሚያሳስቡት አንዱ ነገር ፈስ የተፈጥሮ ጉዳይ ስለሆነ መቆጣጠር የለብንም ወይም ፈስ መያዝ የለበትም ብለው ይመክራሉ! ምክንያቱም ፈስ ውስጥ 7% ሜንቴን ጋዝ አለው፤ ይህ ደግሞ ሲታመቅ (አምቀህ በተደጋጋሚ መያዝ ለሰውነት አደጋ አለው)... ለምን የአንዳንድ ሰዎች ፈስ በጣም ይገማል? ለሚለው ጥያቄ አብዛኛው ሰው ውስጥ 1% ሰልፈር ከፈስ ጋር ይወጣል፤ ይህ ሰልፈር ፈስ ሽታ እንዲኖረው ያደርጋል!! ከዚህ በተጨማሪ አንዳንዶች ብዙ ሰልፈር ያላቸውን ምግቦች ለምሳሌ ባቄላ፣ ጎመን፣ አተር፣ ቺዝ ለስላሳ፣ እንቁላል፣ ፎሶሊያ... የመሳሰሉትን በብዛት የሚመገቡ ከሆነ ሲፈሱ የፈሱ ግማት ሊጨምር ይችላል... አንዳንዴ የጨጓራ በሽታ ካለብህም ፈስህ ግማቱ ይጨምራል! በተለይ በጣም ቅመማ ቅመም የበዛበት ምግቦች የምታበዛ ከሆነ የፈስህ ግማት ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው፤ ስለዚህ የቤቲ ፈሶ ችግር መንስኤ ከዚህ ውጪ አይደለም"

"በነፃነት ፈሳችን ሲመጣ መፍሳት አለብን ነው የምትለው?"

"አልወጣኝም! በኢትዮጵያ ባህል እኮ ሰው ፊት መፍሳት ያስነውራል! ንቀት ነው! እኛ አገር ፈስህ ሲመጣ ይቅርታ ጠይቀህ ተነስተህ ሄደህ ፈስተህ መመለስ አለብህ እንጂ ፈሳችን መጥቶ ፈሳችንን ለማመቅ መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ባህል ሰው ፊት መፍሳት አስነዋሪ ነው:: ይህ የሚበረታታ ባህላችን ነው ባንፃሩ ቻይና ብትሄድ በነፃነት የመፍሳት ባህል አላቸው.. ፈስህን ብታዝረጠርጠው ማንም ከቁብ አይቆጥርብህም... የህንድ ያኖማሚ ጎሳዎች ፈስ ከብር ነው፤ በተለይ ቤታቸው ሄደህ ምግብ ተመግበህ ወዲያው ከፈሳህ ደስታቸው ከፍተኛ ነው እና እዚያ ጎሳ ፈሷ በጣም የምትሸት ሴት ካለች አፍቃሪዎቿ በርካታ ናቸው:: ለምሳሌ የእኛዋ ቤቲ ፈሶ እዚያ ጎሳ ብትሄድ ለፍቅር ሆነ ለጋብቻ ብዙ ወንዶች ይጋደሉባት ነበር... የሚገርምህ ሞተን 18 ሰዓት እስከሚሞላን ራሱ መፍሳታችን ይቀጥላል.. ፔሩ ውስጥ ሰው ፊት ድንገት ብትፈሳ በቦክስ ነው መሬት ላይ የሚያነጥፉህ! ፔሩ ከኢትዮጵያ በላይ ሰው ፊት መፍሳት ትልቅ ነውር እና እንደ ትልቅ ንቀት የሚታይባት አገር ናት!! ባጠቃላይ አንድ ወንድ በቀን ውስጥ ከተመደበለት አስር ጊዜ በላይ ... ለሴቶች ደግሞ ከ14 ጊዜያት በላይ የሚፈሱ ከሆነ የበሽታ ምልክት ስለሆነ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል መሄድ እና



Scanned by CamScanner

መታየት ማለትም ነው ወይም ወዲያው ሁለት ነጭ ሽንኩርት መብላት እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል"

"እና እንደ ቤቴ ፈሶ በጣም Stink የሆነ ፈስ ያላቸው ምን ተሻላቸው??"

"ቀላሉ ዘዴ ቅድም የጠቀስኳቸውን ምግቦች ከመብላት መቆጠብ ሳይሆን መቀነስ ነው፤ በነገራችን ላይ የራስህ ፈስ ለራስህ በብዛት አይሸትህም ፤ ግን የራስህ ፈስ ለራስህ ሸታው የሚታወቅህ ከሆነ በእርግጠኝነት ለሌላ ሰው ይበልጥ ስለሚገማ ሰው ፊት ከመፍሳት መጠንቀቅ ተገቢ ነው! ሰው ፊት ሲጋራ ማጨስ ሆነ ሰው ፊት መፍሳት አንዱ አስነዋሪ ጉዳይ ነው!! አንዱ የራስ ወዳድነት መገለጫ ነው"

ይቺን ፅሁፍ በምርቃት ልጨርሳት! በፈሊጣዊ አነጋገር "ፈሳም!!" ከመባል ያድናችሁ...!!

አሜን::



Scanned by CamScanner

# እኛ እና ካሎሪ

ይህ የሲራክ ሜሲ ታሪክ በአያያ መፅሐፍ ላይ እንደ ምርቃት ለመቅረብ የተዘጋጀ ነበር... ከአያያ ታሪክ ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር ባለመኖሩ እነሆ በዚች ቅንጭብጫቢ ታሪክ የያዘች መፅሐፍ ላይ ስለ ሲራክ ሜሲ ታሪክ ማቅረቡ ተገቢ ሆነ...፡፡

የሲራክ ስም ላይ የሜሲ ስም የተጨመረው የሲራክ አባት ሜሲ ስለሆነ አልያም ሲራክ እንደ ዝነኛው ሜሲ ምርጥ እግር ኳስ ተጫዋች ስለሆነ አይደለም! ይህ ስም የወጣለት ሲራክ እንደ ዝነኛው ሜሲ አጭር ስለሆነ ብቻ ነው፡፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ H.P.E ተመራቂ የነበረ ቢሆንም አሁን ሙያውን በመለወጥ የሥነ ምግብ ባለሙያ ሆኗል እናም ከአጭሩ፣ ፈገግታ ከማይለየው አለም አቀፍ ዜግነት ካለው (አለኝ ብሎ በሚያምነው) ሲራክ ጋር ስለ ምግብ ካወራውት በትንሹ ላቃምሳችሁ (አለም አቀፍ ዜግነት ጋር በተያያዘ መጀመሪያ ትንሽ ልበል፡፡ ሲራክ ዩኒቨርሲቲ እያለን ከዘረኝነት ጋር በተያያዘ ጠብ ሲከሰት የዘወትር ንግግሩ ይቺ ነበረች

"ይህን ዘረኝነት እንዴት ታየዋለህ" ሲባል "አስተሳሰባችን ምን ያህል ኋላቀር እንደሆነ ታያለህ? በዚህ በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አማራ፣ ትግሬ፣ አሮሞ... ወላይታ... እየተባባሉ መጣላት ምን ያህል የጭንቅላት አስተሳሰብ ጥበት እንዳለብን ያሳያል፤ ለነገሩ እኔ ምን አስጨነቀኝ"

"ለምን?"

"እኔ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም"

"እና?"

"አሜሪካዊ፣ ኢንግሊዛዊ... አፍሪካዊ ... ህንዳዊ ... ሁሉንም አይደለሁም!! እኔ ዜግነት የለኝም!! የእኔ ዜግነት አለም አቀፋዊ ነው፡፡ አለም አቀፍ ዜግነት ያወጣው የዓለም ብቸኛው ወጣት እኔ ነኝ" ይል ነበር፡፡)

ለማንኛውም ከሲራክ ጋር ትኩረት በመስጠት የማወራው ስለዘረኝነት፣ ስለአለም አቀፍ ዜግነት! ለመሆኑ አለም አቀፍ ዜግነት አለወይ? ሳይሆን ስለ ምግብ ነው፡፡ ከምንበላው ምግብ በላይ ምን አስደሳች ነገር አለና? አንዳንድ የሥነምግብ ምሁራን ስለማንነትህ



Scanned by CamScanner

ከምትበላው ምግብ በመነሳት ማወቅ ይቻላል ይላሉ you are what you eat ይላሉ! ምግብ ሳንመገብ ስንት ቀናት መቆየት እንችል ይሆን? ከህይወታችን ቁልፍ ነገሮች አንደኛው ምግብ ነው:: ለመሆኑ ስንቶቻችን ስለምንበላው ምግብ በቂ እውቀት አለን ይሆን? እስቲ ይቺን ቀላል ጥያቄ ለመመለስ ጥረት አድርጉ

ጥያቄ 1. ከሚከተሉት ገንቢ ምግብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በቆሎ ለ. ጤፍ ሐ. አቡካዶ መ. አናናስ

ጥያቄ 2. ከሚከተሉት ኃይል ሰጪ ምግብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጎመን ለ. አቾሎኒ ሐ. ማንጎ መ. ቴምር

ጥያቄ 3. ከሚከተሉት በሽታ ተከላካይ ምግብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ብርቱካን ለ ቆስጣ ሐ. ቅቤ መ. መንደሪና

መልሶች

1. ____________________

2. -/3

3. ____________________

"እንኳን በሰላም አገርህ መጣህ" አልኩት ሆን ብዬ ለነገር ነው፤ ሲራክ ፈገግ አለና

"እኔ አለም አቀፍ ዜግነት ያለኝ ብቸኛ ሰው ነኝ! ይህን ስልህ ኢትዮጵያን እጠላለሁ አልያም ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተወለድኩ ደስተኛ አይደለሁም እያልኩ አይደለም! ኢትዮጵያም ከመሬት ከፍሎች አንደኛዋ ነች"

"ይገባኛል! ኖርዌይ እንዴት ናት?"

"ዋው! ድንቅ ነች! የተወሰነ ጊዜ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ የምቆየው የሆነች ኖርዌያዊት ቺክ ስለጠበሰችኝ በቅርቡ ለጋብቻ እመለሳለሁ"

"ስለጠበሰችኝ?"

"አዎ! ወይ ትጠብሳለህ ወይ ትጠበሳለህ! የእኔ ዕጣ ፋንታ መጠበስ ነበር ተጠበስኩ! ምነው ቀናህ እንዴ" ፈገግ አልኩኝ::

ከሲራክ ጋር ስለ ኖርዌይ ቺኮች፣ ስለተመረቀበት የሥነ ምግብ ትምህርት፣ ስለ ኖርዌይ ህዝቦች... በተለይ ስላላቸው የዲሞክራሲ ነፃነት በመጠኑ ተበረጨቅን! ሲራክ



Scanned by CamScanner

እንደነገረኝ ኖርዌይቷ ቺክ ሲራክን የጠበሰችው በሲራክ ቁመና እና የጭንቅላት ብቃት ተስባ ነው፤ እንደነገረኝ በልዩ ብቃት ከሀያ ሁለት አገራት ከመጡ ዜጎች እና በርካታ የኖርዌይ የሥነ ምግብ ተማሪዎች በልዩ ብቃት ነበር አንደኛ ለመውጣት የቻለው፤ እናም በከፍተኛ ማዕረግ ነበር የተመረቀው፤ በዚህ የተነሳ በአንድ የኖርዌይ ባለ 4 ኮከብ ሆቴል ውስጥ ለመስራት ጣጣውን እንደጨረሰ ነግሮኛል:: ይመቸው:: (አሁን እየሰራ ይገኛል)

"ስለ ምግብ እናውራ?"

"የተወሳሰበውን ማብራሪያ ልተወውና በቀላሉ ሰውነታችን ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ እንዲሆንም ሆነ ተገቢውን ስራ በተገቢው ሁኔታ እንዲያከናውን ምግብ መመገብ ወሳኝ ነገር ነው!! ምግብ መብላት ግዴታም ነው!!"

"ሰው በምግብ ብቻ አይኖርም የሚለው አባባልስ?"

"ሳትመገብ ለስንት ቀናት መቆየት ትችላለህ? ያ ከሀይማኖት ጋር በተያያዘ ነው:: እኔ በዚህ አላምንም! ምግብ ባለመብላት እና ሰውነትን በማድከም ሀጢያትን መቀነስ ይቻላል የሚል እምነት አልከተልም! ይህ ምግብ በፆም ወቅት ይበላል! ይህ ምግብ በፆም ወቅት አይበላም በሚለው አላምንም!! የሚያምኑት መብታቸው ነው:: በሰዎች መብት መግባት አትችልም:: አንዱ የመሰልጠን እና የዲሞክራሲ መገለጫ የሰዎችን ሀሳብ አንተ ባታምንበትም ስለማይጎዳህ መቀበል ነው:: እኔ ምግብ ከመብላት በመታቀብ ሳይሆን አንደበትን በመቆጠብ አምናለሁ ወይም ሀጢያት ሊኖር የሚችለው በአንደበታችን ወደ ውጪ በምናወጣው እንጂ ወደ ውስጥ በምናስገባው ነገር ሀጢያት የለም በሚለው መርህ አምናለሁ! ያው ይህ ርዕስ ሌላ ውስጥ ስለሚያስገባን ወደ ምግቡ ወሬያችን እንመለስ"

"እሺ ከመሠረታዊ ሀሳብ እንነሳ?"

"ይቻላል! ከመሠረታዊ ነገር ለመጀመር የምንበላውን ምግብ በሶስት ዋናዋና ዘርፎች መመደብ እንችላለን:: ገንቢ ምግቦች፣ ለሰውነት ኃይል ሰጪ ምግቦች እና በሽታ የሚከላከሉልን ምግቦች በማለት ማስቀመጥ ይቻላል:: በዚያው ልክ መንታ አገልግሎት የሚሰጡ ምግቦችም አሉ:: ለምሳሌ ሰውነትን የሚገነቡ እና ኃይል የሚሰጡ ምግቦች አሉ:: አኩሪ አተር፣ አቾሎኒ፣ ዓሣ፣ ቅቤ፣ ወተት፣ ማር... የመሰሉት መንታ ጥቅም አላቸው:: እየህ አንድ ሰው ሙሉ ጤነኛ ለመሆን በቀን ውስጥ ከሶስቱ የምግብ አይነቶች የተወሰነ የተወሰነ ምግቦች መመገብ ይኖርበታል:: በቀን ውስጥ ገንቢ ምግብ ብቻ አልያም ኃይል ሰጪ ምግብ



Scanned by CamScanner

ብቻ ወይም በሽታ ተከላካይ ምግብ ብቻ ብትበላ ሰውነትህ ላይ ከፍተኛ ጫና ታሳድርበታለህ፡ ለጤናም አደጋ ነው።

"እንዴት ማወቅ ይቻላል?"

" አሪፍ ጥያቄ! የበርካታ ሀገራት ትልቁ ችግራቸው የትኛው ምግብ የትኛውን ጥቅም ይሰጣል? የሚለውን አለማወቅ ነው፤ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ታዳጊ ሀገራት አብዛኛው ዜጋ ስለሚበላው ምግብ በቂ እወቀት የለውም:: በግምት ነው የሚበላው:: በግምት ይኖራል:: በግምት ሕይወትን ይገፋል:: አንዳንድ የሰለጠኑ ሰዎች የሳምንት የአመጋገብ ቻርት አላቸው:: ትልቁ ማወቅ ያለብን ቁርስ፣ ምሳ እና እራት ላይ ቢያንስ የተለያዩ ምግብ መብላት እንዳለብን ማወቅ ግዴታ ነው!! ስለ ምግብ ማወቅማ አንዱ ግዴታችን መሆን አለበት! እንዴ በዚህ አጋጣሚ አንድ ኢትዮጵያዊ ወንደላጤ ጓደኛዬ ቤት ያየሁትን ልንገርህ? ቤቱ ስገባ ግርግዳው ላይ በትልቁ ጥያቄ ምልከት እና ዝርዝር የምግብ አይነቶች ተመለከትኩ::



Scanned by CamScanner

# ?

## መቼ እመገባችሁ ይሆን ...?

| ኃይል ሰጪ ምግቦች | ገንቢ ምግቦች | ከበሽታ ተከላካይ ምግቦች |
|---|---|---|
| ቴምር | ባቄላ | ፎሶሊያ |
| ኑግ | ሽንብራ | ቃሪያ |
| ተልባ | በቆሎ | ቲማቲም |
| ሰሊጥ | ማሽላ | ብርቱካን |
| በሎቄ | ጤፍ | መንደሪና |
| ሱፍ | ገብስ | ዘይቱን |
| አናናስ | አቮካዶ | ፓፓዬ |
| አደንጓሬ | ዱባ | ካሮት |
| ስኳር ድንች | ድንች | ማንጎ |
| ሐባብ | በሬ | ቆስጣ |
| ሽንኮራ አገዳ | ዶሮ | ሰላጣ |
| ጮማ ሥጋ | እንቁላል | ጥቅል ጎመን |
| . | . | . |
| ወዘተ | ወዘተ | ወዘተ |



Scanned by CamScanner

"ምንድን ነው የለጠፍከው?" ስለው፡፡

"አየህ ባልበላም ጠንከሬ ሥርቼ እነዚህን ምግቦች መቼ መብላት እንዳለብኝ እንዳስታውስበት ነው ነበር ያለኝ፡፡ አየህ አንዳንዱ ምን መብላት እንዳለበት ያውቃል፤ የሚበላበት ገንዘብ ግን ከየት ያምጣ? የድህነት አንዱ ግዙፍ ችግር መብላት ፈልገህ እንኳ መግዛት ስለማትችል መብላት ያለብህን ሳይሆን ያገኘኸውን ብቻ ትበላለህ!! ደሀ ስትሆን ምርጫ የለህም! አንድ ጤነኛ ወንድ በ24 ሰዓታት ውስጥ ከ1600-2000 ካሎሪ ሰውነቱ ማግኘት አለበት፡፡ አንዲት ጤነኛ ሴት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ1500-1900 ካሎሪ ማግኘት አለባት፤ ይህ እርጉዝ ሴትን አይመለከትም"

"ላቋርጥህና በዚህ አጋጣሚ ከሴት እና ወንድ ጅብ ማን ነው?"

(ፈገግ ብሎ ተመለከተኝ፡፡ ጅብ የሚለውን ገለፃ አልወደደልኝም መሰለኝ)

"እርግጥ ጅብ ሳይሆን አሣማ ነው የሚባለው! ከጅብ ይልቅ አሳማ ብዙ ይመገባል፤ በኢንግሊዝ እና ጣሊያን በተደረገ ጥናት መሠረት ሴቶች ከወንድ የበለጠ ተመጋቢ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያን አላውቅም! በእርግጥ በማንኛውም አገር ያለች ሴት ፍቅር ካልያዛት ወይም በሆነ ነገር ሙድ አልባ ካልሆነች በስተቀር ከወንዱ የበለጠች ተመጋቢ ናት፤ ነገር ግን በእኛ የምግብ ባለሙያዎች አንድ ሰው ተመጋቢ ነው የሚባለው ያገኘውን ሁሉ እሸር በእሸር የሆነ ምግብ ስለበላ፤ ሆዱን ስለሞላ ሳይሆን ከሶስቱ የምግብ አይነቶች በቂ ምግብ ሲወስድ ብቻ ነው፡፡ እኛ ሀገር በጣም የተሳሳተ ግንዛቤ አለ! ምግብ መብላት ማለት እስከ ቁንጣን ድረስ መብላት ነው ብለው የሚያስቡ በርካታ ምስኪኖች አሉ፤ ሳይጠግቡ ማቆም ጅልነት ይመስላቸዋል!! ከዚው ጋር በተያያዘ ምን በጣም እንደሚያበሳጨኝ ታውቃለህ?"

"ንገረኝ"

"ለምሳሌ ሁለት ሌትር የሚይዝ ጀሪካን ሁለት ሌትር ብቻ ነው ሊይዝ የሚችለው! ሶስት ያዝ ብትለው በጭራሽ አይችልም! በዚህ መልኩ ነው ሆዳችንን ማሰብ ያለብን! አንዳንዱ ንከ ይመስላል በተለይ ሠርግ፣ ልደት፣ ግብዣ... መሰል ላይ ሲጠራ እጅግ ከአቅም በላይ የሆነ ምግብ በማንሳት በልቶ በቁንጣን ይመታል! ለማወራረጃ ብሎ አንበ ውሃ ይጠጣል! በአቅም መብላት የሚባል ሥነ ምግባር እያንዳንዱ ጋር የለም! ለምግብ ክብር የለንም! ቢያንስ ትንሽ በትንሽ እያነሳን ካልጠገብን ማንሳት እንጂ የማንጨርሰውን ምግብ አንስቶ ማጨማለቅ በጣም ያሳዝናል!! ምግብ እኮ ጠላት አይደለም!! ስኬታማ አመጋገብ የሚባለው በመጠኑ መብላት



Scanned by CamScanner

ነው፤ ከዚያ ደግሞ ምግቡ በሚገባ እንዲፈጭ በቂ ውሃ ከምግብ በኋላ መጠጣት ወሳኝ ነገር ነው!! ለሰውነታችን ከምንም በላይ ውሃ መጠጣትን የመሰለ ትልቅ ስጦታ የለም!! ሻይ መጠጣት፣ ለስላሳ መጠጣት፣ መጠጥ መጠጣት፤ ውሃ ሊሰጠን የሚችለውን ጥቅም በጭራሽ ሊተካው አይችልም! ይህንን ብዙዎች አይገነዘቡትም! ከምግብ በኋላ በቂ ውሃ መጠጣት ወሳኝ ነገር መሆኑን በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል"

"ስለ ካሎሪ እናውራ?"

"በሶስት መልኩ ማየት እንችላለን! ከፍተኛ ካሎሪ ያላቸው ምግቦች፣ መካከለኛ ካሎሪ ያላቸው ምግቦች፣ ዝቅተኛ ካሎሪ ያላቸው ምግቦች ፣ በማለት በሶስት ዘርፍ ይመደባሉ:: ቅድም እንዳልኩት አንድ ወንድ በቀን ውስጥ ከ1600-2000 ካሎሪ ሴቶች ከ 1500-1900 የካሎሪ መጠን በ24 ሰዓታት ውስጥ ያስፈልጋቸዋል ብለናል፤ ሁሉንም መዘርዘር ባልችልም ከፍተኛ ካሎሪ ያላቸውን ምግቦች ልነግርህ እችላለሁ"

"አንተ ግን የእያንዳንዱን የምግብ ካሎሪ መጠን ታውቃለህ ማለት ነዋ?"

"ያ! የ400 የምግብ አይነቶችን የካሎሪ መጠን በሚገባ አውቃለሁ! ስራዬ ስለሆነ ስለምሰራው ነገር በቂ እውቀት መያዝ እኮ ግዴታዬ ነው:: ባለሙያ ስትባል እኮ ባለሙያ ስለተባልክበት ነገር በቂ እውቀት አለህ ማለት ነው! አይደለም? እኔ በዚህ መልኩ ነው የምገነዘበው"

"እስማማለሁ! ስለዚህ እስቲ ከሁሉም በተሻለ ትልቅ የካሎሪ መጠን ስላላቸው ምግቦች ብቻ ንገረኝ..."

"ለምሳሌ ከእነዚህ ምግቦች አንዳቸውን ከ250 እስከ 320 ግራም መጠን ከብደት ያላቸውን ብትመገብ የሚከተለውን የካሎሪ መጠን አላቸው:: እኛ ሀገር ተወዳጅ የሆነው ጥሬ ሥጋ 850 ካሎሪ አለው:: የገብስ እንጀራ 780 ካሎሪ አለው:: በጎረቤታችን ኬኒያ ተወዳጅ ምግብ የሆነው የበቆሎ እንጀራ 840 ካሎሪ አለው:: ፓስታ 880 ካሎሪ፤መኮረኒ 510 ካሎሪ፤ የዳጉሣ እንጀራ 780 ካሎሪ፤ የስንዴ እንጀራ 776 ካሎሪ .... ጨጨብሳ 700 ብሎሪ... የፍየል ስጋ 920 ካሎሪ፤ የፈረስ ሥጋ 720 ካሎሪ... የቻይናው ሩዝ 870 ካሎሪ... እነዚህ ከፍተኛ ካሎሪ ያላቸው ተብሎ የሚጠቀሱ ናቸው:: ይህ ነገር ይበልጥ ግልፅ እንዲሆንልህ በምሳሌ ላስረዳህ እኛ ምግብ ስናዘጋጅ የምንመገነው በግራም ነው:: በኛ ባህል የግራም መለኪያ በያንዳንዱ ቤት ስለማይኖር በጭልፋ እናውራ:: ለምሳሌ አንድ መጠነኛ ጭልፋ ከላይ



Scanned by CamScanner

ያሉትን የጠቀስኩልህን የካሎሪ መጠን ያስገኛሉ እንደማለት ነው"

"ስለዚህ የምናወጣውን የሀይል መጠን እና የምንመገበውን የምግብ መጠን ማመጣጠን የሚቻለው እንዴት ነው?"

"ማወቅ ነዋ! የዘመናዊነት አንዱ መገለጫ ስለምግብ ከማወቅ ይጀምራል፡፡ ምግብ መብላት እኮ ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው፡፡ ለምሳሌ በቀን ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የካሎሪ መጠን እንድናወጣ የሚያደርጉት ድርጊቶች (እንቅስቃሴዎች) መሀከል ሩጫ፣ ድብድብ ፣ ቁምብሎ ማሰብ፣ በንዴት መብሰልሰል፣ ከባድ ዕቃ መሸከም ፣ የጉልበት ሥራ መስራት ፣ ሳይክል መንዳት፣ አስተማሪነት ፣ የመድረክ ንግግር ማድረግ፣ ሙዚቃ መጫወት፣ ሰባኪዎች ... ይጠቀሳሉ እነዚህ ከፍተኛ Energy እንድታቃጥል የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ለበርካታ ጊዜያት በእንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ስፔን፣ አሜሪካ፣ የሚገኙ ባለሙያዎች በተደረጉ አሳማኝ ጥናቶች ለምሳሌ በ30 ደቂቃ ውስጥ አንድ ሰው ምን ያህል ካሎሪ ሊያቃጥል ይችላል? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ሁሉንም ባይሆን በጥቂቱ ልንገርህ?"

"እሺ"

"አንድ ሰው ለ30 ደቂቃ የእግር ጉዞ ቢያደርግ 60 ካሎሪ ያቃጥላል፣ ተቀምጠህ ለ30 ደቂቃ ብታነብ 65 ካሎሪ ታቃጥላለህ! በዚህ መሠረት አንድ ጎበዝ ተማሪ ሳይሰለቸው ለሁለት ሰዓት ተቀምጦ ቢያጠና 65x4 =260 ካሎሪ ሀይል ይጨርሳል ወይም ያቃጥላል... ለ30 **ደቂቃ መኪና ብትነዳ** 80 ካሎሪ ታቃጥላለህ፡፡ ለምሳሌ ታክሲ አሽከርካሪዎች በቀን ውስጥ **በትንሹ ለ6ሰዓታት መኪና** ያሽከረከራሉ... ስለዚህ ምን ያህል ካሎሪ ያወጣሉ ማለት ነው?

ለ30 ደቂቃ — 80 ካሎሪ

ለ1 ሰዓት — 160 ካሎሪ

ለ6 ሰዓት — ?

ስለዚህ 6x160 =960 ካሎሪ ያወጣሉ!

|

እግር ኳስ ተጫዋቾች ለ30 ደቂቃ 180 ካሎሪ ያወጣሉ በዚህ ስሌት ስናሰላው አንድ እግርኳስ ተጫዋች በዘጠና ደቂቃ በትንሹ 720 ካሎሪ ያቃጥላል! ታዲያ በጨዋታው ውስጥ ትግል፣ ፍትግያ፣ ካለበት ተጨማሪ ካሎሪ ያቃጥላል፡፡ ለምሳሌ ለአንድ ሰዓት ዋና ብትዋኝ 400 ካሎሪ ታቃጥላለህ! ለአንድ ሰዓት ተኩል ዋና ብትዋኝ 600 ካሎሪ ታወጣለህ.. አንድ ቦክሰኛ በ20



Scanned by CamScanner

ደቂቃ ውስጥ 1400 ካሎሪ ያቃጥላል! እጅግ በጣም ብዙ ነው:: ኮብልስቶን ለአንድ ሰዓት ብትፈልጥ 560 ካሎሪ ታቃጥላለህ! አስበው ድንጋይ ሙሉ ቀን የሚፈልጡ ሰዎች ምን ያህል ካሎሪ እንደሚያቃጥሉ!? ለሁለት ሠዓት ዳገት ብትወጣ 1400 ካሎሪ ታወጣለህ... አንድ አስተማሪ 30 ደቂቃ ሲያስረዳ 140 ካሎሪ ያወጣል ፤ እንግዲህ አንድ አስተማሪ በቀን ውስጥ ለ5 ክፍለ ጊዜ ያህል ቢያስተምር እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ያለው የጊዜ ቆይታ ቢባ

ለ30 ደቂቃ — 140 ካሎሪ

5 x40 ደቂቃ = 200 ደቂቃ

ለ30—140

ለ200 — ?

$$\frac{140x200}{30} = 933 \text{ ካሎሪ}$$

ያቃጥላል:: አየህ አስተማሪነት ምን ያህል Energy የሚያስጨርስ ስራ እንደሆነ?"

"ይገርማል! ስለ ሽሮ እና እንጀራ ንገረኝ! አንዳንዶች ሽሮ እና እንጀራ መብላት ፎርፎር ያስይዛል! የኢትዮጵያ ህዝብ ምቀኛ የሆነው ሽሮ እና እንጀራ ውስጥ የምቀኝነት ቅመም ስላለ ነው ይላሉ! ሀሜተኞች!!"

ሣቀ::

"ከንቱ አባባል ነው! ያልሰለጠነ ህብረተሰብ አንዱ መገለጫው ሀሜት እና ሀሜተኛ መሆን ነው:: ያለ መረጃ ዝም ብሎ መተርተር ነው... ለማንኛውም እውነታውን እስቲ በምሳሌ እንመለከት:: 260 ግራም ወይም አንድ አነስተኛ ጭልፋ ሽሮ ብትበላ 267 መጠን ያለው ካሎሪ ታገኛለህ:: 450 ግራም ወይም አንድ ትልቅ ጭልፋ እንበለው አንድ እንጀራ ብትበላ ከጤፍ ውስጥ 714 ካሎሪ ታገኛለህ፤ በተለይ ቀይ ጤፍ ሀይለኛ ካሎሪ አለው፤ ስለዚህ አባባሉ ተራ ነው! እውነታው ይህ ነው! ብታምንም ባታምንም በ2022 የኢትዮጵያ አቆጣጠር የዓለም አንዱ ዝነኛ ምግብ የሚሆነው እንጀራ ነው"

"ሂሳብ እንዴት ነው የሚሠራው?"

"ማለት?"

"ለምሳሌ በአንድ ቀን ውስጥ ከ1600-2000 ካሎሪ የሚያስፈልገኝ ከሆነ እንዴት



Scanned by CamScanner

ማመጣጠን እችላለሁ?? ለምሳሌ ጠዋት ላይ ቁርሴን ዳቦ በሙዝ ብበላ፣ ምሳ ሰዓት ላይ ዱለት በእርግጥ ዱለት ቁርስ ላይ በብዛት የሚበላ ቢሆንም ብበላ... እራት ላይ እንደው ቀንቶኝ ክትፎ ብበላ... ተጨማሪ ወተት ብጠጣ... ባጠቃላይ ስንት ካሎሪ አለኝ? በቂስ ነው?"

"ማወቅ ይቻላል"

"እሺ እንወቀው!"

| | |
|---|---|
| "አነስተኛ ዳቦ (አምባሻ) | = 470 ካሎሪ አለው |
| አንድ ሙዝ | = 80 ካሎሪ አለው |
| ወተት | = 160 ካሎሪ አለው |
| አንድ ጭልፋ ዱለት | = 260 ካሎሪ አለው |
| መጠነኛ ክትፎ | = 235 ካሎሪ አለው |
| አጠቃላይ | = 1205 ካሎሪ |

አየህ በአንድ ቀን ውስጥ ጤነኛ ወንድ ከ1600-2000 ካሎሪ ያስፈልገዋል! አንተ ያገኘኸው 1205 ካሎሪ ብቻ ነው:: ይህ ማለት

ሀ.
$$\begin{array}{r} 1600 \\ -1205 \\ \hline 395 \end{array}$$

ለ.
$$\begin{array}{r} 2000 \\ -1205 \\ \hline 795 \end{array}$$

ስለዚህ ከ395-795 ካሎሪ ዕዳ አለብህ!! አደጋ ውስጥ ነህ ማለት ነው!! ቁርስ ላይ ሙዝ በዳቦ ከምትበላ እኮ ከተቻለ አንድ ብርጭቆ በሶ ብትጠጣ ለጨጓራህም ለአንተም አሪፍ ነው:: አንድ ብርጭቆ በሶ እኮ 560 ካሎሪ አለው!!"

"በእግዜር ቸርነት ነው የምንኖረው በለኛ? ስለምግብ ከተነሳ ስለ ወሲብ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል:: አንድ ጥናት ሳነብ አሪፍ አሪፍ ምግብ መብላት የወሲብ ችሎታን ይጨምራል ይላል፣ በዚያው ልክ ደካማ የምግብ አበላል ስርዓት ያለው የወሲብ ችሎታውም ደካማ ነው ይላል"



Scanned by CamScanner

"100% ሀቅ ነው"

"እሺ ስለ ምስር መብላት ጥያቄ ላንሳ ምስር ብልት ይቀስር ይላሉ እውነት የወንድ ብልት በምስር ይቆማል?"

ሣቀ... ረጅም ሣቅ!!

"በምሳሌ እንየዋ! ለምሳሌ መጠነኛ የሆነ የምስር ክክ ወጥ ብትበላ፣ የድፍን ምስር ወጥ ብትበላ፣ ጎመን ወጥ፣ እንቁላል ጥብስ፣ የቡላ ገንፎ፣ የቡላ ፍርፍር፣ የቡላ አጥሚት ብትወስድ ያላቸው ካሎሪ የሁሉም ከ300 በታች ናቸው:: በተቃራኒው ከ300 እስከ 400 ካሎሪ መጠን ከምታገኝባቸው መሀከል ድንች ወጥ፣ ዶሮወጥ፣ ዓሣ ጥብስ፣ የአተር ክክ አልጫ፣ የገብስ ገንፎ፣ አብሽ፣ ይጠቀሳሉ... ምስር ብልት ይቀስር የሚባለው የተሳሳተ መረጃ ነው፤ ምክንያቱም ምስር ብትበላ ልታገኝ የምትችለው የካሎሪ መጠን 292 ካሎሪ ብቻ ነው:: አንድ ሰው ወሲብ ቢያደርግ እና ቢረጭ የሚያቃጥለው የEnergy መጠን 500 ካሎሪ ነው!! አንድ ጊዜ ስትረጭ 250 ካሎሪ ታወጣለህ ስለዚህ አንዳንድ ሞኞች እንደ ጅብዱ በአንድ ቀን ውስጥ አራት ዙር እሄዳለሁ! ስድስት ዙር እሄዳለሁ ሲሉ ይገርመኛል፤ በእርግጥ ለጤነኛ ሰው በአንድ ቀን ውስጥ ቢበዛ ሶስት ዙር ችግር የለውም!! በየቀኑ ወሲብ እንድታደርግ ግን ማንም አይመክርህም!! ፍላጎትም አይኖርህም! እስበው እንግዲህ አራት ዙር ለማድረግ በእርግጠኝነት 1000 ሺ ካሎሪ ታቃጥላለህ:: በጣም ብዙ ካሎሪ ነው:: ለመሆኑ አንድ ሺ የሚጠጋ ካሎሪ ወሲብ ከማድረግህ በፊት በልተሃል? ይህን ራስን መጠየቅ ነው!! በዚያ ላይ Hard sex የሚባለውን የምታደርግ ከሆነ ለአንድ ዙር ብቻ 460 ካሎሪ ታቃጥላለህ! በዚህ ስሌት ከፍቅረኛህ ጋር እልህ ይዞህ በወሲብ አርከቴያት የወሲብ ጀግና እባላለሁ ብለህ ሶስት ዙር Hard sex ብታደርግ እስበው 460x3 = 1380 ካሎሪ ታጨሳለህ... በነጋታው ወገቤ ተሰበረ... ከአልጋ ላይ መነሳት አቃተኝ ትላለህ! ሰውነቴ ሸባ ሆነ ትላለህ! ለወሲብ የምታወጣውን ሀይል ለመልካም ነገር ብትጠቀምበት የተሻለ ህይወት እንድትመሠርት ያደርግሃል!! ሌላ ርዕስ ውስጥ አልግባና ምግብ መብላት ራሱን የቻለ ጥበብ አለው! ክብር ጭምር ያስፈልገዋል! በተለይ ለህፃናትም ሆነ ለታናናሾቻችን በሚገባ ልናሳውቃቸው የሚገባው ነገር ስለምግብ ክብር እና ምግብ ሲበላ ያለውን ሥነ ሥርዓት ጭምር ነው፤ በተለይ በኢትዮጵያ ምግብ መስራት ሴቶች ላይ ብቻ የተጣለው ባህል ሙሉ ለሙሉ መሻሻል ያለበት ኋላቀር ባህል ነው!! ወንዶችም ሊሠሩ ይገባል!!"



Scanned by CamScanner

ከሲራክ ሜሲ ጋር ብዙ ነገር ነበር የተጫዋወትነው! ይቺን ያክል ካቃመስኩኝ ይበቃል! ለማንኛውም ስለምትበሉት ምግብ እንድትዋጁ እየተመኘሁ በተለይ የታሸጉ ምግቦችን ስትገዙ ቀናቸው ያላለፈባቸው መሆናቸውን በሚገባ እንድታጣሩ እየመከርኩ በማህተመ ጋንዲ አባባል ይቺን ፅሁፍ ልዝጋት:: እንደፈለጋችሁት ተርጉሙት::

"There are people in the world so hungry, that God can not appear to them except in the form of bread."



Scanned by CamScanner

# እኛ እና ዲሞክራሲ

እነሆ ሐምሌ 18፣2007 ዓ.ም አመሻሽ ላይ የተሰፋይቱን የኢትዮጵያን መሬት የረገጠው የአሜሪካው ጥቁር ፕሬዝዳንት ማከሰኞ ላይ ሹልከ ብሎ ሲወጣ ስለ አሜሪካው ፕሬዝዳንት የኢትዮጵያ ቆይታ ለማውራት በቁጥር አንድ የደወልኩት ለአንድ ወጣት ነበር፤ በሀይሉ ግዛቸው አረጋ! ነቃ ያለ አንባቢ ወጣት!!

ያኔ ገና በገናናዋ የአሜሪካ ምድር፣ በአወዛጋቢዋ የአሜሪካ ምድር! የስልጣኔ ማማ ናት በምትባለው የአሜሪካ ምድር 'Yes we can!' የሚል ሀሳብ ይዞ የተነሳው ፕሬዝዳንቱ ከአሜሪካ ምድር አልፎ በመላው አለም ከሊቅ እስከ ደቂቅ እጅግ በርካታ አድናቂዎች በሚያደርገው ንግግር ለመማረከ ቻለ፤ በተለይ ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ደግሞ በፕሬዝዳንቱ ፍቅር ያበደ! ስከር ያለ! የፕሬዝዳንቱን ስም በከንዱ ላይ ለመነቀስ ሁሉ የደረሰ፣ ስለ ፕሬዝዳንቱ ሁለት መፅሐፍት ታሪከ... ብቻ... ስለ ፕሬዝዳንቱ አውርቶ የማይጠግብ ወጣት በሀይሉ ግዛቸው አረጋ ነበር...

የፕሬዝዳንቱን ሁለት መፅሐፍት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳነብ የሰጠኝ በሀይሉ ነበር... በእርግጥ አንደኛውን ብቻ ለማንበብ ብችልም... ብቻ በሀይሉ የፕሬዝዳንቱ ቀንደኛ አፍቃሪ ነበርና! ፕሬዝዳንቱ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ሲባል ደወልኩለት

"ታዲያስ?"

"ፈጣሪ ይመስገን"

"እንኳን ደስ አለህ"

"ስለምኑ?"

"ትንቢትህ ሰመረልህ"

"የምን ትንቢት ነበር?"

"እንዴ ሰውየው መጣልህ እኮ"

"እ..." አለና ከት ብሎ ሣቀ፡፡ ከዚያ

"አይ አንተ አሁን ጅማ ለስራ ጉዳይ ሄጃያለሁ! ሐሙስ ሽገር እመጣለሁ! በስፋት እናወራለን"

በዚው ተለያየን፡፡ ቀይ፣ ረጅም፣ ሎሜ ፀጉር ካለው! በፕሬዝዳንቱ ፍቅር እና ከሀገር



Scanned by CamScanner

ውስጥ በዶክተር ዳኛቸው አሰፋ ፍቅር ከተለከፈው ወጣት በሀይሉ ጋር በጣም በሚወደው ትንሿ ስታዲየውም ከጅማ ሲመለስ ቢንጎ መጫወቻ ቤት ተገናኘን... ካወራነው በመጠኑ እነሆ!

"ጅማ እንዴት ናት?"

"አለች"

"ትኑር!!"

"በነገራችን ላይ አንተ ካየሀት በኋላ በጣም ሳይሆን በትንሹ ተለውጣለች"

"ከለውጥ በቀር ምን ቋሚ ነገር ምድር ላይ አለ ብለህ ነው?"

"ሀቅ ነው"

"ለማንኛውም ፐሬዝዳንቱ መጣ፤ ሄደ! ለፐሬዝዳንቱ ካለህ ፍቅር የተነሳ ምን ተሰማህ?"

"እውነቱን ልንገርህ?"

"እናሳ!!"

"50 በ 50 ነኝ"

"ይብራራልኝ"

"ኦባማን አሁንም እወደዋለሁ! ልክ የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን ህጋዊ ሲያደርግ ግን በአንድ ጊዜ ጠላሁት!! ይህን ቆሻሻ የሴይጣን ተግባር በቅዲስቲቷ አገር ኢትዮጵያ ያነሳል ብዬ ገምቼ እና ፈርቼ ነበር፤ ያን ባለማድረጉ አድናቆቴ ትልቅ ነው:: የኢንግሊዝ ቀኝ ግዛት በነበረችው በኬንያ ግብረሰዶም/ ሊዚቢያን ቢገኝ የ14 ዓመት እስር እንደሚቀጣ በህጋቸው አርቅቀዋል!! በኢትዮጵያም ይህ ህግ ይበልጥ ተሻሽሎ መፅደቅ አለበት የሚል አቋም አለኝ!!"

"ስለዚህ በኦባማ መምጣት ደስተኛም ሀዘንተኛም አይደለህም ወይም ለውሳኔ ተቸግረሃል?"

"ልክ ነህ!"

"መንግስትስ?"

"ኢህአዴግ ማለትህ ነው?"

"እህ"

"ኢህአዴግማማ በቅርቡ የመጡትን ትልቅ የቻይና መሪን ጨምሮ እስከዛሬ የኢትዮጵያ



Scanned by CamScanner

መሬት ለረገጡት የተለያዩ ሀገር መሪዎችም ሆነ ባለስልጣናት ያላደረገውን ለኦባማ ጭራውን ነው የቆላው! አሸርግዷል! ሙዚቃ ተዘጋጀለት! አሰበው ለአድዋ ድል የሚተኮሰው መድፍ እኮ ነው የተተኮሰለት! ይህ ለእኔ ህዝብን መናቅ ጭምር ነው፤ በእርግጥ የአሜሪካ መንግስት ኢህአዴግን ስልጣን ላይ እንዲወጣ ያኔ ጫካ እያሉ ተመቻምቸው ነበር! ወሮታ መከፈሉ ነው! ዋነኛ ምክንያት የነበረው ግን የኦባማ መምጣት የኢትዮጵያን እድገት ያሣያል፤ በተለይ የኢህአዴግን ስኬት ያሳያል ብለው በማሰብ ደፋቀና የተባለለት ነው! ያሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ! ሞኝ ሲስቁለት ብልህ የሆነ ይመስለዋል የሚባለውን ካለማወቅ ነው"

"እሺ በኢህአዴግ መነፅር ሳይሆን በአሜሪካ መነፅር ጉዳዩን መመልከት እንችላለን"

"ማለት?"

"ማለትማ ባጭሩ አባማ ለምን ኢትዮጵያ መምጣት አስፈለገው?"

"አባማ እኮ ከአፍሪካ ኢትዮጵያ ብቻ አልመጣም! ሌሎች አገራት ሄዷል! ኢትዮጵያ አምስተኛ አገር መሆኗ ነው! ጨዋታን ጨዋታ ያነሳዋልና በዚህ አጋጣሚ ስለ አጭሩ ተንከለኛው ንጉስ ኃይለስላሴ እናንሳ?"

"እሺ"

"አፄ ሀይለስላሴ በ1938 ዓ.ም አሜሪካ ሲገቡ ስንት ሰው ንጉሱን ለማየት እንደተገኘ ታውቃለህ? ስንት ሰው ንጉሱ የአሜሪካን ምድር ከመርገጣቸው በፊት በወቅቱ የአለም ዝነኛ፣ አነጋጋሪ እና አወዛጋቢ! ከንጉስም አልፎ መመለክ ደረጃ የደረሱትን የኢትዮጵያ ንጉስ ለማየት በቦታው ለመገኘት ማመልከቻ እንዳስገባ ታውቃለህ?"

"ፊልሙን አይቻለው! በጣም ነበር የገረመኝ 200,000 ሺ አሜሪካዊያን!! እጅግ በጣም ግዙፍ ቁጥር ነው!! ለማንኛውም ወደ ዋናው ጥያቄ እንመለስ ባንተ እይታ አባማ ለምን ኢትዮጵያ መጣ?"

"በእኔ እይታ ሶስት ነገሮችን ማንሳት ይቻላል"

"ምን ምን?"

"አንደኛ ፖለቲካ (አሜሪካ እና ቻይና) ሁለተኛ እናቱን ለማየት፣ ሶስተኛ በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ መሰብሰቢያ የአፍሪካ መሪዎችን ጥንብ እርኩሳቸውን ለማውጣት ፤ ለመዘርጠጥ... ናቸው:: ከየትኛው ልጀምርልህ?"

"ከፖለቲካው እንጀምር?"



Scanned by CamScanner

[illegible] አሜሪካ ምንግዜም የምታስቀድመው አሜሪካን አሜሪካ ከማንም ጋር ወዳጅነት የምትመሠርተው የምታገኘው ጥቅም ካላት ሂሳባዊ ቀመር አስልታ ብቻ ነው:: የአሜሪካ ህግ አከክልኝ ልከክልህ በሚል ቁማር ላይ የተመሠረተ ነው!! አሜሪካ ምንግዜም ለጥቅሟ ብቻ ዘብ የምትቆም መሰሪ የሆነች ሀገር ነች! ይህ የአሜሪካዊያን ትክክለኛው ገፅታቸው ነው:: ምንም እንኳ ለሟች መለስ ዜናዊ ሊድናቆት ባይኖረኝም በኢትዮጵያዊ ጨዋ ባህላችን ነብሱን ፈጣሪ ይማረውና ትልቁ የሠራው ስራ ለቻይናዊያን አፍሪካ ምርጫቸው እንደሆነች ማሳየት ነበር፤ ከዚያ የአሜሪካ ትልቅ ባላንጣ የሆነችው ቻይና ከአፍሪካ ጋር በፍቅር ወደቀች! የቻይና ኩባንያዎች አፍሪካን ተቆጣጠሯት:: ይህ ጉዳይ ለአሜሪካ የእግር እሳት ሆነባት፤ በተለይ ከቻይና ጋር በፍቅር የእኛዋ ኢትዮጵያ ወድቃለች!! ይህ ለአሜሪካ አልተመቻትም፤ ስለዚህ በቻይና እና አፍሪካ መሀከል ያለውን ፍቅር ለማቀዝቀዝ ትክክለኛው ሰዓትም ሆነ ወቅት ይህ መሆኑ ሲሰማት ከች አለች! በዲፕሎማሲ ቋንቋ አሜሪካ እንደምትለው ለኢትዮጵያ አልያም ለአፍሪካ ጥቅም ሳይሆን ለራሷ ጥቅም ነው:: ይህ ዋናው ቁማር ነው:: ይህን ነጥብ ያዝልኝ እንጂ ኢህአዴግ ህዝቡን ለማሞኘት የአሜሪካው ፕሬዝዳንት መምጣት የኢትዮጵያ እድገት ማሳያ ሲሆንም ራሱ በጭራሽ አይችልም"

"ለአንተ ኢትዮጵያ እንደሚወራው አላደገችም?"

"አታስቀኝ! እርግጠኛ ነኝ እንደ ነገርከኝ የኢትዮጵያን ከተሞች ከሁለት ከተሞች በስተቀር አገርህን 85% እየዞርከ አንተ በዓይንህ አይተሃል? ለመሆኑ ኢትዮጵያ አደገች የምንለው መቼ ነው? ለመሆኑ እድገት ምንድ ነው? እድገት በምንድነው የሚለካው? መንገድ በመስራት? ቤት በመስራት? ግድብ በመስራት? አገሪቷን በእዳ በመዝፈቅ? በብድር አንደኛ በማድረግ? የአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ አስተማሪያችንን ታስታውሳቸዋለህ?"

"እንዴታ"

"ቅኔ ሲያስተምሩን ስለ መንግስቱ ለማ እንስተው ነበር መንግስቱ ለማ በአንድ ምሁራን ነን ባዮች ስብሰባ ላይ ተገኝተው እስቲ ምሁር ከሆናችሁ መርፌ ስሩ? ነበር ያሏቸው... ትዝ አለህ?"

"በጣም"

"ይቺን ቅኔስ?"

"የትኛዋን?"



Scanned by CamScanner

"እኖቲዎች ሊታውንት ከሆናችሁማ ባሉ ቀን ፍጡሩ ሳይመጣ ጨለማ"

"እ... ትዝ ይለኛል"

"ታዲያ የዚያን ወቅት ስለ አገር እድገት ተነስቶ የአማርኛ አስተማሪያችን ያሉንን መቼም አልረሳም '... ልጆች የእውነተኛ ስልጣኔ መለኪያ ግዑዝ ነገር አይደለም!! የእውነተኛ ስልጣኔ መለኪያ ዲሞክራሲ! ፍትህ! ነፃነት! እኩልነት! ሰብዓዊ መብት መከበር እና አድሎ የሌለበት ስርዓት ነው እንጂ እድገት ማለት ቤት መስራት ፣ መንገድ መስራት፣ ቅብርጥሶ አይደለም!! ነበር ያሉት ይህ ትልቅ እውነታ ነው:: ለመሆኑ ማን በሠራው መኪና ነው እየተንቀሳቀስን ያለነው? ቴሌቪዥኑ ፣ ሬዲዮኑ፣ ስልኩ... ሞባይሉ... እኛ ነን የሠራነው? ፈረንጆች ናቸው እኮ!! በዚያ ላይ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ስልጣኔ እና እድገት ካለ እኮ መመስከር ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው! እንደው ሌላውን ተወውና በቂ ንፁህ ውሃ አለን? መብራት አለ? መታከሚያ ሆስፒታል አለ? በቂ ምግብ አለን? በቂ ንፁህ ቦታዎች አሉን? የመናገር ነፃነት አለን? የመፃፍ ነፃነት አለን?... ይህን ስልህ እንደ ጨለምተኛ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ለውጥ የለም እያልኩ አይደለም!! ይህን ያክል ያዙኝ ልቀቁኝ! እሪ! የምንልበት ደረጃ ለመድረስ ገና ይቀረናል! ገና ከሰራናቸው ይልቅ ያልሠራናቸው በርካታ ነገሮች ይቀራሉ! እጅግ በርካታ የቤት ስራዎች ገና ይቀሩናል! ችግሩ ኢህአዴግ እንደ ሀኬተኛ እና ሰነፍ ሴት አውቅና እና አድናቆት ይሻል"

"ማለት?"

"እየህ ሀኬተኛ እና ሰነፍ ሴት ትንሽ ነገር ትሰራና ያዙኝ ልቀቁኝ ትላለች! የሰራቻትን ትንሽ ነገር ይዛ ማጋነን ትወዳለች! ራሷን መካብ ትወዳለች! አድናቆት እና ሞገስ ትሻለች! ጭራዋን ትቆላለች! ትንሽ ነገር ሠርታ ሺ ታወራለች! ሀኬተኛ ሴት ማስፈራራት ደስ ይላታል! ሀኬተኛ ሴት ድክመቷን የሚነግራትን መደቆስ ትወዳለች! ሀኬተኛ ሴት የማያደንቃትን በማሰር፣ በጠላትነት በመፈረጅ ትታወቃለች!! ሀኬተኛ ሴት ሁለት ኪሎ ሜትር ሮጣ 42.5 ኪሎ ሜትር እንደሮጠች ታሽካካለች... ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እውነት ይህ ነው!! ህዝቡን በዘረኝነት መከፋፈል ነው እድገት ? ተቃዋሚዎችን በአሸባሪነት ሰይሞ ፍዳቸውን ማብላት ነው እድገት? የምናነበውን ጋዜጦች ማሳጣት ነው እድገት? የተወሰኑ ሰዎች በሀብትና በስልጣን አገሪቷን እንደግል ንብረታቸው መያዝ ነው እድገት? የአከሌ ዘር ስለሆንክ እና ከእከሌ የተባለ ክልል ስለመጣህ ይህን መሬት ለቀህ እዛ ሄደህ መኖር አለብህ ብሎ ማባረር ነው እድገት?



Scanned by CamScanner

ነዋሪዎችን በአምስት ለአንድ ጠዋትና ማታ ማሰለል እና በፍርሃት ልባቸውን መሙላት ነው አድገት? ንገረኝ እስቲ ኢህአዴግ የሚመካበት እድገቱ የቱ ላይ ነው?? ለማንኛውም ለእኔ ኢትዮጵያ ገና በርካታ የቤት ስራዎች ያሉባት ትርትር የምትል! ድከድክ የምትል አገር ነች፣ በእናትህ ለራሴ ሆድ ብሶኛል ይብልጥ አታስብሰኝ"

"እሺ" አልኩት፡፡

"አይ አንተ! አንተ በቃ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንዳሾፍክ... አሁንም እንዳሾፍክ... ምን ይሻልሃል?"

ፈገግ ቢጤ አልኩኝ፤

"ሁለተኛዋ ምክንያት እናቱን ለማየት ነው ስትለኝ?"

"እውነተኛ እናቱን ነዋ!!"

" ታዲያ ከኬኒያ እኮ ነው እኛ ጋር የመጣው"

"አባክህ ሉሲን ነው የምልህ"

"እ!"

"አየህ አባማ ጥቁር ቆዳ ቢኖረውም የነጭ ጭንቅላት ያለው ግለሰብ ነው፡፡ ለአሜሪካ ዘብ የሚቆም አሜሪካዊ ነው! በዚያ ላይ ለአፍሪካ ምንም ሊያመጣ አይችልም!! አሜሪካን የሚመራት አባማ ሳይሆን CIA ነው፡፡ ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ አባማ በዘረኝነት አያምንም!! የሰው ልጅ ሁሉ መነሻ አንድ ነው!! ዓለም ላይ ያሉት ህዝቦች ሁሉ አንድ እናት አለቻቸው ያቺ እናታቸው የምትገኘው በቅድስቲቷ አገር ኢትዮጵያ ውስጥ ነው በሚል ሉሲን ለማየት መጣ፡፡ ሉሲ የሁላችንም የዓለም ህዝቦች እናት መሆኑዋንም AU ውስጥ ንግግር ሲያደርግ አስመሰከረ! ሰበከ! ሉሲ እኮ አሜሪካ ለጉብኝት ተወስዳ ነበር፤ ይህን ጉዳይ እዛ መናገር አልፈለገም! ትኩረት ለመሳብ ትክክለኛው ቦታ የኢትዮጵያ ምድር ነው!! ይህን በማድረጉ በሌላ በኩል ትልቁን ክብር የሚያገኘው ራሱ አባማ ነው፡፡ ምክንያቱም አባማ ጥቁር የመጀመሪያው የአሜሪካ መሪ ነው፡፡ አየህ ኢትዮጵያ ደግሞ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች! የጥቁር ህዝቦች ተምሳሌት እና መነቃቂያ ነች!! አስበው ይህ ጥቁር መሪ ይቺን አገር ሳያያት እንዴት አባቱ ነው ከስልጣን የሚወርደው?? ለአባማ እኮ የኢትዮጵያን መሬት መርገጥ ክብሩ ነው፡፡ ማንነቱ ላይ ሌላ ማንነት ይጨምርለታል! ኢትዮጵያ ትላንትም ኢትዮጵያ ነች! ነገም ኢትዮጵያ ነች! አባማ ለኢትዮጵያ ክብር አይጨምርላትም! ኢትዮጵያ በመምጣቱ ግን ከነፃይቷ ምድር ክብር ወስዶ ይሄዳል! ይህ



Scanned by CamScanner

ነው የአባማ ሁለተኛው ሚስጢር ለእኔ የሚገባኝ!!"

"አሪፍ እይታ ነው!! በሶስተኝነት ያስቀመጥከው የአፍሪካ መሪዎችን ከመዘርጠጥ እና ጥንብ እርኩሳቸውን ከማውጣት ጋር ነው፤ ይህ ማለት የኢትዮጵያ መሪዎችንም ይጨምራል?"

"ምን ጥያቄ አለው?"

"እሺ አስረዳኝ"

"በኢትዮጵያ ቆይታ ከአባማ ንግግሮች ዋና ዋናውን እና በቃሌ የሸመደድኩትን ልንገርህ፦

⇒ የሰው ልጆች በመሀከላቸው ምንም ዓይነት የአድልዎ ልዩነት ሳይደረግባቸው፣ በሰውነታቸው ብቻ በተፈጥሮ ያገኙትን ክብራቸውን ፣ ሞገሳቸውን አስከብረው መኖር አለባቸው!!

⇒እድገት የነፃነትና የዲሞክራሲ ውጤት ነው!! ነፃነት የሰው ልጆች ሁሉ ዓላማ ነው!!

⇒ ማንም ቢሆን ከህግ በታችና ለህግ ተገዢ መሆን አለበት! ሕገ መንግስቱን ለእሱ እንደሚበጀው እያደረገ በመተርጎም በስልጣን ላይ መቆየት አይቻለውም፤ ሊፈቀድም አይገባም!!

⇒ አንድነት እንጂ በዘር መቆራቆስ አይበጃችሁም!

⇒ Regular election is not real democracy (Formal election is not democracy)

⇒ .... እነዚህን በሚገባ ሰምተሃል?"

"ሰምቻለሁ!!"

"እኔን በተለይ ያስደሰተኝ ንግግር የቱ መሰለህ?"

"እህ"

"እህ አትበል... እሺ በል"

"እሺ"

"እኔ አባማ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ነኝ! ሁለት ጊዜ ተመርጬያለሁ!! ፕሬዝዳንት መሆን በጣም ኢንተረስቲንግ የሆነ ነገር ነው፤ ቢሆንም ለሶስተኛ ጊዜ መመረጥ ብፈልግ እንኳ አልችልም!! ህጉ አይፈቅድልኝም!! እኔ ከህግ በታች ነኝና!! እዚህ አፍሪካ ውስጥ ስልጣን የግል ንብረት ይመስላል! ስልጣን የውርስ ይመስላል ነገር ግን ማንም በህጉ ከተወሰነለት የጊዜ ገደብ



Scanned by CamScanner

በላይ በስልጣን ላይ መቆየት የለበትም! ጋና ላይ ያልኩትን በድጋሚ በአዲስ አበባ ላይም እደግመዋለሁ!! አፍሪካ የምትፈልገው ጠንካራ ድርጅት እንጂ ጠንካራ ሰው አያስፈልጋትም!! ነበር ያለው"

"እዚህ ጋር ጥያቄ ላንሳልህ?"

" ቆይ ከጥያቄህ በፊት ሌላ የማረከኝን ልንገርህ! ስለ ተቃዋሚዎች እና ሴቶች የተናገረው ራሱ በጣም ተመችቶኛል ' አሜሪካ ውስጥ ተቃዋሚዎች በነፃነት ይንቀሳቀሳሉ፣ የተለየ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣ ማንም አይነካቸውም!! ተቃዋሚዎች አስፈላጊ ናቸው:: ዜጋም ናቸው ነበር ያለው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ተቃዋሚ መሆን ጠላት፣ አሸባሪ የሚል ስያሜ ያሰጣሃል! እየህ እውነተኛ ዲሞክራሲ እና የአፍሪካ ዲሞክራሲ ልዩነት?? ስለ ሴቶችም የተናገረው ምርጥ ነው ' ሴቶች ሲማሩ፣ ሴቶች ስልጣን ላይ ሲወጡ ይበልጥ የሚጠቀሙት ሴቶች ሳይሆኑ ወንዶች እና ሀገር ናቸው:: ለምሳሌ አንዲት ሴት ተማረች ማለት ልጇ ተማረ ማለት ነው! እውቀት ተስፋፋ ማለት ነው! አገር አደገች ማለት ነው!... እኛ አገር ሴቶች የሚፈለጉት 50 ብር እየተከፈላቸው ሙቀት ለመፍጠር ብቻ ነው! ለይስሙላ እና ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ ሳይሆን ለሴት የሚገባውን ክብር መስጠት የዲሞክራሲ አብይ መገለጫ መሆን አለበት እያለ ነው፤ ይህ ለእኔ ጣፋጭ ንግግር ነው... ኢህአዴግ ሴቶችን እውነት የሚፈልጋቸው ለአገር ለውጥ ነው? ወይስ ለአብረሃም በግነት?? ይህ የእኔ ጥያቄ ነው፤ በተለይ ቅድም ለጠየከኝ ኢትዮጵያ አድጋለች ጥያቄ የእድገት ፍቺን በተመለከተ እድገት የነፃነትና የዲሞክራሲ ውጤት ነች! ነፃነት የሰው ልጅ ሁሉ ዓላማ ነው!' በሚል ነው ያስቀመጠው:: አሁን ይበልጥ ትረዳኛለህ የሚል ግምት አለኝ:: ወደ አንተ ልመለስ ጥያቄህ ምን ነበር?"

"አባማ እንዳልከው በጋና ይሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በአፅንኦት የተናገረው አፍሪካ ጠንካራ ድርጅት እንጂ ጠንካራ ሰው አያስፈልጋትም የሚል ነው"

"ትክክል"

"የተምታታ ነገር የለውም?"

"ማለት?"

"መጀመሪያ አንተ አንድ ሰው ዓለምን ይለውጣል ብለህ ታምናለህ?"

"እንዴታ! እስከዛሬም ዓለም የተለወጠችው አንድ ሰው በሚያነሳው ሀሳብ ነው!! አንድ ሰው ዓለምን ይለውጣል ብለው ከሚያምኑት 'ግለሰቦች አንደኛው እና ቀንደኛው እኔ



Scanned by CamScanner

ነኝ "ጥሩ! ታዲያ እንዴት ነው ያለ ጠንካራ ሰው ጠንካራ ድርጅት ሊፈጠር የሚችለው? የአባማ ትኩረት ድርጅት ላይ እንጂ ሰው ላይ አይደለም?"

"No! በዚያ መልኩ መታየት የለበትም!! በእርግጥ አሪፍ አሪፍ መሪዎች ወይም ወጣ ያለ ሀሳብ የሚያፈልቁ ግለሰቦች ከሌሉህ አገር ወደፊት ልትራመድ አትችልም:: አባማ ማውራት የፈለገው ድርጅት ሲል ስለ ሲስተም ነው:: ይህ ማለት ለአንድ ነገር ጠንካራ ሲስተም ካስቀመጥክ በሲስተሙ ሰዎች ይመራሉ ነው:: ሲስተም ከሌለ ሲስተሙን ሰው ይመራዋል ነው! ግን ሰው በሲስተም መመራት አለበት ነው!! ወጥ ሲስተም ስለሌላ የአፍሪካ ባለስልጣናት እንደ ፈለጉ ይሆናሉ ነው! በሙስና ይዘፈቃሉ ነው! የሰዎች አንባገነንነት እና አምልኮ ይመጣል ነው:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት የስልጣን ገደቡ ተቀምጧል!! የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ባንፃሩ አልተቀመጠም! ለምን? እንዳሻው ለመግዛት...!! አባማ ማለት የፈለገው ማንም ከህግ በታች መሆኑን እንዲያውቅ የሚያስደርግ ጠንካራ የማይሻር ሲስተም ስር ሊወድቅ ይገባል ነው!! የአፍሪካ ትልቁ ችግር ሰዎች ከህግ በላይ ናቸው!! ባለስልጣናት የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሌላ ህግ እንዳሻቸው ያወጣሉ ነው!! ይህ ነገር መቅረት አለበት ነው"

"ጥሩ! በአንተ እይታ የአባማ በአፍሪካ አንድነት መሰብሰቢያ አዳራሽ ያደረገው ንግግር ለውጥ ያመጣል?"

"እኔንጃ!! አፍሪካ ላይ ትልቅ "መርገምት" አለባት ፤ ስለሆነም በእርግጠኝነት ለመናገር ያስቸግረኛል!! የእኛን አገር ስልጣን ናፋቂ ባለስልጣናት ጨምሮ አብዛኛው የአፍሪካ መሪዎች ትልቁ ዓላማቸው የሀገር ለውጥ ሳይሆን ጣፋጭ የሆነችውን ስልጣን የሙጥኝ የማለት አባዜ በመሆኑ የ 'AU' ንግግር የሚያመጣውን አብረን የምናየው ይሆናል"

"ያኔ ገና ስልጣን ላይ የወጣ ሰሞን አንዳንዶች አባማ የአፍሪካ ቼጉቬራ ይሆናል የሚሉ ነበሩ..."

"ትክክል! እንደእኔ ያሉ አንዳንድ ምስኪኖች"

"እና?"

"እንዳልከው አባማ የአሜሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዝዳንት ሲሆን አባማ የአፍሪካ ለውጥ ይሆናል! አፍሪካ ላይ ንቅናቄ ይፈጥራል! ብለው ያስቡ ነበር:: እኔም አስቤ ነበር:: አርጀንቲናዊው ቼጉቬራ ለእናት አገር ብቻ አይሞትም ብሎ እኔ የዓለም ዜጋ ነኝ ብሎ



Scanned by CamScanner

ለኩባ ነፃነት አስገራሚ ታሪክ የፃፈ ጀግና ነበር!! ኦባማ የአፍሪካ ልጅ ሆነ ማለት የአፍሪካ ቀለም አለው እንጂ አሜሪካዊ ልብ ያለው፣ በአሜሪካዊያን ልብ የሚያስብ አሜሪካዊ ብቻ መሆኑን ተገንዝበናል፤ ስለዚህ የእኛም ሆነ የሌሎች ሰዎች ግምት የተሳሳተ ነበር ማለት ነው፣ ምናልባት ገና ቀሪ ሁለት የስልጣን ዓመቶች ስላሉት የሚሆነውን እናያለን:: እውነታው ግን የኢትዮጵያ ለውጥም ሆነ የአፍሪካ ለውጥ የሚመጣው በአሜሪካ እጅ ሳይሆን በኢትዮጵያ ልጆች ነው፤ መሆን ያለበትም ይህ ነው!! ኢትዮጵያን መለወጥ፤ ማሳደግም ፣ ትልቅ ማድረግም ያለብን እኛው ከኢትዮጵያ አብራክ የወጣን ልጆቿ መሆን አለብን!! አሜሪካ ስለ እኛ ምን አገባት? የራሳችንን ሸክም እኛው ነን ማራገፍ ያለብን!! መሆን ያለበትም ይህ ነው!! ሀቁም ይህ ነው!! ይህን የማይቀበል ካለ የሶቅራጥስን አባባል ኢጋብዛለሁ Do Not be angry with me if I tell you the truth የምትለዋን"

"በምን እንሰናበት?"

ወይ ጉድ! አንዳንዴ የነገሮች መገጣጠም በጣም ያስገርማል፤ ተቀምጠን በምናወራበት መዝናኛ ቤት ውስጥ ተወዳጅ ለመሆን የቻለ ሙዚቃ ተከፍቷል:: በሀይሉ ግዛቸው አረጋ በፈገግታ ተሞልቶ ተመለከተኝ::

"እርግጠኛ ነኝ ይህን ሙዚቃ ሰምተዋል?"

"አዎ" አልኩት::

(... ሙሽሪት ጠጪ ነገር አታምጪ... እናቷን ያያችሁ? አላየንም... አባቷን ያያችሁ? አላየንም ...)

በፍፁም ፈገግታ እየተመለከተኝ... ሙዚቃው ሲያልቅ ጠብቆ...

"እንሰናበት ነው ያልከኝ?"

"እህ"

"ጥሩ ከእኔ ንግግር በኋላ አንተ ማለት የሚጠበቅብህ `አላየንም' የሚል ቃል ብቻ መናገር ነው:: ዝግጁ ነህ?"

"ቀጥል"

"ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲን ያያችሁ?"

"አላየንም!!"

ሲናገር ቃላትን እየመረጠ፣ እየረገጠ፣ በከፍተኛ ስሜት ተሞልቶ ከሚያወራው ታታሪ የስራ ወጣት ከሆነው በሀይሉ ግዛቸው አረጋ ጋር ተሣስቀን ተለያየን...::



Scanned by CamScanner

# እኛ እና አረብ...2

"እስቲ ስለ ኩዌት ትንሽ እናውራ?"

"እሺ."

"ስለ ኩዌት መጠነኛ ታሪክ ንገሪኝ "

"በጣም ታሪክ ያላት አነስተኛ አገር ናት፣ በተለይ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዝነኛ የንግድ ወደብ ነበረች:: አርግጠኛ ነኝ ት/ቤት ስለ ፐርሺያ ጦርነት ፤ ስለ ሚሶፖቶሚያ ስልጣኔ ተምረሃል... የእነዚያ ሁሉ ታሪክ ባለቤት ኩዌት ናት... ገንዘባቸው የኩዌት ዲናር ይባላል::

... አረንጓዴ ፤ ነጭ፣ ቀይ፣ ከጎን ጥቁር ባንዲራ ትጠቀማለች... እኔ በነበርኩበት ጊዜ የህዝቡ ብዛት 4 ሚሊዮን ገደማ ነበር:: ከእነዚህ ውስጥ 60% የኩዌት ነዋሪ አረቦች ሲሆኑ ወደ 1.8% አፍሪካዊያን ነበሩ... የተቀሩት የሌሎች አገር ዜጋዎች ናቸው.. ኩዌት ነፃነቷን ያገኘችው በ1752 ዓ.ም አካባቢ ነበር.. በጣም የሚገርምህ ኩዌት ውሃ የሚባል ነገር በምድሯ የላትም! ውሃ እየገዛች ነው የምትጠቀመው ያው ከፍተኛ ነዳጅ እና ዘይት ስላላት በገንዘባቸው እየገዙ ነው የሚጠቀሙት በትንሹ ይቺን ትመስላለች..."

"አመሠግናለሁ:: ስለ ቋንቋ እናውራ?"

"ቋንቋ?"

"ምን ቋንቋ ትችያለሽ ማለቴ መግባቢያሽ ምን ነበር?"

"ቋንቋ አጅግ በጣም ወሳኝ ነገር ነው! እኔ ኢትዮጵያ እያለሁ ነበር አረብኛ እና እንግሊዝኛ ከመሄዴ በፊት ለአንድ ዓመት ያጠናሁት! በነገራችን ላይ በጣም ፈጣን ነኝ!! አሁን ያለ አንዳች ችግር ሁለቱንም እናገራለሁ በቋንቋ የተነሳ የደረሰብኝ ችግር የለም"

"ችግር ስትይ ወደ አንቺ ታሪክ እንመለሳለን ግን ባጠቃላይ አረብ አገር ስላሉት ኢትዮጵያዊያን የተወሰነ ነገር እናውራ?"

"እሺ"

"አንድ የፊሊፒንስ ሰራተኛ ለቀጠረ አራት ኢትዮጵያዊያን ሰራተኞችን እንመርቃለን ያላሉ ሲባል ሰማሁ"

"ውሸት ነው ለማለት አልችልም"



Scanned by CamScanner

"እንዴት?"

"ፊሊፒንሶች ከመምጣታቸው በፊት ብዙዎቹ እንደነገሩኝ የአንድ ዓመት ስልጠና ወስደው፣ አረብኛ ቋንቋ አጥንተው፣ ስለሚሠሩት ነገር በቂ መረጃ ይዘው ነው።"

"ኢትዮጵያውያን ሴቶችስ?"

"ይቅርታ አድርጊልኝ እኔ አንዳንዴ በአረቦቹ አልፈርድባቸውም፡፡ የእኛ አገር ሴቶች በብዛት አረብ አገር የሚሄዱት ከየክፍላ ሀገሩ የሚመጡ ናቸው፡፡ የቋንቋ እውቀት የለም! በቂ የንፅህና አጠባበቅም የለም! ሙያ የለም! ስለዘመናዊ አኗኗር እውቀት የለም! መንግስትም ሆነ ህገወጥ ደላሎች ብር ለማግኘት መቻላቸውን እንጂ በቂ ስልጠና አይሰጣቸውም፡፡ ስለዚህ አረቦች ለኢትዮጵያዊያን ንቀት ቢያሳዩ አይፈረድባቸውም፡፡ እውነቱን ለመናገር ሄድንባቸው እንጂ አልመጡብንም! በዚያ ላይ ሴቶቹ ቅናተኛ ናቸው! ወንዶቹ የኢትዮጵያ ሴቶችን በሙሉ በሸርሙጣ ሂሳብ ስለሚመለከቱ ማውጣት ይፈልጋሉ... እነዚህ ሁሉ ችግሩን ያባብሱታል"

"ሌላው የሚያነሱት ችግር ባህላችንን አበላሹት! የሀበሻ ሴቶች ሸርሙጥናን አስፋፉት! ወንዶቻችን ተበላሹ ይላሉ! ይህን ሀሳብ? እንዴት ትመለከቺዋለሽ?"

"ውሸት ነው አልልም፤ ግን ሲጀመር ራሳቸው ሸርሙጣ ናቸው፡፡ ከእነርሱ ሀገር ውጪ የመጣች ሴት ጋር ወሲብ ለማድረግ ያላቸው ጉጉት ከፍተኛ ነው! በዚያው ልክ ሁሉም የሀበሻ ሴቶች ሳይሆኑ እንደ እኔ መሰሉ ቶሎ ብዙ ገንዘብ ማግኘት የፈለጉ ሴቶች እንዳልከው እንልክሰከስ ነበር! የማይካደው ሀቅ ግን አረቦች በሙሉ ከወሲብ ጋር የተጨማለቀ ባህል ነው ያላቸው! አምስት ስድስት ሚስት የሚያገባው ማን ነውናስ?"

"ታዲያ ለምን የሌሎች አገር ሴቶች እያሉ የኢትዮጵያ ሴቶችን ብቻ መርጠው ይውጡልን በማለት እንደውሻ አካልበው አስወጡን?"

"ስለሚንቁን ነው!"

"ማለት?"

"እኛ ስለ ኢትዮጵያ ትልቅነት፣ ባለታሪክነት ፣ ገናናነት ስንነግራቸው እና እንደሌሎቹ ክብራችንን ስለማናስነካ በንዴት 'ምን አባሽ ታዲያ ትልቅ አገር ካለሽ እዛው አትሰሪም? ለምን ነባሽ አገርሽን ጥለሽ እኛ ጋር መጣሽ? ድህነትሽን ለማራገፍ አይደለም? መሰል ንግግሮችን እና ድቦችን ትሰማለህ! ያው መቼም ለምን የኢትዮጵያ ሴቶች አረብ አገራት የመጣው ይምጣ ለው ጨከነው ኢትዮጵያን ጥለው ይሄዳሉ? ለሚለው ምክንያቱን ታጠዋለህ ብዬ



Scanned by CamScanner

ለነገሩማ እኛ አገር ያለውን ችግር በሚገባ ታውቀዋለህ?"

"ልክ ነሽ! ወደ አንቺ የግል ታሪክ እንመለስ"

"ይሻላል"

"ዘረኝነት የለም?"

"ጥቁር በመሆናችን ያው ንቀት ነገር አለ፣ በነገራችን ላይ ሴቶቹ ናቸው እንጂ የአረብ ወንዶች በጣም ይወዱናል:: ከአረብ ሴቶች የተለየ አንትን ያለን ይመስላቸዋል:: ከእኛ ጋር ለመተኛት ምኞታቸው ትልቅ ነው:: ሁሉም ናቸው ማለቴ ግን አይደለም"

"እምልሽ እንዴት ሀበሻ ከአንድ አረብ ጋር ተጋብታ መኖር ትችላለች?"

"አዎ! በርካታ ትዳር የመሠረቱ፣ ልጅ ያላቸው፣ ኑሮአቸውን እኮ እዛው ያደረጉ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች አሉ"

"ስለዚህ አንቺም ከአህመድ ጋር ተጋብተን እንኖራለን የሚል ተስፋ በመያዝ የፍቅር ሁን ጀመርሽ?"

"እኔንጃ! በዚያን ሰዓት ስለ ጋብቻ አላሰብኩም:: በቃ ከእርሱ ጋር መሆን ብቻ እርካታ ይሰጠኝ ነበር ፤ ስለ ነገ ብዙ አላሰብኩም ነበር... በፍቅር እኮ ታውሬ ነበር... ምን እንደማደርግ እኮ አላውቅም ነበር"

"እሺ"

"ትልቁ ከተማ Kuwait city ወይም down town ለአስር ቀናት ተቀመጥን:: ከዚያ አንድ ሳምንት Doha ቆየን ከዚያ Mansoriya የምትባል ከተማ ሄድን! አንድ ወር ገደማ ሲሆነኝ እና ለቤተሰቦቼ ገንዘብ መላክ እንዳለብኝ ሲገባኝ አህመድን ገንዘብ ጠየኩት:: ሰጠኝ:: ከዚያ ያለ ስራ ቤት ውስጥ እርሱን ተቀምጦ መጠበቅ ስለሰለቸኝ ስራ መስራት አለብኝ ስለው ከቤት በመውጣቴ ደስተኛ አልነበረም"

"ማለት"

"እርሱ የሚፈልገው እርፌ ቤት እንድቀመጥ ፤ እርሱ የገንዘብ ችግር ስለሌለበት የቤተሰቦቼንም ሆነ የእኔን ወጪ እንደሚሸፍን በተዘዋዋሪ ነገረኝ"

"እና?"

"እኔ በፍቅር ስክር ብዬ ስለ ነበር ሀሳቡን ሁሉ በእሺታ ነበር የተቀበልኩት::

"ከዚያ?"



Scanned by CamScanner

"እኔንጃ! አንድ ዓመት እንዴት እንዳለፈ ተናገሪ ብትለኝ እኔ ራሱ በእርግጠኝነት አላውቅም ... ብቻ አንድ ዓመት አለፈ."

"እሺ."

"ከዚያ እኔን ስራ አስገቡኝ ቤተሰቦቹን ጠይቆ ለመመለስ ወደ ዱባይ ሄደ፡፡ ታላቅ ወንድሙ ዱባይ ነበር ያለው"

"አብረሀ ልሂድ አላልሺውም?"

"ብልም አልችልም ነበር"

"ስራ ጀመርሽ?"

"አዎ"

"ምን አይነት ስራ ነበር?"

"መስሪያ ቤት ውስጥ ነው ካርቶን ማሸግ..."

"ከዚያስ?"

ለረጅም ጊዜ ዝም አለች፡፡ በሀሳብ ባቡር ኩዌት እንደሄደች ገባኝ፡፡ እኔም እስከምትናገር በትዕግስት ጠበኳት... ብዙም ሳትቆይ መናገር ቀጠለች...

"ጠፋ!!"

"ጠፋ??"

"ስልኩን ዘጋ! እርሱም ጠፋ... እስከ ሁለተኛው ወር በትዕግስት ከዛሬ ነገ ይደውላል እያልኩ ጠብቄው ነበር ግን ጠፋ! አህመድን የማገኝበት ምንም አማራጭ ስላልነበረኝ እርሱ እስከሚደውል መጠበቅ ብቻኛ ምርጫዬ ነበር"

"እሺ"

"አንድ ዓመት ሞላ! አልመጣም!!"

"እርሱን የሚያውቀው ሰው አልነበረም? መረጃ የሚሰጥሽ?"

"ያስተዋወቁኝን ሰዎች ብጠይቃቸውም በሚገባ ስለ እርሱ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም"

"ዱባይ ነው ግን የሄደው?"

"አዎ! አየር መንገድ ድረስ በመሄድ ሸኝቼዋለው!!"

"እሺ"



Scanned by CamScanner

"በቃ! ሀሳቡ! ጭንቀቱ... ስለ አህመድ ምንም ፍንጭ አለማግኘቱ ወዘተ ተጨማምሮ በትንሽ በትልቁ መበሳጨት ጀመርኩ... የተሰጠኝን ስራ ባግባቡ መስራት ስላቃተኝ ከስራ ቦታ ተባረርኩ... እንደምንም ሌላ ቦታ የቤት ፅዳት በማግኘት ገባው... አህመድን ካገኘሁ በኋላ ተመልሼ ሽርሙጥናንትን ላለመስራት ወስኜ ነበር ... ሰባት ወር ገደማ በሰላም ሰርቼ ስምንተኛው ወር ላይ በጣም የምቀርባት ያቺ የመን ሽርሙጥና ያስጀመረችኝ ወጣት ኩዌት አንድ ሀብታም ጠብሳ መጥታ ተገናኘን... ያለውን ነገር ስነግራት ላይታች ብላ ስለ አህመድ አጣራችልኝ! አህመድ ሚስት እንዳገባ አወኩኝ! እኔን ለጊዜያዊ ስሜት ብቻ ነበር የፈለገኝ... አዘንኩ! የእጄን ነው ያገኘሁት አልኩኝ"

"እንደሰማሁት ከሁለት ዓመት እስር በኋላ እስርሽን ስትጨርሺ ወደ ኢትዮጵያ ወደ አገር ቤት እንደመጣሽ ነው"

"ትክክል"

"ለምን ነበር የታሰርሽው?"

"አላውቅም!!"

"አላውቅም ማለት?"

"ብቻ በብስጭት እጠጣ፣ አጨስ.... ምናምን ነበር፤ ከዚያ ተጣልቼ ይሁን... ምን ሆኜ ይሁን... ምን አድርጌ እንደሆነ አላውቅም የቀወሱ ሰዎች እስር ቤት ውስጥ ነበርኩኝ... ያው ከሁለት ዓመት በኋላ ሲሻለኝ ወደ አገር ቤት ተላኩኝ"

"ለማወቅ ጥረት አላደረግሽም?"

"ምንም አያደርግልኝም! በዚያ ላይ ማንም እውነታውን የሚነግረኝም የለም"

"በባዶ እጅ ኢትዮጵያ ተመለሽ?"

ለእኔ ምንም ሳትናገር በፍጥነት ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ ተነስታ መሬቱን ሳመችው... ከዚያ ተመልሳ ወንበር ላይ ተቀመጠች፡፡

"የኢትዮጵያ አምላክ ለአገሬ አበቃኝ!! እስር ቤት ስንት ወገኖቻችን አብደው እንዳሉ ብታይ ታዝናለህ! የሚደርስባቸውን በቃላት የማይገለፅ ስቃይ ብታይ ታዝናለህ! የእኔ ትልቁ ፀሎት የአገሬን መሬት መርገጥ ብቻ ነበር!! ፈጣሪ ይመስገን አገሬ ገብቻለሁ!! አሁን አዲስ ህይወት እየኖርኩ ነው! አሁን የገባኝ ህይወት ብዙ ውጣ ውረድ አላት! በተለይ ሴት ልጅ



Scanned by CamScanner

ብዙ ትፈተናለች!!"

"ባዶ እጅሽን ከመጣሽ ያን ያየሁትን በጣም የሚያምር ትልቅ ፀጉር ቤት ለመክፈት እንዴት ቻልሽ? በጣም ዘመናዊ ነው:: ለምሳሌ ስንት ፈጀ?"

"አጠቃላይ ወጪው 140ሺ ብር"

"ያስታውቃል! ታዲያ ብሩ ከየት መጣ?"

"የመን እያለሁ ሁለት አሪፍ ንግግሮች ሰምቻለሁ:: አንደኛው 'አንድ ሰው ፈጣሪን ፍለጋ ከቤት ሲወጣ ፈጣሪ ቤቱ መጥቶ አመለጠው' የሚል ሲሆን ሁለተኛው 'ፈጣሪ አንተን ለማግኘት ሲፈልግ በቀጥታ ፊት ለፊት መጥቶ ሳይሆን በሰው አማካኝነት ያገኝሃል' የሚሉ ናቸው:: እውነታቸውን ነው"

"እንዴት?"

"እኔ ራሱ አንዳንዴ ሳስበው ህልም ይመስለኛል ወይ ፈጣሪ? እንደ ፈጣሪያችን እኮ መልካም የሆነ የለም እላለሁ! ኢትዮጵያ መጥቼ ሁለት ወር ሲሞላኝ የመን እያለሁ የምታውቀኝ ጓደኛዬ የቤታችንን ስልክ ታውቀው ስለ ነበር ደወለችልኝ"

"ለምን ነበር?"

"እርዳታ ከእኔ ፈልጋ ነበር"

"የምን እርዳታ?"

"ቦሌ አየር መንገድ እንግዳ ይመጣል! የላኩት ዕቃ ስላለ እባክሽ ተቀበይና ለቤተሰቦቼ ስጭልኝ የሚል ነበር"

"እሺ"

"ከዚያ ለሰዎቹ የሚደውሉበትን የወንድሜን ሞባይል ቁጥር ሰጠዋት፤ እኔ የግል ስልክ በወቅቱ አልነበረኝም ነበር"

"እሺ"

"ቦሌ አየር መንገድ ሄድኩኝ! በተባለው ሰዓት ተደወለልኝ! ሰዎቹ መጡ... ታውቃለህ በህይወቴ እንደዚያች ቀን ደንግጬ አላውቅም! ብርክ ይዞኝ አያውቅም! የማየውን ማመን ነበር የተሳነኝ! ህልም ነበር የመሰለኝ"

"ምን ገጠመሽ?"

"ናስር እና ሁለቱ ልጆቹ ነበሩ"



Scanned by CamScanner

"ምን?"

"አይገርምም?"

"እንዴት?"

"አስበው! አራት ዓመት ሙሉ ሲጠብቀኝ ነበር! ለማመን ያስቸግራል አይደለም? ግን ከሁለቱ ልጆቹ ጭምር ስለ እኔ ሁሉን ነገር ሰምቶ መጣ"

"የሚደንቅ ሰው ነው?"

"ለዚያ ነው ስለ ፈጣሪ ስራ አስቀድሜህ የነገርኩህ"

"አሁን ገባኝ"

"እንግዲህ ፀጉር ቤቱን የከፈተልኝ እርሱ ነው:: አሪፍ ቤት ገዝቶልኛል... አሁን ሌላ ማንነት ያለኝ ደስተኛ ሴት ነኝ... አሪፍ ሌላ ዜናም እኮ አለኝ"

"ምን?"

"እርጉዝ ነኝ! የልጅ እናትም ልሆን ነው!! ሁሉ ነገር ሲጨልም አንዴ ነው!! ብርሃን ሲሆንም አንዴ ነው!! አሁን ደስተኛ ነኝ! ናስር ከእኔ ጋር በፍቅር እየኖረ ነው! የፍቅር ትርጉሙ በሚገባ የገባኝ በናስር ነው! እድለኛ ሴት አይደለሁም?"

"ምንም ጥያቄ የለውም!!"

ከሶፊያ ጋር የተገናኘነው በአቢሲኒያ 24 መፅሐፍ የተነሳ ነበር... ለሶፊያ በመጨረሻ ያቀረብኩት የሚከተለውን ጥያቄ ነበር

"አሁን እኔና አንቺ እያወራን ባለንበት ደቂቃ እንኳ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ወደተለያዩ አረብ አገራት እየሄዱ ይሆናል ወይም ለመሄድ ጥረት ላይ ይሆናሉ፤ አንቺ ምን ትያለሽ?"

"ምን መመለስ እንዳለብኝ ነው ግራ የሚገባኝ"

"ለምን?"

"አገር ውስጥ ያለውን እውነታ አውቃለሁ! አረብ አገር ያለውን እውነታም አይቻለው! ለመናገር ነው የሚያስቸግረኝ እዚም እሳት አለ! አረብ አገርም እሳት አለ!! ምናልባት ከሁለቱ እሳት የቱ ይሻላል? ካልከኝ እመልስ ይሆናል"

"አስቸጋሪ ጥያቄ ነው?"

"በጣም:: እውነታውን ስለማውቀው እኮ ነው፤ አገር ውስጥ እኮ በቂ ስራ ካለ፣



Scanned by CamScanner

የምትለወጥበት ነገር ካለ፣ ሰው የምትሆንበት አጋጣሚ ካለ... ለምን የማታውቀው አረብ አገር ሄደህ ጨሰህ ትመጣለህ? እኔ እኮ በጣም የሚያሳዝነኝ አረብ አገር ያሉት ሴቶች የሚኖሩት እና ህይወታቸውን መስዋዕት እንኳ የሚያደርጉት ለራሳቸው ሳይሆን ለሌላ ሰው ነው! በቅርቡ እንኳ አንዲት ሳውዲ አረቢያ የነበረች ልጅ መጥታ አብዳ አማኑኤል አስገብተዋታል"

"ምን ሆና ነው?"

"ወንድ ነው ያሳበዳት"

"ማለት?"

"የዛሬ ሶስት ዓመት ስትወጣ በፍቅረኛዋ ስም ባንክ ቡክ ከፍታ የምታገኘውን ሁሉ ታስገባ ነበር፤ ሶስት ዓመት ፈግታ ልጁን ለማግባት አገር ቤት ስትመጣ ከታናሽ እህቷ ጋ በፍቅር ወድቀው ታናሽ እህቷን ይዞ አሰላ ናቸው!! ዜሮ ሳንቲም እንኳ የላትም ... ብቻ ባይሄዱ እመኛለሁ!! የግድ መሄድ አለብን ካሉ ስለቤት ኢያያዝ፣ ስለ አረብኛ ቋንቋ፣ ስለ አረቦች ባህል በሚገባ መሰልጠን አለባቸው! በህጋዊ መንገድ ብቻ መሄድ አለባቸው! እስከሞት ድረስ የሚያደርስ ብዙ ፈተና እንደሚጠብቃቸው ማወቅ አለባቸው!!"

"አመሠግናለሁ"

"እኔም ከልቤ አመሠግናለሁ!!"

# ሶሲ. Rich!

ውይ የኔ ሶሲ አሪፍ ልጅ... ሶሲ ሙድ የገባት ... ስለ ሶሲ ብዙ የሚፃፍ ነበር ግን ስለምንድን ስለ ፍቅረኛዬ አድናቆት የበዛበት ነገር ትፅፋለህን? ስለ ምንድን ከፍከፍ ታደርጋታለህን? የሚል ፍቅረኛ አላት... እናም ስለ ሶሲ ከመቀባጠር ተወሰንኩ።

ከሶሲ ጋር በዩኒቨርሲቲያችን ብሶት አደባባይ የተዋወቅነው በአጋጣሚ ነበር... ውብ በጤ የሆነችው ሶሲ ብሶት አደባባይ ከዘለቀ ጋር ተቀምጠን ነበር ድንገት ሶሲ በአጠገባችን ስታልፍ አጋጣሚ ተዋወቁ ብሎ ሲያቃጥር

"እናቱ አንድ ጆሮ ጌጥ ፋሽን ሆነ እንዴ?" አልኳት።

"አልቀረብህም! አሁን እዚህ ቁጭ ብላችሁ ሴት ከምትላከፉ ምናለበት ይህን ውድ ጊዜያችሁን ቤተመፅሐፍ ገብታችሁ ብታነቡበት? አጠቃዎች! ጀዝባዎች!" ብላን ምን ቅር ምንቅር አያለች ሄደች። የሚገርመው እኔ ልለክፋት አልነበረም። የእውነቴን ነበር። አንድ ጆሮ ጌጥ ነበር ያደረገችው፤ ምናልባት በሆነ ነገር ሳትበሳጭ አይቀርም። ተሳደበች። ምናልባት የወር አበባዋ ላይ ትሆንም ይሆናል። በማለት ዝም አልን። አልሞቀንም አልበረደንም፤ በዚያ ላይ ከበደ ሚካኤል ባልሰለጠነ አገር ልጆች መጀመሪያ የሚሰሙት ትምህርት ሳይሆን ስድብን ነው የሚሉትን ስለምናውቅ ፈገግ ብለን ዝም አልን... እንጂ እኔም ሆንኩ ዘለቀ አጠቃዎችም ሆነ ጀዝባዎች አይደለንም... ብሶት አደባባይ የምንቀመጠው ለመወያየት ነው። ዘለቀ ምርጥ ልጅ ነው ግን ይፈራል! ቅናተኛ ነው... ከዚህ ውጪ ዘለቀ ለማወቅ ጉጉት ያለበት ከሱስ የፀዳ ልጅ ነው። በተለይ ስለ ቶማስ አልቫ ኤዲሰን እና እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ እንዲሁም ስለ ሶቅራጥስ ተጨማሪ እውቀት (መረጃ) የሰጠኝ ዘለቀ ነበር።

የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለን ነበር ስለ አፈወርቅ ተክሌ የተነሳው... እኔ ነበርኩ ጥያቄ ያነሳሁት።

"ከየትኛዋ የኢትዮጵያ ግዛት ነው የመጣኸው"

"አንተ የት ነህ?"

"ከሸገር"



Scanned by CamScanner

"እንዴ? የአፈወርቅ ተከሌ ከተማ እኮ ነው?"

"ልክ ነህ"

"ስለ አፈወርቅ ተከሌ ታውቃለህ?"

"አባቴ በጣም ይወደዋል! ሁሌ ስለ አፈወርቅ ተከሌ እየነገረኝ ነበር ያሳደገኝ፤ አንተም አድገህ እንደ አፈወርቅ ተከሌ ትንሿን አንኮበርንም ሆነ ትልቋ አገርህን ኢትዮጵያን ማስጠራት አለብህ ይለኝ ነበር"

"ምን ምን ነገሩህ?"

"ብዙ ነው"

"ትንሽ አቃምሰኝ"

"ዝነኛው አፈወርቅ ተከሌ ጥቅምት 13/1925 ዓ.ም እኔ በተወለድኩበት ሰፈር እንደተወለዱ፣ ገና አስራ አምስት ዓመት ሲሞላቸው በ1940 ለከፍተኛ ትምህርት እንግሊዝ አገር ንጉስ ኃይለስላሴ እንደላኳቸው... እንግሊዝ አገር ለንደን ከተማ ከዝነኛዋ ሲልቪያ ፓንከረስት ቤት እንዳረፉ... በርካታ ድንቅ ስራዎችን እንደ ሰሩ:: ለምሳሌ በሐረር የሚገኘውን የልዑል ራስ መኮንን ሀውልትን፣ በ1950 ዓ.ም የአፍሪካ አዳራሽ መግቢያ ላይ የሚታየውን በመቶ ሀምሳ ሜትር የተሳለውን ትልቅ እጅግ የሚያምር እና አስገራሚ የመስታወት ስዕል እንደሣሉ... ከምንም በላይ ለስራቸው ከፍተኛ ፍቅር እንዳላቸው! እጅግ በጣም ቀጠሮ አክባሪ እንደነበሩ! ከዓለማችን በርካታ ዝነኛ ሰዎች ጋር እንደተገናኙ... ከሀያ አገራት በላይ የስዕል ኤግዚብሽኖችን እንዳሳዩ ... ለመጀመሪያ ጊዜ 200 ታላላቅ የዓለማችን የአገር መሪዎች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ሳይንቲስቶች፣ ደራሲያን፣ ሠዓሊያን... ተመርጠው ስማቸው እና የህይወት ታሪካቸው ተፅፎ ወደ ጨረቃ ሲላክ የአፈወርቅ ተከሌም የህይወት ታሪክ ተፅፎ ወደ ጨረቃ እንደተላከ... ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ስም በትልቁ ያስጠሩ ድንቅ የኢትዮጵያ ኩራት የሆኑ የአንኮበር ልጅ እንደ ሆኑ ይነግረኝ ነበር! ታዲያ እኔም እድለኛ ነኝ"

"እንዴት?"

"አዲስ አበባ ሙዚየም ያሉትን ስዕሎቻቸውን ሆነ ሀዋሳ ቪላ አልፋ ያሉትን ከሀያ በላይ የሚጠጉ ውብ ስራዎችን አዲስ አበባ በሚገኘው አጎቴ አማካኝነት በዓይኔ ለማየት ችያለሁ"

"እድለኛ ነህ!!"



Scanned by CamScanner

"አልኩህ እኮ"

"አባቴ ከአፈጣሪዎች ተከሰሉ በተከታታይ የማን አድናቂ መሰለህ?"

"እህ"

"የቶማስ አልቫ ኤዲሰን"

"መብራት የፈጠረልን?"

"ትቀልዳለህ እንዴ? ብዙ ሰው የሚያውቀው መብራት መፍጠሩን ብቻ እንጂ ቶማስ በአንድ ሺ ዘጠና ሰባት የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶች ባለቤት የሆነ አስገራሚ ሰው ነበር!! አንተ ራስህ ይህን እርግጠኛ ነኝ አታውቅም! ለማንኛውም ስለ ቶማስ አልቫ ኤዲሰን አባቴ በአድናቆት ይነግረኝ ነበር"

"በእናትህ ምን ነገሩህ?"

"ብዙ ነው"

"ቢያንስ የተወሰነ ንገረኝ"

"ምን ልንገርህ?"

"ለምሳሌ አባትህ ስለ ቶማስ ሲነግሩህ በእርግጠኝነት በአንተ ላይ የሆነ ነገር ለማሳደር በሚል አላማ ነው ወይስ ለታሪክ ብቻ?"

"ለቁም ነገር እና እኔን ለማነቃቃት ነው እንጂ"

"ስለዚህ ነጥብ ያደረከውን አውጋኝ"

"ገባኝ! በዚች የተወሰነች ዓመት ብቻ በምንኖርባት አለማችን ላይ ውጤት እና ስኬት የሚመጣው ያለመሰልቸት በተደጋጋሚ በመሞከር እንደሆነ፣ ቶማስ አልቫ በጣም ከፍተኛ አንባቢ እንደ ነበሩ እና ለንባብ ክብር እንደነበራቸው! እኔም አንባቢ እንድሆን! ለማንበብ ፍቅር እና ክብር እንዲኖረኝ በተለይ የገረመኝ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"ንገረኝ"

"የአፍሪካ መዲና ነች የምትባለው አዲስ አበባ የተመሠረተችው 1878 ዓ.ም ነው:: አስበው እንግዲህ የእኛዋ አዲስ አበባ ገና ሳትመሰረት ቶማስ አልቫ በ12 ዓመቱ ወደ ንግድ ዘርፍ በመግባት በ1851 ዓ.ም ላይ በአሜሪካ የባቡር መንገድ በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋበት ዘመን ስለ ነበር ገና በልጅነቱ በጠዋት እየተነሳ ከባቡር ለሚወርዱ ሆነ ለሚሳፈሩ ሰዎች ከረሜላ እና ጋዜጣ መነገድ የጀመረው! አየህ ገና ከልጅነቱ ነው የስራ ሰው መሆን የጀመረው...



Scanned by CamScanner

በተጨማሪ አባቴ ከቶማስ አልቫ በርካታ አባባሎች አስራ አራቱን በቃሌ እንድይዝ ያስጠናኝ ነበር፤ በዚያው የማስታወስ ችሎታዬንም እንዳሻሽል ነበር"

"አባባሎች?"

"አዎ"

"አባባል እወዳለሁ!"

"እኔም"

"ቢያንስ ለዛሬ አራቱን ንገረኝ"

"ይቻላል"

"አንደኛ"

"ጥበበኛ ሰው ማንንም ሰው ቂል አይልም:: ቂሎች ግን አዋቂ ሰዎችን ቂሎች ይላሉ"

"ሁለተኛ"

"ዓለም ከማንም ሰው ዕዳ የለባትም:: እያንዳንዱ ሰው ግን ከዓለም ዕዳ አለበት"

"አሪፍ ነው! ሶስተኛ"

"ብዙ ሺ ሀሳቦችን ይዘው ምንም ከማይሰሩ ሰዎች ይልቅ አንድ ሀሳብ ኖሮት እሷኑ ተግባራዊ ለማድረግ የማያቋርጥ ጥረት ለሚያደርግ ሰው የተለየ አክብሮት አለኝ"

"ትልቅ አባባል!!"

"የመጨረሻ... አንድን ነገር ለማግኘት አስቀድመህ በጣም ተመኝ!! ይጠቀሳሉ"

"እውነት አባትህ አሪፍ ሰው ናቸው! ስለ ስራቸው ማወቅ እችላለሁ"

"የኮሌጅ አስተማሪ ነው"

"እ.. አሪፍ ነው! አንተም አስተማሪ የመሆን ህልም አለህ?"

"የግል ስራ መስራት ነው የምፈልገው በእርግጠኝነት ኢንተርፕሬነር እሆናለሁ"

የዚያን ዕለት ሶሲ ከእኛ ስትርቅ በዓይኑ ዘለቀ እየተከተላት ነበር:: ይቺ አጋጣሚ ሳትሆን አትቀርም የዘለቀን ልብ የሳበችው... እኔም ወዲያው ነጀስኩት::

"ዘሌ!"

"አቤት"

"ቂጧ ግን ደስ አይልም?"

"እኔ የቂጥ ሳይሆን የጭንቅላት አድናቂ ነኝ"



Scanned by CamScanner

"አይልም ወይ? እኮ ነው ያልኩት የግል አስተያየት ነው"

"ገብቶኛል! አረ ተመልሳ መጣች" አለኝ፤ በእርግጥም ተመልሳ ሶሲ መጣች፤ ዝም አልናት፤ አጠገባችን ስትደርስ ቆመች... በማይረሳ ፈገግታ ተሞልታ...

"በጣም ይቅርታ ለከፋ መስሎኝ ነበር..."

በዚች መሰል አጋጣሚ ከሶስና ጋር ተዋወቅን:: ሶሲ አንባቢ ናት... ሶሲ ጎበዝ ተማሪ ናት... ሶሲ የተረት አፍቃሪ ናት... ቁጥሩን እርግጠኛ ባልሆንም ሶሲ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በነበረን ቆይታ... ከ60 በላይ አሪፍ አሪፍ ተረቶችን ነግራኛለች:: ተረት አፍቃሪ እንደሆነች ያወኩት በትውውቃችን አንድ ወር ቆይታ በኋላ ነበር... አስታውሳለሁ የተማሪዎች መዝናኛ ውስጥ ተቀምጬ ለአንድ ቀን ብቻ የተበደርኩትን የዶ/ር ጆንሰን ስፔንሰር ስራ የሆነውን እና በአዜብ ግርማ ትርጉም የተሰራለትን አይቤን ማን አሸሸው (Who moved my cheese) የተሰኘችውን አነስተኛ 66 ገጽ ያላትን አነቃቂ ታሪክ እያጣጣምኩ ነበር ሶሲ የመጣችው

"who moved by cheese?" አለችና አጠገቤ ተቀመጠች::

"አንብበሹዋል?"

"አዎ በአማርኛ ሳይሆን በኢንግሊዝኛ አስራ ሁለተኛ ክፍል እያለሁ አንብቤያታለሁ! ትንሽ ግን አሪፍ የሆነች ታሪክ ናት! በነገራችን ላይ አጠር ያሉ ታሪኮችን እና ተረቶችን አሰባስባለሁ"

"ማለት?"

"ለምሳሌ የአሾን መፅሐፍት ስታነብ ሀሳቡን ይበልጥ ለማጠናከር የሚጠቀምባቸውን አይነት አጫጭር ታሪኮች"

"አ! ገባኝ እንደዚያ አይነት ታሪኮችማ በጣም አሪፍ ናቸው:: ታዲያ እስከ ዛሬ ስንት አሰባሰብሽ?"

"ከ140 የተለያዩ መፅሐፍት ላይ ወደ 300 የሚጠጉ"

"300??"

"ትንሽ ነው?"

"ብዙ ነው እንጂ!!"

"ገና እቀጥላለሁ"

"መጨረሻቸውስ?"



Scanned by CamScanner

"ማለት?"

"ወደ መፅሐፍትነት የመቀየር ሀሳብ አለሽ?"

"ኡ... አስቤው አላውቅም"

"አስቢበት! አባባል እያሰባሰቡ ያሳትሙ የለም እንዴ? ለሰዎች ጠቃሚ ስለሚሆኑ ቢታተሙ መልካም ይመስለኛል"

"አስብበታለሁ"

"ለዛሬ አንድ ሶስት አውጊኝ"

"እሺ ቡና ጋብዘኝ"

"በጣም ይቅርታ... ዛሬ ችስታ ነኝ"

"አትዋሽ! ኪስህ ውስጥ ምንም የለም?"

"ምንም"

"በል ና እኔ ልንከባከብህ"

የተማሪዎች መዝናኛ ውስጥ ግርግሩ በርካታ ስለነበር እያወራን የአስተማሪዎች መዝናኛ ጋር ሄድን፤ ምቹ ሊባል የሚችል ቦታ ፈልገን ተቀመጥን... ብዙም ሳልቆይ ወደ ጥያቄ አመራሁ፡፡

"ከህንድ አጫጭር ታሪኮች ጀምሪልኝ"

"እሺ... በህንድ አንድ ዝነኛ ወደ ሆነ የቡዲዝም መምህር ጋር አንድ ልጅ ይሄድና ተኩላ አይቶ እንደፈራ ይነግራቸዋል፤ መምህሩ በእርጋታ ልጁን እየተመለከቱ 'ልጄ ይልቅስ መፍራት ያለብህ በዓይንህ ያየኸውን ተኩላ የተባለ እንስሳ ሳይሆን በአንተ ውስጥ ዘላለም የሚኖሩትን ሁለት ተኩላዎችን ነው'

'ሁለት ተኩላዎች?'

'አዎ! ሁለት ተኩላዎች'

'ምንድናቸው መምህር?'

'ልጄ ትልቁ መፍራት ያለብህ ውስጥህ ያሉትን ሁለት ተኩላዎችን መሆን አለበት፡፡ እነዚህ ሁለት ተኩላዎች መሀከል ትልቅ ጦርነት ይከናወናል፡፡ አንደኛው ተኩላ ክፋት ነው፡፡ መገለጫዎቹም ንዴት ፣ ቅናት፣ ስድብ፣ ፀፀት፣ ሀዘን፣ መስገብገብ፣ ግትርነት፣ ቁጭት፣ በደል ፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ውሸት፣ ትዕቢትና ኩራት፣ የበታችነት ስሜት፣ የበላይነት ስሜት... ናቸው፡፡



Scanned by CamScanner

ሁለተኛው ተኩላ ደግሞ መልካምነት ወይም ቀናነት ነው:: መገለጫዎቹም ደስታ፣ ፍቅር ፣ ሰላም ፣ መተሳሰብ፣ ተስፋ፣ እርጋታ ፣ ትህትና፣ ልግስና፣ አንድነት፣ ርህራሄ፣ ሃቀኝነት፣ ትዕግስት፣ እምነት ፣ ክብር፣ መቻቻል... ናቸው:: አሉት'

'ልጁም መምህሩን ሲያዳምጥ ቆየና ንግግራቸውን ሲጨርሱ 'መምህር ታዲያ ከሁለቱ ተኩላዎች የትኛው ተኩላ ነው የሚያሸንፈው?' ሲል ይጠይቃቸዋል:: መምህሩም ልጁን በፍቅር እየተመለከቱት 'ልጄ ያ አንተ በሚገባ የምትንከባከበው ተኩላ ያሸንፋል' አሉት:: ይቺ አጭር ታሪክ በህይወታችን ውስጥ ስንኖር የትኛውን አይነት አመለካከት ማዳበር እንዳለብን ያሳየናል"

"አሪፍ ታሪክ ነች"

"እንዲሁ አንድ ወጣት በጣም እየተበሳጨ እኚህ መምህር ጋር ይመጣል፡፤ ለምን እንደተበሳጨ ይጠይቁታል:: 'ተጨባጭ መረጃ ቢኖረኝም ላሸንፍ አልቻልኩም! በዚህ የተነሳ ነው የተበሳጨሁት ለመሆኑ የተከበሩ መምህር ሆይ ሰው እንዴት እውነትን ይዞ አያሸንፍም?' አላቸው:: መምህሩም ለዚያ ወጣት ይህን ታሪክ ነገሩት:-

አንድ ወጣት አንድ ጊዜ የሞኞች አገር በሚባል ከተማ ያልፋል:: ታዲያ ያ መንገደኛ በእርጋታ ሲጓዝ እጅግ በርካታ ገበሬዎች ተደናግጠው ሲሮጡ ይመለከታል:: ምን ሆናችሁ ነው ሲላቸው

'ተመልከት! እዛ ማሳ ውስጥ አንድ አውሬ አለ' አሉት:: መንገደኛው ወጣት ወደ ማሳው ሲመለከት አንድ ትልቅ ሃብሃብ ብቻ እንጂ ሌላ አንዳች አውሬ የሚባል እንደሌለ አጤነ:: ከዚያ ሰዎቹን በመሰብሰብ አውሬውን እንደሚገልላቸው በማስረዳት በፍጥነት ማሳው ውስጥ በመግባት ሰንጢውን አውጥቶ ሃብሃቡን ሁለት ቦታ ከፍሎ መብላት ጀመረ:: በዚህ በወጣቱ ሁኔታ ሰዎቹ በጣም ተደናገጡ! ያን መንገደኛ ወጣት ከሃብሃቡ የበለጠ ፈሩት 'ይህን ወጣት መንገደኛ በፍጥነት ደብድበን ካላባረርነው ቀጥሎ እኛን ነው የሚበላን' እያሉ በያዙት ዱላ እየቀወሩት ከአካባቢያቸው አባረሩት! ታዲያልህ በሌላ ወቅት ሌላ አንድ ብልህ መንገደኛ በነዋሪው ሰፈር ሲያልፍ ተመሳሳይ ነገር አጋጠመው፤ ይሁን እንጂ አውሬውን ልግደልላችሁ ከማለት ይልቅ ስለ አደገኛነቱ እያወራ እንደሰዎቹ ሃብሃብ ባየ ቁጥር እየደነገጠ የእነሱን አመኔታ ማግኘት ቻለ:: ከዚያ በየቤታቸው በመሄድ ከሃብሃብ ፍርሃታቸው ነፃ የሚወጡበትን እውነታ ቀስበቀስ ያስተምራቸው ያዘ:: አንድ ወር ሳይሞላ ከፍርሃታቸው ነፃ በማውጣት



Scanned by CamScanner

እነዚያ ነዋሪዎች ሃብሃብን ማምረት እንዲችሉ አደረጋቸው!! አየህ አንዳንዴ እውነታ ብትይዝም ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ሌላ መላ መቀየስ አለብህ! እውነትን ብትይዝም እንዴት እና መቼ እንደምትጠቀምባት ካላወክ ጨርሶ ማሸነፍ የማትችልባቸውም አጋጣሚዎች እንዳሉ መገንዘብ ብልህነት ነው የእኔ ልጅ' ሲሉ መከሩት::"

ራሴን ነቀነኩላት:: የመምህሩ ሀሳብ እውነትም ነበር:: ከዚያ ሶሲ በትኩረት እየተመለከተችኝ ጥያቄ ሰነዘረች::

"የሰው ልጅ ሁሉ ደካማ ጎን አለው ብለህ ታስባለህ?"

"ያለ እንከን ማን ይፈጠራልና? ግን ይህ ራሱን የቻለ ህይወትን ውብ የሚያደርጋት ነገር ነው"

"ግን በተለይ በእኛ በሀበሻ ባህል አንድ ሰው ዘጠኝ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትና አንዲት ደካማ ጎን ወይም እንከን ብትኖርበት በእኛ በኢትዮጵያ ባህል ጎልቶ የሚወጣው የቱ ነው?"

"ምን ጥያቄ አለው እንከኗ ነቻ!!"

"አስበው ምን ዓይነት አስጠሊታ የሆነ ባህል እንዳለን!! እርግጠኛ ነኝ የኋላ ቀርነታችን መገለጫ አንዱ ይህ ከጠንካራ ጎናችን ይልቅ እንከን ብቻ የመፈለግ አባዜያችን ነው! በዚያ ላይ የራሳችንን ችግር ሆነ እንከን ሳንመለከት የሰውን እንከን የማየት ችሎታችን ለእኔ መርገምትነት ነው!! ለማንኛውም አንድ ወጣት ወደ አንድ የህንድ ምሁር ጋር ሄደ:: 'መምህር ሆይ በተፈጥሮ ባለኝ ድክመት ሰዎች እያጠቁ አስቸገሩኝ ምን ተሻለኝ?' አላቸው:፤ መምህሩ ወጣቱን በትኩረት እየተመለከቱ

'ልጄ አትገረም! በዓለም ላይ ካሉት የሰው ልጆች ይቅርና ቡድሃ እንኳን እንከን አለበት፤ ሰዎች አንተን በድክመትህ ሊያሸንፉህ ቢጥሩ አንተ ጠንካራ ጎንህ ላይ ትኩረት ማድረግ ብቻ ነው፤ አንተ አሁን ለሰዎች የሰጠሃቸው አብዝቶ የተሰጠህን ጥንካሬህን ሳይሆን ትንሿ ድክመትህን ነው:: እንዳልኩህ አምላካችን ቡድሃ እንኳ ድክመት አለበት ግን ድክመቱ በጥንካሬው ይዋጣል:: አየህ የዓለም ጠቢብ ሰው ማለት ድክመቱን ሳይረሳ ጥንካሬውን ለማጉላት የሚጥር ነው" ሲሉ መከሩት::'

"እርግጠኛ ነኝ ሌላ ጊዜም ብዙ እናወራለን?"

"ቀላል! አንተ ጥሩ አዳማጭ ሁን እንጂ የህንድ፣ የቻይና፣ የፐርሺያ፣ የአፍሪካ... ብዙ አጫጭር ታሪኮችን እነግርሃለሁ፤ ይልቅ ከህንድ ሳንወጣ በጣም ስለምወዳቸው ሴት እና የእኔ



Scanned by CamScanner

ጀግና ስለሆኑት ሴት እናውራ?"

"ስለ ማዘር ትሬዛ ነው?"

"በምን አወከ?"

"ማዘር ትሬዛ እኮ የዓለም እናት ናቸው!! የመልካምነት ምሳሌ ናቸው!! ማዘር ትሬዛ እኮ ናቸው በስንቶች የዓለማችን ሴቶች ልብ ውስጥ በመግባት የመልካምነት መነቃቂያ የሆኑ አለም አቀፍ እናት ናቸው:: ለምሳሌ ከኢትዮጵያ እንደ አበበች ጎበና ላሉት መልካም ሴቶች የመንፈስ እናት ናቸው!!"

"አንተም እንደ እኔ ትወዳቸዋለህ?"

"በጣም!! በተለይ ሁለት የምወድላቸው ንግግሮች አሏቸው"

"አስታውሰኝ"

"ራሳችንን ዝቅ ካደረግን ምንም ነገር አይለውጠንም:: መደነቅም መጣጣልም አይለውጠንም! ሰዎች ሲተቹን ዝቅተኝነት አይሰማንም:: ሰዎች ሲያደንቁንም ኩራት አይሰማንም!! ይህችን ዓለም ስንሰናበት የምንገመገመው ባሉን የትምህርት ደረጃዎች፣ በሰራናቸው ጥሩ ስራዎች ሳይሆን ለምንሰራው ስራ በሰጠነው ፍቅር መጠን! የፈጣሪን መንገድ ባወቅንበት መጠን ነው!"

"ጥሩ ምክር ነው:: ለማንኛውም ማዘር ትሬዛ ከ1902-1989 ዓ.ም ማለትም ለ87 ዓመታት በምድር በቆዩበት ጊዜያት አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ጨምሮ በመላው ዓለም ውስጥ በ123 አገራት ከ620 በላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን አቋቁመዋል!! ማዘር ትሬዛ ስለ ፖለቲከኞች ተጠይቀው ነበር እሳቸውም ሲመልሱ

'እኔ ለእነሱ መናገር የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው:: ፖለቲከኞች ለፀሎት ያላቸው ጊዜ ትንሽ ነው:: ተንበርክከው አይፀልዩም:: እኔ እንደማምነው ተንበርክከው ቢፀልዩ የተሻለ ይሆኑ ነበር' ሲሉ ነበር የመለሱት:: በሰው ልጆች ፍቅር ልባቸው የሸፈተው ማዘር ትሬዛ እንዲሁ ስለ ሰላም ተጠይቀው ነበር:: ይህን ጥያቄ ሲመልሱ

'በእርግጠኝነት ሰላምና ጦርነት ከቤት ይጀምራል:: የአለምን ሰላም በእውነት የምንፈልግ ከሆነ ቤተሰቦቻችን እርስ በእርሳችን እንዋደድ:: ደስታን ማባዛት ከፈለግን እያንዳንዱ ቤተሰብ ደስታ እንዲኖረው እናድርግ ነበር' ያሉት:: ማዘር ትሬዛ ስለ ድህነት



Scanned by CamScanner

ተጠይቀው እንዲህ ሲሉ መለሱ

`ተናገሪ ካላችሁኝ በዓለም ላይ የከፋ ድህነት የሚባለው ብቸኝነት ነው:: ብቸኝነት የድህነት አንዱ መገለጫ ነው:: አዛውንቶችን ማንም ከቤት መጥቶ የሚጠይቅ ሰው ማጣት ትልቅ ድህነት ነው:: ሊድማጭ ያጡ ሰዎችን ማዳመጥ እጅግ በጣም ቆንጆ ነገር ነው ሲሉ ነበር የመለሱት::"

ከሶሲ ሪች ጋር አያሌ ነገሮችን አውርተናል:: አሪፍ የዩኒቨርሲቲ የጓደኝነት ጊዜያትን አሳልፈናል:: ሶሲ የእርጋታ እና የእውቀት ባለቤት ነበረች:: አንባቢ ነበረች:: ባለ ትልቅ ህልም ነበረች:: የሶስተኛ ዓመት ተማሪ እያለን አንድ ምሽት መኝታ ቤት እያለሁ የአንኮበሩ ዘለቀ እያለከለከ መጣ:: በምልከት ከመኝታ ቤት ተከትዬው እንድወጣ ጠቀሰኝ:: አብረን ወጣን::

"ምነው?" አልኩት::

"ደንግጫለው አይደለም?"

"ቀላል!"

"ፍቅር ሲይዝህ ለካ በፍርሃት ትያዛለህ? ለካ ፍቅር ሲይዝህ የምታውቀው ሁሉ ይጠፋብሃል? ይህ ዛሬ ነው የተገለፀልኝ"

"እንዴት? ምን አጋጠመህ?"

"ቆይ መጀመሪያ ጥያቄ ልጠይቅህ! መቼም እኔ በተፈጥሮዬ መሳሳት እንደማልወድ ሆነ ለሰው ስህተት የሆነ መረጃ መናገር እንደማልወድ ታውቃለህ?"

"እናውቃለን ንጉስ ሆይ"

"አትቀልድ የምሬን ነው"

"አውቃለው"

"እሺ መጀመሪያ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

"ቀጥል"

"ሶቅራጥስ የአባቱ ስም ማን ነበር?"

"አልተጠቀሰም"

"መቼ ነበር የኖረው?"

"እህ ከ469-399 ዓ.ዓ በ70 ዓመቱ ሞት ተፈረደበት"

"ሶቅራጥስ ከጨቅጫቃዋ ሚስቱ ስንት ልጆች ነበር የወለደው?"



Scanned by CamScanner

"ሶስት"

"እርግጠኛ ነኝ As for me, all I know is that I know nothing ያለው ሶቅራጥስ ነበር?"

"እንዴ እርግጠኛ ከሆንክ ለምን ትጠይቀኛለህ?"

"በእናትህ ዝም ብለህ ንገረኝ"

"ልክ ነህ!"

"True knowledge exists in knowing that you know nothing እና Beauty is a short lived tyranny ያለውም ሶቅራጥስ ነበር??"

"ነበር!!"

"እየህ ሶሲ ስለ ሶቅራጥስ ጠይቃኝ እያወራሁላት ነበር እና ከማንም በተለየ ለሶሲ ስህተት የሆነ ነገር ነግሬያት እንድትታዘበኝ አልፈልግም! በሶሲ ፊት ላይ መሳሳት አልፈልግም"

"በነገራችን ላይ ብዙ ጊዜ ከሶሲ ጋር ስትሆን ነፃነት አላይብህም የሚሰማኝን ልንገርህ?"

"ተናገር"

"ፍቅር የያዘህ ከሶሲ ነው?"

ዝም አለኝ::

"ልብህ ከጅሎዋታል አይደለም?"

ዝም አለኝ::

በዚያች ደቂቃ ያለኝ ብቸኛ አማራጭ ዘለቀ የልቡን እንዲናገር ዘና ማድረግ ነበር፤ እናም

"በነገራችን ላይ ለሶስና አንተን ማግኘት መታደል ነው:: ያው አንድ ሁለት አስቸጋሪ ፀባይ ቢኖርህም! ትመቻቻላችሁ የሚል ግምት አለኝ፤ በዚያ ላይ አንዴት ነው አንኮበር ሙጠምጢም ወይም መስተፋቅር ነገር የለም እንዴ?" በማለት ደካማ ጎኑን ነካ ስላደረኩበት ወዲያው በንዴት ግሎ

"እናንተ የሸገር ልጆች ደግሞ የክፍለሀገር ተማሪዎችን ሁሉ በጥንቁልና የሚያምን ታስመስሉታላችሁ!! እንደውም ሀቁን ንገረኝ ካልከ ብዙ ጠንቋይ ቤት የሚመላለሱት የአዲስ አበባ (ሸገር) ነዋሪዎች ናቸው:: እኔ በፈጣሪ የማምን ነኝ !! በተዓምር አሷን ለማግኘት

መስ፡ፋቅር አልጠቀምም!!"

"እሀ... በመስተፋቅር ታምናለህ ማለት ነው?"

"ማመን ሌላ... መጠቀም ሌላ"

"ለማንኛውም ስቀልድ ነው! አንተ እንዲህ እንደማታደርግ በአስር ጣቴ እፈርማለሁ! ይልቅ ሶሲን እንዴት አፈቀርካት?"

"ምን አይነት ጥያቄ ነው?"

"እሺ ቀለል ላድርገው! ምኗ ተመቸህ?"

"አመለካከቷ ድንቅ ነው፡፡ በዚያ ላይ የቃል ሳትሆን የተግባር ሴት ናት!! ከሁሉም ደስ የሚለኝ ለሰው ያላት ክብር ነው! በዚያ ላይ ማለፊያ ውብም ናት"

"ሳትፈራ ጠይቃት"

"እውነትህን ነው?"

"ከልቤ ነው፡፡ በእርግጠኝነት መናገር ባልችልም ሶሲም የምትወድህ ይመስለኛል"

"አመሠግናለው"

"መቼ ትጀነጅናታለህ?"

"መጀንጀን ሳይሆን መጠየቅ"

"እሺ መቼ ትጠይቃታለህ?"

"በቅርቡ"

እውን ፍቅር አለ? እውን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተጀመረ ፍቅር ዘላቂ ነው? እውን ስንቶች ህይወታቸው የሚበላሸበት የዩኒቨርሲቲ ፍቅር ለሁለቱ ወጣቶች አደጋ የለውም? ለምርቃት አንድ ዓመት የቀራቸው እነዚህ ሁለት ወጣቶች በፍቅር የተነሳ ችግር ላይ ሊወድቁ አይችሉም?... የሚሉ ፍራቻዎች ነበሩኝ.. ግና የሶስና እና የዘለቀ ፍቅር የእውነት ነበር፡፡ ስሜታዊ ፍቅር አልነበረም፡፡ ከሆሳዕና የመጣቸው ሶስና እና የአንኮበሩ ዘለቀ በፍቅር ተዋሀዱ... በመልካም ውጤት ተመረቁ... እነሆ እስከ ዛሬም አብሮው ናቸው፡፡ ሁለቱም ይቺን ህይወት የምንላትን ጉድ በአንድነት እየመሯት ይገኛሉ... ቀናውን እስከ መጨረሻው እመኝላቸዋለው!! የፍቅር አምላክ ፍቅራቸውን የትየለሌ ያድርግላቸው...

እንግዲህ ከዚህ በፊት በታተሙት መፅሐፍት ውስጥ ያሉትን አጫጭር ተረት መሠል ታሪኮች የነገረችኝ ሶሲ ናት፡፡ ከዚህ በላይም ሥነፅሁፍ ውስጥ እንድገባ ይወተውቱኝ ከነበሩት



Scanned by CamScanner

"እነታቂዎቹ" መሀከል ግንባር ቀደሟ ነበረች... ባለሸበት ግራሲያ ሶሲ ብያለሁ:: የሶሲ እና የዘለቀን ቅንጫቢ ታሪክ በማዘር ትሬዛ አባባል መዝጋቱ ተገቢ መሰለኝ...

"ሰላም የሚጀምረው በፈገግታ ነው፤ ትንሿ ፈገግታ ትልቅ ስራ ትሰራለች!!"



Scanned by CamScanner

# ኦኔሲሞስ

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ በጣም ከሚቆጨኝ አጋጣሚ አንደኛው ይህን ወጣት ለአንድ ዓመት ብቻ ማወቄ ነው፡፡ ምነው አስቀድሜ ባውቀው ኖሮ ስንት እውቀት እሸምት ነበር፡፡ ለአንድ ዓመት ቢሆንም በቂ እውቀት ግን ሰጥቶኛል፡፡ ፍጹም እርጋታ የተሞላበት! ፍፁም ኢትዮጵያዊነት የነበረው ወጣት ነበር፡፡ ምንም እንኳ የእርሱን መንገድ ባልከተልም ስለ ገጸባህሪያት አሳሳል ያስተማረኝ እርሱ ነበር፡፡

ከወጣቱ ኦኔሲሞስ ጋር በርካታ ነገሮችን በዚያች የአንድ ዓመት ትውውቃችን ለማውራት ችለናል፡፡ ይበልጥ ያግባባን ሁለታችንም ለሥነፅሁፍ የነበረን ፍቅር ነበር፡፡ እኔ በወቅቱ የፍልስፍና መፅሐፍትን አድናቂ ነበርኩ፡፡ እርሱ ለታሪክ መፅሐፍት ልዩ ትኩረት ይሰጥ ነበር፡፡ በሥነፅሁፍ ላይ ግን አንድ ባቡር ውስጥ ነበርን፡፡

እንዴት ተዋወቅን?

በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ በርካታ ሴቶች የሚገኙበት እና ታዋቂው የሴቶች ህንፃ ተፋጠጥ ይባል ነበር፡፡ በርካታ ወጣቶች ተፋጠጥን ሳይረግጡ አይውሉም ነበር፤ በዚያ ላይ የተፋጠጥ ህንፃ አማካኝ ቦታ ላይ ነበር፤ እናም እኔም ከተፋጠጥ ህንፃ ውስጥ አስጠርቼያት የምጀነጅናት ሴት ባትኖርም አይናቸውን እያቁለጨለጩ ከተፋጠጥ የምትወጣ ቺካቸውን የሚጠብቁትን፣ በአይን ፍቅር ተይዘው ከተፋጠጥ የከጀሏት ሴት እስከምትወጣ የሚጠባበቁትን ወንዶች ከተፋጠጥ ፊትለፊት በሚገኘው የተማሪዎች ላውንጅ በመቀመጥ መመልከት አንዱ መዝናኛዬ ነበር፤ በዚህን ወቅት ነበር አጠገቤ ወጣቱ ኦኔሲሞስ የመጣው

"ታዲያስ"

"አለው"

"ላስቸግርህ ነበር"

"የምችለው ከሆነ..."

"ከተፋጠጥ አንዲት ሴት አስጠርተህ ይህን ደብዳቤ መስጠት"

"የፍቅር ነው? ምናልባት ሌላ ነገር..?"

"አትፍራ! እኔ መሆኔን ካወቀች ስለማትመጣልኝ ነው፡፡ የፍቅር ደብዳቤ ነው፡፡ አድርሰህ ስትመለስ ታሪኩን ከፈለከው እነግርሃለው"



Scanned by CamScanner

"ይመችህ" አልኩትና የልጅቷን ስም እና አድራሻ በመቀበል ተፋጠጥ በመሄድ አንዷን ሴት አባክሽ ራሔልን ከ204 ጥሪልኝ በማለት አስጠራዋት... ኦ! አውነቱን ለመናገር አያዩ የመሰለች ነች! ለማንኛውም ውበቷ ለእኔ አልታየኝ ይሆናል... ብቻ ሰጥቼያት ተመለስኩኝ::

"ምን አለች?" አለኝ በጉጉት::

"ምንም! ተቀበለች! ሄደች"

"አመሠግናለው"

"ኮርታብህ ነው?"

"ቀላል! በጣም ነው የምወዳት! እስካሁን ሰባት ደብዳቤዎች ሰጥቼያታለው! አሺም እንቢም አላለችም!! ይህ ይበልጥ ፍቅር ጨመረብኝ"

"በእርግጥ የሰው ልጅ በመልክ ባይመዘንም ቆንጆ ነገር ግን አይደለችም:: ለአስተያየቴ ይቅርታ"

ፈገግ አለ::

"ግልፅነትህ ተመችቶኛል! መፅሐፍ ቅዱስ ላይ በመፅሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 31 ቁጥር 30 ላይ ምን ይላል መሰለህ? 'ውበት ሐሰት ነው ደምግባትም ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርሷ ትመሰገናለች' ይላል:: ሴትን ልጅ ማፍቅር ያለብህ በውበቷ ሳይሆን በጥንካሬዋ ነው"

"እስማማለሁ! ቅድም ያልከኝ ሰባት ተመሳሳይ ደብዳቤ ነው?"

"የተለያየ ነው እንጂ"

"ተስፋ እንዴት አልቆረጥከም?"

"ስለ ራሔል እና ያዕቆብ ታሪክ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ አላነበብከም? ያዕቆብ ራሔልን ለመጀመሪያ ጊዜ አይቶ ልቡ የተመኛት የአባቷን በጎች ውሃ ልታጠጣ ወደ ጉድጓድ ስታመራ ነበር፤ ከዚያ ያዕቆብ ራሔልን ለማግኘት 7 ዓመታት መጠበቅ እና ስለ ፍቅር ሲል መስዋዕት መሆን ነበረበት"

"እና አንተም 2555 ቀናት እጠብቃለው እያልከኝ ነው?"

"ለጨዋታ አልኩህ እንጂ እኔ አሺ ወይም እንቢ እስከትለኝ ብቻ ነው!! ያን ያህል ለፍቅር የሚከፈል መስዋዕት ይኖረኛል የሚል ግምት የለኝም!! በዚያ ላይ ስንመረቅ የት አገኛታለው?"

"ማለት?"

"እኔ የነቀምቴ ልጅ ነኝ! እርሷ የደብረማርቆስ ልጅ ነች"

ስሜን ነገርኩት:: እርሱም ስሙን ነገረኝ:: እነሆ ስሙን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ስለ ነበር ትርጉሙን ጠየኩት::

"ኦኔሲሞስ ምን ማለት ነው?"

"ታዋቂ ምሁር ነበር:: የኢሉባቦር ተወላጅ የነበረ ሲሆን ሙሉ ስሙ ኦኔሲሞስ ነሲቡ ይባል ነበር:: መፅሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ የለወጠ ምሁር ነበር፤ አባቴ ነው በእርሱ ስም የጠራኝ"

በዚህ መልኩ ነበር ከነቀምቴው ልጅ ጋር የተዋወቅነው፤ ታዲያ የፍቅሩን መጨረሻ ለማወቅ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ሰላምታ እየሰጠሁት እጠይቀው ነበር፤ በተለይ የተማሪዎች ላውንጅ ስለማይጠፋ በቀላሉ ለመግባባት ችለን ነበር:: አንድ ጊዜ ተቀምጠን እያወራን አንድ ጓደኛው 'ሠላም ነው ነገሕባ' ብሎት ሄደ:: እኔ ወዲያው

"እንዴ ሌላ ስም አለህ?" አልኩት::

"እየቀለደብኝ ነው"

"ለምን?"

"የመኝታ ቤት ሎከሬ ላይ የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አባባል አለ፤ ሁሌ ስለ ነጋድራስ ገብረሕይወት ስለማወራቸው የቅፅል ስም አውጥተውልኝ እኮ ነው"

"ምን ከነጋድራስ ገብረሕይወት ጋር ዝምድና ቢጤ አላችሁ?"

"በጭራሽ"

"እና?"

"የታሪክ መፅሐፍትን ማንበብ በጣም እወዳለሁ:: የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ የአምባሳደር ባህሩ ዘውዴ እና የተከለፃዲቅ መኩሪያ ከፍተኛ አድናቂ ነኝ:: በተለይ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አሁን ድረስ የሚነበቡ ሁለት ምርጥ መጽሐፍትን ፅፈው ያለፉልን ሰው ናቸው:: የአጤ ምኒልክና ኢትዮጵያን በ1912 ዓ.ም እንዲሁም መንግስትና የሕዝብ አስተዳደርን በ1916 የፃፉ ናቸው፤ የትኛውን አንብበሃል?"

"ሲባል ሠምቻለሁ ግን አላነበብኩም"

"በል እኔ አውስህና አንብበህ ትመልሳለህ:: ሁለቱን መፅሐፍት ስታነብ ነው ሰውየው



Scanned by CamScanner

ምን ሲባል የሚገርም ጭንቅላት እንደነበረው የምትረዳው ራሱን በራሱ ያስተማረ ሰው ነበር"

"እንዴት?"

"ብዙዎች ታሪክ ፀሐፊያን በሚስማሙበት ንብረህይወት ባይከዳኝ የሞላት ግን በ33 ዓመታቸው ታመው ነበር። የሚገርመው ግን ገና ጨቅላ ብላቴና እያሉ ነበር ያለ አንዳች ፍርሃት በመርከብ ተደብቀው አውስትራሊያ በመሄድ በከፍተኛ ትጋት ህክምና በማጥናት ወደ አገራቸው የመጡት፤ ግን ከተመረቁበት ህክምና ይልቅ የፖለቲካ ነገር ላይ ትኩረት በማድረግ በተለይ በእንግሊዝ ቀኝ ግዛት ስር ወድቃ የነበረችውን ሱዳንን በሚገባ ከተመለከቱ በኋላ በነፃይቷ ኢትዮጵያ እና ሱዳን መሀከል የነበረውን የእድገት ልዩነት ሲመለከቱ ኢትዮጵያ በፍጥነት ታድግ ዘንድ ለኢትዮጵያ ለውጥ ጡሩንባ ለመንፋት የመጡ ምሁር ነበሩ። ሁለቱን ምርጥ መጽሐፍት አዘጋጅተዋል። በእርግጥ የተወሰኑ ምሁራን ለልጅ እያሱ ጭምራቸውን ያቆሉ ነበር ይላሉ፤ ግን ትልቁ ቁም ነገር ኢትዮጵያ በስልጣኔ እንድትራመድ ከፍተኛ መሻት ነበራቸው። መፅሐፋቸውን አሰጥከና አንብበህ ትፈርዳለህ። በተለይ ምንግዜም የማስታውሳቸውን ንግግሮች ልንገርህ?"

"በጣም ደስ ይለኛል! መፅሐፉን እንዳነበው ጉጉት ያሳደርከብኝ ገና ስለ ልጅነት ዘመን ውሳኔያቸው ስትነግረኝ ነው"

"እውነት ነው። ከዘመኑ በላይ የሆኑ አሳቢ እና ለውጥ ፈላጊ ነበሩ፡-

⇒ ስርዓት ከሌለው ሰፊ መንግስት ይልቅ በሕግ የምትኖር ትንሽ ከተማ ሙያ ትሠራለች (ትበልጣለች)!

⇒ አዕምሮ የሌለው ሕዝብ ሁሉ የእግዚአሔርን ቃል ሳያውቅ የእግዚአብሔር ጠበቃ ሊሆን ይወዳል!"

"በተለይ የኢትዮጵያን የታሪክ መፅሐፍት ስታነብ ወገንተኝነት እና ተጨባጭ መረጃ ያለመኖር እንዲሁም የመረጃ አሰባሰብ ድክመት ታያለህ፤ የትኛው ነው ትክክል እያልክ ትወዛገባለህ..

ይህን ጉዳይ በተመለከተ እርሳቸው እውነተኛ ታሪክ ለመፃፍ ሶስት ስጦታዎች ያስፈልጋሉ የሚል እምነት ነበራቸው

1. ተመልካች ልቦና (የተደረገውን ለማስታወቅ)

2. የማያዳላ አዕምሮ (በተደረገው ለመፍረድ)



Scanned by CamScanner

3. የጠራ የቋንቋ አገባብ (የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ..."

የነቀምቴው ተወላጅ አኔሲሞስ ችኩል ወጣት አይደለም:: እርጋታ የበዛበት ልጅ ነበር:: እሮምኛ ባልችልም በኦሮምኛ ሲያወራ ቅላፄው ደስ ይል ነበር... አኔሲሞስ የታሪክ ተማሪ አልነበረም:: የኢንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ነበር:: ስለ ታሪክ ግን ከታሪክ ተማሪዎች በላይ ያውቅ ነበር:: በጣም አንባቢ ነበር፤ ታዲያ አንድ መፅሐፍ ሳይሆን ለማነፃፀር ስለ አንድ ነገር በተለያዩ ሰዎች የተፃፈውን እንደሚያነብ ነግሮኛል፤ እኔም ተረድቻለሁ... ከንግግሩም ማወቅ ይቻላል:: አፍ ሲከፈት አዕምሮ ይታያል የሚለውን ያወኩት በእርሱ ነበር:: ጣፋጭ አንደበት ነበረው:: ስለ አፄ ቴዎድሮስ በሆነ አጋጣሚ ተነስቶ ካነበብኩት የበለጠ እርሱ በርካታ መፅሐፍትን ስላነበበ የተሻለ መረጃ እንዲሰጠኝ ጠየኩት

"አንድ ታሪክ አንብቤ ግራ ተጋባው" አልኩት

"ስለምን?"

"ስለ አፄ ቴዎድሮስ እና ከሚሲዮናዊያን ጋር የተያያዘ ነው"

"እሺ"

"አፄ ቴዎድሮስ ይበልጥ ወዳጅነት የነበራቸው ከየትኞቹ ሚሲዮናዊያን ጋር ነበር?"

"በእርግጥ አፄ ቴዎድሮስ የህዝቡን ተቀባይነት ለማግኘት አንድ ህዝብ አንድ ሀይማኖት የሚል ነገር ለማስረፅ በአዋጅ መልክ 'አቡነ ሰላም የሚሉትን ሃይማኖት ያልተቀበል ከላይ አንገቱ ከታች ባቱ ይቆረጣል' ሲሉ ሕዝቡ ሁሉ የኦርቶዶክስ ሀይማኖትን እንዲቀበል ቢያደርጉም ውስጣቸውን ስንመረምር ግን ሌላ ነበር"

"ማለት?"

"ሌላ ስልህ በኦርቶዶክስ አያምኑም ማለቴ ሳይሆን እየሀ አጠገባቸው በወቅቱ አገሪቱ ውስጥ በርካታ ሚሲዮናዊያን ነበሩ፤ በተለይ ካቶሊኮች እና ፕሮቴስታንቶች ነበሩ፤ ታዲያ ንጉሱ ትልቁ ግባቸው ሀይማኖት ሳይሆን የትኛው አገር የተሻለ ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስገባልኛል? ማን ትልቅ የነበረውን የኢትዮጵያን ህዝብ ወደ ትንሽነት ከተለወጠበት መልሶ በማንሳት ወደ ትልቅነት ያነሳታል? ባጠቃላይ ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን የሚለውን አመለካከታቸውን እውን ለማድረግ ማን ለአገሬ የተሻለ ቴክኖሎጂ አለው?? የሚል ነበር፤ ስለዚህ ከካቶሊኮች ይልቅ ምርጫቸውም ሆነ ቀልባቸው የነበረው ከፕሮቴስታንቶች ጋር ነበር"



Scanned by CamScanner

"እየሀ በወቅቱ የነበሩ ካቶሊኮች በብዛት ከፈረንሳይ አገር ጋር ይወግኑ ነበር፤ በዚያ ላይ ድብቅ ሊጀንዳ ነበራቸው፤ ባንፃሩ ፕሮቴስታንቶች ዋናው አላማቸው እምነታቸውን ማስፋፋት እንጂ አገርን ለመሰለል ሆነ ድብቅ አጀንዳ ከካቶሊኮች አንፃር ትንሽ ነበር ፤ በዚያ ላይ ፕሮቴስታንቶቹ ለውጥ ፈላጊ ነበሩ፤ በወቅቱ ለበርካቶች ሀበሻዊያን የእጅ ሙያዎችን (እናጢነት፣ ግንበኝነት፣ ዘመናዊ ቤት አሰራርን ፤ ሸንት ቤት አሰራርን) መሰል ያሳዩ ነበር:: የጠራ ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰዎች ጭምር ነበሩ፤ ከዚያ በተጨማሪ ኢንግሊዞች ነበሩ፤ ሌላው ምክንያት የአፄ ቴዎድሮስ የቅርብ ወዳጅ የነበሩት ቤልና ፕላውዲን የፕሮቴስታንት እምነት የሚያራምዱ ነበር... ያው ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በመጨረሻ በመድፍ ስሩ የተነሳ ለእስር በመዳረጋቸው ከኢንግሊዝ ጋር ቁርሾ በመግባት ለመቅደላ ጦርነት ቢያበቃቸውና ራሳቸውን ለመግደል ቢያበቃቸውም ለተወሰነ ጊዜያት ቢሆንም ተመቻምቸው ነበር!! ንጉሱ እኮ በአንድ ጀንበር ለውጥ የሚፈልጉ! ለኢትዮጵያ ትልቅ መሆን ከፍተኛ ህልም የነበራቸው ንጉስ ነበሩ፤ ግን በርካታ ጠላት በዚያው ልክ ነበረባቸው:: በርካታ ፈተና ነበረባቸው:: ስለዚህ ያገኘሁው መረጃ በብዛት የተዋጠ እና የማይነሳ ታሪክ ቢሆንም ሀቅ ላይ የተመሠረተ ታሪክ ነበር"

ከኦኔሲሞስ ጋር ብዙ ነገር አውርተን ነበር:: ኦኔሲሞስ ልንመረቅ አንድ ሳምንት ሲቀረን አካባቢ በደስታ ተሞልቶ አየሁት::

"ተደስተሃል" አልኩት::

"እጅግ በጣም!!"

"ተሳካ እንዴ?"

"ምኑ?"

"የደብዳቤው ጉዳይ"

"በግማሽ"

"ግማሽ ማለት?"

"ግልፁን ነገረችኝ"

"ምን?"

"ባትወደኝም አትጠላኝም"

"ምን?"

"ባትወደኝም አትጠላኝም" አለ በድጋሚ::

"ማለት?"



Scanned by CamScanner

"አወራን፡፡ ተማመንን፡፡ የምልህ ለእኔ ጥሩ ስሜት አላት ፤ ግን በእምነቷ እንደማትደራደር ነገረችኝ!! ቢቃ እንደምትወደኝ ማወቁ ለእኔ በቂ ነው፡፡ ሌላውን በቀስታ የምፈታው ይሆናል"

"እምነት ማለት?"

"ሀይማኖት"

ኦኔሲሞስን ስለ ሀይማኖቱ እስከዛሬ ጠይቄው አላውቅም፤ ሲጀመር "ዘር እና ሀይማኖትህ ምንድ ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን ጠይቄ አላውቅም፡፡ ለጓደኝነት ምርጫ ሰው መሆን እና ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻ ይበቃኝ ነበር... የዚያን ዕለት ግን መጠየቅ ግዴታ ሆነብኝ

"አንተ ምንድነህ? እሷስ ምንድነች?"

"ኦርቶዶክስ ነኝ፤ እርሷ ፕሮቴስታንት ናት"

"ስለዚህ?"

"ወደፊት የሚሆነውን አብረን እናያለን"

"ለጊዜ ተዋችሁት"

"ለጊዜ ሳይሆን ለእውነታ"

ከዩኒቨርሲቲ ከተመረቅን በኋላ በወሬ በወሬ ኦኔሲሞስ ሰባት ደብዳቤዎች ከፃፈላት "ፍቅረኛው ጋር" ሳይሆን ከሌላ ሴት ጋር የፍቅር ሀሁ እንደጀመሩ ሹክ ብለውኛል፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ምርቃት በኋላ ከኦኔሲሞስ ጋር ተለያይተናል፡፡ አሁን በእርግጠኝነት የደረሰበትን አላውቅም... ብቻ ባለበት ቀናው ይግጠመው፡፡ በሥነ ፅሁፍ እንድገፋበት ካደረጉኝ አነቃቂ ወጣቶች መሀከል ግን አንደኛው ነበር፤ ይህን የኦኔሲሞስ ታሪከን በጥያቄ ለመጨረስ ፈለኩ፡፡ መልሱን ለተደራሲያን ትቼዋለሁ፡፡

በጣም የምትወዱት ፍቅረኛችሁ ከእናንተ የተለየ ሀይማኖት የሚያራምድ ቢሆን ምን ታደርጉ ይሆን...?

ሀይማኖት የፍቅር መሰናክል መሆን ይገባዋልን?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ችግሩስ ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________ ::



Scanned by CamScanner

# እንደ ኮከብ

# ያበሩ!!

ሀገሬ ኢትዮጵያ በምንላት ሀብታችን በሰው ችግር የለባትም:: በየዘመናቱ ታሪካዊ ሰዎችን አፍርታለች! አፍርታችም ትኖራለች! ወደፊትም ታፈራለች...!! እያንዳንዱ ሰው የራሱን ታሪክ በዚች ምድር ላይ ይመግባል:: ጥቂቶች ደግሞ እንደ ኮከብ ነጥረው ለመውጣት ችለዋል:: እነ ከበደ ሚካኤል በኢትዮጵያ ታሪክ በስነፅሁፍ አሻራ ለማስቀመጥ... እነ አበበ ቢቂላ ኦሎምፒክ የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ ለማድረግ... እነ አበበ አረጋይ... እነ በላይ ዘለቀ... እነ አክሊሉ ለማ... እነ ነጋድራስ ገብረሕይወት... ብቻ ሊያሌዎች በኢትዮጵያ ምድር የራሳቸውን ታሪክ ሰርተው አልፈዋል... ወደ ፊትም ሌሎች እየተወለዱ ይሠራሉ... ታሪክ::

አንዳንዶች የህይወት ጥሪያቸው በሙዚቃ ይሆናል ፣ አንዳንዶች በጋዜጠኝነት ፣ አንዳንዶች በሥነፅሁፍ ፣ አንዳንዶች በፖለቲካው... አንዳንዶች በአስተማሪነት... አንዳንዶች በጋዜጠኝነት... አንዳንዶች በታሪክ ፀሐፊነት... አንዳንዶች በእግር ኳስ ... . አንዳንዶች በሰባኪነት... አንዳንዶች በወታደርነት... አንዳንዶች በሹፌርነት... ብቻ ሁሉም የልብ ትርታውን እያዳመጠ አንዳች ታሪክ ሰርቶ ወደ ማይቀረው ሞት ይጓዛል!!

በኢትዮጵያ ታሪክ አሻራቸውን አስቀምጠው ካለፉ ሰዎች አንደኛው ከ1905-1992 ዓ.ም ለ87 ዓመታት የኖሩት እጅግ ታታሪ፣ ከፍተኛ ዝና ያተረፉ ፣ ከንጉስ ኃይለስላሴ እስከ መንግስቱ ኃይለማርያም! ከመንግስቱ እስከ ጃሞኬኒያታ! ከጃሞኬኒያታ እስከ ዓለም አቀፍ!! በታታሪነታቸው የተመሠከረላቸው! የተጨበጨበላቸው ኢትዮጵያዊ ናቸው!! የልብ ትርታቸውን ተከትለው ታሪክ ሠርተው ያለፉ! በርካታ ሽልማቶችን በክብር የተቀበሉ...!!

እነሆ ስለ ጋሽ በቀለ በጥቂቱ ላወራ ነው:: በኢትዮጵያ የሆቴል ታሪኮች ታላቅ ታሪክ የሰሩ፣ እጅግ በርካታ ሆቴሎችን የገነቡ... ለሰራ ታላቅ ክብር የነበራቸው! ሠለቸኝ፣ ደከመኝ



Scanned by CamScanner

የማያውቁ ኢትዮጵያዊ!! ለሁላችንም አርአያ መሆን የሚችሉ ጠንካራ ኢትዮጵያዊ!! የኢትዮጵያ የሆቴሎች ታሪክ የማይረሳ ታሪክ ፅፈው ያለፉ ታታሪ ኢትዮጵያዊ...!!

እርግጥ ነው ዛሬ በመላው አገሪቱ በተለይም በሀዋሳ፣ በባህርዳር፣ በመቀሌ... በተለይ በመዲናችን አዲስ አበባ ላይ ቁጥራቸው የበዛ ከዜሮ ኮከብ እስከ አምስት ኮከብ ሆቴሎች እንጉዳ አሸን እየፈሉ ይገኛሉ...!!

እሰየው ያስብላል! ግና ያኔ አንዳች ነገር ባልነበረበት፣ ያኔ ሆቴል ብርቅ በነበረበት ጊዜ! በ1935 ዓ.ም ጋሽ በቀለ ሞላ በፊት ሲሰሩ የነበሩትን እንቁላልና ዶሮ ንግድ፣ የቡናና እህል ንግድ በማሻሻል ወደ ሆቴል ሙያ በመግባት "ሀ" ብለው ስራ ጀመሩ... ትልቅ ህልም ይዘው! ትልቅ አላማ ሰንቀው! ኢትዮጵያን ሆቴል በሆቴል ለማድረግ ወጥነው!!

እናስ?

እናም ከ1935 –1945 ዓ.ም ድረስ ብቻ በሞጆ፣ በመቂ፣ በዝዋይ፣ በላንጋኖ ፣ በሻሸመኔ፣ በናዝሬት፣ በሀዋሳ፣ በወላይታ፣ በሶዶ፣ በአርባምንጭ፣ በባሌሮቢ፣ በሞያሌ ፣ በደብረዘይት... ታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ የሆቴል ስራቸውን አጥለቀለቁት! በተለይ በአገር ውስጥ ቱሪስቶች ሆነ ከውጪ በመጡ ቱሪስቶች ዝነኛ የሆነው የላንጋኖ ሀይቅ ሆቴላቸው በብዙዎች በየዓመቱ ይጎበኛል! ያዝናናል!

የታታሪነታቸው ዝና እጅግ ገኖ ስለ ነበር በንጉስ ኃይለስላሴ ታላቅ አክብሮት ቤተመንግስት ድረስ ተጋበዙ

"ለምን በአርባምንጭ ሆቴል አትሰራም?" ተባሉ:: ጋሽ በቀለ በእሺታ የንጉሱን ሀሳብ በመቀበል በ1962 ዓ.ም ስምንተኛ ሆቴላቸውን አሁን ድረስ በውበቱ ብዙዎች የሚያደንቁትን ሆቴላቸውን በአርባ ምንጭ ሠሩ::

መስራት ያሸልማል! መስራት ያስከብራል! መስራት ለራስም ለሀገርም ለውጥ ያመጣልና... ጋሽ በቀለ እጅግ በርካታ ሽልማቶችን የማግኘታቸውን ያህል እና እጅግ በርካታ አድናቂዎችን በማፍራት 'እኔም እንደ በቀለ ሞላ መሆን እፈልጋለው!!' የሚሉ እንደነበሩ ሁሉ... አንዳንድ የህይወት ጥሪ ያልገባቸው እኩዮች ደግሞ ወደ ታታሪው ጋሽ በቀለ ጠጋ እያሉ

"በቀለ! አሁን ይህ ሁሉ ንብረት አለህ! ሀብታም ነህ! አይበቃህም? ሁላችንም እንሞታለን! ለመሆኑ ለየትኛው ዕድሜ ነው? ነገ አንድ ነገር ብትሆንስ? ለምሳሌ አገሬን አላየህም? ያሰበውን ሳያደርግ ቀረ አይደለም?" እያሉ የሚጎነትሉት ነበሩ... የጋሽ በቀለ ምላሽ



Scanned by CamScanner

ግን አጭር ነበረች

"እንዲህ የሚሉኝን ሰዎች ብሰማ ጥሮ ግሮ ደሮ የቆመ ሞተ እሞት ነበር! መስራት እኮ ክቡር ነው"

ታታሪው ጋሽ በቀለ በንጉስ ኃይለሰላሴ ብቻ አይደለም በፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ጭምር ትልቅ ክብር የተሰጣቸው ነበሩ፡፡ መንግስቱ ስልጣን ላይ ሲወጣ መላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ሁሉ ተወርሰው ነበር

"የበቀለን እንዳትነኩበት! በላቡ ጥሮ ያገኘው ነው!!"

የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ከፕሬዝዳንት መንግስቱ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ፕሬዝዳንት መንግስቱ በስራ ፍቅር እብድ ያሉትን ጋሽ በቀለን በክብር በማስጠራት ባሌ ከተማ ሆቴል እንዲከፍት ጠይቆ አሺታውን በመቀበል ቀድሞ መንግስት ከጀመረው ሆቴል በፍጥነት የጋሽ በቀለ ሞላ ሆቴል በመጠናቀቁ የተገረመው ፕሬዝዳንቱ "በቀለ የመንግስት ሆቴል ቀድሞ ተጀምሮ እንዴት የአንተ በፍጥነት ሊያልቅ ቻለ?" የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው ታታሪው ጋሽ በቀለ ያለ እንዳች ፍርሃት "ጌታዬ የመንግስት ሆቴል እኮ ባለቤት የለውም" የሚል ምላሽ መስጠት ችለው ነበር፡፡

ጋሽ በቀለ የሆቴሉን አሠራር ከሰለጠነው ዓለም ጋር ለማነፃፀር እና የተሻለ መረጃ ለማግኘት (ለማዘመን) በንጉስ ኃይለስላሴ አማካኝነት ኢጣሊያ፣ ጀርመን፣ ስዊዝ ፣ አሜሪካ በመሄድ መረጃ ይዘው በመምጣት ይበልጥ የሆቴሎቻቸውን ጥራት መጨመር ቀጠሉ፡፡

"በህይወቴ ማድረግ የምፈልገው መስራትን ነው፤ ለዚህም እግዚአብሔር በረከቱን ሰጥቶኛል! ጠንክሬ እሰራለሁ! ስራን አከብራለው" የሚሉት ታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ... ከብዙዎች አድናቆት ያተረፈላቸው ከታታሪነት እና ጠንካራ ሰራተኝነታቸው በተጨማሪ ማንኛውንም ጉዳያቸውን ለማሳካት እንደዘመኑ ስግብግብ ሀብታሞች አንድን ጉዳይ በፍጥነት ለማስፈፀም በጉቦ ወይም በሙስና መጠቀም የማይቃጣቸው መሆናቸውና ለሀቅ ዘብ የቆሙ መሆናቸው ጭምር ነበር!!

ብዙዎች ባለስልጣን ለመሆን ከፍተኛ ጥማት ባለባት ኢትዮጵያ ውስጥ! ብዙዎች ራሳቸውን ከፍ አስደርገው ለማስጠራት ሽኩቻ በሚገቡባት ኢትዮጵያ ውስጥ! ብዙዎች ትንሽ ነገር እንኳ ሠርተው የተራራ ያክል እንዲወራላቸው በሚጋደሉባት ኢትዮጵያ ውስጥ...!! ታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ ለሥራ እንጂ ለዝና፣ ክብር፣ እውቅና ትኩረት አልነበራቸውም



Scanned by CamScanner

... ለዚህ ጥሩ ምስክር ማንሳት ይቻላል፡፡

"ለስራዎት ከብር 'ቀኛዝማች' የሚል ማዕረግ እንዲሰጡት ሲጠየቁ ለምን እንቢ አሉ?" ተብለው ሲጠየቁ ምላሻቸው ይህ ነበር

"እውነት ነው! ቀኛዝማች እንበልህ ብለውኝ ነበር፤ ቀኛዝማች ወጥ አምጣ፤ ቀኛዝማች አሮስቶ አምጣ፣ ቀኛዝማች መኮረኒ አምጣ... መባል ኢያምርምና ለሙን ከማበላሸት ኒሻን ይሰጠኝ ብዬ ኒሻን ተሰጠኝ፡፡ እኔ እንዲህ ያለ ነገር ጨርሶ አልፈልግም!!"

ታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ ሊነገርላቸው የሚገባ ብዙ ታሪክ አላቸው፡፡ ስለታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ ሙሉ አስገራሚ እና አነቃቂ እውነተኛ ታሪካቸውን ማንበብ የምትፈልጉ (በቀለ ሞላ የትጋት አርአያ 1905-1992 የህይወት ታሪክና ትውስታዎች) መፅሐፋቸውን እንድታነቡ በመጋበዝ በኢትዮጵያዊ የጨዋነት ባህላችን ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልን እያልኩኝ ስለታታሪው ጋሽ በቀለ ሞላ ያነሳዋትን ቁንፅል ታሪክ ለልጆቻቸው ዘወትር ይሉት በነበረው ንግግራቸው መጨረስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

... እንደ ጋሽ በቀለ ሞላ ያሉ ታታሪ ሰዎችን ኢትዮጵያችን አትጣ!! እንደ ጋሽ በቀለ ሞላ ያሉ ታታሪ ሰዎችን የወለዱ እናቶች ክብር ይድረሳቸው...!!

"የእውቀትና የሞያ ባለቤት እንጂ የንብረት ባለቤት ላደርጋችሁ አልችልም!! ንብረት ጠፊ ነው፡፡ የሙያ ባለቤትነታችሁን ግን ማንም ሊወስድባችሁ አይችልም!!"

(ለመሆኑ የአባታቸውን ህልም ልጆቻቸው አሳክተው ይሆን ...???)

ኢትዮጵያችን በክብር ትኑር!!

ሙስና የማይወዱ ባለሃብቶች ይብዙላት...

አሜን፡፡



Scanned by CamScanner

# ጂሀድ አውጃለው!!

ጅማ ያገኘሁት የባጃጅ ሹፌር አስገርሞኛል፡፡ ወጣት ነው፡፡ አ የሚያምር ፀጉር አለው… ክልስ ቢጤም ይመስላል… የጅማ ከተማን በሚገባ በባጃጅ እንዲያሳየኝ ነገርኩት… ሂሳብም ሰጠሁት…

ጨዋታ ጀመርን፡፡

"ይህ ዩኒቨርሲቲው ነው… ይህ የጅማ ትልቁ እስር ቤት ነው… ከየት ነው የመጣኸው?"

"ሸገር" አልኩት፡፡

"ሸገር የት ነበር"

"አዲስ አበባ…"

"አ… የድሮ ስሟ ነው?"

"አንዳንዶች አሁንም ሸገር እያሉ ነው የሚጠሯት፡፡ እስከዛሬ አንተ አዲስ አበባን አላየሃትም?"

"አላየዋትም! ማየትም አልፈልግም"

"ለምን?"

"እባክህ ህይወቴ የተበላሸው በአንዲት የአዲስ አበባ ሴት የተነሳ ነው! አላህ ይመስገን አሁን ግን በራሴ ላይ ለውጥ አድርጌያለው"

"ማወቅ እችላለው?"

"ጅማ ዩኒቨርሲቲ የምትማር የአዲስ አበባ ልጅ ነበረች… ትዝታ ትባላለች… 60ሺ ብር ጨርሼባታለው"

"60 ሺ ብር?"

"አዎ"

"ምን ተፈጠረ?"

"እርግጥ እሷ ጥፋት የለባትም እኔ ነኝ የማትሆነኝን ሴት አፍቅሬ የከሰርኩት"

"በምን ተዋወቃችሁ?"



Scanned by CamScanner

"ሴንትራል ጅማ እና ሰይፍ ሆቴልን አይታቸዋለ?"

"አዎ"

"እዛ እመላልሳት ነበር"

"የተማሪ ሸሌ ነበረች?"

"በምን አወክ?"

"ማታ ያደርኩት ሰይፍ ነበር አስተናጋጁ በዝርዝር ነግሮኛል፤ በርካታ ተማሪዎች የሚቀመጡት እዛ እንደሆነ... ወዘተ"

"ልክ ነው"

"እና?"

"ቢቃ ማታ ማታ በተፈለገች ቁጥር ሳመላልሳት ሳላስበው ፍቅር ያዘኝ... እሷን ለመማረክ ማውጣት ጀመርኩ... ከስሬ ቀረው"

"አፈቀርካት?"

"ቀላል"

"ጨዋ እንዳልሆነች እያወክ?"

"እንዴት እንደገባሁበት እኔ ራሱ አላውቅም... ብቻ ከልቤ አፍቅሬያት ነበር"

"ለስንት ጊዜ"

"ሁለት ዓመት"

"ነገርካት?"

"አልነገርኳትም... ትረዳኛለች እያልኩ መጋበዝ እና ማዝናናት ብቻ ነበር... እንዳላጣት ፈርቼ ዝምብዬ ነበር... በመሀከል እርግዛ ከጅማ ጠፋች... ሁለት ዓመት ሆነኝ አሁን ፍቅሬ በርዶልኛል... የልጅቷን መጨረሻ ግን አላውቅም!!"

"ያሳዝናል"

"በጣም"

"ቢያንስ ብትነግራት ይወጣልህ ነበር"

"ዳር ዳር እማ እል ነበር ግን ትመክረኝ ነበር! ትቆጣኝም ነበር! የሚገርመው እኮ ጥሩ ልጅም ናት!! በነገራችን ላይ ብወድሽስ ስላት! NO አንተ ጥሩ ወጣት ነህ እንደኔ ያለች የተጨማለቀች ሴት አትሆንህም! ትለኛለች ውድ ቤት ስጋብዛት ... አንተ ልጅ የዩኒቨርሲቲ



Scanned by CamScanner

ተማሪን አምነህ ገንዘብ አታውጣ! ገንዘብህን ያዝ አድርገህ ራስህን ብትለውጥ ይሻልሃል ትለኝ ነበር... ብቻ በራሴ ላይ ጂሀድ አውጄ ራሴን ለወጥኩ!!"

"ጂሀድ አውጂ??"

"አትደንግጥ! ጂሀድ ሁለት ትርጉም አለው! ብዙዎች የሚያውቁት የተሳሳተውን ፍቺ ነው:: ጦርነት ፤ በቀል! ግድያ! አክራሪነት! የክርስቲያን ጠላት የሚል የተሳሳቱ ፍቺዎችን ነው ፤ ግን ትክክለኛው የጂሀድ ፍቺ ቅዱስ ጦርነት ማለት ሲሆን ፍቺው ከራስ ጋር መግጠም! ከክፉ ዝንባሌ ጋር መግጠም! ከአሉታዊ አስተሳሰብ ጋር መግጠም! ራስን መቆጣጠር! ራስን መግዛት! ራስን ለመሆን መታገል ማለት ነው ለዚህም ነው ነብዩ ሙሀመድ ትልቁ ጂሃድ ከራስ ጋር መፋለም ነው (The Greatest Jihad is the war within oneself) ያሉት!! ስለዚህ የዓለም ትልቁ ጦርነት ከራስ ጋር የሚደረግ ጦርነት ነው!! ራሱን አንዳሸነፈ ሰው ማንም አሸናፊ የለም!! እናም በራሴ ላይ ጂሀድ አውጂ! ወደ ራሴ ተመለስኩ! አሁን በጣም ደስተኛ ነኝ! አንዳንዴ ግን አስታውሳታለው! ትዝታ ራሱን የቻለ ሸክም ነው! እንዳልከው ግን የሚቆጨኝ ውስጤ ያለውን ፍቅር ባለመናገሬ ነው"

"አሁንም ማታ ማታ ተማሪዎችን ታመላልሳለህ?"

"ባላመላልስ ደስ ይለኝ ነበር ፤ ግን ስራ ነው ምን ታደርገዋለህ?"

"ማለቴ የሴቶች ስልክ አንተ ጋርም አለ?"

"አለ!"

"የስንት ?"

"ወደ ዘጠኝ..."

"አንተ ከተማሪ ጋር አድረህ ታውቃለህ?"

"በጭራሽ! መቼም አላደርገውም! በጣም እንቃቸዋለው! በዚያ ላይ ከበፊት ጥፋቴ ብዙ ለመማር በራሴ ላይ ጂሀድ አውጃለው!! ይህን የባጃጅ ስራ ለሰባት ወር ብሰራ ነው ፤ አሁን በቂ ገንዘብ ስላጠራቀምኩ ወደ ንግድ እገባለሁ"

ከወጣቱ አሪፍ የጅማ የባጃጅ ሹፌር ጋር ብዙ ተጨዋውተን ነበር... ጅማን በሚገባ አሳይቶኛል! ከምንም በላይ ስለ "ጂሀድ" ትክክለኛ ፍቺ ነግሮኛል... ከእያንዳንዱ ሰው የምንማረው አንዳች ቁም ነገር አለ:: ይቺን ጢኖ ታሪክ ከወጣቱ ንግግር በወሰድኩት መዝጊቱ ተገቢ መሰለኝ::

"የዓለም ትልቁ ጦርነት ከራስ ጋር የሚደረግ ጦርነት ነው!!"



Scanned by CamScanner

# እኛ እና ንግድ

"ከመጠጥ እንጀምር?"

"ደስ እንዳለህ"

"የአልኮል መጠጥ እንደ አባብ ይናደፋል የሚል መርህ ትከተላለህ አሉኝ"

"ትክክል"

"እስከ ዛሬ ጠጥተህ አታውቅም?"

"በጭራሽ"

"ስንት ዓመት ሆነህ?"

"27 ሆነኝ"

"የገረመኝ ነገር ለሁለት ዓመት ማታ ማታ የመጠጥ ቀጂ ነበርክ ወይም ባርማንነት ትሠራ ነበር?"

"ትክክል"

"ትልቅ ሆቴል?"

"የተጋነነ አይደለም ግን ብዙ ደንበኛ ያሉት ሆቴል ነበር"

"እና ሁለት ዓመት ሙሉ ባርማን ሆነህ አንድም ቀን አልኮል አልቀመስኩም እያልከኝ ነው?"

"አልቀመስኩም! ወደፊትም አልቀምስም"

"መጠጥ መጠጣት ሀጢያት ነው የሚሉ እንዳሉ ሁሉ እንዲሁም ሳይበዛ መጠጣት ለጤናም አሪፍ ነው የሚሉ አሉ?"

"አውቃለው"

"አንተ ከሁለቱም የለህበትም?"

"ስለሰዎች አመለካከት ሆነ ሳይንስ ስለ አልኮል መጠጥ ስለሚለው ብዙ ትኩረት የለኝም:: የእኔ የግል ፍልስፍና አለመጠጣት የሚል ነው:: እርግጥ እንዳልከው ገንዘብ ማግኘት ስለነበረብኝ መስራት ነበረብኝ:: የግድ መጠጣት ግን አለብኝ ማለት አይደለም"

"ፈተና እንዴት የለውም ብዬ ነው"



Scanned by CamScanner

"ፈተና እማ አለው! ለውሳኔህ ፅኑ ከሆንክ ግን ችግር የለውም:: ብዙ ጊዜ ለችግር የምትዳረገው እኮ ውሳኔ ሳይኖርህ ሲቀር ነው ወይም ወላዋይ ከሆንክ ነው"

"አንተ ወላዋይ አይደለህም?"

"በጭራሽ"

"ወላዋይ ሴቶች የሚል መፅሐፍ አንብበሃል?"

"ዩኒቨርሲቲ እያለሁ"

"አሪፍ መፅሐፍ ነው?"

"ሥነልቦና? ስለሆነ ጥሩ ነው:: በተለይ ለሴቶች ጥሩ ነው"

"ወደ ተነሳንበት ልመለስ?"

"እሺ"

"መጀመሪያ ወደ ትምህርት እንሂድ"

"ይቻላል"

"ተመርቀሃል?"

"በሚገባ"

"ከየት?"

"ከዲላ ዩኒቨርሲቲ"

"በምን ነበር?"

"አስተማሪነት"

"የምን"

"የኢትዮጵያ ተማሪዎች በሚቦኩት"

"ምን?"

"በሂሳብ"

"አስተማሪ የመሆን ህልም ነበረህ?"

"በጭራሽ"

"እና?"

"አራተኛ ምርጫዬ ነበር:: የመጀመሪያ ምርጫዬ ፍልስፍና መማር ነበር:: አባቴ ጳጥሮብኝ ነበር አልተሳካልኝም፤ አራተኛ ምርጫዬ ደረሰኝ፤ ተመረኩኝ"



Scanned by CamScanner

"ቆጥሮብኝ ማለት?"

"አባቴ ሆነ መላው ቤተሰብ ፍልስፍና እንዳጠና ሆነ በፍልስፍና እንድመረቅ በጭራሽ አይፈልጉም ነበር፤ ዋናው ምክንያት በፍልስፍና ስራ አታገኝበትም የሚል ምክንያት ነበር"

"ብዙ ቤተሰቦች በልጆቻቸው ምርጫ ይገባሉ! ጥሩ ነው? ጥሩ አይደለም?"

"በጣም አስቸጋሪ ጥያቄ ነው"

"ምክንያት?"

"ወላጆች ሆኑ ቤተሰቦች ልክ የሚሆኑበት አጋጣሚ አለ፤ እንዲሁም ልክ የማይሆኑበት አጋጣሚም አለ:: ለምሳሌ አብዛኛው ተማሪ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ምን ማጥናት እንዳለበት አያውቅም! ህልም የለውም! የተወሰነ መድረሻ የለውም! በዚህ ጊዜ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ግዴታ ነው:: ይህን አጥና! ይህን አታጥና! ማለት ይጠበቅባቸዋል:: በሌላ በኩል አንተ ዩኒቨርሲቲ ገብተህ ምን ማጥናት ሆነ ምን መሆን እንደምትፈልግ በእርግጠኝነት የምታውቅ ከሆነ በአንተ ምርጫ ቤተሰቦችህ ጣልቃ ባይገቡ ጥሩ ነው:: እኛ አገር ያለው ትልቅ ችግር እኔ እንዳየሁት አብዛኛው ተማሪ በግልፅ የተቀመጠ አላማ የለውም!! ያ ነገር ይመስለኛል ቤተሰቦች አምባገነን እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ፤ እኔ ልጅ ስወልድ በእርግጠኝነት በምርጫው አልገባም:: ለልጄ አባትም ጥሩ ጓደኛም መሆን ነው የምፈልገው፤ ከዚያ እንደ ጓደኛ በምርጫው ላይ የምክር እና የመረጃ አገልግሎት እሰጠዋለሁ እንጂ በግድ ይህን አጥና በማለት በልጄ ህይወት ላይ ክችች አልልም"

"ስንት ዓመት አስተማርክ?"

"ሰሶስት ዓመት ብቻ"

"ከዚያ?"

"እኔ ከልጅነት ጀምሮ ተቀጥሮ መስራት የሚል ህልም አልነበረኝም! ትንሽም ነገር ብትሆን የራሴን ነገር መስራት ነበር የምፈልገው፤ ስለዚህ ሶስት ዓመት አስተማርኩ! ባለኝ ትርፍ ሰዓት የግል የሀብታም ልጆችን አስጠናለው... መጠጥ ቀጂነት እሰራ ነበር... የምፈልገውን የገንዘብ መጠን ሳገኝ ወደ ህልሜ ተመለስኩ"

"ምን ነበር?"

"ከፍልስፍና በተጨማሪ ንግድ ደስ ይለኛል:: አንድ የማውቀው ልጅ ነበር በእርሱ እርዳታ ወደ ንግዱ ገባሁ:: አራት ዓመት ሆነኝ:: አሁን የተለያዩ ቦታዎች ሰባት ሱቆች አሉኝ::



Scanned by CamScanner

ንግድ በጣም አሪፍ ነው፡፡ በተጨማሪ አሁንም ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት እና እውቀትን ማካፈል ደስ ስለሚለኝ ተማሪዎችን እስጠናለው!!"

"ስንት ሰራተኞች አሉህ ማለት ነው?"

"14 ደርሰዋል"

"አ! ለ14 ሰዎች የስራ እድል ከፍተሃል ማለት ነው?"

"ገና እቀጥላለው!!"

"ኑሮ ውድ ነው ይባላል፤ ግን ብዙ የልብስ ቡቲኮች በየጊዜው ይከፈታሉ! በዚያው ልክ ይሸመታል!"

"ጥሩ ታዝበሃል?"

"ምክንያቱ ምንድ ነው?"

"ውስጥህ ባዶ ሲሆን በአልባሳት ለመድመቅ ጥረት ታደርጋለህ"

"እ"

"መሳደቤ ግን አይደለም!"

"እረዳሃለው! ስለ አልባሳት ዋጋ እናውራ?"

"እናውራ"

"ከአንድ ዕቃ ስንት ታተርፋለህ? ሳትዋሽ?"

"በቅድሚያ ሁለት ዓይነት የዋጋ አተማመን አለ፡፡ ህገወጥ እና ህጋዊ አተማመን"


"በዝርዝር አስረዳኝ"

"እኛ ሀገር ያለው የዋጋ አተማመን ሁሉም ነጋዴ ለማለት ቢያስቸግረኝም ለሁሉም ትንሽ የቀራቸው ነጋዴዎች በሙሉ የዋጋ አተማመናቸው ህገወጥ ነው፡፡ ከአንድ ዕቃ ላይ 60% ...70%...80%... 90%...100% ...200%...300% ሁሉ የሚያተርፉ ነጋዴዎች አሉ፡፡ በጣም ታዝንባቸዋለህ!! አብዛኛው ነጋዴ የዋጋ ተመን የሚያወጣው የቤት ኪራይን፣ የሰራተኛ ወጪን ፣ የትራንስፖርትን ፣ የግብርን ወዘተ አካቶ ነው አንድ ዕቃ ላይ ዋጋ የሚያወጣው፣ ይህ ወንጀልም ነው፤ ይህ ሞራል አልባነትም ነው፡፡ ይህ አንዱ የስግብግብነት መገለጫም ነው፡፡ በአንድ ቀን ሀብታም ለመሆን ከንቱ እቅድ ነው!! ለምሳሌ ላስረዳህ አንድ ዕቃ በሀያ ብር ገዛህ እንበል፡፡ ይህን ዕቃ ስትገዛ ምን ያህል ነው ከሀያ ብር ዕቃ ላይ ማትረፍ ያለብህ? አራት ሱቆች



Scanned by CamScanner

ብትገባ አራቱም ጋር የተለያየ ዋጋ ሲሸጡ ታገኛቸዋለህ:: አንዱ ሀያ ብር የገዛውን ዕቃ




ይሸጣል!! 20 ገዝቶ 25 የሸጠው ቀና ነጋዴ ነው:: 20 ብር ገዝቶ 40 የሸጠው ጅብ ነው:: 20 ገዝቶ 50 የሸጠው አሣማ ነው:: 20 ብር ገዝቶ 100 ብር የሸጠው የብር አምላኪ ነው:: ይህ እንግዲህ ህገወጥ ነጋዴነትን ቀላል ማሳያ ምሳሌ ነው"


"ወደ ህጋዊ ነጋዴዎች እናምራ?"

"በሰለጠኑት አገራት ቅን ስለሆኑ፣ ደንበኛ ንጉስ ነው የሚለውን ደንብ ከልባቸው ስለሚያከብሩ፣ ሆዳም ስላልሆኑ በተለይ ከአንድ ዕቃ ላይ ብቻ ሳይሆን ከብዛት ማትረፍ ስለሚፈልጉ በአንድ ዕቃ ላይ የተቀመጠው የትርፍ መጠን ከ12%- 22% ብቻ ነው:: ለቅንጦት ዕቃዎች የተቀመጠው የትርፍ መጠን ደግሞ ከ 56% - 210% ነው:: ከዚህ ፐርሰንት በላይ አሸጣለሁ ቢል የሸማቾች ህብረት ስላላቸው በህብረት ስለሚያምፁበት የሚገዛው የለም!! በዚህ መሠረት እስቲ በ20 ብር የተገዛ ዕቃ በህጋዊ መንገድ ዝቅተኛው እና ከፍተኛው ዋጋ ስንት ሊሆን እንደሚችል እንመልከት"



Scanned by CamScanner

"እንዳልኩህ ከአንድ ዕቃ ላይ ትርፋቸው ከ12% – 22% ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሠረት አንድ በሀያ ብር የተገዛ ዕቃ በስንት ብር ሊሸጥ እንደሚችል እንመልከት፡፡




ይህን ያህል ትርፍ ካንዷት ዕቃ ላይ ታገኛለህ፡፡ ሁለተኛ ምሳሌ እንይ፤ ለምሳሌ አንድ በ10,000 ሺ ብር የተገዛ ዕቃ ላይ ስንት ታተርፋለህ?

በ12% = $\frac{12 \times 10,000}{100}$ = 1,200 ብር ትርፍ

በ15%= 1,500 ብር ትርፍ

በ18%= 1,800 ብር ትርፍ

በ22%= 2,100 ብር ትርፍ ልታገኝበት ትችላለህ! እኛ አገር ያለው እውነታ ፍፁም ከዚህ የራቀ እና ስግብግብነት የተሞላበት አሠራር ነው፡፡ ነጋዴዎቻችን እያንዳንዱን ነገር የሚሸጡት ለቅንጦት ዕቃዎች በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት



Scanned by CamScanner

ነው:: የምልህ ነፃ ገበያ ቢባልም እያንዳንዱ ነገር እኮ ገደብ እና ያልተፃፈለት ህግ አለው! ህሊና የሚባል መኖርም አለበት!!"

"አንተስ?"

"ሀቁን ለመናገር የውጪውን ከ12%-22% ብቻ አተገብራለሁ አልልህም፤ ግን የፈለገ ቢሆን ከ35% በላይ አትርፌ አላውቅም:: ዋጋው ተለጥፎበት ስለሚቀመጥ ሰራተኞቼም እየጨመሩ አያጭበረብሩም:: የሚገርምህ ከእኔ እየገዙ 100% አትርፈው የሚሸጡ ነጋዴዎች ራሱ በርካቶች አሉ:: የምልህ የእኛ አገር የንግድ ስርዓት ገና አልተሰራበትም! ብዙ መሻሻል የሚቀረው ነገር አለው"

"ግን እኮ በዚያው ልክ ሳይከራከሩ የሚገዙም ብዙ ናቸው!!"

"ልክ ነህ!! ለገንዘብ ክብር የሚኖርህ እኮ ገንዘብን በምታገኝበት መልኩ ይወሰናል:: ላብህን ጠብ አድርገህ! የወር ደመወዝ ጠብቀህ የምታገኝ ከሆነ እና በሙስና ሆነ ከውጪ ያልሠራህበትን ገንዘብ የምታገኝ ከሆነ እኩል ለገንዘብ ክብር የለህም:: ምሳሌ ልስጥህ ዲላ ዩኒቨርሲቲ እያለሁ አንድ የሀብታም ልጅ ነበር:: አባቱ ለአንድ ወር 3200 ብር ይልኩለት ነበር:: ለእኔ አባቴ በአንድ ወር የሚልኩልኝ 150 ብር ብቻ ነበረች:: ይህ ተማሪ ተመርቆ አስተማሪ ሆነ:: ከአስራ አምስት ቀናት በላይ አልሰራም:: በወር 3200 ብር ማጥፋት የለመደ ልጅ እንዴት ብሎ 1800 ብር ደሞዝተኛ ሆኖ መኖር ይችላል? ሴተኛ አዳሪዎች ከችግራቸው (ወሲብ ንግዳቸው) እንዳይወጡ ከሚያስራቸው ነገር አንዱ ይህ ነው:: በአንድ ቀን እስከ 1000 ሺ ብር ሊያገኙ ይችላሉ! ታዲያ እንዴት ብለው የሁለት ሺ ብር ደሞዝተኛ ለመሆን ያስባሉ? ባጠቃላይ ለገንዘብ ያለህ ክብር የሚወሰነው ያን ገንዘብ ለማግኘት ባወጣኸው ጉልበት እና ጊዜ መጠን ይሆናል:: በቀላሉ የምታገኘው ከሆነ በቀላሉ ታጠፋዋለህ:: ቅድም እንዳልኩህ በሥነልቦና የበታችነት የሚሰማህ እና ውስጥህ ባዶ ጭንቅላት ከሆነ በልብስ ለመድመቅ ትጥራለህ፤ ይህን ስልህ የሚዘንጥ ሁሉ ጭንቅላቱ ባዶ ነው እያልኩህ እንዳልሆነ መቼም ትገነዘብልኛለህ"

"እገነዘብልሃለሁ!! ከሴትና ወንድ ማን ይገዛል?"

"እኔ የሁለቱንም አልባሳት እሸጣለሁ! አንተም አይተሃል... ሴቶች በጣም መግዛት ይወዳሉ! መከራከር ላይም ጎበዝ ናቸው:: ወንዶች መከራከር ከብራቸውን የሚቀንስ ስለሚመስላቸው አይከራከሩም:: ጅንን ለማለት ይሞክራሉ፤ በተለይ አንድ ወንድ ከሴት ጋር



Scanned by CamScanner

ከመጣ ብከራከር ገብጋባ ነው ብላ ትንቀኛለች ከሚል ያለው መስሎ ለመታየት ካላቸው ትልቅ ከንቱ ጉጉት በመነጨ ሳይከራከሩ በውስጣቸው ቅጥል እያሉ ይገዛሉ! ይህ የሚያበሳጨኝ የወንዶች እጉል እና ደካማ ባህሪያቸው ነው!! ይቺን የእኛን አገር ወንዶች ድክመት ሴቶቹም ጠንቅቀው ስለሚያውቁ አንድን ወንድ እያንከረፈፉ ይመጡና ኪሱን አራቁተውት ይወጣሉ"

"ቺክ አለችህ?"

"ከቺክም አልፋ ሚስት ለመሆን እየሞከረች ናት"

"እንዴት ናት ዕቃ መግዛት ላይ?"

"አሪፍ ናት! እንደ ብዙዎቹ ሴቶች ኮተት አታበዛም፡፡ በብዛት እኮ ሴቶች ገዝተው ያስቀምጣሉ እንጂ አይለብሱትም!! ፋሽን ምናምን የሚሉት ጉድ ስላላቸው ያቺ ወቅት ስታልፍ የገዙትን ዕቃ መልሰው የማያዩት በርካቶች ናቸው፡፡ እኔ አንዳንዴ ሴቶች ሁለት ሆነው ይመጡና የ3000 ሺ ፣ የ4000 ሺ ፣ የ7000 ሺ ብር ዕቃ ገዝተው ሲሄዱ እውነቴን ነው የምልህ እንደ ነጋዴነቴ ከመደሰት ይልቅ እደነግጣለው!! ይሄ ሁሉ ምን ይሠራላቸዋል? እላለው!! እንዳልኩህ የእኔ ቺክ በዚህ አትታማም! በጣም የምወድላት ያላትን በንፅህና ትጠቀማለች፡፤ ከልብስ ይልቅ የሚነበቡ ነገሮች መግዛት ትወዳለች"

"ማን ጠበሰ?"

"ማለት?"

"አንተ ወይስ እሷ?"

"እ... እሷ ነች!!"

"የት?"

"ልብስ ልትገዛ መጥታ"

"ልብስ ቤትህ ሚስትም ሰጠህ ማለት ነዋ?"

"ህይወት እንደዚህ ነው! ሚስትህን በምን አጋጣሚ እንደምታገኛት አይታወቅም"

"አጋጣሚውን ንገረኛ"

"ያጋጣሚ ሆኖ ገና የመጀመሪያ ልብስ ቤቴን የከፈትኩ ጊዜ ነበር፡፡ አየህ ያኔ ገና ጀማሪ ስለነበርኩ እና በቂ ገንዘብ ስለሌለኝ ለብቻዬ ነበር የምሠራው እና ፍቅረኛዬ ድንገት የእኔ ቡቲክ ገባችና 'Hi' ብላ ሠላምታ በመስጠት 'ለወንድ የሚሆን ጥሩ ሱሪ አለህ ወይ?'



Scanned by CamScanner

አለችኝ::"

'ስንት ቁጥር ነው?'

'32'

'ጂንስ? የጨርቅ ሱሪ? ካኪ...?'

'ጂንስ ይወዳል' ስትለኝ አሪፍ አሪፍ ጂንሶች የተቀመጡበት ቦታ አሳየዋት:: ብዙ ስታማርጥ ቆየችና አንደኛውን ጂንስ በማንሳት በትኩረት የጂንሱን ማርክ በሚገባ ስታይ ቆየችና

'ይህ ጂንስ ዋጋው 320 ብር ብቻ ነው?'

'አዎ'

'እውነት?'

'አዎ'

'ወይኔ!'

'ምነው?'

'አንተ ምን አይነት ሌባ ነው! በቀደም ፒያሣ አንዱ ቤት ገብቼ 660 ብር ነው ያለኝ:: ገንዘብ ሲኖረኝ እመለሳላው ብዬው እኮ ነው!'

'ሌላ አይነት ጂንስ እንዳይሆን?'

'በጭራሽ ማርኩ ራሱ ነው'

'ዝም አልኳት:: በግርምት እየተመለከተችኝ:-

'አንተ ጥሩ ነጋዴ ነህ ማለት ነው?' አለች

'እንዴት?'

'ይህን ማርክ ሌላ ቦታም ጠይቄ 500 ብር ብለውኛል'

'ያው ከቦታ ቦታ ይለያያል'

የዚያን ቀን ገዝታኝ ሄደች:: በስንተኛው ጊዜ ከአንድ ወጣት ወንድ ጋር ተመልሳ መጣች:: ወንዱ ከእኔ የገዛችውን ጂንስ ሱሪ ነበር ያደረገው::

'አያምርበትም?' አለችኝ::

'በጣም'

'እዚህ ሁሉ ነገር ርካሽ ነው! ሌላ ጊዜ ከእርሱ ግዛ! ለጓደኞችህም ቤቱን አሳያቸው!



Scanned by CamScanner

ለልጇ አለችው:: መልካቸው በጣም ይመሳሰል ነበር.. በተለይ አንድ አይነት አፍንጫ ነበራቸው"

"ወንድምሽ ነው?" አልኳት

"አዎ"

"ትመሳሰላላችሁ! በተለይ አፍንጫችሁ" አልኳት:: በዚህ መልኩ ይበልጥ ተዋወቅን:: ደንበኛዬ ሆነች:: ከዓመት በኋላ የፍቅር ጥያቄ አቀረበችልኝ:: በእሺታ ተቀበልኩ... አለቀ:: እርሷም የመንግስት ስራ አላት... እኔንም ብዙ ሱቆች በተጨማሪ እንድከፍት እና ንግዱን ይበልጥ እንዳሳድገው ቀንደኛ አማካሪዬ ነች.. ብቻ ተስማምተናል:: ፈጣሪ ይመስገን አሪፍ አጋር ነው የሰጠኝ::

"ትወዳታለህ?"

"አፈቅራታለሁ!!"

"የምታደንቅላት?"

"ስራ ትወዳለች:: መጨቃጨቅ አትወድም:: ችግር ፈቺ ጭንቅላት አላት! ራሷንም እኔንም ታከብራለች! ትልቅ ህልመኛ እንድሆን አድርጋኛለች! ትንሽ ህልም ማለም ምንም ህልም ከሌለው ሰው እኩል ነው የሚል መርህ አላት! ወደፊት በተመጣጣኝ ዋጋ ዕቃ የሚገኝባቸው እጅግ በርካታ የንግድ ቤቶችን ለመክፈት እቅድ እና ህልም እንዲኖረኝ አድርጋኛለች ብቻ ፤ እርሷን የመሰለች አጋር በህይወቴ በማግኘቴ እድለኛ ነኝ"

"ማን ነው ስሟ?"

"ቤዛዊት አለማየሁ"

"ምን አይነት አጋጣሚ ነው?"

"ምኑ?"

"የአንተ ስም መስፍን አለማየሁ እኮ ነው"

"እኔም ስገረም ነበር"

"ከንግዱ ሳንወጣ አንዳንዴ የምንሰማቸው ነገሮች በጣም ያሳዝናሉ! እውነት እነዚህ ኢትዮጵያዊያን ናቸው?? የሚል ጥያቄ እንድታነሳ የሚያደርጉ ሁሉ አሉ:: ለምሳሌ በቅርቡ ከበርበሬ ጋር ሸክላ አደባልቆ በመፍጨት ሲሸጡ መርካቶ በጥቆማ ተይዘዋል! የጅብ ስጋ ከበሬ ጋር አደባልቀው ሲሸጡ ተይዘዋል.. ዘመኑ ያለፈበት ዘይት ሆነ መድኃኒት ቀኑን



Scanned by CamScanner

እየፋቁ ሌላ ቀን እየኤጠፉበት የሚሸጡም በርካቶች ናቸው... ይህን መሰል አሳዛኝ ነገር ስትሰማ ምን ይሰማሃል?"

"እኔ ገንዘብ የሚያመልክ ሰው ንግድ ውስጥ ሲገባ ይህን መሰል ዘግናኝ ነገር ማድረጉ አይቀርም:: የገንዘብ ፍቅር እኮ ከባድ ነው:: መፅሐፍ ቅዱስ ላይ እኮ ምንድነው የሚለው?

⇒ ማቴ 6:7 _ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጥላል ሁለተኛውንም ይወዳል ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል! ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም...

⇒ መክ.5:10_ ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም! ባለጠግነትን የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም...

⇒ ገንዘብ መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሀይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ... (ወደ ጢሞቴዎስ 2:6÷10)

... ዋናው ጥያቄ ይህን መሰል አስነዋሪ ድርጊት ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሲባል በግደለሽነት የሚሠሩት ምን አይነት ሰዎች ናቸው? የሚለው ነው:: በዚህ መልኩ የምታገኘው ገንዘብ እንደው በረከት ይኖረዋል? ገንዘቡን ተቀብለህ በሰላም ለሽብለህ ትተኛለህ ወይ? የሚል ጉዳይ ይነሳል:: እኔ በግሌ እግዚአብሔርን የሚያውቅ እና ፈርሐ እግዚአብሔር ያለበት ሰው ይህን ያደርጋል የሚል እምነት በጭራሽ የለኝም! ለገንዘብ ሲባል የገንዘብ አምልኮ ያለባቸው ሰዎች ግን ከዚህም የከፋ ድርጊት ያከናውናሉ! ከመንግስት ጥብቅ ቁጥጥር ያስፈልጋል! እኛም የሚያጠራጥረንን ነገር ስናይ ለህግ አካላት ጥቆማ መስጠት ነው፤ በተለይ ለምንወዳቸው ህፃናት ወንጀልን እንዲጠሉ ስለ መልካም ሥነምግባር በሚገባ እየተኮተኮቱ ማደግ አለባቸው!! ብቻ ብዙ ፈጣን ለውጥ የሚያስፈልጉ ነገሮች ሀገራችን ውስጥ አሉ!!"

"ስለዚህ ሰው የገንዘብ ጠላት እንጂ ገንዘብ የሰው ጠላት አይደለም በሚለው ወርቃማ መርህ ታምናለህ?"

"ቀላል:: እንደውም ስለ ገንዘብ በዚህ አጋጣሚ ቶማስ በርተን የተባለ ደራሲ ያለውን ላንሳልህ:: 'ባለሀብት ከሆንክ ይህን አስተውል! እግዚአብሔር ገንዘብን በእጅህ ላይ እንዲሆን ያደረገበት ብቸኛ ምክንያት በመልካም ነገር ላይ በማዋል ደስታ እንድታገኝበት ነው' ይላል::



Scanned by CamScanner

እውነቱን ነው ገንዘብ የፈጣሪ ስጦታ ነው፡፡ መገልገያችን ነው! ግን ማስተዋል ከሌለን በገንዘባችን ሀጢያት ማድረግም እንችላለን"

"በምሳሌ እንየው?"

"ለምሳሌ መመገብ ሀጢያት ነው?"

"አይደለም"

"አየህ መመገብ ሀጢያት አይደለም! ባንፃሩ ስግብግብነት ሀጢያት ነው! ቁንጣን እስከሚይዝህ መብላት ሀጢያት ነው፡፡ መተኛት ሀጢያት አይደለም! ብዙ መተኛት ግን ሀጢያት ነው፡፡ የስንፍና እስረኝነት ነው፡፡ ወሲብ የእግዜር ስጦታ ነው፡፡ ዝሙት ካደረከው ግን ሀጢያት ነው፡፡ በዚያው ልክ በገንዘብህ ክፋት ከሰራህበት ሀጢያት ነው! ገንዘብ ለማግኘት ብለህ ያልተገባ ድርጊት ማድረግ ሀጢያት ነው..."

"እስቲ የህይወትን ምንነትና ስኬትን አጣምረህ በመጠኑ ግለፅልኝ"

"አሪፍ ጥያቄ"

"ቆይ እዚህ ጋር አንዲት ጥያቄ አስቀድሜ ላንሳ?"

"ቀጥል"

"አሁን የደረስክበት ደረጃ ለመድረስ በሀሳብ እገዛ ያደረጉልህ የተወሰኑ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል፤ የገንዘብ እርዳታ ያደረጉልህ አሉ? በእርግጥ ሀሳብ ራሱ ገንዘብ ነው"

"በጭራሽ!! በዚያ ላይ በጣም የምጠላው ነገር ከሰዎች ገንዘብ መለመን እና ይህን አድርጉልኝ ማለት ነው፡፡ ሰዎችን ማስቸገር በጣም የምጠላው ነገር ነው"

"ስለዚህ መነሻህ በሙሉ የራስህ የላብ ውጤት ነው?"

"ትክክል"

"ቤተሰቦችህ እንኳ..."

"በጭራሽ! እኔ ከቤተሰቦቼ እንኳን በቁማቸው ሞተው እንኳ ምንም ነገር እንዲያወርሱኝ አልፈልግም፡፡እኛ ሀገር ውርስ የሚባል ጣጣ አንዱ የስንፍናችን ምክንያት ነው፡፡ አባትም ሆነ ቤተሰብ ለልጁ ማውረስ ያለበት እውቀት እና ሥነምግባርን ብቻ እንጂ ገንዘብም ሆነ ግዑዝ ነገር መሆን የለበትም! አየህ ከቤተሰብህ ምንም የማትፈልግ ከሆነ አንተም የራስህን ንብረት ለማፍራት ወጥረህ ትሰራለህ! እኔ በዚህ ነው የማምነው፡፡ውርስ የሚባል ነገር ከዓለም ላይ ራሱ ጨርሶ መቅረት አለበት፡፡የዚያን ጊዜ ወጣቶች ምንም እንደማይኖራቸው



Scanned by CamScanner

ሲያውቁ የራሳቸውን ሸክም መሸከም ይጀምራሉ! ወደው በግድ ጠንካራ ይሆናሉ”

“አከራካሪ ቢሆንም አሪፍ ሀሳብ ነው”

“እውነቴን እኮ ነው”

“ግብህ ገብቶኛል:: ወደ ጥያቄያችን እንመለስ?”


“እሺ! በማንበብ ያወኩትን የምሁራን አልያም የፈላስፎች ስለ ህይወት ሆነ ስኬት ያላቸውን እይታ ሳይሆን የግሌን አረዳድ ነው ማወቅ የምትፈልገው?”

“እየኖርከበት ያለውን?”

“ቀለል ባለ ቋንቋ ህይወት መኖር ነው:: መኖር ደግሞ መለወጥ ነው:: መለወጥ ደግሞ ማደግ ነው:: ማደግ ደግሞ ለማያቋርጥ ስኬታማነት ራስን የበለጠ ማዘጋጀት ነው... ባጭሩ ከእናትህ ማህፀን ዘጠኝ ወራት ቆይታ እስከ ልጅነት— ወጣትነት — ሽምግልና— ሞት ሁልጊዜ ያለው ቋሚ ነገር ለውጥ ብቻ ነው:: በእያንዳንዷ ሴኮንድ ሆነ ቀን ፈለግንም አልፈለግንም በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ነን:: የዓለም ትልቁ ሀቅ ሁሌ በለውጥ ውስጥ መሆናችንን ማመን ነው:: ይህን ወሳኝ ነጥብ ያዝልኝ”

“ያዝኩልህ”

“አሁን ደግሞ ስኬትን እና ህይወትን በጥምረት እንመልከተው:: ለእኔ አንድ ሰው ስኬታማ ነው የሚባለው ሁለት ነገሮች ሲኖሩት ነው:: ይህን የስኬት ቀመር በሁለት ጎራ መድበን ማየት እንችላለን”






Scanned by CamScanner

"አሁን በዝርዝር እንመልከት ለምሳሌ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ትልቁ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ጥረው ግረው በላባቸው እየሠሩ እንዲበሉ ነው፡፡ ስለዚህ መስራት ግዴታ ነው፡፡ ሳይሠሩ መብላት ሀጢያት ነው! የሌላውን የላብ ውጤት ቁጭ ብሎ ማጨረስ ራሱን የቻለ ወንጀል ነው፡፡ ትልቁ የስንፍና መገለጫም ነው፡፡ ይህን እውነት በሚገባ ከተረዳን ራስን ጥያቄ መጠየቅ ነው"

"ምን አይነት ጥያቄ ነው?"

"ለምሳሌ የህይወት ትልቁ ጥያቄ ነው ተብሎ የሚታወቀው ለምንድን ነው የተፈጠርኩት? እዚች ምድር ላይ ለምን መጣሁ? ኖሮ ኖሮ ለመሞት ነው? ምንድንነው የምሠራው? ምን ብሰራ ደስተኛ እሆናለሁ? መሰል ጥያቄዎችን እንጠይቃለን..."

"ወደ ፈጣሪ ብንመጣስ?"

"ያውነው ! እዚም ጥያቄ አለ፡፡ በፈጣሪ ማመን ካለብህ ወይም ካንተ በላይ የሆነ ታላቅ ሀይል እንዳለ ማወቅ ካለብህ ሆነ በእርሱ ማመን ካለብህ አሁንም ማንሳት ያለብህ ጥያቄዎች አሉ፤ ለምሳሌ በፈጣሪ ማመን ለምን አስፈለገኝ? በፈጣሪ ባላምንስ ምን አጣለሁ? በፈጣሪ ሳምን ምን አገኛለው? እንዴት ነው ማመኔስ የሚታወቀው? እዚህ ጋር የሶቅራጥስን ጥያቄ አንበለው ሎጂክ መጠቀም ተገቢ ነው፤ በዚህ መሠረት ለምሳሌ ሶቅራጥስ የሚያነሳው 'ጥያቄ በእግዚአብሄር የምታምነው እመን ስለተባልክ ነው ወይስ በእግዚአብሔር የምታምነው እግዚአብሔርን ማመን ስላለብህ ነው? ለመሆኑ ማመንስ ምንድን ነው? ስለማመንህ ምን ተጨባጭ ማስረጃ አለህ?... ወዘተ የመሰሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ነው?"

"ስለዚህ?"

"ስለዚህ አንድ ሰው ስኬታማ ነው የሚባለው በስኬት ቀመር ሙሉ ስኬት የሚባለውን (መንፈሳዊ + ዓለማዊ) ስኬት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ በአንዱ ብቻ በተለይ በዓለማዊ ነገር ብቻ ስኬታማ ከሆንክ ግማሽ ስኬት ብቻ ነው ያለህ!! በሁለቱ ነገር (ሙሉ ስኬታማ) ለመሆን አስተዋይ መሆን አለብህ! የህይወትን ትርጉም በጥንቃቄ ማወቅ አለብህ፡፡ ብዙዎች ግን ስኬታማ የሚሆኑት በአንድ ነገር ብቻ ወይም በግማሽ ስኬት ብቻ ነው፡፡"

"አንተ ሙሉ ስኬታማ ነኝ ትላለህ?"

"አሁን?"

"እህ?"



Scanned by CamScanner

"50/50! ምክንያቱም ህይወትም ሆነ ስኬት ማቆሚያ የላቸውም፡፡ ስኬትን በምግብ መስለው፡፡ ለምሳሌ ዛሬ አሪፍ የሚባል ቁርስ ብትበላ ያቁርስ የሚሰራው ለዛሬ ብቻ ነው፡፡ ትላንት አሪፍ ቁርስ በልቻለው ብለህ ነገ ከመብላት አትቆጠብም! ቢቃ ስኬት በየቀኑ እየቀጠለ የሚሄድ ነገር ነው እንጂ ማቆሚያ የለውም!! ተኝተህ በተነሳህ ቁጥር ሌላ ህይወት ነው ያለህ!! ስለዚህ መስራት አለብህ፡፡ እኔ አሁን ሙሉ ስኬታማ ነኝ ለማለት የማጥገረው ለዚህ ነው! አንድ ነገር ሰርተህ ሲሳካልህ ወዲያው ማሰብ ያለብህ ተጨማሪ ሌላ ነገር ለመስራት ብቻ መሆን አለብህ!! ስኬትን በዚያ መልኩ ነው መገንዘብ የሚገባህ! ይህን እውነታ ደግሞ ከተረዳህ ስኬት መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ የላትም የሚለውን እውነታ ትረዳለህ! ገባህ?"

"በሚገባ፡፡ እንደነገርከኝ 27 ዓመትህ ነው? በቅርቡ ታገባለህ?"

"ከሁለት ዓመት በኋላ ነው ያቀድነው"

"እሺ ማግባት ልጅ ወልዶ ማሳደግ፣ የትዳር ህይወት ... ራሱን የቻለ የስኬት መገለጫ ነው??"

"ምን ጥያቄ አለው? ለዚያ እኮ ነው ስኬት የማያቋርጥ ጉዞ ነው ያልኩህ!! በእያንዳንዷ የህይወት ጉዞ ላይ አለቀ! ደቀቀ! የሚባል ነገር የለም! በእያንዳንዷ ቀን ኃላፊነት አለብን! በእያንዳንዷ ሴኮንድ ሀላፊነት አለብን! በእያንዳንዷ ማይክሮ ሴኮንድ ሀላፊነት አለብን!!"

"የአብዛኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች ችግር እንበለው ድክመት ምን ይመስልሃል?"

"ግዴለሽነት"

"ይብራራ እስቲ"

"እኔ ከዩኒቨርሲቲ ጀምሮ ስራ ቦታ ላይ ተቀጥሬ ከብዙ ወጣቶች ጋር አሳልፊያለው! የወጣቶችን ሁኔታ ለመረዳት ጥረት አድርጌያለው፡፡ በጣም ደስ የሚለው የኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉ የእውቀት ችግር የለባቸውም! ስለማንኛውም ነገር ብትጠይቃቸው ያብራሩልሃል! እንዴት እንደሚከናወን ይነግሩሃል! አሪፍ አሪፍ ሀሳቦች እያፈለቁ ይነግሩሃል! አንድን ነገር ለመረዳት ፈጣን ጭንቅላት አላቸው፤ ግን ያን እውቀታቸውን መሬት ላይ አውርደው መጠቀሙ ላይ የእናቴ መቀነት አይነት ምክንያቶች ያቀርባሉ! በርካታ ሰበቦችን መደርደር ይወዳሉ!



Scanned by CamScanner

አይወዱም! አብዛኛውን ጊዜያቸውን በሱሶች ተጠምደው ያሳልፋሉ! ስለ እውቀት ደግሞ የግሪኮች ሀሳብ በጣም ያስማማኛል"

"የትኛው?"

"አንድ ሰው እውቀት አለው አልያም አዋቂ ነው የሚባለው ያን ያወቀውን ነገር በተግባር ሲጠቀምበት! ህይወቱን ሲለውጥበት ነው፤ በተጨማሪ አንድን ነገር አውቀህ ያን ያወከውን ነገር በተግባር የማትጠቀምበት ከሆነ እውቀትህ ከንቱ ነው!! የምልህ በሀገሪቷ ውስጥ ብዙ ችግሮች አሉ፤ ሥራ ለማግኘት ከፖለቲካ ጋር፣ ከዘረኝነት ጋር፣ ከትውውቅ ጋር፣ ከሙስና ጋር... ወዘተ ይቆራኛሉ! ታዲያ ለዚህ መፍትሔ የሚሆነው ምክንያት እየደረደሩ መቀመጥ ነው ወይስ እንቅፋቶች እንዳሉ አውቆ ጉዞን መቀጠል ነው?? ለእኔ ምክንያት ውጤት ስለማይለወጥ እስከመጨረሻው ድረስ ጥረትን በመቀጠል አምናለው!! ተስፋ መቁረጥን የመሰለ ትልቅ ድክመት የለም:: ባጠቃላይ በእኔ እይታ ወጣቱ ግዴለሽና በትንሹም በትልቁም ነገር ሰበብ መደርደር ይወዳል:: የኋላ ቀር ህዝቦች አብይ መገለጫ ደግሞ ሰበብ ደርዳሪ መሆን ነው!!"

"ወደ ንግድ እንመለስ?"

"እሺ"

"ቻይናዊያን ፈገግታ የሌለው ግለሰብ ነጋዴ አይሁን ይላሉ"

"አምንበታለው!"

"ጣሊያኖች መዋሸት የማይችል ሰው ነጋዴ መሆን የለበትም ይላሉ"

ራሱን በጣም ነቀነቀ::

"አትስማማበትም?"

"አልስማማበትም! እኔ አልተስማማሁበትም ማለት ሀሳቡ ልክ አይደለም ወይም ሚዛን አይደፋም እያልኩ ግን አይደለም እንደ መልካችን እይታችን የተለያየ ነው፤ ሁሉም ነጋዴ ውሸታም ነው! ለሀቅ የሚሰራ ነጋዴ የለም ማለት አይቻልም:: የምልህ የእውነተኛ ነጋዴ አብይ አላማ አሪፍ አገልግሎት እየሰጠ ትርፍ ማግኘት ነው:: ለፅድቅ ብሎ ንግድ ውስጥ የሚገባ እኮ የለም:: በእርግጥ የውሸት ትልቅ ሆነም ትንሽ የለም በሚለው ህግ በሀሳቡ እስማማለሁ!!"

"ነጋዴ ውሸታም መሆን አለበት በሚለው ማለት ነው?"



Scanned by CamScanner

"ቃል በቃል እኮ አላልኩም፤ በLogic ካየነው ብቻ ነው ያልኩህ! በንግድ ውስጥ እንዳንተም ውሸት የሚባል እኮ የማያውቁ አሉ"

"ጥቂቶች?"

"እሱ ልክ ነህ"

"ግን አገር የዕቃ ዋጋ በአንድ አጋጣሚ ከፍ ካለ እየጨመረ ይሄዳል እንጂ ወርዶ ሲቀንስ አይታይም፤ አንተስ ምን ትላለህ?"

"የብራችን የመግዛት ሀይል መዳከም እንዳለ ሆኖ ይህ ሌላው የስግብግብነት መገለጫ ነው፡፡ መተዛዘን የሚባል እኮ እየቀረ ነው፡፡ በዚያ ላይ አንዳንድ ስግብግብ ሰዎችም አሉ፤ አንተ ለምን ተወደደ? እያልክ ስትከራከር እነርሱ በሃገ መጥተው በተጠየቁበት ዋጋ የሚገዙም አሉ፡፡ ዋናው ችግር የመጣው ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተወሰኑ ሀብታሞች አሉ፤ እጅግ ብዙ ደሀዎች አሉ፡፡ የሚገርምህ ሀገሪቱ የምትመራው በጥቂቶቹ ሀብታሞች እጅ ነው፤ በዚያ ላይ ስርዓታዊ የንግድ አካሄድ ያለመኖሩ ጭምር የኢትዮጵያን የንግድ ሂደት ህዝቡ መቆጣጠር ሲገባው በተቃራኒው የንግዱን ስርዓት የሚቆጣጠረው ራሱ ነጋዴው በመሆኑ ለነጋዴዎች እንዳሻቸው መፈንጨት ምክንያት ሆኗ"

"አጭር ምክር"

"ያለ ምንም ክርክር (መከራከር) ዕቃ መግዛት የለብንም፤ በዚያ ላይ ከአንድ ቦታ ዕቃ ከመግዛታችን በፊት ቢያንስ አንድ ሶስት ቦታዎች ላይ ዋጋውን ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለብን፤ ቢያንስ ይህ ልምድ ገንዘባችንን በከንቱ ከመበላት ያድነናል፤ ቢቻል ደግሞ ለምሳሌ በዓል መጣ ብለን ዕቃ ከማግበስበስ በእቅድ እየተመራን ዕቃ የመግዛት ባህል ልክ እንደ ፈረንጆቹ ብንለምድ አሪፍ ነው፡፡ ፈረንጅ ጫማ እገዛለሁ ብሎ ገበያ ከወጣ ጫማ ብቻ ገዝቶ ነው የሚመለሰው፡፡ ሀበሻ ጫማ እገዛለሁ ካለ ሌሎች ተጨማሪ ኮተቶችንም ገዝቶ ይመለሳል ይህ አጉል ደካማ ባህላችን ነው"

"የመጨረሻ ጥያቄ... ስለ ታላቅ ቅናሽ ፍቺ ንገረኝ እስቲ! በተለይ ከጀርባ ያለውን ሚስጢር"

"እም፡፡ በነጋዴዎች ቋንቋ ካውንተር አታክ ትባላለች፡፡ እየህ በእኛ የሀበሻ ባህል በብዛት ህዝቡ ከባዓላት ጋር በተያያዘ ገንዘብ ያለ ፕሮግራም እንደ ግብዝ ሰው ያወጣል፤ ስለዚህ የህዝቡን የመግዛት ፍላጎት ይበልጥ ለማናር ታላቅ ቅናሽ የሚል ነገር ትለጥፋለህ፡፡



Scanned by CamScanner

ቃሉ ደግሞ ይበልጥ ትኩረት ይስባል። በእርግጥ አንዳንዴ የንግድ ስራህን ለማቆም ስትፈልግ ታላቅ ቅናሽ በመለጠፍ ትሸጣለህ፣ ፋሽን ያለፈባቸውን ነገሮችን ታላቅ ቅናሽ ብለህ ትሸጣለህ፣ ሊበላሹ ሁለት ወር ወይም ሶስት ወር የቀራቸውን የታሸጉ ምግቦች በታላቅ ቅናሽ ትሸጣለህ...በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎችን በርካሽ ዋጋ ስትገዛ በታላቅ ቅናሽ ትሸጣለህ... ዋናው አንተ ማወቅ የፈለከው ጀርባውን ስለሆነ የጠቀስኩልህ እውነታዎች እንዳሉ ሆነው አብዛኛው ቤት የሚለጠፈው የታላቅ ቅናሽ ዋጋ የውሸት ነው። የሥነልቦና ጨዋታ በጣም ይበዛበታል። ለምሳሌ አንተን ፌክ ለመስራት "400 ብር የነበረው 200 ብር" ገባ የሚል ዋጋ ይለጠፍበታል! የሚገርምህ ግን በብዛት የዚያ ዕቃ ዋጋ በፊትም የሚሸጠው 200 ብር ነበር። በብዛት እንዲህ አይነት የተቀናበሩ ፌኮች ይበዛሉ... በዚያው ልክ በጣም ጥቂት ነጋዴዎች ደግሞ ታላቅ ቅናሽ ብለው የምራቸውን በታላቅ ቅናሽ የሚሸጡ አሉ!!"

"ወሬያችንን በምትወዳት አባባል እንጨርስ"

ትንሽ የዝምታ እፍታ ወሰደና ተናገረ...

"ሰውን መለወጥ ከፈለክ መጀመሪያ አንተ በቅድሚያ ተለወጥ!!

## ማስናበቻ

ቋ... አላለቀም ፣ ሊያልቅም አይችልም! እናስ?... ቋ... ሁለትን በተጨማሪ 26 አጫጭር የማጠቃለያ ታሪኮች ስብስብ...!! ይጠብቁ.... ሰናይ ህይወትን ለውድ ተደራሲያን ተመኘቻለው!!

አዘርግ 2008

አዲስ አበባ።



Scanned by CamScanner

# የ2009 የአዘርግ ስጦታ

ሁለት አወዛጋቢ ታሪኮችን
የያዙ ሁለት መፅሐፍት በአንድ ጥራዝ ...!!

## ሎሆ!!

## እና

## ለሚስቴ ባል ፍለጋ

.... ከ 18 እስከ 38 ዓመት ላሉ አንባቢያን።



Scanned by CamScanner




ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር
011 156 53 52

ዋጋ 55.65

Scanned by CamScanner